
# የተራራው ስብከት



የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሳልሣዊ እንዳጻፉት

አያሌው ኢያሱስ እንደተረጎመው

ግንቦት 1993 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የተራራው ስብከት

የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ቅዱስነታቸው አብነ ሺኖዳ ሳልሣዊ እንደፃፉት

የእንግሊዝኛው ርዕስ - Contemplation on Sermon on the Mount

አያሌው ኢየሱስ እንደተረጎመው

የሽፋን ስዕል ዲ. ሲራክ ወጋየሁ

www.ethiopianorthodox.org

# ምሥጋና

የትርጉሙን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፣ ለዲ. ወንድምስሻ ገብሬና ለመስፍን ለማ ፣ የትርጉሙን ረቂቅ በኮምፒዩተር በመጻፍና በማስተካከል ለረዱኝ ለእህቶቼ ዘላለም ወጋየሁ እና ለእሌኒ ወጋየሁ ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

የኮምፒውተር ለቀማው ለህትመት እስኪበቃ ድረስ ለካሜራ ዝግጁ በሆነ መልኩ በማቀናበር እጅግ አድካሚውን ሥራ ለፈፀመልኝ ውድ ወንድሜ ዘውዱ ተካ እና በሁሉም መስክ ሁሉንም በማድረግ ከውጥኑ እስከ ፍጻሜው ለደከመው ውድ ወንድሜ ያዕቆብ ሰንደቁ መንፈሳዊ ምሥጋናዬ እጅግ የላቀ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ሥርዓቷን ጠብቆ የተዘጋጀ።

ካለ አሳታሚ ፈቃድ ማተም ክልክል ነው
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
*All Rights Reserved*

አድራሻ፡
☎51 96 80
20 0438
✉ 9673
አዲስ አበባ



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

## ከተርጓሚው

ይህን መጽሐፍ "የተራራው ስብከት" በማለት ስተረጉመው መጽሐፉን የሚያነቡ ወገኖቼ ሁሉ አንብበው በቃል እንዲናገሩት ወይም እንዲሰብኩት ብቻ ሳይሆን ያነበቡትን በሥራ ለማሳየት እንዲነሳሱ በማሰብ ጭምር ነው ። ይህ ካልሆነ ማንበባችን ለእውቀት ብቻ ሆኖ ይቀራል ። ክርስትና ደግሞ አውቆ በቃል መናገር ብቻ ሳይሆን አውቆ በጽድቅ ሥራና በእምነት መዳን ነው ።

ምንም እንኳ በቅድስቲቱ ቤተ ክርስቲያናችን የተራራው ስብከት የሚባለው የወንጌል ክፍል ከማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ያሉትን ሦስት ምዕራፎች የሚያጠቃልል መሆኑን ባውቅና ይህ መጽሐፍ ደግሞ ያካተተው በምዕራፍ 5 ውስጥ ከቁጥር 1-16 መሆኑን ብረዳም ከእንግሊዘኛው ርዕስ የቃል በቃል ትርጉምና 'እንቀጸ ብፁዓን' ከሚለው ርዕስ ይልቅ "የተራራው ስብከት" የሚለውን ይበልጥ ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት በዚሁ ርዕስ ተርጉሜዋለሁ ።

"የተራራው ስብከት" የሰማችሁትን አድርጉ ትድናላችሁ ፤ ድርጊታችሁም በፍጹም የዋህነት ይሁን ነው የሚለው ። "የተራራው ስብከት" ክርስትና የሰሙትን ማስመሰል ሳይሆን መሥራት ወይም ማድረግ እንደሆነም ይመሰክራል ። የማስመሰል ወይም የታይታ ትህትና ከልብ ወይም ከእምነት ከመነጨ ትህትና ብዙ ልዩነት እንዳለውም ያብራራል ። ስለሆነም እምነት ብቻ እንጂ ሥራ አያስፈልግም ለሚሉ ለአንዳንዶች በቂ ትምህርት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ ።

እዚህ ላይ ነው የመጽሐፉ ጠቀሜታ ። እኛ ብዙ አንባቢዎች ፤ ብዙ ተርጓሚዎች ፤ ብዙ ተናጋሪዎች ፤ ብዙ ሰባኪዎች እንጂ ጥቂት እንኳ አድራጊዎች አይደለንም ። እንደምንናገረውና እንደምንሰብከው ብንሠራ ጌታ ያዘዘውን ወይም አድርጉ ያለውን ለማሳየት በአብዛኛው መጽሐፍ ቅዱስን ፍለጋ አንሄድም ነበር ። መልካሙ ሥራችን ጌታችንን ያስነብብ ነበር እንጂ ። ሰባኪ ወይም ቃለ እግዚአብሔርን የሚያስተምር ሰው ሊደነቅና ሊወደድ ወይም ሊከበር የሚገባው በአነጋገር ስልቱ ቃላት በማሳመሩና በማሳካቱ ሳይሆን ሕይወቱም በክርስቲያናዊ ሥራዎቹ የክርስትናውን ስልት በመከተል የተሳካ ሲሆን ነው ።

ጌታችን አስተማረ ያስተማረውን አደረገው ፤ ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ሰበኩ የሰበኩትን በሥራ ገለጹ ። እኛ ግን እንሰማለን ፤ እንናገራለን ፤ እንሰብካለን ፤ እናስተምራለን ነገር ግን አናደርግም ። "የተራራው ስብከት" ግን ሰምታችሁ ተናገሩ ተናግራችሁ አድርጉ ይለናል ።

እግዚአብሔር አምላካችን ያነበብነውንና የሰማነውን እንድንናገር የተናገርነውንም እንድናደርገው እርሱ በቸርነቱ ይርዳን! አሜን።

አያሌው ኢየሱስ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ ።


መቅድም

ተራራው ። — 7

መግቢያ

አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው ። — 11

ከስብከቱ የተወሰዱ ዐበይት ነጥቦች ። — 11

ምዕራፍ አንድ

1. በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ። — 13

ሀ. ብፁዓን ። — 13

ለ. የመንፈስ ድህነት ። — 14

ሐ. የድህነት መለኪያዎች ። — 17

መ. ውሳጣዊ ድህነት ። — 18

ሠ. ድህነት በሰዎች ፊት ። — 20

ረ. ድህነት በእግዚአብሔር ፊት ። — 24

ሰ. ድህነት ብርኩሳን መናፍስት ፊት ። — 26

ሸ. መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ። — 27

ምዕራፍ ሁለት

1. የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው ፤ መጽናናትን ያገኛሉና ። — 31

ሀ. ለማልቀስ የሚያነሳሱ ወይም ከማልቀስ የሚያግዱ ምክንያቶች ። — 36

ምዕራፍ ሦስት

1. የዋሆች ብፁዓን ናቸው ፤ ምድርን ይወርሳሉና ። — 41

ሀ. የዋሆች እነማን ናቸው ? — 41

ለ. የዋህነትና መንፈሳዊ ቅንዓት ። — 46

ሐ. ምን ዓይነት ምድርን ይወርሳሉ ? — 47

ምዕራፍ አራት

1. ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ፤ — 48

ሀ. ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ የሚለው ሐረግ ትርጉም ። — 48

ለ. የሰማያዊው ሕይወት ፍቅር ። — 49

ሐ. መራብና መጠማት ከጸሎት አኳያ ። — 51

መ. ይጠግባሉና ። — 54

ምዕራፍ አምስት

1. የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ፤ ይማራሉና ። — 55

ሀ. ምሕረት ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ነው ። — 55

ለ. የምሕረት ጠቀሜታ ። — 56





ሐ. የምሕረት ታላቅነትና ምልክቱ ። — 58

መ. ጭካኔ ። — 60

ሠ. የእግዚአብሔር ምሕረት የሚገለጠው ለማነው ? — 61

ምዕራፍ ስድስት

1. ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው ፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና ። — 66

ሀ. ታላት ዋጋ ። — 66

ለ. እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን አያይም ። — 66

ሐ. ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን አያዩትም ። — 67

መ. ሕሊና የዋህነትና መከራዎች ። — 68

ሠ. እግዚአብሔርን በህያውነቱ ማየት ። — 69

ረ. የልብ ንጽህና ። — 69

ምዕራፍ ሰባት

1. የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። — 74

ሀ. የሚያስተራርቁ የሚለው ቃል ትርጓሜ ። — 74

ለ. ሰላም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ። — 74

ሐ. ሰላም በሰዎች መካከል ። — 77

መ. ውሳጣዊ ሰላም ። — 79

ምዕራፍ ስምንት

1. ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው ። — 81

ሀ. የክፉ አድራጊዎች አርአያዎችና ትግሮቻቸው ። — 86

ለ. የተጋዙና የተሰደዱ ቅዱሳን አርአያዎች ። — 89

ሐ. ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ ። — 93

ምዕራፍ ዘጠኝ

1. እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ። — 95

ሀ. የሚያስደንቅ ቅደም ተከተል ። — 95

ለ. እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ። — 96

ሐ. ምሳሌ የመሆን ተልዕኮ ። — 97

መ. ከሞቱም በኋላ ምሳሌ መሆን ። — 99

ሠ. ጨውና ብርሃን ለምን ተለይተው ተመረጡ ? — 101

ረ. የምስጋና ቃላት ። — 101

ሰ. የጨው ጠቀሜታ ። — 103

ሸ. ጨውና ብርሃን ። — 106

ቀ. እግዚአብሔር በስሙ ይጠራናል ። — 108

በ. በተራራ ላይ ። — 110

ተ. ጨው አልጫ ቢሆንስ ? — 110


www.ethiopianorthodox.org

ቸ. በሰዎች መረገጥ ። ______ 114
ነ. ወደ ውጪ መጣል። ______ 117

ምዕራፍ አሥር ______ 120
1. ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ። ______ 120
ሀ. ከተማና መብራት ። ______ 121
ለ. ሊሰወሩ አይቻላቸውም ። ______ 123
ሐ. ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው ። ______ 124
መ. መገለጥና መሰወር ። ______ 125
ሠ. ታላቅነት ከእግዚአብሔር ነው ። ______ 127
ረ. በሰማያት ያለው አባታችሁ ። ______ 128
ሠ. መንግሥተ ሰማያት ______



## መቅድም ።

### ተራራው።

አንዳንድ ሰዎች የተራራው ስብከት የክርስትና [illegible] ሕግና ደንብ ነው ይላሉ ። እኛም በዚህ ላይ የምናክለው አለ ። በሰዎች ዘንድ የታወቀ ረዥሙ መመሪያም ጭምር ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ትምህርቱን ያስተማረው ለሕዝቡ ሁሉ ነው ። በዚህም ፍጽምና ለሁሉም ሰው ሊታደል እንደሚችልና ማንኛውም ሰው ከውሳጣዊ ነፍሱ እነዚህን ትዕዛዛትና መመሪያዎች የማድመጥ አድምጦም በፍቅር ከተቀበላቸው በኋላ ፈቃዱን እንዳይፈጽም ምንም ዓይነት መሰናክል ቢገጥመው እነርሱን ሙሉ ለሙሉ በውዴታ መፈጸም የሚያስችለው ዝግጅት እንዳለው አረጋግጦልናል ።

እነዚህ ሰማያዊ ቃላት ከተራራ ጫፍ ላይ መተላለፍ ነበረባቸው ። ምክንያቱም አድማጮቹ ወደዚያው በወጡበት ጊዜ እንዲህ ያለውን መመሪያ ለማድመጥና ለመረዳት ነፍሶቻቸው ከቦታው የአቀማመጥ ሁኔታ ጋር አብረው ከፍ ስለሚሉ ነው ። በተራራ ላይ ወጥቶ ለሚቀመጥ ደግሞ በምድር ላይ ያለው ነገር ሁሉ ለእርሱ በጣም አነስተኛና ደቃቅ ሆኖ እንደሚታየው አይጠረጠርም ።

የብሉይ ኪዳን ሕግጋትም ሕዝቡ በአርያም ያለውን አምላክ ታላቅነትና ክብር ሊያስተውሉ ከሚችሉበት ከተራራ አናት ላይ እንደተሰጡ መዘንጋት የለብንም ። ስለዚህ ጌታ የአዲስ ኪዳንን ሕግጋት ለሕዝቡ ከተራራ ላይ ሆኖ ሲሰጥ ሕዝቡ የሲና ተራራን ያስታውሱ ዘንድ አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላቸው ነበር ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እነዚህን ሁለት ተራራዎች በማነፃፀር እንዲህ ሲል ጽፏል ፤ "ሊዳሰስ ወደሚችል ወደሚቃጠልም እሳት ወደ ጭጋግም ወደ ጨለማም ወደ ዓውሎ ነፋስም ወደ መለከት ድምፅም ወደ ቃሎችም ነገር አልደረሳችሁምና ፤ ያንም ነገር የሰሙት ሌላ ቃል እንዳይጨመርባቸው ለመኑ ... ነገር ግን እናንተ ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል ... ወደ አዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ ..." ዕብ 12: 18-24 ።

ከአዲስ ኪዳን ትዕዛዛት በተቃራኒው የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የተሰጡት በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ስለነበር ነቢዩ ሙሴ "በፍርሃት እንቀጠቀጥ ነበር" አለ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚናገረው በትህትና ነበር ። በቡራኬውም መቅድም ላይ ትህትናን አወድሷል ። ስለዚህም ሕዝቡ እሳትም ሆነ ጭጋግ እንዲሁም የምድር መናወጥ አላሰጋቸውም ። የእግዚአብሔርንም ቃል መካከለኛ ያስተላልፍላቸው ዘንድ ሙሴ አላስፈለጋቸውም ። ጌታ ራሱ እንደ አንድ ተወዳጅ አባት በመካከላቸው

www.ethiopianorthodox.org

[illegible] ራቸው ነበር ። በሚያስገርም መልኩ ይናገራቸውም ስለነበር [illegible] ብለው ተጽፏል። "ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ ፤ እንደ ጸፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና ።" ማቴ 7: 29 ።

ጌታ በተራራው አናት ላይ ሆኖ ሲናገራቸው አንዳችም ስሜታቸውን የሚያውክ ሁኔታ ስላልነበር መልካም ሆኖላቸዋል ። ስለዚህም ልቦናቸውን ሙሉ ለሙሉ ሰጥተው ያዳምጡት ነበር ። ትምህርቱን ያስተማራቸው ተብለጭልጫ ከምትታየውና በውስጧ ተድላና ደስታን ፤ ስጋትና መጨናነቅን አካታ ከያዘችው ዓለም ራቅ ብሎ አንዳችም የሚያውክ ነገር በሌለበት ሥፍራ ነው ። በቤት አሊያም በሥራ ቦታ በጭንቀትና በመዝናናት እንደሚማረኩበትም ያለ መማረክ አልነበረም ። የነበረው ጌታ ብቻ ነበር ። ማር ይስሐቅ በተባለው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ውስጥ "በምድረ በዳ እንደ ቀላል የሚመለከቱት ሁሉ በሰው ልቦና ውስጥ ያለውን ዓለማዊ መሻት እንዲዳከም ያደርገዋል።" ተብሎ የተጠቀሰው አባባል ትክክለኛ ነው ። ስለዚህም ነበር ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአብዛኛው ሕዝቡን ምንም ወደማይታይበትና ወደ ምድረ በዳ ይወስዳቸው የነበረው። ሉቃ 9:10 ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ባሕር ዳርቻ አሊያም ሐይቅ ወዳለበት አካባቢ ይዞአቸው ይሄድ ነበር ። ይህንንም የሚያደርግበት ዋነኛው ምክንያት ከሚታይ ነገርና ከዓለም ውጣ ውረድ ርቀው ሁለንተናቸውን ለእርሱ እንዲሰጡ ነው ። እግዚአብሔር አብርሃምን ከአገሩ ከወገኑና ከቤተ ዘመዶቹ ተለይቶ እንዲወጣ እንዳደረገው ማለት ነው ። ዘፍ 12:1 ። ሕዝቡም ጌታን ተከትለው ወደ ተራራው መውጣታቸው መልካም ነበር ። የጌታ የሚማርክ ቁመናው ፤ የሚሰጠው መመሪያ ፤ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ እርሱ የሰጠው ምስክርነት ፤ ደቀ መዛሙርቱ ስለ እርሱ ያወሩት ዝናውና ያደረጋቸው ድንቅ ድንቅ ተአምራቱ ብዙ ሕዝብ እንዲከተሉት ምክንያቶች ሆነዋል ። "ብዙ ሕዝብ የሚከተሉት ሰው" የሚል ቅጽል የወጣለት አምላካችን ይህ ስሙ እስከ ስቅለት ድረስ አብሮት ተጉዟል ። ያለማቋረጥ ብዙ ሺህ ሰዎች ተከትለውታል። በየሥፍራውም በብዙ ሰዎች ተጨናንቋል ። ስለ እርሱም ሕግ አዋቂዎች "እንግዲህ ዓለሙ ሁሉ በኋላው ተከትሎት እንደሄደ ተመልከቱ" ተባብለዋል። ዮሐ 12:19 ። እንዲህም ተብሏል "ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ ይመሰጡ ነበር" ። ሉቃ 19:48 ።

አስቀድሞ ሙሴን እንዳወጣው አሁንም ሕዝቡን ያወጣቸው ወደ ተራራ ነው ። ቀድሞ በብሉይ ኪዳን ኤልያስ የተራራ ላይ ኑሮን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። በተለይም በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ። እንዲያውም እርሱና ሌሎች የነቢያት ልጆች በዚያ ኖረዋል ። መጥምቁ ዮሐንስም የምድረ በዳን ኑሮ ልክ እንደ ኤልያስ ተለማምዶታል ። ቅዱሳን መነኮሳትና ባሕታውያን በጸሎትና እግዚአብሔርን በመፈለግ ጥልቅ ምርምር እንዲተጉ ተራራና



ምድረ በዳ የተጫወቱትን ዐቢይ ሚና እንዋያይ ብንል ብዙ ጊዜ ይፈጅብናል። ተራራ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ እንኳ ጉልህ ድርሻ አለው ።

የመዝሙራት ሁሉ መዝሙር በተባለው በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ውስጥ ስለ እርሱ እንዲህ የሚል ቃል አለ ። "እነሆ የውዴ ቃል ! በተራሮች ላይ ሲዘልል ፤ በኮረቶችም ላይ ሲወረወር ይመጣል ።" መኃ 2:8 ። ጌታ ከተጠመቀ በኋላ ለ 40 ቀናት በተራራ ላይ በጸሎት ቆይቷል ። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ከመቀመጡ በፊትና ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በነበሩት ጊዜያት መካከል ከጥቂት ዕረፍት ጋር በገለልተኝነት ኖሯል ። በዚያን ወቅት ወሳኝ የሆኑ የሥራ መመሪያዎቹን አውጥቷል ። እነዚህ መመሪያዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለፊት በዚያ ተራራ ላይ ከሰይጣን ጋር ሲቆም በገሀድ ታይተዋል ። ከዚህ በኋላ ነው ያ ተራራ "የፈተና ተራራ" በመባል የተጠራው።

## ከፈተና ተራራ ወደ ስብከት ተራራ ከዚያም ወደ ወይራ ተራራ ።

የወይራ ዘይት የሚወጣበት ተራራ በኢየሱስ ክርስቶስ ተወዳጅ ከነበሩት ሥፍራዎች አንዱ ነበር ። ይህ ቦታ ጥቂት የሚያርፍበት ፤ አዘውትሮ የሚጸልይበትና ከአባቱ ጋር የሚገናኝበት ቦታ ነበር ። በዮሐ 7:53 እና 8÷1 ስለ ጌታችን የተነገሩት ቃላት ምንኛ ደስ ይላሉ ? "እያንዳንዱም ወደ ቤቱ ሄደ ። ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ።"

የጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራም ለእኛ በጸሎት መትጋትን ያስተማረባት ሌላዋ ተወዳጅ ሥፍራው ናት ። ይህን የፈጸመው እጁ ከመያዙና መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ሌላኛው ተራራ ከመሸጋገሩ በፊት በነበሩት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነው። ይህ ጌታ በመጨረሻ የወጣበት ተራራ ታላቁን የፍቅር ታሪክ ያስመዘገበበትና ራሱን ስለ ሰው ልጆች ድኅነት ሲል መስዋዕት አድርጎ ያቀረበበት የቀራንዮ ተራራ ነው ። በዚህ ተራራ ላይ የጌታ ደም ፈሷል ። በዚህ ተራራ ላይ ከበስተቀኙ የተሰቀለውን የወንበዴውንና የሰው ልጆችን ሁሉ ኃጢአት ይቅር ብሏል ። በእርግጥም የመከራ የሥቃይና የፍቅር ተራራ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ጌታ በመስቀል ላይ ነፍሱን የሚሰጥባት ሰዓት ከመድረሷ አስቀድሞ ተከታዮቹ በእምነት እንዲጠነክሩ ለማድረግ መለኮታዊ ክብሩን የገለጠበት ተራራም አለ ። ይህ ክብር የተገለጠበት ተራራ የታቦር ተራራ ሲሆን ከዚህ በኋላ "የመለወጫ ተራራ" በመባልም ተጠርቷል ። በዚህ ከፍተኛ ተራራ ላይ ሙሴና ኤልያስ እንደተገኙም ተጠቅሷል ። እነዚህ ሁለት ነቢያት ደግሞ በምድረ በዳና በተራራ መኖርን ጠንቅቀው የሚያውቁ ነበሩ። ከዚህ ሌላ እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን አወድሶበታል። "የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" በማለት ። ማር 9:7 ። የደብረ ዘይት ተራራ አምላካችን ከሚወዳቸው ሥፍራዎች አንዱ በመሆኑ በመጨረሻ ያረገው ከዚሁ ተራራ ጫፍ እንደ ሆነ ተነግሯል ።

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን የተራራን ሕይወት ይወድ ስለነበር እንዲህ ያለውን ድንቅ ስብከት በተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ መስጠቱ አያስደንቅም ። ወንጌላዊው ማቴዎስም ስለ እርሱ "ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ ... አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው" በማለት ጽፏል ። ማቴ 5÷1-2 ። ወደ ተራራ የወጡት ሕዝብም ከበላያቸው አንዳችም ነገር አይመለከቱም ነበር፤ ሰማዮንና ማለቂያ የሌለውን ሰፊ አድማስ ብቻ እንጂ ። ምንም ዓይነት ቁሳዊ እንቅፋት አልነበረም ። ይህ ማለቂያ የሌለው አድማስ ከሚታይበት ሥፍራ ስለ ወጡ እና ከቁሳዊው ዓለም ስለራቁ ነው ጌታ አፉን ከፍቶ ሲያስተምራቸው ልብ ብለው ሊያደምጡት የቻሉት ።



## መግቢያ

### አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው ።

ምናልባት "አፉን ከፍቶ" የሚለውን ቃል ወስዶ "ምን ለማለት ነው?" የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ። ቅዱስ አውግስጢን "ቀደም ባሉት ጊዜያት ኢየሱስ ክርስቶስ በነቢያቱ ላይ እያደረ ሕዝቡን ይናገር ነበር ። አሁን ግን እርሱ ራሱ ተናገረ።" በማለት ይህን ጥያቄ ይመልሳል ። ስለዚህ ሁኔታ መሪያችን ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ይላል ። "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ ... በዚህ ዘመን መጨረሻ ደግሞ በልጁ ተናገረን ።" ዕብ 1:1-2 ። ይህም የሚያስረዳን ጌታ በተራራው ስብከቱም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ባስተማረው ትምህርቱ እኛን የተናገረን በነቢያቱ አፍ ሳይሆን በራሱ አንደበት መሆኑን ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ ክሪስቶምም " ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፉት ዘመናት ይናገርና ያስተምር የነበረው ትዕዛዛዊ ምሳሌዎችን በመስጠት ብቻ ነበር እንጂ አፉን አልከፈተም። አሁን ግን በአንደበቱ ተናገረ ። " ብሏል ።

### ከስብከቱ የተወሰዱ ዐበይት ነጥቦች ።

1ኛ/ ስብከቱ "እምነት ብቻ ይኑርህ" እያሉ እምነት ብቻውን በቂ እንደሆነ በሚያስተምሩ ሰዎች ላይ የተነጣጠረ ሆኖ ለእነርሱ በቂና አጠቃላይ መልስ በመስጠት ላይ ያተኩራል ። በአጠቃላይ ስብከቱ መንፈሳዊ ባሕርይን የሚዳስስ ነው ። ስለ እምነት የሚናገር አንድም ቃል የለም ። ትምህርቱ ሁሉ ስለ መልካም ምግባር ፤ ስለ ልብ ንጽህና ፤ በጎ ጠባይን ስለሚያሳዩ ምሳሌዎች፤ ከሰው መግባባትን ፤ ጸሎትን ፤ ጾምንና የብሉይ ኪዳንን ትዕዛዛት በትክክል መረዳትን የሚያመለክት ነው ። የሚጠናቀቀውም መንፈሳዊ ጥቅምን በመጠቆም ነው ። "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ። ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ።" ማቴ 7:16-24 ።

2ኛ/ጌታ በዚህ ስብከቱ ስለሚገለጥ ሕይወት ተናገረ ። የሕግ አስተማሪዎች ከአይሁድ ጋር ይወያዩባቸው ስለነበሩት አንዳንድ ሥርዓት ነክ ድርጊቶችና ልማዶች ምንም አልተናገረም ። ስለዚህም ከአፉ ይወጡ የነበሩት ቃላት ወደ ሕዝቡ ልቦና ጠልቀው ይገቡ ነበር ።

3ኛ/ስለ ፍጽምና ሕዝቡን ሁሉ በእኩል ዓይን በመመልከት ይናገር ነበር ። ከወንዶችና ከሴቶች ከሽማግሌዎችና በተለያዩ የቅድስናና የዕድሜ ደረጃ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ተነጋግሯል ። ወደፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ያመለክታቸው ነበር ። ይህንንም ያደረገው ወደ ከፍተኛ ሥፍራ ካወጣቸው በኋላ ነው ። እያንዳንዱም እንደ ተሰጠው ቅድስናና አቅም መጠን

www.ethiopianorthodox.org

እንዲመላለስ ፈቅዷል ። መንፈሳዊ ጉዞአቸውንም ከአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ደርሰው እንዲገቱት ስላልፈቀደም "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ ።" ብሏቸዋል ። ማቴ 5:48 ።

4ኛ/ ጌታ በተራራው ስብከቱ እግዚአብሔር አብ የሰማዩ አባታችን እንደሆነ አሳይቶናል ። "የሰማዩ አባታችሁ" የሚለውን ቃልና ከዚሁ ጋር የሚዛመደውን አገላለጽ አስራ አንድ ጊዜ ያህል ተናግሮታል ። በተጨማሪም ሕዝቡ " አባታችን ሆይ ! በሰማይ የምትኖር ..." ብለው እንዲጸልዩ አስተምሯቸዋል ። ይህም በአባትና በልጅ መካከል ምን ያህል ፍቅርና መግባባት እንዳለ ያረጋግጥልናል ።

5ኛ/ "መንግሥት" እና "ሰማያት" የሚሉትን ቃላት አብዝቶ ደጋግሞአቸዋል ። ይህን በማድረጉም ለምድራዊ ሀብት ያላቸውን ጥልቅ ስሜት ለውጦ ከዓለም ምኞትና ኃላፊነት በላይ ጠልቀው በመሄድ ሰማያዊውን መንግሥት እንዲያዩ አድርጓቸዋል ።

6ኛ/ ጌታ በትምህርቱ የሰዎችን ፍላጎትና ስሜት አንዳችም ጊዜ ሲያቆላምጥ ወይም ሲያሞካሽ አልታየም ። ከሮማውያን ባርነት ነፃ ሊያወጣቸው እንደመጣም አልተናገራቸውም ። ይልቁንም ፤ " እጀ ጠባብህን እንዲወስድ ለሚወድ መጎናፀፊያህን ተውለት " እና " ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ ። " በማለት ተናገራቸው እንጂ ። ማቴ 5:39-41 ። ሊያጌጡ የሚገባቸውም በውጪያዊ ትዕቢት ሳይሆን በውሳጣዊ ንጽህና መሆን እንዳለበት ገልጦላቸዋል።

አቤቱ ጌታ ሆይ ! ድሆች ብፁዓን ናቸው ፤ ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ግራውን አዙርለት ፤ ወይም ደግሞ ክፉውን አትቃወሙ ብለህ ስትናገር በጽኑ ፍላጎት ወደ አንተ የሚቀርብ ማን ይሆን ? ምናልባት ጌታዬ፤ "እኔ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ሰዎች በሙሉ ፍላጎት እንዲቀርቡኝ ሳይሆን ቢሰቅሉኝ እንኳ ይህ ደንዳና ልባቸውን ለመለወጥ ነው ። በመሆኑም በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ፤ መንግሥት ሰማያት የእነርሱ ናትና። ብዩ ትምህርቴን በመጀመሪያ ተቃውሞ አይኖርብኝም ።" በማለት ይመልስልኝ ይሆናል ።

በዚህ ጽሑፋችን ከመጀመሪያው ስብከት የብፅዕና ደረጃ ተነስተን እንናገራለን።



# ምዕራፍ አንድ

## 1.በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው።

### ሀ. ብፁዓን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስብከቱን የጀመረው በዘጠኝ ብፁዓን በሚያስኙ ቃላት ነው ። ብፁዕ የሚለው ቃል ደስታና በረከት በአንድነት ተጣምረው የሚፈጥሩት ቃል ነው እንጂ ከሁለት አንዱን ያላካተተ አይደለም። አንዳንድ በቅርብ እየወጡ ያሉ ትርጓሜዎች የቃሉን ፍቺ እኩሌታውን ያጠፉታል ። በአንዳንድ የእንግሊዘኛ ጽሑፎች ላይ " የተባረከ " የሚለውን ትርጉም ሲይዝ በሌሎቹ ደግሞ "ደስተኛ" የሚለውን ትርጉም በተናጥል ይዞ ይገኛል። ትክክለኛው ግን ሁለቱን አጣምሮ የያዘ ነው ። ደስታ የበረከት ፍሬ ነው ፤ በበረከት መካከልም ደስታ አለ።

ጌታ በዚህ ስብከቱ ሰዎች ወደ ደስታና በረከት የሚደርሱበትን መንገድ ነው ለሕዝቡ እየገለጸላቸው ያለው ። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ልጆቹ የሆኑ ሁሉ ደስታን ያገኙ ዘንድ ይመኛል ። ስለዚህም ስብከቱን ደስ በሚያስኙ ቃላት እንዲህ በማለት ይጀምራል። "ልጆቹ ሆይ! የደስታና የበረከትን መዝጊያዎች እከፍትላችሁ ዘንድ ወደ እኔ ኑ !"

ቅዱስ ወንጌል ራሱ የምሥራች ቃል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ብሥራት ለእረኞቹ ያበሰረው መልአክ እንዲህ ነበር ያለው ። "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና ። " ሉቃ 2:10 ።

ሰዎች ሁሉ ደስታና በረከት ለሚሉት ቃላት ያላቸው አመለካከት አንድ ስላልሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ "ብፁዕ" የሚለውን ቃል ትክክለኛ ቃል ይገልጽላቸው ዘንድ በተራራ ላይ ተቀመጠ ። በወቅቱ ጽኑ ሥልጣን ፤ የተደላደለ ኑሮና ድንቁርናን በአንድነት የያዙት ሮማውያን የመንፈስ ድህነት ወደ ደስታ ይመራል በሚለው አባባል ለመስማማት ምንም ምክንያት ሊኖራቸው አይችልም ። በሮማውያን ተረግጠው ይገዙ የነበሩትም አይሁድ ይህ ድህነት ወደ በረከት የሚያደርስ ጥርጊያ ነው የሚለውን አሳብ ሊቀበሉት አይችሉም። ለአብርሃም የተሰጠው ቡራኬ ሰፊ ግዛት ፤ ብዙ ልጆችና ታላቅ ሀብት ያገኝ ዘንድ ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን ወይም የልጅ ልጆቹን የባረከው በድህነት ሳይሆን ማርና ወተት በምታፈስ ምድር ነው። ዘጸ 3:8 ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከገሪዛን ተራራ ሆኖ በረከትን ሰጠ ። ዘዳ 27:11። እንዲህም አለ " እግዚአብሔር በረከቱን በአንተ ላይ ፤ በጎተራህ በእጅህም ሥራ ሁሉ እንዲወርድ ያዝዛል ፤ አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህም ምድር ይባርክሃል ። " ዘዳ 28:8 ። በዚህኛው ስብከቱ ግን ጌታ

www.ethiopianorthodox.org

ያስተማረው ስለ መንፈሳዊው እንጂ ስለ ሥጋዊው በረከት አይደለም ። በብሉይ ኪዳን የተትረፈረፈው የሥጋ በረከት በአዲስ ኪዳን ለተገለጠው መንፈሳዊ በረከት ምሳሌና ጥላ ነው ። ይህም ሰዎች በረከትን በመንፈሳዊነቱ ለመረዳት መንፈሳዊ ብስለት እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክተናል ።

ከእነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች አንዱና የመጀመሪያው የመንፈስ ድህነት ነው ።

### ሀ. የመንፈስ ድህነት

ቃሉ የአዳምንም ሆነ የሰይጣንን ስህተት ለማጥፋት የተወሰደውን ዘዴ ያዘለ ነው። ሰይጣን ታላቅ ለመሆን በመሻት " ራሴን ከሁሉ የበላይ አደርጋለሁ" አለ። ኢሳ 14:14። በተመሳሳይ ኃጢአት የመጀመሪያ ወላጆቻችንን "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ።" ዘፍ 3:5 በማለት አሳምኖ አሳታቸው። የመንፈስ ድህነታቸውን ካጡ በኋላም እግዚአብሔርን መምሰልና ገነትን ጭምር አጡ። በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ኃጢአታቸውን በማጥፋት ወደ ቀደመ ክብራቸው ይመልሳቸው ዘንድ መጣ ። እንዲህም አለ " በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ። "

እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ዝቅ በማድረግ የባሪያውን መልክ ይዞ ስለመጣ ትዕቢተኝነትን አይወድም ። ፊል 2:7 ። እንደዚህም ተብሏል "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ፤ ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል ። " ያዕ 4:6 ። ከዚህ በተጨማሪ በኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ ላይ እንዲህ ተብሎ ተጻፈ " እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር ፤ ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሁት ፤ መንፈሱም ወደ ተሰበረ ፤ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ ። " ኢሳ 66:2 ። ልበ አምላክ ዳዊትም "እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ማነው ? በላይ የሚኖር ፤ በሰማይና በምድር የተዋረዱትን የሚያይ ፤ ከአለቆች ጋር ከሕዝቡም አለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ ችግረኛን ከመሬት የሚያነሳ ... " ይላል ።

የመንፈስ ድህነት በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት ውስጥ በማያሻማ መልኩ ተገልጿል ። " የባሪያይቱን ትሕትና ተመልክቶአልና ... ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል ፤ ገዥዎችንም ከዙፋናቸው አዋርዷል ፤ ትሁታንንም ከፍ አድርጓል ። " ሉቃ 1:48-52 ። ከዚህ ሌላ ይኸው የመንፈስ ድህነት በዳዊት ሕይወትና በመዝሙራቱ ግልጽ በሆነ መልኩ ተዘግቦ እናገኛለን ። ዳዊት ስለ መንፈስ ድህነቱና እግዚአብሔርን ስለ መሻቱ እጅግ ብዙ ተናግሯል ። በተደጋጋሚም የእግዚአብሔርን ዕርዳታና ድል ማድረግ ጠይቋል ። ወደ አምላኩ ምን ብሎ እንደጮኸ አስተውል ። " እኔ



ችግረኛና ምስኪን ነኝ ፤ ወደ እኔ ፈጥነህ ና ! አቤቱ ጌታዬ ረዳቴ ታዳጊዬም አንተ ነህ፤ አቤቱ አትዘግይ ። " መዝ 69 ።

ታላቅ ንጉሥ ፤ የሕዝቡ የበላይ ፤ ነቢይና በእስራኤል ላይ ፈራጅ የነበረው ዳዊት እነዚህን ቃላት ተናገረ ። ይህ ድንቅ ነገር ነው! በፊቱ ታላላቅ ሰዎች ነቢያትና ልዑላን የሚንበረከኩለት ዳዊት ፤ በፊቱ ነገሥታት የሚርዱለት ዳዊት ይህን አለ ። ዳዊት በሰዎች ሁሉ ፊት ይህ ሞገስ ይኑረው እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ችግረኛና ምስኪን ነበር ። ስለዚህም በመዝሙሩ እንዲህ አለ ። " አቤቱ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል ፤ ችግረኛና ምስኪን ነኝና።" መዝ 85 ። ምንም እንኳ ዳዊት በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ሞገስን ያግኝ እንጂ ከነበረበት መንፈሳዊ ውጊያ አኳያ በእግዚአብሔር ፊት በመንፈስ ድሀ ምስኪንና መከረኛ እንደ ሆነ ቆጠረ ።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የተወደዱ ነገር ግን በመንፈስ ድህነታቸው ምሳሌ የሚሆኑ ብዙ ሰዎችን ይጠቁመናል ። ከእነዚህም መካከል አንዱ አቤል ነው ። ከጨካኙና በምድር ላይ የመጀመሪያው ነፍስ ገዳይ ከሆነው ከወንድሙ ከቃየን ጋር ሲነፃፀር አቤል በመንፈሱ ድሀ ነበር ። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ከአቤል ሞት በኋላ ለእርሱ በመቆሙ ገዳዮን በሰው ልጆች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በወረደው እርግማን እንዲመታ ፈርዶበታል ። ዘፍ 4:11 ። በተመሳሳይ መልኩ በወንድሙ በኤሳው ፊት ድሀ የነበረውን ያዕቆብን እግዚአብሔር ረድቶታል ። ኤሳው " ወንድሜ ያዕቆብን እገድለዋለሁ " በማለት ተናግሮ ነበር ። ዘፍ 27:41 ። እግዚአብሔር ግን ያዕቆብን ስለባረከው ከኤሳው አዳነው፤ ከልጅ ልጁም ተወልዶ ሥጋን ለበሰ።

እግዚአብሔር ወንድሞቹ ወደ ውኃ ጉድጓድ ከጣሉትና እንደ ባሪያ ከተሸጠው ከዮሴፍም ጋር ነበር ። ዮሴፍ በጲጥፋራ ሚስት ያለ ጥፋቱ ተወንጅሎ ነበር ። ምንም እንኳ ባያጠፋም ከመታሰር አልዳነም ። እግዚአብሔር ግን ወንድሞቹን ድል በመንሳት ስሙን እጅግ ከፍ ከፍ ስላደረገለት ለፈርዖን አባት በመንግሥቱም ውስጥ ሁለተኛ ሰው አደረገው ። ከአሥራ ሁለቱም ነገድ ሁለቱን ለእርሱ ሰጠው ። እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና " ስለ ድሆች መከራ ስለ ችግረኞችም ጩኸት እግዚአብሔር አሁን እነሳለሁ ይላል ። " መዝ 11:5 ።

አንተ በመንፈስ ድሀ ከሆንህ እግዚአብሔር ከጎንህ ይቆማል ፤ ይረዳህማል ። ነገር ግን አንተ በተቃራኒው ጨካኝና በአንተ ዘንድ ያሉትን ያለ ምንም ርኅራኄ የምትደበድብና የምታንገላታ ከሆንህ እግዚአብሔር አንተን በመቃወም ለተጠቁትና ለድሆቹ በረከትን ያድላል ። እግዚአብሔር ከድሀው ከአልዓዛር ጋር እንጂ ከባለጸጋው ከነዌ ጋር አልነበረም ። ስለዚህም አልዓዛር በሞተ ጊዜ መላእክት ነፍሱን ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዷት ። ጥቂት ቆይቶም ባለጸጋው ነዌ ሞተና ተቀበረ ። ከዚህ በኋላ ነዌ በሲዖል ከፉኛ ሲሠቃይ አልዓዛር ግን በምቾት ተቀመጠ ። ሉቃ 16:22-25 ።

www.ethiopianorthodox.org

ዳዊት ራሱም ቢሆን በከዳው በልጁ በአቢሴሎም የጭካኔ ሥራ ላይ በመንፈሱ ፍጹም ድሀ ነበር ። አቢሴሎም ሕዝቡን በአንድነት በማሳመጽ ነበር በአባቱ ላይ ጦርነት ያወጀው ። ምንም እንኳ ዳዊት ባዶ እግሩን ከአቤሴሎም ፊት ቢኮበልልም የማታ ማታ በእግዚአብሔር ርዳታ የጊራ ልጅ በሆነው በሳሚ ወቀሳ ድል ሊቀዳጅ በቅቷል ። እንዲሁ ንጉሥ ዳዊት በጦር አበጋዙ በኢዮአብ ፊት ድሀ ነበር ።

በተጨማሪ እግዚአብሔር አምላክ ከጠፋ በኋላ " ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም " በማለት ወደ አባቱ ቤት ከተመለሰው ልጅ ጋር ነበር ። በአንፃሩ ወደ ቤት ገብቶ የወንድሙ ደስታ ተካፋይ—ለመሆን ታላቅየው በኩራት ታጅሎ አሻፈረኝ አለ ። ይባስ ብሎም አባቱን በድፍረት ወቀሰው ። እንዲህ ያለው ምግባር መልካም አይደለም ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ልጅ ወደ አባቱ ቤት መመለስ የሚለው ነገር የለም። እግዚአብሔር ምስኪኑን ቀራጭ ሲረዳ ወደ ኩሩው ፈሪሳዊ ግን አልተመለከተም። "እግዚአብሔር ሆይ ! እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ።" በማለት በልቡ ቀራጩን ከጠላው ይልቅ የተጠላው ጻድቆ እንደተመለሰ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ። ሉቃ18:11 ፤ 14።

እግዚአብሔር ከእርሱ በስተ ቀኝ በመስቀል ላይ ከተሰቀለው ወንበዴም ጋር ነበር። ይህ ሰው በመስቀል ላይ ሳለ " በእኛስ ይህ እውነተኛ ፍርድ ነው" በማለት ነበር የተናገረው። በአንፃሩ ግን ሌላው ወንበዴ የሠራውን ኃጢአት ዘንግቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድፍረት መናገሩን ስለቀጠለ ሊጠፋ በቅቷል ።

ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር " ... ቡችሎችም እንኳ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ ።" ማቴ 15:27 ። በማለት በተሰበረ ልብ ከተናገረችው ከደሀይቱ ከነናዊት ሴት ጋር ነበር። ይህች ሴት ራሷን በማዋረዷ እግዚአብሔር በመላዋ እስራኤል ያላገኘውን እምነት ከእርሷ ዘንድ አገኘ ።

በእርግጥም ጌታ የመጣው ስለ ድሆች ነው ። " የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ፤ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፤ ለተማረኩትም ነፃነትን፤ ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል ። " ኢሳ 61:1። ስለ እነዚህ ስለ ድሆች ሲል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጣ። እርሱ ለግብዞች ወይም በኩራት ለሚታጀሉት ወይም ደግሞ ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማነፃፀር ቅን አድርገው ለሚያመጻድቁም አልመጣም። ስለሆነም እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረው በጣም ቅርብ ነውና በመንፈስ ድሆችና ትሁታን ሁኑ።

በአንድ ወቅት ሰይጣን ከጻድቃኑ ወገን የነበረውን አንድ ጻድቅ በከንቱ ትዕቢት ካሳመነው በኋላ ከእርሱ ጋር ውጊያ ሊከፍት ወደደ። ስለዚህም ወደዚያ ጻድቅ ሄደና " በጎቹ እነማን ናቸው ? ፍየሎቹስ ? " ሲል ጠየቀው ።



ያም ጻድቅ ሰው " እኔ የማውቀው ከፍየሎቹ አንዱ መሆኔን ነው ። በጎቹን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው ። " በማለት ይመልስለታል ። በዚህ ሰዓት ያ ሰይጣን የዚህን ጻድቅ ሰው ትህትና መሸከም ስላቃተው ተሸንፎ ተመለሰ ።

## ሐ. የድህነት መለኪያዎች

ከክርስትና አስቀድሞ ሰዎች ስለ ማንኛውም ነገር የሚገምቱበት የተለያየ የማስተዋል ደረጃ ነበራቸው ። ከእነዚህ ደረጃዎቻቸው መካከል ግን ድሀ የሆነውን ሰው ታላቅ ነው ብሎ መቀበል የቻለ አንድም ደረጃ አልነበረም። ክርስትና ሲመጣ ግን ይህን ግምት ለወጠው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሰዎች መካከል ቆሞ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው " በማለት ተናገረ ።

የመንፈስ ድህነት ከሥጋ ድህነት ጋር የተለየ እንደሆነ በጣም ግልጽ ነው። አንድ በሥጋው የደከመ የደኸየ የተጎሳቆለና የታመመ ሰው ይኸው ሳያንሰው በዚሁ በታከተ ሥጋው ኩሩ ቁጡና በትዕቢት የተሞላ ሊሆን ይችላል። በመንፈስ ድሀ የሆነ ግን በነፍሱም ድሀ ነው ። ይህም ማለት ይህ ሰው ትሁትና ገራገር ነው ማለት ነው ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንም እንኳ በማዕረጉ ከፍ ያለ ቢሆንም እርሱነቱ በትቢያና በአመድ ላይ እንዳለ ይቆጥራል። ራሱን ከሌሎች በላይ ከፍ አያደርግም ። ራሱን በሰዎች ዘንድ እንደተከበረ አድርጎም አይመለከትም ። ሰዎችም ካለው ከፍተኛ ማዕረግ የተነሳ እንዲያከብሩትና እንዲያገኑት አይጠይቃቸውም ።

የአባቶች ሁሉ አባት የሆነውን አብርሃምን እስቲ በምሳሌነት እንመልከት ። ይህ አባት በኖረበት ዘመን ታላቅ ሰው ነበረ ። ከኮሎደጎሞር ጋር በተደረገው ጦርነት በእርሱ ላይ የተባበሩትን አራት ነገሥታት ድል አድርጎ የሰዶምን ቅኝ ተገዥነት አጥፍቷል ። ከዚህ በኋላ የሰዶም ንጉሥና የሰላም ንጉሥ የተባለው መልከ ጻዴቅ ሊገናኙት ወጡ ። ዘፍ 14:17፤18 ። ይህን ሁሉ ያደረገ አብርሃም በቂርያትአርባቅ የነበረችውን ዋሻ ከኬጢያውያን ለሚስቱ ለሣራ መቀበሪያ ትሆን ዘንድ ሲገዛ በዚያ ሀገር ባሉት ሰዎች ሁሉ ፊት ዝቅ ብሎ ሰግዷል ። ዘፍ 23:12 ። እነርሱም " አንተ በእኛ መካከል ከእግዚአብሔር አለቃ ነህ ። " እያሉ ይጠሩት ነበር ። ከዚህ በተጨማሪ እነዚያ ሦስት እንግዶች በጎበኙት ጊዜ የተቀደሰ ማንነታቸውን ባያውቅም እንኳ ሊቀበላቸው ፈጥኖ በመውጣት በፊታቸው ሰግዷል ። ዘፍ 18:12 ። አብርሃም በዚያን ወቅት የመቶ ዓመት አዛውንት ነበር ። " ጌቶቼ ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና " በማለት እጅግ ትህትናን ተላብሶ ነበር እነዚህን ሦስት እንግዶቹን የተቀበለው ። በእርግጥም አብርሃም ትሁት ነበር። ከዚያ በኋላም በማዕረግ ከፍ እያለ ቢሄድም በመንፈሱ ድሀ ስለነበር አንዳችም ጊዜ ራሱን ከፍ አላደረገም። ነቢይና ንጉሥ የነበረው ዳዊትም በመዝሙሩ " እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ" መዝ 69 በማለት ተናግሯል ። ንጉሥ ዳዊት ዘውድ ጭኖ ፤ በዙፋን ላይ ተቀምጦ ፤ ያን ሁሉ ጦር እየመራና ሕዝቡ ሁሉ በፊቱ

www.ethiopianorthodox.org

እየሰገዱለት ሳለ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለአምላኩ የነበረውን ልቦና አለወጡበትም። በጌታው ፊት እያነባ “ ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ! ” ይል ነበር። መዝ 6 ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ ከመንፈስ ድህነት ”ጋር አያይዞ መንፈሳችን ትሁት እንጂ ትዕቢተኛ እንዳትሆን አሳስቧል ። እንዲህ ከሆነ ሥጋችን መንፈሳችንን በመከተል ሁለቱም አንድ ይሆናሉ ። መንፈሳችን በትዕቢትና በኩራት የተሞላች ከሆነ ሥጋችንም እንደ እርሷ ትሆናለች ። በእንጻሩ ነፍሳችን በላይ ያለውን የምትሻ ከሆነ ሥጋችንም ይህንኑ ትሻለች ። ኩራት የዕብሪተኛን ሰው ማንነት ይሸፍናል ። ኩራተኝነት በመልክ ፤ በቅርጽ፤ በእንቅስቃሴ ፤ በአቀማመጥና በአካሄድ በግልጽ ይታወቃል ። ከዚህ በተጨማሪ በአነጋገር አልፎ ተርፎም በዝምታም ይገለጣል ። እነዚህ ሁሉ ራስን የማግነንና ያለማመዛዘን ምልክቶች ናቸው ። “ አፍንጫው እስከ ሰማይ ይደርሳል ። ” የሚለው ተረትም ይህንኑ የሚያጎላ ነው ።

የመንፈስ ኩራት ያለ ጥርጥር የሥጋ ኩራትን ያመጣል ። በተቃራኒው የመንፈስ ድህነት ጨዋ ባሕርይን ያላብሳል ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በልቡ ትሁት ነው ። አስተያየቱ የርኅራኄ ፤ አረማመዱ የረጋ ፤ አቀማመጡ ትህትናውን የሚያጎላና ከአንደበቱ የሚወጣውም ቃል ጣፋጭ ነው ። ትህትናና ሰላም ከአንደበቱ ይቀዳሉ ። “ The Paradise of Monks ” በተባለው መጽሐፍ ውስጥ “ ድምፁ የሰከነ አረማመዱ የረጋ” ተብሎ እንደተገለጸው ማለት ነው ።

ማንኛውም የመንፈስ ድህነት በሥጋ ጉስቁልና ሊደገፍ ይገባዋል ። ማንኛውም የሥጋ ድህነት ግን ባለቤቱ በመንፈስ ጭምር ድሀ መሆኑን ሊያረጋግጥ አይችልም ። ሰው በመንፈስ ድሀ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን የብፅዕና ደረጃዎች ለመቃደል ምን ዓይነት ባሕርይ ሊኖረው ይገባል ? ይህ ሰው በውስጡ ራሱን ያዋረደ ፤ በእግዚአብሔር ፊት በጸጸት የተሞላ ፤ በሰዎች ሁሉ ፊትና በርኩሳን መናፍስት ፊት ጭምር ልቦናው የተሰበረ ሊሆን ይገባዋል ። ይህ የነጠረ ሰው ነው ።

### መ. ውሳጣዊ ድህነት

በውሳጣዊው ሕይወቱ ድሀ የሆነ ሰው የራሱ መብት እንዲጠበቅለት አይናገርም ። ትዕቢተኛም አይደለም ። ራሱን ለምንም የማይጠቅም አድርጎ ይቆጥራል ። እርሱነቱንም ደካማና ኃጢአተኛ አድርጎ ይመለከታል ። ሰዎች ስለ እርሱ ማንነት መልካም አስተያየቶችን ቢሰነዝሩለትም እንኳ እርሱ ውሳጣዊ ማንነቱን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ አይቀበላቸውም ። በእርሱ ላይ ያለው ጉድለት በዓይኖቹ ፊት ጉልህ ሆነው ይታዩታል ። እርሱን የሚያሞጋግሱ ቃላቶችንም ቢያደምጥ የማይገቡት አድርጎ ይቆጥራል ። ሰዎች በእርሱ ማንነት እንደተሞኙም አድርጎ ይመለከታል ። ምናልባት ራሱን ከሰዎች



አንፃር ሲመለከት በውጪ በኖራ ተለስኖ አምሮ እንደሚታይ መቃብር ይቆጥራል ። ማቴ 23 ። ውጪያዊ መልክ ብቻ !

አንድ ሰው በሚናገራቸው አንዳንድ የትህትና ቃላት ላይ ተመርኩዘን እገሌ በመንፈስ ድሀ ነው ልንል አንችልም ። እንዲህ ያሉ ቃላት እጅግ ይነገራሉ ። ሰዎችም አነዚህን ቃላት ሊናገሩ ይችላሉ ። ነገር ግን ቃላቱ የሰውየውን ትክክለኛ ውሳጣዊ ማንነት ሊገልጹ አይችሉም ።

እንበልና አንድ ሰው “ እኔ በኃጢአት የተሞላሁ ነኝ ” ቢላችሁ እናንተ መሳሳቱን ገልፃችሁ ብትወቅሱት ሊታገሳችሁ ስለማይሞክር ሊያውካችሁ ይችላል ። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንም እንኳ ድህነቱን በማስመሰል ሊያሳያችሁ ቢሞክርም በመንፈስ ድሀ አለመሆኑን ያለ ጥርጥር ታውቃላችሁ ። በመንፈስ ድሀ የሆነው ግን የትህትናን ቃላት ከውሳጣዊው እርሱነቱ አፍልቆ ይናገራል ። በትክክለኛነታቸው በማመን ሆን ብሎ ይናገራቸዋል እንጂ እንደ ዋዛ ፈዛዛ በቁልምጫ አያወጣቸውም ። እርሱ ደካማ ኃጢአተኛና ረብ የሌለው እንደሆነ ይናገራል ። ስለ እነዚህ ሁሉ ባሕርያቱ እርሱ እውነተኛ ነው ። ልቦናውም እንደ አንደበቱ ንጹህ ነው ። ሌሎች በእነዚህ ባሕርያቱ ቢጠሩት አይበሳጭም ።

አንተ ግን ብዙ ጊዜ ወድቀሃልና ወደፊትም ካለህ ድካም አኳያ ለመውደቅ የተጋለጥህ ነህና በመንፈስ ድሀ ብትባል ይሻልሃል። ሰይጣን በከፉና በሚያስቀይሙ ኃጢአቶች ሊያሸንፍህ ይችላል ። በእነዚህ ውስጥ ተዘፍቀህም ለረዥም ዓመታት ሳትወጣ ትቀራለህ። በመንፈስ ድሀ የሆነ ግን ባይወድቅም እንኳ ራሱን እንደተዋረደ አድርጎ ይቆጥራል ። ለራሱም እንዲህ ይላል ፤ “ ምናልባት ርኩሳን መናፍስት በእኔ ላይ ጦርነት ያላወጁት ከነመኖሬም ትዝ ስላላላቸው አሊያም መንፈሳዊ ተጋድሎዬን በመናቅ ድካሜ የእነርሱን ውጊያ ሊቋቋም እንደማይችል ስለተረዱ ይሆናል ። ”

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት መነኩሴ ብዙ መንፈሳዊ ተጋድሎዎችን ከርኩሳን መናፍስት ጋር ወደተጋደለው ወደ አባ ቢሾይ በመቅረብ ርኩሳን መናፍስት ከፈቱብኝ ስላለው ውጊያ አምርሮ ይነግረዋል ። በዚህ ጊዜ ይህን የሰማው ሰይጣን ለአባ ቢሾይ “ለመሆኑ ይህ አሁን የመጣው ወጣት ማነው ? እኛ ቃል ኪዳን መቀበሉን እንኳ አልሰማንም ። ያ መሆኑን ብናውቅ ኖሮ ገና በፊት አስቀድመን ውጊያ እናውጅበት ነበር ። ” አለው ።

በመንፈስ ድሀ የሆነው ግን “ አጋንንት በእኔ ላይ ጦርነት እንዳወጁብኝ አድርጌ የማስብ ከሆነ ራሴን አስታብያለሁ ። ስለዚህም የምወድቀው በራሴ ድክመት እንጂ በአጋንንት ውጊያ አይደለም ። ” ይላል ። ይህ በክፍል ፈተና የወደቀውን ተማሪ ይመስላል ።ኩራት ወደ እርሱ አይቀርብም ። መውደቁን አምኖ የሚቀበል በመንፈስ የተሰበረ ነው። ማንም አንተ አዋቂና ብልህ ነህ ቢለው አያምነውም ። መውደቁን አምኖ የሚቀበል በመንፈስ የተሰበረ ነው ። ስለዚህ አንተም ኃጢአትህን ባስብህ ቁጥር እንደዚህ ሰው ሁን። ባትወድቅም እንኳ እንደምታጠፋና እንደምትሳሳት

www.ethiopianorthodox.org

በማወቅ በመንፈስ ድሀ ሆነህ ቆይ ። መጽሐፍ " ትዕቢት ጥፋትን ፤ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል ። " ይላልና ። ምሳ 16:18 ።

ስለ ትዕቢትና ኩራት ጸጋ እግዚአብሔር ከሰዎች ይለያል ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ደግሞ በሰይጣን ፊት ደካማ ስለሚሆን በቀላሉ ይወድቃል ። ከወደቀበት የሚነሳውም ድካሙን ተገንዝቦ ዳግመኛ አለመታበዩን ሲረዳ ነው። ስለዚህም ሰው እንዳይወድቅ ይረዳዋልና የራሱን ድካም ማወቅና መረዳቱ ለእርሱ መልካም ነው ። በመንፈስ ድሀ መሆን ሰዎችን ከውድቀት ይከላከላል ። በመንፈስ ድሀ የሆነ በገዛ ጥንካሬው አይመካም ፤ አይተማመንምም ። ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር በድካሙ እንዲረዳው ይማጸናል ። በዚህ ጊዜ በመዝሙራት እንደተጻፈ "እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው ፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል ።" መዝ 33:18 ተብሎ እንደተጻፈው ርዳታው በአፋጣኝ ይደርስለታል ። ራሳቸውን በማዋረድ ለሚያምኑ ለእነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ጸጋ ያለማቋረጥ ያግዛቸዋል ። ስለሆነም ከብዙ የጦርነት ፍላፃዎች ያመልጣሉ ። በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው ራሱን በውስጡ ማዋረዱን ከሌሎች ጋር በሚፈጥረው ግንኙነት ይገልጣል።

## ሠ. ድህነት በሰዎች ፊት

በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው ድካሙ ስለሚሰማውና ኃጢአቱንም ስለሚገነዘብ ምግባሩ የታረመና ሰዎችንም በዚሁ ተመሳሳይ ምግባሩ የሚቀርብ ይሆናል ።

እርሱ ራሱን በሰዎች ፊት ከፍ ከፍ የሚያደርግና የሚያገን አይሆንም። ለራሱም "እኔ እንደዚህና እንደዚያ ያደረግሁ ሰው ነኝና ከእኔ እጅጉን በሚልቁ ሰዎች ፊት ራሴን አስታብዬና ከፍ ከፍ አደርግ ዘንድ እኔ ማነኝ?" ይላል። ስለዚህም ሁሉን ሰው እንደ እድሚያቸውና ጠባያቸው ሊሰጣቸው በሚገባው ክብር ሁሉ ያከብራል ። በዕድሜና በማዕረግ የሚያንሱት ቢሆኑም እንኳ ያከብራቸዋል ። ይህ ሰው ምንጊዜም ቢሆን የተናቀውንና ዝቅተኛውን ሥፍራ ይመርጣል ። እንዲህም የሚያደርገው ትዕዛዛትን ለመፈጸም ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያሉትን ተግባራት መፈጸም የመንፈስ እርካታን ስለሚሰጡትም ጭምር ነው ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘልቆ ሲገባም ከሚዜመው ጣዕመ ዜማ ጋር ራሱን እንዳዋሐደ ሆኖ አይሰማውም ። ይልቁንም ራሱን የተሰበሰቡትን ክርስቲያኖች መልክ እንደሚያጠፋ ጉድፍ አድርጎ ይቆጥራል ። ስለዚህም ከማንም ጋር ሲቀርብ እንደ ባለ ሥልጣን አያወራም ። ስለማንኛውም ነገርም ከበላዮቹ ጋር እኩል አይነጋገርም ።

በአጠቃላይ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ራሱን ከሁሉ የመጨረሻና የሁሉ አገልጋይ አድርጎ ይቆጥራል ። አንድ መንፈሳዊ አባት " በሄድክበት ቦታ ሁሉ በወንድሞችህ መካከል ታናሽ በመሆን አገልግላቸው ። " ብለዋል ። በመንፈስ



ድሀ የሆነ ሁሉ ማንንም አይገስጽም ፤ በማንም ላይ አይቆጣም ፤ ማንንም አያሳዝንም ። ነገር ግን ሁሉም እንዲባርኩትና እንዲጸልዩለት ይጠይቃል ። ይህ ዓይነቱ ሰው ማንንም አይከስም ፤ በማንም ላይም አይፈርድም። አንዳችንም ሰው አያዋርድም፤በማንኛውም ሰው ላይም አያፌዝም ። ምንጊዜም ያለማቋረጥ ቃለ እግዚአብሔርን ከፊቱ ያስቀድማል። በተለይም እንዲህ የሚለውን "ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት ።" ዮሐ 8:7 ። ሰው ልቦናው የተሰበረ ሲሆን ራሱን የማንም የበላይ አድርጎ አይቆጥርም ።

በአንጻሩ በቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአንደኛው ክፍለ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን እያገናዘበ ሕፃናትን እንዲያስተምር የተመደበ የአንድ ወጣት ሁኔታን እንመለከታለን ። ይህ ወጣት በኃይለኛነትና በድፍረት ተነሳስቶ ራሱን አለቃና የቤተ ሰዎቹ መሪ አድርጎ ይቆጥራል ። የቤተሰቡን ሥነ ሥርዓት ነክ ጉዳዮችና ሌሎች ድርጊቶቻቸውንም በበላይ ተቆጣጣሪነት ለመመልከት ይሞክራል ። አልፎ ተርፎም ከቤተሰቦቹ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ከአንዳንድ ሁኔታዎች በመነሳት ወላጆቹን ያለ አንዳች ትህትናና አክብሮት ሊገስጽና ሊቆጣ ይጀምራል ። ልክ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ትውውቅ ራሱን ከማዋረድ ይልቅ በትዕቢት ወደ ማጀል እንዲያደላ ያስተማረው ይመስል በትዕቢት ተነፍቶ ምናልባትም ከስድብ ጋር የወላጆቹን አመለካከት ወደ እግዚአብሔር ትዕዛዛት ሊመራ ይወዳል ። እንዲህ ያለውን ሰው ስለዚህ ምግባሩ ብትወቅሰው እውነትን ለማስጠበቅ ሲል እንዳደረገው ይናገራል ። በዚህ መልሱ በጣም ተደንቀህ ሳለህ በአዕምሮህ ውስጥ እነዚህ ጥያቄዎች እንዲፈጠሩ ትገደዳለህ ። "እውነትን ራስን ካለማዋረድ ጋር እንዴት ማስጠበቅ ይቻላል ? ይህን ማድረግስ ስለ ምን ጥላቻን አስከተለ ? " ።

በእርግጥ በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው እውነትን ከትህትና ጋር ማስጠበቅ ይችላል ። ከሁሉም በፊት ደግሞ ይህንን መብት ከሰዎች ከመጠየቁ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ከራሡ ይጠይቃል ። ለሰዎች ሊሰጥ የሚወደውን ማንኛውንም ዓይነት ምክር እርሱ ራሱ በሕይወቱ የሚከተላቸው መሆን አለበት ። ምናልባትም እውነትን ማስጠበቅ የሚችለው ሕይወቱ የእውነት ምስክር ሆና ስትገኝ ብቻ ነው ። ይህኔም እርሱ አንዳች የቁጣ ቃል በሰዎች ላይ ሳይሰነዝር ሕይወቱ ሌሎችን የምትገስጽ ትሆናለች ። በመንፈስ ድሀ እንደሆነ ይኖራል ማለት ነው ። ይህ ቁጣ አልባ ብቃቱ ሰዎችን ከጥፋት በማነጽ ረገድ አርአያ ይሆናል ።

እውነትን የሚያውቃትና የሚወዳት እርሷን ደግፈው ምስክርነት እንዲሰጡ ሌሎችን መሳደብ እንደሌለበት ጠንቅቆ ይረዳል ። በመንፈስ የደቀቀውም ሁል ጊዜ ተማሪ እንጂ አስተማሪ መሆንን አይመርጥም ። በጉባኤ መካከል ሲቀመጥም በህሊናው "ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን ።" ያዕ 1:19 የሚለውን ቃል ስለሚያሰላስል ለመናገር የመጨረሻው ሰው ይሆናል። ዝምታን መምረጡ መልካም ምግባርን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን በጉባኤው ላይ የሚነገረውን ለማድመጥ የልቦናው ፍላጎት

www.ethiopianorthodox.org

ስለሆነም ጭምር ነው። ስለዚህ ባሕርይው ጥያቄ ቢቀርብለትም "እናንተ ብፁዓን ናችሁ ፤ እኔ ማድመጥ ከማደምጠውም መጠቀምን እወዳለሁ" ይላል። በእርግጥም እንዲህ ያለው ሰው መልካም ምግባር ሌሎች ሲናገሩ ጣልቃ ገብቶ እንዳይናገር ያደርገዋል ።

እኔ ካልተናገርኩ በማለት ሌሎችን እንዳይናገሩ የሚያግድ ሰው ግን ሌሎችን ወደ ታች መመልከት ይጀምራል ። የእርሱ ንግግር ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ትክክለኛና የተመረጠ ንግግር እንደሆነ ይሰማዋል። እንዲህ ያለው ሰው ራሱን የሌሎችን ንግግር አራሚ አድርጎ ይሾማል። ስለሆነም ይህ ትክክል ነው፤ ያ ትክክል አይደለም ማለትን ይጀምራል። እንዲህ በማድረጉም የልቦናውን መዋረድና የአንደበቱን ንጽህና ያጣል።

ለመሆኑ የልቦና መዋረድና የአንደበት ንጽህና ለምን ይጠቅማል ?

አንዳንድ ክፉ አድራጊዎች ለክፉ ሥራቸው ይቅርታን የሚጠይቁት ከልባቸው ሳይሆን በአንደበታቸው ብቻ ነው። አንድ ክፉ አድራጊ "ለሠራሁት ስህተት ይቅርታ እጠይቃለሁ" ብሎ በሚናገርበት ጊዜ ይቅርታ ተቀባዩን ይህ አነጋገሩ አያረካውም። ስለዚህም ይቅር ባዩ ይህን አባባሉን አይቀበለውም ። ምክንያቱም እንዲህ ሲል ቃላቱን የሚያወጣው በማስተዋል ከልብ በትህትናና ከልብ በመነጨ ፍላጎት ስላልሆነ ነው ። ስለሆነም ይቅር የሚለው ሰው በዚህ አይረካም። ይህም በመሆኑ ይቅርታ ጠያቂው በፊቱ ዝቅ ቢልለትም እንኳ ይቅር ባዩ አይቀበለውም ። ዝቅ ማለቱ በሥጋው እንጂ በመንፈሱ አይደለምና። ተራ ሽር ጉዶች በመንፈስ ያይደሉ ማስመሰያዎች ናቸውና ተቀባይነት የላቸውም ። ተመልከት ! የመዝሙረኛው ጥዑም ቃል ምን እንደሚል! "ራሴን በትቢያ ላይ አስቀመጥሁ ። " መዝ 119 ።

ራሱን በትቢያ ላይ ያስቀመጠ ሰው እግዚአብሔር አብን በእውነትና በመንፈስ የሚያመልክ ሰው ነው ። ዮሐ 4:23 ። እንዲህ ያለው ሰው ሁሉም ሰው እንደዚህ ትሁት እንዲሆኑ ይመርጣል ። ትሕትና ሲባል ግን አንዳንዶች በመጥፎ እልከኝነት በዝቅተኛው ሥፍራ ለመቀመጥ የሚመርጡና ሌሎችንም በተመሳሳይ መልኩ የሚያስገድዱ ስላሉ እንደዚህ ዓይነቱ የመንፈስ ድህነት የሌለበት ትህትና- ትህትና አይባልም ። እነዚህ ሰዎች እነርሱን እንዲመስሉ ካስገደዷቸው ጋር ንትርክ መፍጠራቸው አይቀሬ ነው ። የኋላ ኋላም በዚህ ንትርካቸው አሸንፈው በዝቅተኛው ወንበር እንዲቀመጡ ያደርጓቸዋል ። እንዲህ ዓይነቱ ግትርነትና እልከኝነት ግን ከመንፈስ ድህነት ጋር ሕብረት የለውም ። ዝቅተኛ ሥፍራ ማለት በማዕረግ ዝቅተኛ ማለት እንጂ በቦታው አይደለም ። አንተ በማዕረግ ራስህን የሁሉ የበታች ካደረግህ ሁሉን ለመታዘዝ ፍሬ የምታፈራ ትሆናለህ ። ሌላው ግን ሌሎችን በመገፋፋት ቦታውን እንዲይዙ ስለሚያስገድድ አስተዋይነት የጎደለው ነው ። ለሌሎች ክብርና የበላይነትን በመስጠት እነርሱን ማስቀደም የአንተ ተግባር መሆን አለበት ። ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ስትነግራቸው እንቢ ቢሉህ እንኳ ደጋግመህ



ያንኑ እንዲያደርጉ ንገራቸው ። ከዚህ በኋላ ግን በዚሁ እንቀጥላለን ካሉ ከሕግጋቱና ከትዕዛዛቱ ጋር ምንም የሚያጣላህ ነገር እስከሌለ ድረስ አንተ ያን ቦታ ለሌሎች ተው ።

ለምሳሌ አንድ ሰው ሲጋራ እየጋበዘህ በክፉ ሥራው እንድትተባበረው ቢጠይቅህ ሙሉ ለሙሉ ትቃወመዋለህ ። ይህ እንቢ ባይነትህ ግን በመንፈስ ድህነትና ኀስቋላነት ላይ እልከኝነትን መፍጠር ነው ሊባል አይችልም ። የጋባዥህን አሳብ ትህትናን በመላበስ " ይቅርታ አድርግልኝ ፤ እኔ በጣም ሰነፍ ሰው ነኝ ፤ ከጀመርኩ ቶሎ ማቋረጥ አልችልም። ስለዚህም አንዴ ማጤስ ከጀመርኩ ሲጋራ ማጤስ ልወጣው የማልችለው ዓመል ይሆንብኝና ይቀራል ። እናም ባላጤስ ይሻለኛል።" ትለዋለህ። ከዚህ በተጨማሪ " ጤናዬም ሆነ ያለኝ ገቢ ሲጋራ ማጤስን አይቋቋምልኝም ። ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነቱ መጥፎ ልማድ መራቁ ለእኔ ይበጀኛል ። ሌላው ቀርቶ የሲጋራ ጢስ ሲሸተኝ እንኳ ይደክመኛል ። " በማለት ታስረዳዋለህ ። በዚህ ዓይነት መንገድ ሰውየውን ይቅርታ ትጠይቀዋለህ ፤ አሳቡን ትቃወማለህ ፤ ትቋቋመዋለህም ። ራስን ከማዋረድና ከትህትና ጋር ማለት ነው ።ከዚህ ሌላ ቀጠል አድርገህ " እመነኝና ሲጋራ ማጤስ የሚያስከትለውን ችግር ስለሰማሁ ማጤስ በጣም ያስፈራኛል ። " ትለዋለህ ። በዚህ ጊዜ " ድፈር እንጂ አትፍራ !" የሚል መልስ ከሰጠህ አንተ ማጤስን ከሚፈሩት ሰዎች መካከል አንዱ መሆንህን በግልጽ ንገረውና ሲጋራ ማጤስን እንደፈራህና እንደሸሸህ እንድትዘልቅ ይጸልይልህ ዘንድ ጠይቀው ። እንዲህ ከሆነ ተቃውሞህ ራስን ከማዋረድና በመንፈስ ድሀ ከመሆን ጋር በምንም መልኩ አይጋጭም። እነዚሁኑ ቃላቶችህን ለሌላ ተመሳሳይ የኃጢአት ሥራዎች ምላሽ አድርገህ መስጠት ትችላለህ። ኃጢአትንና ፈተናን አሻፈረኝ ለማለት የምትይዘው አቋም በጉስቁልናና በመንፈስ ድህነት ላይ መንቻካነትን እንደሚፈጥር ሊቆጠር አይገባውም ።

የመንፈስ ድህነት ማለት ማንኛውንም ኃጢአት ለመሥራት ራስን አሳልፎ መስጠት ማለት አይደለም ። በመንፈስ ድሀ የመሆን መልካም ምግባር ሊያዝ የሚገባው ከቅድስናና ከንጽህና ጋር ነው ። አንዲቱንና ታናሺን መልካም ምግባር ይዞ ሌሎቹን መቃወም ወይም መቃረን መጥፎ ልማድ ነው። መልካም ምግባራት እርስ በእርሳቸው ይደጋገፋሉ እንጂ አይቃወሙም ። ከሰዎች ጋር ሲደራደር በመንፈስ ድሀ የሆነው ሰው እርሱን ለመቃወም ከሚሰነዘሩበት አሳቦች ራሱን ለመከላከል አይሞክርም ። እርሱ ኃጢአተኛ መሆኑን ስለሚያውቅ ራሱን ለመደገፍ አይናገርም ። ራሱንም በሰዎች ፊት ነፃ ለማድረግ አይሞክርም ። ሕሊናው ከማንነቱ ውጪ የሆነ እርሱነቱን ያሳያቸው ዘንድ እንዲሞክር አይፈቅድለትም ። ስለዚህም እነርሱ ሲናገሩ እርሱ አንደበቱን ጠብቆ ያዳምጣቸዋል ። ጉዳዩን በልቦናው ሲያመላልስም እንዲህ ይላል " ኃጢአተኛ መሆኔን ነገሩኝን ? አዎን ኃጢአተኛ ነኝ ። አሁን በተነሳው ጉዳይ ላይ ኃጢአተኛ ባልሆንም እንኳ በሌላው የተያዝኩ ነኝ ። በእነዚህ

www.ethiopianorthodox.org

በሁለቱ መካከል ደግሞ የጎላ ልዩነት የለም ። የሁለቱም ውጤት ያው ነውና።" ይላል ።

አንዳንድ ጊዜ ይህ ሁኔታው ሌሎችን የሚያደነዝዝ አድርጎ ስለሚሰማው ራሱን ይከላከል ዘንድ ያስባል ። ለምሳሌ አንድ ሰው በሌላው ላይ በሚያየው አንድ ባሕርይ ሊናደድ ይችላል ። ይኸው ሰው ይህ የዚህ ሰውዬ ባህርይ እውነት መሆኑን ሲያረጋግጥ ደግሞ ከፊተኛው ይልቅ ይጨምራል ። ምናልባትም ለእርሱ ያለውን ፍቅር ሊያጣ ይችላል። በዚህ ጊዜ ሌላኛው ሰው ራሱን ነፃ ለማውጣት ሳይሆን የሰውዬውን ንዴት ለማብረድና ለእርሱ ያለውን ፍቅር እንዳያጣበት ሲል ሁሉን ነገር በግልጽ ይነግረዋል ። እንዲህ ያለው ድርጊት ከመንፈስ ድህነትና ከጉስቁልና ጋር አይጋጭም ።

በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው በእርሱ ዘንድ ያለውን ችሎታና ልምድ በተለይም እርሱን ከፍ ከፍ በሚያደርጉት ሰዎች ፊት አይናገርም ። እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት የእርሱ ብቻ ምሥጢር ነው ። ጌታችን የራስን መልካም ምግባር ስለመሸሸግ ጠቀሜታ በማቴ 6 ላይ አስተምሯል ። ያለ አንዳች መጠራጠር ቀደም ሲል በምድር ላይ ለማንም ያልተከናወነ ተአምር ለድንግል ማርያም ቢከናወንላትም አልተናገረችም ። ስለሆነም እርሷ የምስጢርና የበጎ ምግባር መዝገብ ናት ። " እናቱም ይህንን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር ። " ሉቃ 2:51 ።

በመንፈስ ድሀ የሆነ እርሱነቱን ከሌሎች ሁሉ በላይ ከፍ አድርጎ የሚያስቀምጠውን ንጽጽር አይፈጽምም ። ስለ ሌሎች ሰዎች ሲናገርም " ይህ ሰው ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነው ፤ ያ ደግሞ ከእኔ ይልቅ አዋቂ ነው ፤ ይሄኛው ከእኔ በሁሉም ነገር የተሻለ ነው ፤ ይህ ሰው ደግሞ ጥንቃቄውና ትክክለኛነቱ ከእኔ የበለጠ ነው ። " ይላል ። ሰዎች ምንም ዓይነት ስህተት ቢፈጽሙም በትህትና ያወያያቸዋል ። እርሱ አስቀድሞ የፈጸመውን የስህተት ሥራ ያውቃልና ። የጠላት ውጊያ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ይረዳዋል ።

በሰውና በራሱ ዘንድ በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ድሀ ነው ።

## ረ. ድህነት በእግዚአብሔር ፊት

ይህ ድሀ በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም ባዶነቱ እየተሰማው ነው ። እንዲህ ያለው ስሜቱ ከአንደበቱ በሚወጡትና የቀራጩን ጸሎት በሚመስሉት በተሰበሩ ቃላቶቹ ይገለጻል ። በጸሎቱ መካከል እንደ ፈሪሳዊው መታበይን አይሻም ። አጠቃላይ ጸሎቱን በተሰበረ ልብ ሆኖ ያቀርባል ።

ለምሳሌ " አቤቱ ጌታ ሆይ ! በፊትህ ቆሜ ከአንተ ጋር እነጋገር ዘንድ እኔ ማነኝ? በአንተ ፊት የሚቆሙት እኮ መላእክትና ሊቃነ መላእክት ናቸው ! አቤቱ ጌታዬ አንተ እንደ እኔ ያለውን ኃጢአተኛና ትቢያ ታደምጥ



ዘንድ ትሑት ነህ ። " በማለት ይጸልያል ። በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ይገባኛል ባይ አድርጎ አይቆምም ። በጸሎቱ ራሱን የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅና ወራሽ አድርጎ እንደሚያቀርበውም ሰው ይህ ይገባኛል ብሎ ለመናገር አይደፍርም ። ልቦናው የተሰበረለት " እኔ በኃጢአት ብዛት የተተበተብኩና እለት እለት ኃጢአትን እያደረግሁ በመጨረሻው ፍርድ የምጣል ሰው ምንም የይገባኛል መብት የለኝም ። " ይላል ።

ወንጌላዊው "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ... ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን ።" ይላል ። 1ኛ ዮሐ 3:9 ፤ 1ኛ ዮሐ 5:18 ።

በመንፈሱ ድሀ የሆነ ሰው ሰማያዊ ስጦታዎች ይታደሉት ዘንድ ደፍሮ የሚጠይቅበት ጠንካራ ልቦና ያለው ይመስላችኋልን ? ወይስ " ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ " 1ኛ ቆሮ 12:31 የሚለውን ቃል አይረዳው ይሆን ? ይደንቀኛል! ልቦናው የተሰበረ ሰው ተአምራትን ፤ ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን ፤ ምልክቶችንና አስገራሚ ነገሮችን አድራጊ እንዲሆን ይመኝ ይሆን ? በአዲስ ቋንቋስ ይናገራልን ? ሰዎችስ በስጦታዎች የታደለ ጻድቅ አድርገው እንዲመለከቱት ይገፋፋ ይሆን ? ስጦታ የሚታደለው ሊቀበለው ለሚችል ሰው ነው ። እንዲህ ያለው ሰው ደግሞ ስጦታዎች እንዲታደሉት አይጠይቅም ። ሳይጠይቅ የሚታደለው ከሆነ ደግሞ የሚሰጡት ስጦታዎች ሊሸከማቸው በሚችለው መንገድ ከትህትና ጋር ነው ። ስጦታዎች ይታደሉት ዘንድ የሚጠይቀው ግን ራሱን ባለ ዋጋ አድርጎ ስለሚቆጥር በቀላሉ በከንቱ ክብር ይወድቃል። ስለዚህ ከዚህ ክፉ ምግባር ራቅ ።

"መጠየቅ" ከሚለው ቃል ይልቅ "ይገባኛል" የሚለው ቃል እጅጉን ይከብዳል ። የሚጠይቅ የሌለው ወይም ድሀ ነው ። ስለዚህም ከእርሱ ይልቅ ባለጸጋ የሆነውን ይጠይቃል። ነገር ግን መብቴ ነው ብሎ ይገባኛል የሚለው የራሱ የሆነ ነገር ያለው ነው ። ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱ ሰው መልሶ እንዲሰጠው የሚሰጠውን ሰው በጎ ፈቃድ ሳይመለከት መብቴ ነው ማለትን ብቻ ያከናውናል ።

"ይገባኛል" የሚለው ቃል በባለ ዕዳው ሰውና በአበዳሪው በእግዚአብሔር መካከል ሊጠቀስ አይችልም ። ምክንያቱም መጠየቅ የሚገባው አበዳሪው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው ። ሁሉን ችላ በማለትም ባለ ዕዳው ዕዳውን ለመክፈል ገንዘብ እንደሌለው አውቆ በፍቅር የሚያልፈውም እርሱ እግዚአብሔር ነው ። ሉቃ 7:42 ።

በመንፈስ ድሀ የሆነው ሰው አሁን በንስሐ እንደታደሰ ወደፊትም ምንም ኃጢአት እንደማይሰራ ሆኖ ለመታየት አይሻም ፤ በየዕለቱ ኃጢአት እንሰራለንና ። "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን ፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ።" 1ኛ ዮሐ 1: 8። አንተ ከዳንህ ከታደስህ ከጸደቅህና

www.ethiopianorthodox.org

ከተባረክህ ስህተትንም የማትፈጽም ከሆንህ በእግዚአብሔር ፊት በቆምህ ጊዜ "እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን..." ማቴ 6:12 ። ብለህ እንዴት ልትጸልይ ትችላለህ ? ነገር ግን በተሰበረ መንፈስ ሆነህ " አንተ ለእኔ የዋልህልኝ ውለታና ቸርነት እስከ ዘለዓለም አልረሳም ። በእርግጥ ጌታዬ አንተ በሂሶጵ አንጻኝ ፤ እነጻማለሁ ። ያንን ብታደርግልኝም ቅሉ ድጋሚ ተመልሼ ራሴን አረክሰዋለሁ ። " ማለት ትችላለህ ።

በመንፈስ ድሀ የሆነ ሰው በራሱ በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ድሀ እንደሆነ ሁሉ በርኩሳን መናፍስት ፊትም ድሀ ነው ።

## ሰ. ድህነት በርኩሳን መናፍስት ፊት

በትዕቢታቸው ምክንያት የወደቁትን ርኩሳን መናፍስት በትዕቢት ልታሸንፋቸው አትችልም ። ራስን በማዋረድ ግን ታሸንፋቸዋለህ ። ቅዱሳኑ በዚህ መንገድ ተጠቅመው ርኩሳን መናፍስትን ድል አድርገዋቸዋል ።

ለምሳሌ አባ እንጦስ ርኩሳን መናፍስት ወደ እርሱ በተሰበሰቡ ጊዜ "እናንተ ኃያላን ስትሆኑ እንደ እኔ ካለው ደካማ ሰው ምን ትፈልጋላችሁ ? " በማለት ከጠየቃቸው በኋላ " እኔ በእናንተ ዘንድ በጣም ታናሽ ከሚባለው ጋር እንኳ ለመዋጋት እጅግ በጣም ደካማ ነኝ። " ብሏቸዋል ። ከዚህ በኋላ ግን ይህ ቅዱስ ሰው " አቤቱ ጌታዬ ሆይ ! እኔን ባለ ዋጋ አድርገው ከሚቆጥሩት ከእነዚህ ከርኩሳን መናፍስት እጅ አድነኝ ። " ብሎ ጮኸ ። በዚህ ጊዜ ይህን ጸሎቱንና ጩኸቱን የሰሙት እነዚያ ርኩሳን መናፍስት ከአጠገቡ እንደ ጉም በነው ጠፉ ።

በአንድ ወቅት ደግሞ ይኸው አባ እንጦስ የርኩሳን መናፍስት ወጥመድ በምድር ሁሉ ላይ ተጠምዶ ከተመለከተ በኋላ "አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ከእነዚህ ወጥመዶች ማን ሊያመልጥ ይችላል?" በማለት ጥያቄ ያቀርባል። በዚህ ጊዜ "ትሑት የሆነ ሁሉ ያመልጣል።" የሚል ድምፅ ከአርያም መጣለት።

እንዲህ ያለው ርኩሳን መናፍስትን የሚረቱበት የመንፈስ ድህነት በታላቁ ጻድቅ በአባ መቃርስ አባባል ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል ። በአንድ ወቅት ሰይጣን ወደዚህ አባት ቀረበና "አንተ ልታደርገው እኛ ግን ልንፈጽመው የማንችለው ምን ዓይነት ሥራ አለ? አንተ ትጾማለህ - እኛም ከምግብ እንታቀባለን ፤ ሌሊቱን ሙሉ ሳትተኛ ታድራለህ - እኛም አንተኛም፤በምድረ በዳና በበረሃ ትኖራለህ - እኛም በዚያ እንኖራለን። ያም ሆኖ ግን በአንድ ነገር ትበልጠናለህ ።" ይለዋል ። በዚህ ሰዓት ያ ጻድቅ መቃርስ ይህ የሚለው አንድ ነገር ምን እንደሆነ ሲጠይቀው ፤ "በትህትና ትበልጠናለህ ።" ብሎ መለሰለት ።



## ሸ. መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

ጌታችን ስለ መንፈስ ድህነት ወይም ጉስቁልና ብቻ በሚናገርበት ጊዜ ሰዎችን ይህ ንግግሩ ላያረካቸው ብሎም እንዲህ ያሉትን መመሪያዎች በሥራ እንዲተረጉሙ ላያሳምናቸው ይችል ይሆናል ። ስለዚህም እንዲህ ያሉትን መመሪያዎች ይቀበሉ ዘንድ ከፊት ለፊታቸው እየታየቻቸው የምታበረታቸው መንግሥቱን እንደሚያወርሳቸው ነገራቸው ። "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ።" በማለት ። ማቴ 5:3።

እዚህ ላይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአድማጮቹን ህሊና ከምድር ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎታል ። ትኩረታቸውን ለምድራዊው ግዛት ከመስጠት ይልቅ ለሰማያዊው መንግሥት እንዲሰጡና ያቺንም መንግሥት ለመውረስ የሚያበቁትን ለየት ያሉ መልካም ምግባራት ጠንቅቀው እንዲረዱ ብሎም ዋጋቸውን እንዲያገኙ አድርጓቸዋል ። በዚህም ጌታችን የሰዎች ህሊና ከዚህ ከምድራዊው ዓለም ወደ ሰማያዊው መንግሥቱ እንዲጓጓዝ አድርጎታል።

ሕዝቡ ሁሉ በዚህ ዓለም እንደ ነዳዩ እንደ አልዓዛር ( ሉቃ 16) በመንፈስ ድሀ ሆነው ኖረው በመጨረሻ ከሞቱ በኋላ በሰማያዊዋ መንግሥት ለዘላለም ቢኖሩ ይሻላቸዋል ። ከዚህ በተጨማሪ ጌታ " ... ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ ... ለእናንተ በሰማያት መዝገብ ሰብስቡ ። " በማለት ተናግሯቸዋል ። ማቴ 6: 19:20 ። እንደዚሁ " ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል ሥሩ ። " ዮሐ 6:27 ።

ስለሚያገኙትም ዋጋ አምላካችን ወደ መንግሥተ ሰማያት ነው የወሰዳቸው ። "መልካም ነገርን ሁሉ እንደ ግብዞች ለታይታ በሰዎች ፊት አታድርግ ። እውነት እላችኋለሁ እነርሱ ዋጋቸውን ተቀብለዋል ። " ማቴ 6:5። ይልቁንም መልካም ምግባርን በስውር አድርግ ። ይህን ካደረግህ በሰማያት ሆኖ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጽ ይከፍልሃል ። ስለዚህ በምድር ሳለህ በመንፈስ ድሀ ከሆንህ ዋጋህን እንደምታገኝ አረጋግጠሃል ማለት ነው ። የትኛውን ዋጋ ? ብትል ፤ " ሰማያዊዋን መንግሥት " ። ስለ መኖሪያው ቦታም አንተ በምድር እንግዳና መጻተኛ ከሆንህ መጠለያህ መንግሥተ ሰማያት ትሆናለች ማለት ነው ።

" የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለም ። " ሉቃ 9:58 ብሎ የተናገረውና ለአንተ መኖሪያ ሊያሰናዳ ወደ ሰማይ ያረገው ጌታ " በአባቴ ቤት ብዙ ማደሪያ አለ።" ብሏል ። ዮሐ 14:2 ። ስለዚህም ነው በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች ሆነው ለኖሩትና የተሻለውን ሰማያዊውን ዓለም

www.ethiopianorthodox.org

ለሚናፍቁት በዕ 11:13 እና 16 ላይ የተጻፈላቸው ። በዚህ የሚሆን ዘላለማዊ ከተማ የላቸውምና ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ የተነሳ ነው ፍላጎትህ በሰማያዊው ሀብት ላይ እንጂ በምድራዊው ላይ እንዳይመሠረት የወደደው ። ይህም ስለሆነ ነው ወንጌላዊው ዮሐንስ " ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ .... ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉና" ያለው ። 1ኛ ዮሐ 2:15 ፤ 19 ።

በመሆኑም ጌታ ገና የተራራው ስብከቱን ሲጀምር እርሱ ወደዚህች ምድር የመጣው በወቅቱ የነበሩት መሪዎቻቸው እንደሚያስቡት ምድራዊ መንግሥት ለመመሥረት ሳይሆን ሰማያዊ መንግሥት ለመመሥረት መሆኑን ሊያውጅላቸው ስለወደደ ትኩረታቸውን ሁሉ ወደ ሰማያዊ መንግሥቱ እንዲያደርጉ የመራቸው ። እርሱ የመጣው " መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም " ዮሐ 18: 36 ለማለትና ደቀ መዛሙርቱም "የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል ።" ያዕ 4:4 እንዲሁም "ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ።" 1ኛ ዮሐ 2:15 ብለው እንዲያስተምሩ ነው ።

በተራራው ስብከት ውስጥ "መንግሥተ ሰማያት" ፤ "ሰማያት" እና "የሰማዩ አባታችሁ" የሚሉት ቃላት በተደጋጋሚ ተጠቅሰው እናገኛለን ። እነዚህም የአዲስ ዓለም፤ የአዲስ መንግሥትና እጅግ ከፍ ብላ በክብር ያለች መንግሥት መግለጫዎች ናቸው ።

ግን ለምን ? " መዝገብህ ባለበት ልብህ በዚያ ይሆናልና ። " ማቴ 6: 21 ። ይህን ቃል ጌታ በዚሁ በተራራው ስብከቱ ውስጥ ነው የተናገረው ። ምክንያቱም የሰዎች ልቦና እዚሁ ምድር ላይ ካለው ነገር ሁሉ በላይ ከፍ ብሎ ምኞታቸውም ደስታቸውም ተስፋቸውም በሰማይ እንዲሆን ስለወደደ ነው ። እንዲህ ከሆነ ነው በመንፈስ ድሀ መሆንን ታግሰው መስቀሉን መሸከም የሚችሉት ። ተስፋው ሁሉ በምድር ላይ የተመሠረተና ክብርን የሚፈልግ ሰው መስቀሉን ሊሸከም አይችልም ። የተራራው ስብከትም ሙሉ ለሙሉ እንዲህ ያለውን ሰው ባለመሆን ላይ የሚያተኩር ሆኖ ነው የምናገኘው። ስብከቱ የሚያሳየን ግራ ጉንጩን ሲመቱት ቀኙን የሚያዞር ፤ አንድ ምዕራፍ እንዲሄድለት ግድ ሲለው ሁለት የሚሄድ ፤ እጀ ጠባቡን ሲወስዱበት መጎናጸፊያውን የሚተውና ለሚለምኑት ሁሉ የሚሰጥ ሰውን ነው ።

በአጠቃላይ በተራራው ስብከት ውስጥ ስለ ትዕግስትና ይቅር ባይነት የተሰጡት ትምህርቶች መስቀሉን ለመሸከምም ሆነ ሰዎች የመስቀሉን ነገር እንዲቀበሉት ለማድረግ ተግባራዊ መሰናዶዎች መሆናቸውን ነው ። ለምን እነዚህ አስፈለጉ ቢባልም እነዚህ ሁለቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመምራት ዋነኞቹ ተግባራት ስለሆኑ ነው ። ክብራችንስ ? ብንል መልሱ ፤ የአንተ ክብር ጌታንና የቀደሙትን ነቢያት ለመምሰል መስቀሉን ስትሸከምና በመታገስህ ብዛት የሚገኝ ነው የሚል ይሆናል ። ለዚህም ነው ስለ ሰማያዊው መንግሥቱ



ሲያስተምራቸው " ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ። " ያላቸው ። ማቴ 5:11 ።

አቤቱ ጌታ ሆይ ! ግን ብፅዕና ለምን እንዲህ ? ብንለው የሚሰጠን መልስ "ዋጋችሁ በሰማያት ነውና ደስ ይብላችሁ፤ ሐሴትም አድርጉ ። " የሚል ነው ። ማቴ 5:12 ።

በእርግጥ የተራራውን ስብከትና በውስጡ የተካተቱትን የክርስትና መመሪያዎች በሙሉ " መንግሥተ ሰማያት " በሚለው ቃል ብርሃንነት ካልተመለከቱት በስተቀር ማንም ሊረዳው አይችልም ። ቀድሞ በብሉይ ዘመን የነበሩት ሰዎች ስለ መንግሥት ሰማያት አንዳችም እውቀት አልነበራቸውም ። መምህራኑም " የአባታችን የዳዊት መንግሥት " እያሉ በምድር ያለች መንግሥትን በመመሥረት ላይ ያተኮረ ትምህርት እንጂ ስለ ሰማያዊ መንግሥት ማንም አልነገራቸውም ። ማር 11:10 ። በምድራዊው ንብረትና ብልጽግና ተጠምደው የነበሩትም እንኳ ይጨነቁ የነበሩት ስለሚበሉትና ስለሚጠጡት አሊያም ስለሚለብሱት ብቻ ነበር ። ማቴ 6:25 ። ስለ ሰማያዊዋ መንግሥት ማንም አያስብም ነበር።

ከዚህ አኳያ ይህች ሰማያዊ መንግሥት ከተደበቀ ሀብት ጋር ተመሳሳይነት አላት ማለት ነው ። ለዚህም ነው አስተማሪያችን ቅዱስ ማቴዎስ ጌታችን በምዕራፍ 13 ላይ ስለ መንግሥተ ሰማያት ደጋግሞ በምሳሌ መናገሩን ከጻፈልን በኋላ በአንደኛው ምሳሌ ውስጥ " ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረን መዝገብ ትመስላለች ፤ ሰውም አግኝቶ ...." ማቴ 13:44 በማለት የገለጸልን ። ታዲያ ያገኛት ሰው ምን አደረገ ? " ከደስታውም የተነሳ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።" ይለናል።

ጌታ ይህንን ያደምጡት ለነበሩት ሰዎች በሙሉ መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት ያላችሁን ሁሉ ሽጡ ፤ ያላችሁን ሁሉ ተዉ ፤ ሌላው ቢቀር ራሳችሁን ካዱ ፤ አልፎ ተርፎም ሞትን ያውም የመስቀል ሞትን በጸጋ ተቀበሉ እያለ ሲያስተምራቸው የነበረው። በማቴ 13 ውስጥ ስለ መንግሥተ ሰማያት በምሳሌ የተሰጠው ትምህርት ይህ ብቻ አይደለም- ሌሎችም አሉ ።

መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መካከል መልካም ዘር የዘራን ሰው ትመስላለች ። መንግስተ ሰማያት የሰናፍጭ ቅንጣትን ትመስላለች ። እርሾንና በባሕር መካከል የተጣለ መረብን ትመስላለች ። ይህም እንደ ማንኛውም ገበዝ ከዕቃ ቤቱ አዲሱንና አሮጌውን ሀብት አንደሚያወጣ ዓይነት ያለ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ በሌሎች ምዕራፎች ላይም ስለ መንግሥተ ሰማያት በርከት ያሉ ምሳሌዎች ተሰጥተዋል ። ዋናው ቁም ነገር ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡ ሁሉ አሳባቸውን ወደ ሰማያዊ መንግሥቱ እንዲያደርጉ መፈለጉ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የተራራው ስብከት ቅዱስ ማርቆስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ዜና ነው ብሎ በገለጸውና " ኢየሱስም የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ መጣ "ማር 1:14 ። የሚለው ቃል መቅድም ነው ። ልክ ጌታችን የመጣበትን ዓላማ ስለ መንግሥቱ ማስተማር እንደጀመረው ሁሉ የመጨረሻዋ ሰዓት ላይም ያ በስተቀኙ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ " ጌታ ሆይ ! በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ " ሉቃ 23:42 ብሎ ሲማጸነው እንሰማለን ።

ስለዚህች ስለ መንግሥቱ ሲሉም ደቀ መዛሙርቱ ሁሉን ትተው ተከትለውታል ። አንዳንዶቹ መረቦቻቸውንና የዓሣ ማስገር ሥራቸውን ሲተው ሌሎች ደግሞ ቀረጥ ሰብሳቢነታቸውን ትተዋል ። ሁሉም ደግሞ ወገኖቻቸውን ቤተሰቦቻቸውን ቤቶቻቸውንና ከተሞቻቸውን ትተዋል ። ቅዱስ ጴጥሮስ ታዲያ ይህን ሁሉ በአንድ ላይ አጠቃሎ እንዲህ ብሎት ነበር ። " እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ። " ሉቃ 18:28 ። ጌታም እንዲህ ሲል መልሶለታል ።" እውነት እላችኋለሁ ፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቤትን ወይም ወላጆችን ወይም ወንድሞችን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን የተወ በዚህ ዘመን ብዙ እጥፍ በሚመጣውም ዓለም የዘላለምን ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።" ሉቃ 18: 29-30። በዚህም ቃሉ ጌታ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣው ዘመንና ዘላለማዊ ሕይወት ለክርስትና እምነት እጅግ ጠቃሚ መሠረቶች እንደሆኑ አስተማረ ።



# ምዕራፍ ሁለት

## 1. የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና።

በአስተማሪያችን በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ውስጥ "እናንተ አሁን ፣ምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ ፤ ትስቃላችሁና ።" የሚል ቃል አለ ። ሉቃ 6:21 ።

በውኑ የክርስትና ሕይወት ሐዘንና ለቅቀን ነውን ? ደስታስ ከኃጢአት ተቆጥሮ ይሆንን ? አይደለም ። እንዲያውም በመጽሐፍ ቅዱስ ደስታ ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው። ገላ 5:22 ። ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ "ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ፤ ልባችሁም ደስ ይለዋል ። ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።" ዮሐ 16:22 በማለት ተናግሯቸዋል ። ቅዱስ ጳውሎስም ማለቂያና ማብቂያ ስለሌለው ደስታ እንዲህ ብሏል። " ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ ። " ፊል 4:4።

ስለሆነም ክርስትና የሰዎችን ትኩረት ወደ ደስታ ማለትም በእግዚአብሔር ወደሚገኝ ደስታ ይጠራል ማለት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ ሰዎችን ከኃዘናቸው በሚያረጋጋው በመንፈስ ቅዱስ ሊያረጋጋቸው ይጠራቸዋል ። ለመንፈሳዊ ደስታ የሚሆኑ ምሳሌዎች አሉ ። ይህ ደስታ ኃጢአትን ድል ከማድረግ ወይም ከንስሐ ሕይወት የሚገኝ ሊሆን ይችላል ። ከዚህ ሌላ " ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማያት ደስታ ይሆናል። " ሉቃ 15:7 ስለሚል ሰማያት በዚህ ደስታ ውስጥ ታላቅ ድርሻ እንዳላቸው እንገነዘባለን ። ማንም መንፈሳዊ የሆነ ሰው በኃጢአት ላይ በሚቀዳጀው ድል ደስታ ይሰማዋል ። እንዲሁ ደግሞ ሌሎች እንደ እርሱ ኃጢአትን ድል ሲነሱ ደስ ይለዋል ።

ሌላው መንፈሳዊ ደስታ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ስትስፋፋ ከማየት የሚመጣ ነው ። ይህ ደስታ የእግዚአብሔር ቃል ሲስፋፋ፤ ቤተ ክርስቲያን ስታድግና ሰላም በየሥፍራው ሲሰፍን ከማየት የሚመነጭ ደስታ ነው ። ሌላው የተቀደሰ ደስታ ምሳሌ ደግሞ መልካም ሥራንና ውጤቱን ከማየት የሚፈልቀው ነው። ለዚህ አብነት የሚሆነው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ። ይህ ፍቁረ እግዚእ ለተመረጠችው እመቤት "ከልጆችሽ በእውነት ከሚሄዱ አንዳንዶችን በእውነት ስላገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል።" 2ኛ ዮሐ 4 በማለት ገልጾላታል ። ይኸው ሐዋርያ ለሚወደው ውድ ባልንጀራው ለጋይዮስ" ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንዲከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ ። ወንድሞች መጥተው አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ እጅግ ደስ ብሎኛልና ።

www.ethiopianorthodox.org

ልጆቹ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም ። ” ብሎ ጽፎለታል ። 3ኛ ዮሐ ቁ. 2 እና 4 ።

እንዲህ ከመንፈስ ቅዱስ የሚመነጨውና በሰዎች ልቦና የሚፍለቀለቀው ደስታ ነው እውነተኛ ደስታ ። በዓለም ያለው ደስታ ግን ልክ እንደ ሐዘኑ የውሸት ነው ። ጌታችን በዚህች ምድር ሳለን እናለቅስ ዘንድ የጠየቀን እንባችን የተቀደሰ እንባ ሆኖ ወደ ሰማያዊው ደስታ የሚያስገባን በመሆኑ ለእኛው ጥቅም ሲል ነው ። ይህም አንድ የአባቶችን ምሳሌ እንድናስታውስ ያደርገናል ። “እንድታለቅስ ያደረገህ ሰው ያለቅስልሃል ፤ እንድትስቅ ያደረገህ ግን ይስቅብሃል ።” ስለዚህ ሐዋርያው እንደተናገረው በዚህች ምድር ሳለህ ጥቂት ጊዜ አዝነህ በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለም ደስተኛ ሆነህ መኖር ለአንተ ይሻልሃል። “እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ጸጸት የሌለበትን ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና ።” 2ኛ ቆሮ 7: 10 ።

የሕይወት ዘመኑን ሙሉ ለዘላለም ሕይወት ትኩረት ሳይሰጥና ኃጢአቱን ሳይተው በምድራዊ ተድላና ሳቅ የሚያሳልፍ ሰው ኋላ በእውነተኛው አምላክ የፍርድ ዙፋን ፊት ሲቆም ይህ የውሸትና ኃላፊ የሆነው ደስታ አይጠቅመውም። ስለዚህ እያነቡ መኖር ከኃጢአታቸው በንስሐ የተመለሱ ሰዎች ባህርይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ ባህርይ መሆኑን እንረዳለን ። እንዲያውም ማልቀስ የታላላቅ ቅዱሳን አባቶች ልዩ ባህርይ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ የምንጠቅሰውን የእነዚህን የቅዱሳን አባቶች የማንባት ታሪክ በሰፊው ዘግቦልን እናገኛለን። እነዚህ አባቶች በምድር ሳሉ ለጊዜው ማልቀሳቸው ለዘላለም እያለቀሱ ከመኖር እንደሚያድናቸው በሚገባ አምነዋል ። በመጨረሻዋ የፍርድ ቀን በምድር ሳሉ ያነቡ ሰዎችን ዕንባቸው ቀድማ በመሄድ በዙሪያቸው ይንቀለቀል የነበረውን የእሳት ነበልባል ታጠፉላቸዋለች። ምድራዊ ኃጢአትን ስላጧት የሚያነቡት ግን የሚጠብቃቸው አባብለው ሊገቱት የማይቻል እንባ ይሆናል ። መጽሐፍ ቅዱስ “በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል ።” ይላል። ማቴ 8:12። አዎን! በእርግጥም እግዚአብሔር እንደዚህ ያሉትን አያባብላቸውም ።

ታላቁ ቅዱስ መቃርስ በሞት አፋፍ ላይ ሳለ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ደስ የሚሉ ናቸው! መቃርስ እድሜው ዘጠና ደርሶ አረጀ ። ሞቱም ቀረበች ። መነኮሳቱም በመኝታው ዙሪያ ተሰብስበው በመቆም ነፍሱ ከስጋው የምትለይበትን ሰዓት ይጠባበቃሉ ። እርሱም ሊያሳዝናቸው ስለሚገባ ነገር ብዙ ከተናገራቸው በኋላ በመጨረሻ እንዲህ አላቸው ። “ወንድሞቼ ሆይ! ዛሬ መጽናናትን ወደማናገኝበት ቦታ ሄደን ከማንባታችን በፊት እዚሁ በምድር ሳለን እናንባ ።” አላቸው። በዚህ ጊዜ እርሱን ተከትለው መነኮሳቱ ሁሉ



አለቀሱ። ታላላቅ ሰዎች ተብለው በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱትና ብዙ በማንባታቸው ከሚታወቁት መካከል ቀደምቱና ዋነኛው ነቢዩ ዳዊት ነው ።

ንጉሥ ዳዊት ፈራጅ ፤ የጦር መሪ ፤ የብዙ ቤተሰብ አባትና ደስታን በሚሰጡ ነገሮች ሁሉ የታጀበ ሰው ነበር ። ብዙ ስጦታዎችም ነበሩት ። ገጣሚ ዘማሪና የተዋጣለት ጦረኛ ነበር ። በአንድ ወቅት ግን ኃጢአት ሠራ ። ታዲያ የንስሓን እንባ ማንም ከማወቁ በፊት ያወቀ እርሱ ነበር ። ስለዚህም ነበር “ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፤ በእንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ ።” ያለው። መዝ 6:6 ። “አጥባለሁ” የሚለው ቃል የእንባውን ብዛት ሲገልጽልን “ሌሊቱን ሁሉ” የሚለው ደግሞ እለት እለት ከዋለበት ሥራው ሲመለስ ማልቀሱን ስለሚቀጥል እርሱ ስለ እርሱነቱ ያረጋገጠው የተዋበ ንጉሥ መሆኑን ሳይሆን በእንባው የሚታጠብ ሰው መሆኑን ይገልጽልናል። ይደንቀኛል! ለመሆኑ ያለቅስ የነበረው ሌሊት ሌሊት ብቻ ይሆን? አይደለም። ምክንያቱም “ እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ።” ብሏልና ። መዝ 41: 3 ። ከዚህ በተጨማሪ በመዝ 101: 9 ላይ “መጠጤንም ከእንባዬ ጋር ቀላቅያለሁና።” ይላል ።

ከእነዚህ የእንባ ዘለላዎች ከፊሉ ለንስሓ የጎረፉ ሲሆኑ ከፊሉ ደግሞ ለሰማያዊው መንግሥት የጎረፉ ናቸው ። በመዝ 118: 136 ላይ “ሕግህን አልጠበቅሁምና የውኃ ፈሳሽ ከዓይኖቼ ፈሰሰ ።” በማለት ተናግሯል ። የነቢዩ የኤርምያስም እንባ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው ። በተለይም ሐዘኑን የገለጸበት ኤር 9: 1 ። የዕዝራና የነህምያም ልቅሶ የዚሁ ተመሳሳይ ነው ። ዕዝ 10: 1፤ ነህ 1 ። በትንቢተ ኢዮኤል ላይ የምናገኘው የእነዚያ የቀሳውስቱ ሐዘንና ኢዮ 2: 17 ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ስለሚኖሩት ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስ ያለቀሰው ልቅሶም ተመሳሳይ ናቸው ። ፊል 3:18 ።

በዝምታቸው መካከል የሚወርደው የቅዱሳን እንባ በእግዚአብሔር ጆሮዎች የሚደመጥ ጩኸት ነው ። ለዚህ ነው ቅዱስ ዳዊት በመዝ 6 ላይ “ እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና ” ፤ “ እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ ” ፤ “ እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ ” ያለው ። የአንዳንዶቹ እንዲህ ያሉት ልቅሶዎቻቸው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ዘልቀው የታዩ መሆናቸው ደግሞ የሚደንቅ ነገር ነው ።

እግዚአብሔር የዳዊትን መጸጸት ከነቢዩ ከናታን ከሰማ በኋላ ይቅር አለው ። ዳዊት ያለቀሰው ግን ኃጢአቱ ይቅር እንዲባልለት ሳይሆን እንባው ቅርብ ስለነበረም ጭምር ነው። እንዴት ብንል እርሱ የወደደው ንስሓውን በማወጅ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ማሳየት ብቻ ነው ። ይህ እንባው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከእርሱ አልተለየም ። ከዚህ የእንባ ባሕር ውስጥ ያወጣው ሞቱ ነው ። ስለዚህም ወደ ሞት አፋፍ በተቃረበ ጊዜ “ ነፍሴ ሆይ ! ወደ እረፍትሽ ተመለሺ ፤ እግዚአብሔር መልካም አድርጎልሻልና ፤ ነፍሴን

www.ethiopianorthodox.org

ከሞት ዓይኔንም ከእንባ እግሬንም ከመሰናከል አድኖአልና ። ” ያለው ። መዝ 114: 7-8 ።

ሌላው እንዲሁ በማንባቱ የሚታወቀው ሰው ደግሞ ታላቁ ቅዱስ አርሳኒዮስ ነው ። ይህን ሰው ሊመስለው የሚችል ማን እንደሆነ ሳስበው እደነቃለሁ ። አርሳኒዮስ እድሜውን ሙሉ በብቸኝነት የኖረ የሰላምና የፀጥታ ሰው ነው ። ይህን ገዳማዊ ፓትርያርኩ ቴፊለስ ራሡን ዝቅ በማድረግ ወደ እርሱ እየሄደ ሊያየውና ከቃሉም በረከት ሊቀበል ብዙ ጊዜ የጠየቀው አባት ነው ። ይህ አባት ፀሐይ ጠልቃ ድጋሚ ንጋት ላይ እስክትወጣ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ በጸሎት የሚያሳልፍ አባት ነበር ። ታዲያ ለጌታው ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ የዓይኖቹ ሽፋሽፍት አንድ በአንድ እየተነቀሉ በመውደቅ እስኪያልቁ ድረስ ያነባ ነበር ። ቁጭ ብሎ በሚሠራበት ጊዜ ሁሉ እንባውን ይመጥለት ዘንድ በጉልበቶቹ ላይ ፎጣ ያነጥፍ ነበር ። ልቡናው ለአምላኩ ካለው ጥልቅ መንፈሳዊ ፍቅር የተነሳ ገና የጌታው ስም ሲጠራ ያለቅሳል ። ዘወትር በሰውነቱ ያለው ድካምና ዘግይቶ ወደ ጌታው መቅረቡን እያሰበ በእንባው ይታጠባል ። ከመሞቱ ከጥቂት ቀናት በፊት ታዲያ ያ ፓትርያርክ ቴፊለስ ስለ እርሱ “ አቤቱ አርሳኒዮስ ሆይ! እድሜህን ሁሉ እስከዚህች ሰዓት ድረስ ስላነባህ ብፁዕ ነህ ።” ብሎ መስክሮለታል ።

ቅዱስ አይሲዚሮስ የተባለው የመነኮሳት አበምኔትም እንዲሁ ብዙ በማልቀሱ ይታወቃል ። በእርሱ ሥር ሦስት ሺህ መነኮሳት ይተዳደሩ ነበር ። ይህን ታላቅ አባት ርኩሳን መናፍስት በጣም ይፈሩት ስለነበር በእርሱም ጎጆ ሆነ ከእርሱ ጎረቤት ሆነው በጸሎቱ ጥላ ሥር ተከልለው በሚኖሩ በመነኮሳት ተማሪዎቹ ጎጆ ደጃፍ አያልፉም ነበር ። ይህ አባት ባለ ራዕይ ከመሆኑ በተጨማሪ ርኩሳን መናፍስትን ከሰዎች በማስወጣቱ ይታወቃል ። ታዲያ በአንድ ወቅት ይህ አባት ሌሊት በሚጸልይበት ጊዜ እየተንፋረቀ ሲያለቅስ ከጎረቤቱ ያለው ተማሪው ያደምጠውና በማግስቱ ወደ እርሱ ቀርቦ “ አባቴ ሆይ! ስለ ምንድርን ነው ስታለቅስ ያደርከው ? ” ብሎ—ቢጠይቀው “ ስለ ኃጢአቴ ብዬ ነው ።” በማለት ይመልስለታል ። በዚህ ጊዜ ግራ የተጋባው ተማሪው የተሰማውን ሳይሸሽግ “አንተ አባቴ እንዴት የሚያስለቅስ ኃጢአት ሊኖርብህ ይችላል?” ሲል መልሶ ይጠይቀዋል። እርሱም “ልጄ ሆይ! እግዚአብሔር ኃጢአቶቼን ሁሉ ቢገልጣቸው እንባዬን በመጋራት ሦስት ወይም አራት ሰዎች እንኳ አብረውኝ ቢያለቅሱ እንባችን በቂ አይሆንም ።” በማለት መለሰለት ።

በእኛ ግን እንደዚህ አይደለም ። እኛ ዓለምን በመተዳደፋችን ሞልተናት ሳለን ባልጨት ድንጋይን የመጭመቅ ያህል ዓይኖቻችንን ብንጨምቃቸውም እንኳ ለንስሓ የምትሆን አንዲት ዘለላ እንባ ጠብ ማድረግ አልቻልንም ። ቅዱሳኑ ግን ስለ አንዲት በደላቸው ወይም ያለ አንዳች በደላቸው እድሜያቸውን ሙሉ ሲያለቅሱ ይኖራሉ ። እኛ ውኃን የመጠጣት ያህል ወደ ኃጢአት እንጠልቃለን ። ነገር ግን አንዳች ጊዜ እንኳ አናለቀስም።



እግዚአብሔር በእኛ ያልተወደደ ያህል ልቦናዎቻችን ስለ እርሱ ጠጣሮች ናቸው ። ከዚህ በማስከተል ኃጢአቱ ተሰምቶት ስላነባ አንድ ሰው ተጨማሪ ምሳሌ እናቀርባለን ።

ቅዱስ ጴፍኖቴዎስ ይባላል። ከታላቁ አባት ከቅዱስ መቃርዮስ ተማሪዎች አንዱ ነው። መቃርዮስ ከሞተ በኋላ በእግሩ የተተካው እርሱ ነበር። ይህ ቅዱስ ሰው ርኩሳን መናፍስትን ያወጣ ዘንድ እግዚአብሔር ጸጋውን ያበዛለት ጻድቅ ነው። ልክ እንደ አርሳኒዮስ ፓትርያርኩ ቴፊለስ የቃሉን በረከት ይቀበል ዘንድ ይጎበኘው ነበር። ታዲያ በአንድ ወቅት ይህ ታላቅ ጻድቅ ለተማሪዎቹ እንዲህ ይላቸዋል። “ልጆቼ ! ያኔ እንደ እናንተ ልጅ ሳለሁ በመንገድ ላይ ስሄድ አንድ በመንገድ ላይ የወደቀ ዱባ ተመለከትሁ። ዱባው ከተሸካሚዎቹ ከአንዱ እንደ ወደቀ እያወቅሁ ያን ዱባ በላሁት። ይህን ድርጊቴን ሳስታውሰው ሁል ጊዜ አለቅሳለሁ ።”

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ አንዳችም ኃጢአት ሳይኖርበት አልቅሷል። ያለቀሰው ስለ ሌሎች ኃጢአትና በዚሁ ኃጢአታቸው የሚደርስባቸውን ሞትና ሲዖል በማሰብ ነው ። ጌታችን በአልዓዛር መቃብር አካባቢ የተገኙት ሰዎችና እህቱ ማርታ በእግዚአብሔር መልክና አርአያ የተፈጠረው አልዓዛር ሞቶ በመቆየቱ ጠረኑ መለወጡንና ሌላውንም እያነሱ ሲያለቅሱለት ተመልክቶ አልቅሷል ። ዮሐ 11 ። የኃጢአትን ደመወዝ ሲመለከትና እንዴት ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶ ለቁጣው እንደሚያጋልጠው ሲመለከት ኢየሱስ ክርስቶስ አለቀሰ ።

በእኩለ ሌሊት በሚደርሰው ጸሎት ላይ ስለዚያች በእንባዋ የጌታን እግሮች ያጠበችው የዘማዊቷን ሴት ታሪክ የሚጠቅሰው ክፍል አሳዛኝ ነው ። ሉቃ 7:38 ። በዚህ የጸሎት አንቀጽ ውስጥ “ አቤቱ ጌታ ሆይ ! ለዚያች ለዘማዊቷ ሴት እንደ ሰጠሃት ያለ በእንባ ጎርፍ የሚያጥለቀልቁ ምንጮችን ለእኔም ፍጠርልኝ ። ” የሚል ሐረግ አለ ። እንዲህ ያለውን ጥያቄ እግዚአብሔርን መጠየቅ ያለብን አንድ የተለየ ነገር ሲያጋጥመን ወይም አሁን ታይቶ ለሚጠፋ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዷ ሌሊት መሆን አለበት ። ቅዱሳን በምድር ላይ በሕይወት ሳሉ እንባ ተለይቷቸው አያውቅም ። ከእነዚህ ቅዱሳን አንዱ “የምታነባውና ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ፊት የተሰበረችው ነፍስ እግዚአብሔር <የመዝሙራት ሁሉ መዝሙር> በሆነው የሚያነጋግራት ናት ።” ብሏል ። “አውከውኛልና ዓይኖችሽን ከፊቴ መልሺ” መኃ 6:5 ።

በየምሽቱ አንተ ራስህም ብትሆን በተሰበረ ልብ እግዚአብሔር ፊት ቆመህ “አቤቱ ጌታዬ ! ስለ ትዕቢቴ ፤ ስለ ግትርነቴ ፤ ስለ ንዴቴና ስለ ሥጋዊ ስሜቴ በእንባ ጎርፍ የሚያጥለቀልቁ ምንጮችን አድለኝ ። ከዚህ በተጨማሪ ለዓለም ስላለኝ ፍቅር ፤ በልቤ ስላደረው ጥላቻ ፤ በሌሎች ላይ በተንኮል የበላይ ለመሆን ስላለኝ ፍላጎትና ጠላትነት የማነባበትን በእንባ የተሞላ ምንጭ ስጠኝ ። አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ከአንደበቴ ስለሚወጡት የኃጢአት ቃላቶች ፤

www.ethiopianorthodox.org

በሰውነቱ ስለሚፈፀሙት ኃጢአቶችና በኅሊናዬ ስለማመላልሳቸው ተቆጥረው ስለማያልቁ ኃጢአቶችም የማነባበትን የእንባ ምንጭ ፍጠርልኝ ::" ልትለው ይገባል ::

ራስህን የምትመረምር ሰው ከሆንህ ታለቅስ ዘንድ ግድ የሚሉህን ብዙ ምክንያቶች ታገኛለህ። ሕይወትህ ንጹህና የጠራ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለህ አድርጎ ነፃ የሚያወጣህን የራስ ላይ ፍርድ ግን በማስተዋል መርምረው :: አለበለዚያ ታለቅስ ዘንድ የሚያበቃህ ምክንያት አይኖርም :: በየእለቱ ስለ ጉድለታችንና ስለ ኃጢአታችን እናለቅስ ዘንድ የእንባ ዘለላዎች ለእኛ ያስፈልጉናል። እግዚአብሔር አምላካችንም "በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ ::" ይለናል። ኢዮኤል 2:12 :: እንዲህ ያለው ንስሓ በኃጢአት ብዛት ከከበደ ልቦና ፈንቅሎ የሚወጣ እውነተኛ ንስሓ ነው ::

ጠቢቡ ሰሎሞን ሕይወትን ከነ ሙሉ ደስታዎቿ ከመረመራት በኋላ "ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል ፤ እርሱ የሰው ሁሉ ፍፃሜ ነውና ፤ ሕያውም የሆነ በልቡ ያኖረዋልና :: ከሳቅ ሐዘን ይሻላል፤ ከፊት ሐዘን የተነሳ ልብ ደስ ይሰኛልና ::" መክ 7:2-3 :: እነዚህን ቃላት የተናገረው አንድ ምስኪንና ድሀ ሰው ቢሆን ኖሮ በዚህ ሕይወት ውስጥ ስላለ ነው እንል ይሆናል :: ነገር ግን ይህን የተናገረው በዓይኖቹ የገቡትንና የተመኛቸውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት የሚችለው ታላቁ ባለጸጋ ንጉሥ ነው :: መክ 2:10 :: በዘመኑም ብር እንደ ድንጋይ የበዛለት ሰው ነው :: 1ኛ ነገ 10:27 :: ብዙ ወርቅና ዕንቁዎችም ነበሩት :: ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ሀብት ይልቅ ማልቀስ በእጅጉ የተሻለ መሆኑን ቆጠረ ::

### ሀ. ለማልቀስ የሚያነሳሱ ወይም ከማልቀስ የሚያግዱ ምክንያቶች።

1ኛ- ከሁሉ አስቀድሞ ለማልቀስ በቀላሉ የሚሰማው ልቦናና የረጋ መንፈስ ያስፈልጋሉ :: በቶሎ የሚሰማው ሰው በቀላሉ ስለሚነካ ወዲያውኑ ያለቅሳል :: ለዚህ ነው ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለማልቀስ ፈጣኖች ሆነው የምናገኛቸው :: ሆኖም ግን ወንድ ሲያለቅስ ልቅሶው ጥልቅና ጠንከር ያለ ነው። ልቅሶው ከውስጥ ታምቆ በቆየ ኃይል የሚገነፍል ስለሆነ የመቋቋም ኃይሉን ሲያንቀጠቅጠው ይታያል :: አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የድንጋይ ያህል ጠጣሮች ናቸው :: ሁሉን ነገር ይታገሳሉ :: እንዲህ ላሉት ሰዎች ማልቀስ ከባድ ነው :: ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንደኛው ቢያለቅስ ያ ያስለቀሰው ጉዳይ እጅግ በጣም ከባድ መሆን አለበት ::

መንፈሳዊው ሰው ግን ኃጢአት ከእግዚአብሔር የሚለየው አደገኛ ወንጀል መሆኑ ስለሚሰማው ያለቅሳል :: ልበ ደንዳና ለሆኑ ሰዎች ማልቀስ አስቸጋሪ ነው :: ጭካኔ ከሰው ጋር አብሮት የተፈጠረ ባሕርይው አይደለም :: እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በመልኩና በአርአያው ነው :: የእግዚአብሔር



መንፈስ ደግሞ የስከነ መንፈስ ነው :: ስለሆነም በሰዎች ላይ የጭካኔና የአረመኔነት ባሕርይ ከተመለከታችሁ እነዚህ ባሕርያቱ ከሌላ የተገኙ መሆናቸውን አስተውሉ :: እናንተም የማልቀስን ስጦታ ለመቀበል የምትወዱ ከሆናችሁ ከጭካኔና ከአረመኔነት ራቁ :: እንባና ጭካኔ እርስ በእርሳቸው አይስማሙም :: በጭራሽም አንድ አይሆኑም :: አንድ የሚሆኑት እሳትና ውኃ አንድ መሆን ሲችሉ ብቻ ነው :: ስለዚህ ከጭካኔና ከልጆችዋ ራቁ ::

2ኛ- እንባ እንዲደርቅ ከሚያደርጉት ሌሎች ምክንያቶች መካከል ደግሞ ሰዎች አንድ ክፉ ሥራ ለመሥራት በሚወስዱት የከበደ እርምጃ ላይ ከበስተጀርባ ሆኖ ማማትና መፍረድ ዋነኞቹ ናቸው :: ሌላው ደግሞ ሰዎችን መውቀስ ነው :: ይኼኛው በተለይ የሰዎችን ሁናቴ ስያጤኑ በአደባባይ የተደረገ እንደሆነ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው :: ሰዎችን ስህተተኛ የሚያደርግ ሰው ስለ ኃጢአቶቻቸው እንጂ ስለ ራሱ ኃጢአት አያስብም :: አንተ ስለ ራስህ ኃጢአት የምታስብ ከሆንህ ግን እንባ በዓይኖችህ ይሞላል :: በአንጻሩ የሌሎችን ኃጢአት በማሰብ እነርሱን ለመወንጀል የምታሰልስል ከሆነ የዓይኖችህ የእንባ ምንጮች ከመቅጽበት ይደርቃሉ ::

እግዚአብሔር እኛ ሌሎችን እንደምንወነጅለው እርሱ እኛን ቢወነጅለን ማንም አይድንም ነበር። ነቢዩ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ምን እያለ ይነጋገር እንደነበር ተመልከት! "ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለምና ከባሪያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ ::" መዝ 142:2 ::

"በአንድ የእምነት ድርጅት ጥላ ሥር ተሰባስበው በጸሎታቸው ጊዜ ጮክ ብለው ስለሚጸልዩ ሰዎች ምን አመለካከት አለህ? " ተብለህ ልትጠየቅ ትችል ይሆናል :: እኔ ብሆን ግን የምሰጠው መልስ " ከእንባ ጋር ጸሎትን የሚያቀርብ ሰው የሚያለቅሰው በእግዚአብሔር ፊት ስለሆነ በሰዎች ፊት አሰምቶ ማልቀስ የለበትም :: ለማልቀሱ ምስክር ይሆኑለት ዘንድ ሰዎች በዙሪያው እንዲሰባሰቡለት አያደርግም :: " የሚል ይሆናል :: በጸሎቱ መካከል የሚያነባው መንፈሳዊው ሰው ልቦናው የተሰበረ ሰው ነው :: በዚህች ወቅት ከአምላኩ ጋር ብቻ እንዲሆን ነው የሚፈልገው ፤ ልክ እንደ ሃና :: የነቢዩ የሳሙኤል እናት ሃና ልቦናዋ ሲያለቅስ እንባዎቿ ድምፅ ሳያሰሙ ፀጥ ባለ ኃዘን የሚወርዱና የሚያቃጥሉ የእንባ ዘለላዎች ነበሩ :: እንዲህ ያሉት እንባዎች በሚወርዱበት ጊዜ ስለመነባታቸው አዋጅ አያውጁም ፤ መለከትም አስነፉም።

አንዳንድ ጊዜ ግን ልክ ዳዊት ለልጁ ለአቤሴሎም ( 2ኛ ሳሙ 19:4::)፤ ወይም ደግሞ ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ሲገናኝ ( ዘፍ 45:2 ::) ያለቀሱት ዓይነት ይሆንና ያለውዴታ ድምጽ አውጥተው እንዲያለቅሱ ያደርጋቸዋል ::

አንዳንድ ሰው ወዳድ የሆኑ ሰዎች ደግሞ ስለ እነዚያ ሰዎች ኃጢአት ሲሉ ያለቅሳሉ። ይህም ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ከእነርሱ ጋር በማዘን እንዳለቀሰውና ዕዝራና ነህምያም የኢየሩሳሌም ሕዝብ በግዞት ሳሉ ስለፈፀሙት ኃጢአት ያለቀሱት ዓይነት ልቅሶ ማለት ነው። ዮሐንስ ሀጺር

www.ethiopianorthodox.org

(አጭሩ ዮሐንስ) በመባል የሚታወቀው ጻድቅ ደግሞ አንድ ሰው ኃጢአት ሲፈጽም ባየ ቁጥር ያለቅስ ነበር። ሰይጣን የሰው ልጆችን በኃጢአት ለመጣል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እያሰበም ዘወትር ያነባ ነበር። ሁልጊዜም "ወንድሜ ዛሬ በኃጢአት ወደቀ። ምናልባት እኔ ደግሞ ነገ እወድቅ ይሆናል። እርሱ ከወደቀ በኋላ በንስሓ ሊነሳ ይችላል ። እኔ ግን እዚያው ወድቄ ልቀር እችላለሁ።" ይል ነበር። እኛ ግን ስለ አንድ በኃጢአት ስለ ወደቀ ሰው ስንሰማ ያን ሰው ያለአግባብ ስንፈርድበትና ኃጢአቱን ስናበዛው ነው የምንገኘው። ግን ለምን?

በአቅራቢያህ በምትገኝ ከተማ አንድ ያመለጠ አንበሳ አንድ ሰው እንደገደለ ብትሰማ ያ ሰው ከዚያ አንበሳ ማምለጥ ባለመቻሉ ትፈርድበት ይሆን? "ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና።" 1ኛ ጴጥ 5:8። ወይስ በአንዲት ከተማ ውስጥ ተላላፊ የወረርሽኝ በሽታ ገብቶ በፍጥነት እየተዛመተ መሆኑን ብትሰማ ስለ ከተማዋ ነዋሪዎች ታለቅስላቸዋለህ ወይስ ጥፋተኞች አድርገህ ትፈርድባቸዋለህ? የማልቀስ ስጦታው አልታደለኝም ነው የምትል ወይስ እንባህን ገድበህ ታስቀረዋለህ? አዎን! እንባህን በጭካኔ በወንጀለኛና በአረመኔነት ነው የምትገድበው። አዎን! እንባህን በጭቅጭቅና በክርክር ፤ በልቅሶና በዋይታ ፤ በሌሎች ኃጢአት ላይ በማትኮርና የራስን ኃጢአት በመዘንጋት ግድብ ትገድበዋለህ ።

3ኛ- ቁጣና ብስጭትም የእንባን ምንጭ ያደርቃሉ። ብስጩና ግልፍተኛ ሰው ቁጡ እሳት የሚተፋና ተናዳጅም ጭምር ነው። በብስጭቱና በቁጣው ምክንያት ከእንባ ጋር የማይነጣጠለውን የልብ ገርነት ያጣዋል። አንድ ሰው ቀርቦህ "እገሌ እኮ ግልፍተኛ ነው። ከቁጣው የተነሳ ያለቅሳል።" ቢልህ ያ ሰው ምናልባት ያለቀሰው ስለተቀለደበትና ልክ ኤሳው በረከቱን ባጣ ጊዜ በእንባው መካከል "ወንድሜ ያዕቆብን እገድለዋለሁ።" ያለው ዓይነት ልቅሶ ነው ። ዘፍ 27:38-41 ። ይህ እኛ የምንለው መንፈሳዊ ልቅሶ አይደለም። ከወላጆቿ አንድ ነገር ሽታ ባለማግኘቷ አሊያም እንድታገኘው ማሳመን ተስኗት ወደ መኝታ ክፍሏ ሮጣ በመግባት እንደምታለቅሰው ልጃገረድ ዓይነት ልቅሶም ልናለቅስ አይገባም ።

ቁጣ የልቅሶን ጥበብ ያጠፋዋል። ሰው በጋለ ቁጣ መካከል ሲሆን የሌሎችን ኃጢአት እንጂ የራሱን አይገነዘብም ። ራሱን ተበዳይና ያለአግባብ የተገፋ ነገር ግን ትክክለኛ እንደ ሆነ አድርጎ ይቆጥራል ። ክብሩንም የተነጠቀ ይመስለዋል ። እነዚህ ሁሉ ስሜቶች ከእንባ ጋር አይስማሙም ። እነዚህ ሙሉ ለሙሉ እንባን ያደርቋታል እንጂ አያመነጯትም ።

4ኛ- ወደ ቅንጦት ደስታና ሕግ የመጣስ ሕይወት መዘፈቅም እንባን ያጠፋል ። የኃጢአትን ደስታ የተለማመደ ሰው ያለቅስ ዘንድ አይችልም ። በኃጢአት ጥም ታውሮአልና ። የሚያገኘው የደስታ ስሜትም ለተቀደሰ ኃዘን ዕድል ፈንታ አይሰጠውም ። የጠፋው ልጅ ገንዘቡን ከጓደኞቹ ጋር ሲያባክን



እንዳችም ኃዘን አልተሰማውም ። ወደ ልቡ ሲመለስ ግን ራሱን አዋረደ ዝቅም አደረገ ። ራሱን በትዕቢት ከፍ ከፍ ያደረገና በዓለማዊ ደስታ ፋታ ያጣ ሰው ግን እንዴት ሊያዝን ይችላል ? ነገር ግን እንደ ንጉሥ ሰሎሞን ሁሉም ነገር ከንቱ መሆኑንና ነፋስን እንደመከተል ያለ መሆኑን ቢረዳ ራሱን ያዋርድ ነበር ።

እንባ ከኃጢአት ጋር አይስማማም ። ነገር ግን ከኃጢአት በንስሐ ለመውጣት ይጠቅማል ። እንዲህ የሚሆነው ግን ኃጢአተኛው በራሱ ተሸንፎ ኃጢአትን መቋቋም የማይቻለው ሲሆን አይደለም ። ኃጢአትን ከሠራ በኋላ ያለቅሳል ። ከልቅሶውም ጋር ከዚያ ኃጢአት እንዲወጣ ያለቅሳል ። ከልቅሶውም ጋር ከዚያ ኃጢአት እንዲወጣ ይጠይቃል ። ከዚህ በኋላም ኃጢአትን ቢሠራ ድጋሚ ጸጋ እግዚአብሔር እስኪጎበኘውና እስኪያድነው ድረስ በእንባ ይለማመናል ።

5ኛ- ኩራት ትዕቢትና ራስን የማፍቀር ስሜትም እንባን ያደርቁታል። በተቀደሰ ኃዘንና በመንፈሳዊ እንባ የሚታደለው የተዋረደና የተሰበረ ልብ ያለው ሰው እንጂ ኩራተኛው አይደለም ። ትዕቢተኛ ሰው የራሱን ክብር ይወዳል ። ስለ ራሱ በማሰብና በዚህች ዓለም ታዋቂ ለመሆን በሚያደርገው ሩጫ ባተሌ ይሆናል ። ስለ ዘላለማዊነት የሚያስበው ግን ያለቅሳል ። ይህን በማድረጉም የዚህች ዓለም ክብርና ደስታ ከዓይኖቹ ፊት ይጠፋሉ ።

6ኛ- በማልቀሱም የሚደሰት ሰው እንባውን ያጣል ። አንድ ሰው እርሱ የእንባ ምንጭ መሆኑን በማመን ሲደሰት መኩራራት ይጀምራል ። ኩራትና እንባ ደግሞ እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ እንጂ አይስማሙም ። ሐሴትን ማድረግ ራሱ የእንባ ተቃራኒ ነው። ሌላው ቢቀር በራሱ ስለሚደሰት ብቻ እንባ ለዚህ ሰው አያስፈልገውም። ቅዱሳን እንዲህ ይላሉ። "በምታለቅስበት ጊዜ ደስታ የሚመጣብህ ከሆነ ስለ እንባህ ሳይሆን የሚያስለቅስህን ምክንያት አሰላስል። በዚህ ጊዜ ራስህን ማዋረድ ትጀምራለህ።"

ሰው እንባውን ከሌሎች ሰዎች አይደለም ከገዛ ራሱ መደበቅ ካለበት እነዚህ በአደባባይ ሰው በተሰበሰበበት ከፍ ብሎ በሚሰማ ድምፅ በጸሎታቸው መካከል ለማልቀስ የሚወዱትን ምን እንላቸዋለን ?! እነርሱ ግን ይህን ባሕርያቸውን መንፈሳዊ ምግባር እንደሆነ አድርገው ነው የሚቆጥሩት።

* መከራና ፈተና እንባን ያመነጫሉ ። ሰዎች መንፈሳቸው እንዲሰበር እግዚአብሔር መከራን እንዲቀበሉ ፈቅዷል ። በዚህም መድከሙ ስለሚሰማው ይህች ዓለም ለምንም እንደማትጠቅም ይረዳል ። ከዚህ በኋላ የጉዞ አቅጣጫውን ወደ እግዚአብሔር ያቀናል ። መከራ እንዲያለቅስ ሊያስገድደው ይችላል ። በአንፃሩ ከፈተና ርቆ ያለ ሰው ልበ ደንዳና ነው የሚሆነው ።

* ሞትን ማስታወስና መቃብርን መጎብኘት እንባን ያመጣል ። ቅዱሳን ሞታቸውን በማስታወስ በጣዕመ ዜማቸው "አቤቱ ጌታዬ! የእድሜዬን ማለቂያና የቀሩኝን ቀናት ቁጥር አሳውቀኝ ። ሕይወቴም ምን ያህል ብልጭ

www.ethiopianorthodox.org

ብላ የምትጠፋ መሆኗን እንዳውቅ እርዳኝ ::" ይላሉ :: ሰው ሞቱን ሲያስታውስ ያለፈው ዘመን ኩራቱና ለዓለም የነበረው ተገቢ ያልሆነ ፍላጎት ከእርሱ ይርቃሉ :: ይህኔም ንስሐ ገብቶ ራሱን ለዘላለም ሕይወት ያዘጋጃል ::

* የከፉ ኃጢአቶችንም ማስታወስ እንባን ያወርዳል :: እንዲህ ያለው ማስታወስ በሐዘንና በንስሐ ሊታጀብ ያስፈልገዋል :: ከዚህ ሌላ ህሊናው ዕረፍት ሲያጣና ሥራው ሲፀፅተው በኃጢአት መውደቁም ሊሰማው ይገባል:: እንዲህ ከሆነ " ጌታዬ ሆይ ! ለዘማዊቷ ሴት የቸርሃትን የእንባ ምንጮች ለእኔም አድለኝ ይላል :: "



# ምዕራፍ ሦስት

## 1.የዋሆች ብፁዓን ናቸው ፤ ምድርን ይወርሳሉና ::

### ሀ. የዋሆች እነማን ናቸው ?

የዋህ ሰው መንፈሱ የሰከነ ነው :: የዋሁ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸው ነበር "ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና::" ማቴ 11: 29 :: ከዚህ ሌላ ስለ አምላካችን እንዲህ ተብሏል:: "አይከራከርም አይጮህምም ፤ ድምፁን በአደባባይ የሚሰማ የለም ..... የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም ፤ የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም::" ማቴ 12:19-20 :: "አይጮህምም" የምትለው ቃል የየዋህነት ባሕርይውን ታኅላልናለች ::

በየዋህ ሰው ንግግር ውስጥ ትክክል ነኝ ባይነትና ጩኸት ፍፁም አይገኝም:: ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ድምፁን ከፍ አያደርግም አይቆጣም አያመናጭቅምም:: የዋህ ሰው ዝምተኛና መልካም ተፈጥሮ ያለው ነው:: ምንጊዜም ቢሆን የሚሻው በሰዎች የሚያስፈቅረውን ነገር ነው :: "ፍቅር አይበሳጭም" 1ኛ ቆሮ 13: 5 :: ስለዚህም የዋህ ሰው ምድርን ይወርሳል :: በምድር ሳለ በርጋታ የሰዎችን ፍቅር ይይዛል ፤ ኋላም መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል ::

እዚህ ላይ ግን በረጋውና በቀዘቀዘው መንፈስ መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ እወዳለሁ :: እንደ በግ ግልገል የቀዘቀዘው ሰው ጥልቅ ስሜት አይኖረውም :: ሰዎችን ሊያነቃቃም አይችልም :: መንፈሱ ለቁጣ የዘገየው ግን ደርሶ አይበሳጭም :: ይልቁንም በቀላሉ በሰዎች ዘንድ መደነቅን ይፈጥራል :: በሚጠየቅበትም ጊዜ በዚሁ በረጋው መንፈስ ስለሚመልስ የሰዎችን ህሊና ያሳርፋል :: የዋህ ሰው በሰዎች ዘንድ የሰከነ መንፈስ እንዲኖር ያረጋጋል :: ይህ ሰው ልበ ቅንም ነው :: ሁሉን ሰው ደስ እያሰኘ በመልካም ግንኙነት አብሮአቸው መኖርን ይመርጣል :: ማንም ምንም ቢፈጥር አይቆጣም :: አንድ ሰው በእርሱ ምክንያት ከተበሳጨም ሰላም አያገኝም :: የታላቁን ጻድቅ የአባ እንጦስን " ሁሉ ይባርክህ ፤ በረከትንም ያድልህ ! " የሚለውን ቃል መመሪያው ያደርጋል :: ስለሆነም ፍቅርና ሰላምን ከሁሉም ሰው ጋር ይጋራል ::

የየዋህ ሰው ርጋታ ውጫያዊ ብቻ ሳይሆን ውሳጣዊም ጭምር ነው :: እንደ አንዳንድ ሰዎች በውጪ ሲታይ የረጋ መንፈስ ያለው መስሎ ውስጡ በሸብርና በሁከት የተሞላ አይደለም :: እንዲህ ያሉት ሰዎች ቁጣቸውን ለማቆም የሚሞክሩት ስለ አንድ መንፈሳዊ ወይም ሌላ ምክንያት ሲሉ ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

እንዳንዴም የበላዮቻቸውን ለማክበር አሊያም ንዴት የሚያመጣውን መዘዝ ስለሚያውቁ ብቻ ቁጣቸውን ያምቃሉ ። የዋህ ሰው ግን ፍፁም የሆነ ርጋታ አለው ። ስሜቱ አስተያየቱና ፍላጎቱ ሁሉ የሰከኑ ናቸው ። የልብ ደስተኝነትን ይመርጣል ። በቀላሉ አይገነፍልም ፤ ክፋትንም አይይዝም ። በፊቱ ገጽታ ላይ የሚነበበው ፈገግታ ከእርሱ ጋር ለመወያየት ወይም ለመመካከር የሚሹ ሰዎችን ያቀርብለታል ። ሰዎች የተቋጠረ ግንባርም ሆነ በቁጣ የቀሉ ዓይኖችን በገጽታው ላይ አይመለከቱም ።

ስለዚህ በውስጡ ታዋኪ ሆኖ የረጋ መንፈስ ያለው ለማስመሰል የሚሞክረው ሰው እርሱ በእርግጥ የዋህ አይደለም ። ስለ እርሱ ማለት የምንችለው ቢኖር የዋህ ለመሆን ራሱን በማለማመድ ላይ ያለ መሆኑን ብቻ ነው ።

የዋህ ሰው ስለ ራሱ አይሟገትም ። የሚበቀልም አይደለም ። በአብዛኛው የሌሎችን የበላይነት በጸጋ ይቀበላል ። ስለ ገዛ መብቱ ብሎም ብዙዎችን ማጣት አይፈልግም ። እነዚህን መብቶች ከማስጠበቅ ይልቅ ከሰዎች ጋር ሰላም በመፍጠር ላይ የበለጠ ትኩረት ይሰጣል ። እነዚህን ሁለቱን በሚዛን ላይ ቢያስቀምጣቸውም ያለ ጥርጥር ከሰዎች ጋር በሰላም መኖሩ ሚዛን ይደፋል ። እንዲህ ያሉትን ሥራዎች የዋህ ሰው ከራሱ ህሊና ጋር እንኳ መወያየት ሳያስፈልገው ወዲያውኑ ይፈጽማቸዋል ። መጽሐፍ ቅዱስም "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል ፤ እናንተም ዝም ትላላችሁ ።" ነው የሚል ። ዘጸ 14:14 ። ከዚህ በተጨማሪ ሐዋርያው " ተወዳጆች ሆይ ፤ ራሳችሁ አትበቀሉ ፤ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው ፤ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና ።" ይለናል ። ሮሜ 12: 9 ። ስለዚህ የዋሁ ሰው አይበቀልም ። እግዚአብሔርም በቀልን ይበቀልልት ዘንድ አይጠይቅም ። እግዚአብሔር የሚከላከልለት ስለሚበቃው ምንም ዓይነት ጉዳት አይደርስበትም ። በተመሳሳይ መልኩ ማንም በእርሱ ምክንያት ወይም ስለ እርሱ ብሎ እንዲጎዳ አይፈልግም ።

የዋህ ሰው ከሰው ጋር ይግባባ ዘንድ ለእርሱ በጣም ቀላል ነው ። ከእርሱ ጋር በሚወያየውም ሰው ላይ ምንም ችግር አይፈጥርም ። እንዲህ በሚያደርግበት ጊዜም እነርሱ የበላይ እንዲሆኑና እንዲያተርፉ እንጂ እነርሱን ሊጠቀምባቸው አይሞክርም ። ስለሆነም ያለውን ለሌሎች ሲለቅ ያለ እንዳች ሀዘንና ቅሬታ ነው ። አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች የዋህ ሰው አይከብድም ይላሉ ። አንተም ብትሆን ራስህን " እንዳልከብድ የሚገፋፋኝ ምንድርን ነው?" ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። እንዲህ የምትል ከሆነ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል ። ስለሆነም አንተ ለሰዎች ስትል ካጣኸው የበለጠ እርሱ ለአንተ ይሰጥሃል። መጽሐፍም " የዋሆች ብፁዓን ናቸው ። " ነው የሚለው።

ከየዋህ ሰው ጋር በምትወያይ ወይም በምትነጋገርበት ጊዜ ምንም የማይከብድና ግልጽ ሆኖ ታገኘዋለህ። አይከራከርም ግልቃም አይገባም። በክርክርና በውይይት መካከልም ከአንተ ይልቅ የበላይ ሆኖ



መታየትን ስለማይወድ ውይይቱም ሆነ ክርክሩ የሃይማኖትን መሠረት የሚያናጋ እስካልሆነ ድረስ የወደድከውን ያህል እንድትናገር ዕድሉን ይሰጥሃል። ውይይቱ ሃይማኖት ነክ ጉዳዮችን የሚያካትት ከሆነም ጠንካራ አስተያየቱን ቀለል ባለና ግልጽ በሆነ መልኩ የሚሞግተውን ሰው ስሜት ሳይጎዳ ይሰጣል። ምናልባት ለዚያ ሰው " ምን አስተያየት አለህ? እንዲህና እንደዚያ ማለት ትክክል አይደለምን?" ይለዋል። አስተያየቱን እንደዚህ በጥያቄ መልኩ ካቀረበ በኋላ ያ ጠንካራ ትክክለኛና የተዋጣለት አስተያየቱ ራሱን እንዲገልጽ ያለ እንዳች ትዕቢትና ኩራት ይተወዋል። ስለ አጠቃላይ ጉዳዮች ከሆነ ግን ይኼኛውም ሆነ ያኛው አስተያየቱ ለእርሱ ምንም ለውጥ አያመጡም። የዚህች ከንቱ ዓለም ውጣ ውረድ በእርሱ ዘንድ ፋይዳ የለውም። በንግግርና በውይይቶችም አሸናፊ የመሆን ፍላጎት የለውም። ሌሎች የወደዱትን ይናገሩ ዘንድ ይፈቅድላቸዋል። የሚሹትንም እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸዋል።

ስለሆነም ከንስሓና ከዘላለም ሕይወት ጋር ግንኙነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ከሰዎች ጋር አይወያይም አይከራከርምም። በእርግጥም ምድራዊና ቁሳዊ ነገሮች ለእርሱ የሚፈይዱለት ጉዳይ የለም ። አንዳንድ ጊዜ በስብሰባ መካከል መኖሩ እንኳ እስኪያጠራጥር ድረስ ዝም ብሎ ይቀመጣል። ቀድሞውንስ እርሱን በሚመለከተው ጉዳይ ላይ እንዲናገር ካልተጠየቀ ወይም ካልተጋበዘ በስተቀር ለምን ራሱን ይገልጣል? አንዱ ተነስቶ እንዲናገር ቢጋብዘውም " ለእኔ የሌሎችን አስተያየት በማድመጥ መጠቀሙ ይሻለኛል ።" አሊያም ደግሞ "እገሌና እገሌ ከእኔ ይልቅ ብፁዓን ናቸው ።" ይላል። ከተናገረም ከእርሱ ቀደም ብለው የተናገሩትን በማወደስ ይናገርና "የእኔም አስተያየት እንደ እገሌና እገሌ ነው።" በማለት አሳቡን ያጠቃልላል። በእርግጥም ይህ ሰው ጨዋ ሰው ነው ። ዝም ሲል እንኳ ሰዎች ዝምታውንና ርጋታውን ይወዱለታል ። ሲነጋገርም በአነጋገሩ ስልትና ለዛ ይማረካሉ ።

ምናልባት አንዳንዶች "የየዋሆች ዝምታ በራሳቸው አሳብ ከመዋጥ የሚመጣ ይሆንን?" ብለው ይጠይቃሉ። መልሱ አይደለም ነው ። በራሱ አሳብ የተዋጠ ሰው ከማኅረሰቡ አባላት ጋር እንዴት መወያየት እንደሚችል እንኳ አያውቅም ። ራሱን ወዳድ ስለሆነም በዙሪያው ያለው ሰው ሁሉ ማንም ይሁን ማን ደስ አያሰኘውም ። የዋህ ሰው ግን ከሌሎች ጋር የሚያደርገው ውይይት የተዋጣለት ነው። ተወያዮቹን ይወዳቸዋል እነርሱም ይወዱታል። ስለዚህ ዝም ቢል እንኳ በራሱ አሳብ በመዋጥ ሳይሆን ስለ ትህትናና ስለ ፍቅር ነው ። ሌሎች እንዲናገሩም ሆነ እነርሱ የወደዱትን እንዲመርጡ ዕድል ፈንታውን ይሰጣቸዋል። ሮሜ 12: 10 ። ከሌሎች አንደበት በሚወጡት ቃላትም ለመጠቀም ሲል ዝም ይላል። በክርክር መካከል በሚፈጠር ጠብ ውስጥም ድርሻ የለውም። ሰላም ወዳድ ስለሆነም መናገር የሚወዱ ሁሉ ተናግረው ደስ እንዲሰኙ ያደርጋል ።

www.ethiopianorthodox.org

የዋህ ሰው ማንንም አያስጨንቅም ፤ ኃይልንም አይጠቀምም ። ሌሎችን በመጫን ያለ ውዴታቸው ለማሳመን አይጣጣርም ። የገዛ ምኞቱን ለማሳካትም ምንም ዓይነት የውትወታ ዘዴ አይጠቀምም ። ከእርሱ ምኞት ይልቅ የሌሎችን ምኞት ይጠብቃል ። ከዚህም የተነሳ ከእርሱ ጋር ሕብረት ያላቸው ሁሉ በእርሱ ባልንጀርነት ሰላም ያገኛሉ። ከእርሱ ጋር የሚነጋገር ሁሉ "እገሌ እኮ ጨዋ መንፈስ ያለው ሰው ነው ። ከእርሱ ጋር ስወያይ ሰላም አገኛለሁ ።" ይላል። አንተም እነዚህን ባሕርያት ከያዝህ የዋህነትን ይዘሃል ማለት ነው ። የዋህ ሰው የራሱ አሳብ ወይም አስተያየት አሸንፎ እንዲወጣ አይሟገትም። ይህ ማለት ግን ትክክለኛ መመሪያዎችን ያፋልሳል ማለት አይደለም ። በተመሳሳይ መልኩም እነርሱ እንዲረቱ ግብግብ አይፈጥርም ። ይህ ደግሞ ምናልባት የዋህነትን ከጥበበኝነት ጋር አጣምሮ መያዝን ይጠየቃል።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለዚህ የሚለው አለ። " ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማነው ? በመልካም አንዋዋሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ ።" ያዕ 3:18 ። አንዳንድ ብልጣ ብልጥ የሆኑ ሰዎች በቅርበትና በአድልዎ የተሞሉ አስተያየቶቻቸው ተቀባይነት እንዲያገኙ ግድ ሲሉ ይታያሉ። እንዲህ ያሉት ብልጣ ብልጦች ግራ መጋባትንና መለያየትን የሚፈጥሩ ናቸው ። እንደነዚህ ላሉት ሰዎች ደግሞ ሐዋርያው እንዲህ ይላል። "እንዲህ ያለው ጥበበኝነት ከሰማይ የወረደ አይደለም ።" የዋህነት የሌለበት ጥበበኝነት ነውና ። ስለሆነም "ጥበብ ከየዋህነት ጋር ይዋሐድ" አለ። "ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽህት ናት ። በኋላም ታራቂ ፤ ገር ፤ እሺ ባይ ፤ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት ፤ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት።" ያዕ 3:17 ። በመጨረሻም ይኸው ሐዋርያ ስለዚህች እሺ ባይ የዋህነትና ጥበብ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቶ ነው የሚያጠቃልለው ። " የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል ።" ያዕ 3:18 ።

በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች ጥበብን ሲታደሉም ሆነ ራሳቸውን ጥበበኞች አድርገው ሲቆጥሩ መመልከቱ እንግዳ ነገር ነው ። እነዚህ ሰዎች የየዋህነትን ሕይወትና የመንፈስ ርጋታን ስለሚያጡ አሳባቸውን ለማስጠበቅ ሲቆጡ ይስተዋላሉ። በእነርሱ አሳብ የማይስማማውን ሁሉ ስሜቱን ይጎዱበታል ፤ ያንቋሽሹትማል ። ምናልባት ኃይልን መጠቀም የሰዎችን ዓላማ ለማሳካት እንዲረዳ ቀላሉና አቋራጩ መንገድ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የዋህ ሰው ይህን ሊጠቀምበት አይችልም። እግዚአብሔር ከሰማይ የሚታደለውን ጥበብ ከሰጠው እርሱ ደግሞ በርጋታ ያለ ሁካታ በጨዋነት መንፈስ በመልካም ሁኔታ ለሕዝቡ ያድላል ። በማንኛውም አጋጣሚ ሕዝቡ ቢቃወሙትም አይበሳጭም ለቁጣም አይነሳሳም ። ሰዎች ለመቀበል ዘገምተኞችና ወደ ኋላ የሚሉ ቢሆኑም እንኳ የሚወደውን እስኪፈጽሙ ድረስ በመታገስ ይጠብቃቸዋል ።



ስለዚህ ነው የየዋህ ሰው ገመዱ ረዥም ነው የሚባለው። ይህም ታጋሽ መሆኑን ያመለክታል። የዋህ ያልሆነው ግን ምንም እንኳ አሳቡ የሚያስከትለው ውጤት ጥሩት ቢሆንም ጉዳዩ በቶሎ እንዲከናወንለት ይመኛል ። የዋሁ ሰው ግን የእርሱ አድማጭና እንደ ችሎታው መጠን ከእርሱ ለመማር ለሚወደው ዕድሉን ይሰጣል ። ዛሬ ባይሳካ ነገ ፤ ካልሆነም ከነገ በስቲያ ይሳካለታል ። ሁሉም ነገር የሚወሰነው እኛ ልንቆጣጠረው በማንችለው በጊዜ ላይ ነውና ።

ይቅር ባይነት የየዋህ ሰው አንዱ ባሕርይ ነው ። አንተ ጥፋተኛ ብታደርገውም እርሱ በተመሳሳይ መልኩ ሊመልስልህ ወይም እንዲህ ያለ ጠባይ ሊያሳይህ አይሻም ። ብትሰድበው አይገስጽህም ። ልዩና ገደብ ያለው ከዚያም አልፎ ሊሄድ የሚችል የረጋ መንፈስ አለው ። እንደ ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ አባባልም መመሪያዎቹን ባለመጣስ ራሱን ይጠብቃል ። ስለዚህም ሰይጣን ሊጎዳው አይችልም ። 1ኛ ዮሐ 3:9 ።

የዋህ ሰው የበላይ ሆኖ በሥልጣን አይናገርም ። ምንጊዜም ሥልጣኑ ከፍተኛና ሌሎችን የሚመራ ቢሆንም ያ ትዝ አይለውም ። ይረሳዋል ። የበታቾቹን የሚመራው ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆኖ ነው ። እነዚህ ሠራተኞችም እንዲህ ያለው አለቃቸው የልብ ወዳጃቸው እንደሆነ ይታወቃቸዋል ። እንደ ታላቅ ወንድማቸው ሆኖ ያለ አንዳች ጋጠ ወጥነት እንደሚያስተላልፍላቸውም ይሰማቸዋል ። ስለሆነም ትዕዛዛቱን ሁሉ ያለ ግዴታ በውዴታና በፍቅር ይቀበላሉ ።

የዋህ ሰው ስለ እርሱ ሰዎች ይከላከሉለታል እንጂ እርሱ አይከላከልም። የተወሰኑ ሰዎች ቢያጠቁት እንኳ እነዚህ ሰዎች "ከዚህ ከመልካም ሰው በስተቀር ሌላ የምታጠቁት ሰው የላችሁምን?" በማለት ይቃወሙለታል ። አልፎ ተርፎም ምናልባት የዚያ የአጥቂው ሕሊና የወሰደው እርምጃ በጭፍኑ በመጥፎ ሰው ላይ የተወሰደ አድርጎ ስለሚቆጥር ወዲያውኑ ሊበርድለት አይችልም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ያለ አንዳች ጥርጥር የገዛ ሕሊናው ራሱን ሊከላከል በማይችል ሰው ላይ እንደተነሳሳ ይወቅሰዋል ።

የዋህ ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚፈጽም ሰው ነው ። " እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን ሁሉ አትቃወሙ ።" ማቴ 5:39 ። ከዚህ ሰው ጋር የሚኖሩ ሰዎች ግን ይህ የዋህ ሰው ሲጠቃ የደረሰበትን ጉዳት ያለውን ሰላም ባለማጣት በትዕግስትና በርጋታ ሲቀበል ሲመለከቱ ይናደዱበት ይሆናል ። ምንም የከበደ መከራ ቢደርስበትም ያለ አንዳች ማጉረምረምና ስሞታ ሁሉን በትዕግስት በመቀበል ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል ።

የዋህ ሰው ታማኝ እንጂ ግድ የለሽ አይደለም ። ማንም ሰው በጥፋት ቦታ ላይ እንዲገኝ ቢጋብዘው ባለመስማማት ይቅርታ ይጠይቃል ። ጥያቄውን ያለ አንዳች ተግሳጽ በርጋታ እንደማይቀበለው ይገልጻል ። ሌሎች ሰዎች ተደናቅፎ ወደሚወድቅበት የኃጢአት ሥፍራ እንሂድ ሲሉት " እንደ እኔ ያለው ደካማ ሰው እንዲህ ያለው ቦታ ቢሄድ የበለጠ ይደክማል ። አብሬያችሁ

www.ethiopianorthodox.org

ልሄድ ባለመቻሌ ይቅርታ አድርጉልኝ ::" ይላቸዋል ። በዚህ መልኩ የማንንም ስሜት ሳይጎዳ ቅን አሳቡን ይገልጽላቸዋል ።

ልቦናው የተሰበረ የዋህ ሰው ማንኛውንም ነገር በበጎ ሕሊና ይቀበላል። ከፊቱ " ሁሉ ለበጎዎች ንጹሕ ነው " ቲቶ 1: 15 የሚለውን ቃል ያስቀድማል። ሌሎች ሊጎዳው ይችላል ወይም መናቁን ያመለክታል ብለው በእርሱ ላይ የሚሰነዝሩበትን ቃላት ሁሉ በቅን እምነት ያለ ምሬት ይቀበላቸዋል ። ከመካከላቸው አንዱ የሰነዘሩበት ቃላት የሚነኩት መሆናቸውን ሊገልጽለት ቢሞክርም ጆሮውን አይሰጠውም ። " ፍቅር በደልን አይቆጥርምና። " 1ኛ ቆሮ 13: 5 ። በተፈጥሮው የዋህ የሆነ ሰው ይህ የረጋ መንፈሱን ወደ ቁጠኝነት ለመለወጥ አይሞክርም ። ቢሞክርም እንኳ ስለማይሆንለት አያዋጣውም። እያንዳንዱ ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ የራሱ የሆነ የሚመቸው ባሕርይ አለው ። የርጋታ ባሕርይ ለርግብ ሲመቻት የድፍረት ባሕርይ ደግሞ ለአንበሳ ይስማማዋል ።አንበሳ የርግብን የስከነ ባሕርይ አስመስላለሁ ቢል አይሆንለትም ። ርግብም እንደ አንበሳ አስፈሪ ልሁን ብትል አይሳካላትም ። ይህ ምናልባት ከእግዚአብሔር ትዕዛዛት አንዱን ያስታውሰናል ። "ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ፤ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ ::" የሚለውን ። ዘዳ 22:5 ። ሁለቱም የሚለብሱት ለየራሳቸው የሚመቻቸውን ነው ። ይህ ለልብስ እንደተጠቀሰ ሁሉ ስለ ሰው ባሕርይም ሊጠቀስ ይችላል ።

## ለ. የዋህነትና መንፈሳዊ ቅንዓት

እዚህ ላይ አንድ የዋህነትን በተመለከተ የሚቀርብ ዐቢይ ጥያቄ አለ። "የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና " መዝ 68:9 የሚለውን የመዝሙራት ቃል የዋህ የሆነው ሰው ሊፈጽመው አይገባው ይሆንን ? በዚህስ የክፋት ጥርጊያን ከሚያመቻቹ ከመናፍቃን ጋር አንድነትን ፈጥሮ እምነትን ማድማት አለበትን? የሚል ።

መልሱ እንዲህ ነው። የዋህ ሰው በማንም ሳያፌዝና ማንንም ሳይሰድብ ፍጹም በሆነ ትሕትና ከመናፍቃንና ከተቃዋሚዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ በመንፈሳዊ ቅንዓት እምነቱን ማስከበር ይችላል ። ዓላማውን ሳይስትም ይናገራል ። ዓይነ ስውሩ ቅዱስ ዲዲሞስን እዚህ ላይ እንዳስታውሰው እገደዳለሁ ። ይህ ሰው ከፈላስፎችና ከመናፍቃን ጋር ብዙ ጊዜ ይከራከር ነበር ። መከራከሩ ግን ለማሳመን እንጂ ድል ለማድረግ አልነበረም ። በእርሱ ምክንያትነት ብዙዎች ፈላስፎች ክርስትናን ሲቀበሉ ብዙ መናፍቃንም ጥርጥራቸውን ትተው ተመልሰዋል ። ታዲያ ያሳምናቸው የነበረው ያለ አንዳች ጸያፍ ቃላት ያለ አንዲት ማንጓጠጥና ያለ ምንም የስድብ ናዳ ነበር ። እርሱ የሃይማኖት ጠላቶች የሆኑ ሃይማኖትን እስኪጠሉ ድረስ የሚሳደብ አልነበረም ። ስለዚህ ቅንዓታችን በፍቅርና ራስን በማዋረድ የተሞላ



ቅንዓት ይሁን ። "የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና" ከሚለው ሐረግ አጠገብ "በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።" የሚለውን እናስቀምጥ ። 1ኛ ቆሮ 16: 14 ። በተጨማሪም "ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሰጽ አላቋረጥሁም።" ሐዋ 20: 31 የሚለውንም የሐዋርያውን ቃል እናስተውል ።

እዚህ ላይ አንድ መንፈሳዊ ምክር ልሰጥ እወዳለሁ ። የክርስቲያን መልካም ምግባራት እርስ በእርሳቸው የተያያዙ እንጂ የተነጣጠሉ አይደሉም። አንዱ ከሌላው የተዋሐደ ነው ። መንፈሳዊው ቅንዓት የሚገለጥበት መልካም ምግባር ከክርስትናው ሕይወት የተለየ ወይም ብቻውን የሚቆም አይደለም። ይልቁንም ከየዋህነትና ከጥበበኝነት ጋር የተዋሐደ ነው። ከጨዋነትና ከፍቅር ጋርም እንደዚሁ። በዚህ መንገድ ነው የተሟላውን የክርስትና ሕይወት የምናገኘው። በእርግጥም መልካም ምግባራት እርስ በእርሳቸው አይቀዋወሙም ፤ ይደጋገፉሉ እንጂ ። በዚህም መንፈሳዊው ሰው ትክክለኛውን የፍጽምና ደረጃ ይቀዳጃል ።

## ሐ. ምን ዓይነት ምድርን ይወርሳሉ ?

1/ ምድሪቱ መዝሙረኛው በመዝሙሩ የገለፃት የህያዋን ምድር ናት። "የእግዚአብሔርን ቸርነት በህያዋን ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ ::" መዝ 26:13 ። ወይም ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ የተመለከታት " አዲሲቱ ምድር " ናት። ራእይ 21: 1 ። ወይም ደግሞ ቅዱሳኑ የሚኖሩባት " የቅዱሳን ግዛት " ናት ። ወይም በሌላ ትርጉሜ .....

2/ የዋህ ሰው የሚወርሳት ይህችኑ የምንኖርባትን ምድር ነው ። ከሰማያዊው ውርስ በተጨማሪ የዋህ ሰው በየዋህነቱ በምድር ባሉ ሰዎች ሁሉ ይወደዳል ። ስለሆነም ስለ የዋህ ሰው በሦስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ቢባል የበለጠ ይስማማዋል ።

3/ ይህችኛይቱንም አዲሲቷንም ምድር ይወርሳል ። ይህም ማለት ምድራዊቷንም ሰማያዊቷንም ምድር ይቀዳጃል ማለት ነው ። በዚህችኛይቱ ምድር የሚኖሩት ሰዎች በረከትና ከዚህችኛይቱ ተለይተው ወደ ህያዋን ምድር የገቡት ሰዎች አጋርነት ከእርሱ ጋር ይሆናሉና ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

## 1. ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ...

### ሀ. ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ የሚለው ሐረግ ትርጉም

ይህ ሐረግ ለጽድቅ ሥራ የሚጓጓ ሰው ሁናቴን የሚገልጽ ነው። በልቶ ጠጥቶ ከሚጎለምስ ይልቅ ከጽድቅ ጋር መራብን ይመርጣል። ከዚህ ሌላ ስለ እግዚአብሔር ስለ መንገዱ ስለ ትእዛዛቱ ስለ ዝርዝር መልካም ምግባራትና መንፈሳዊነት ሲል ይራባል ይጠማልም። ረዘም ባለው በመዝሙረኛው ጥዑመ ዜማ ውስጥ እንዲህ የሚል ስንኝ አለ። "ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው። ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ።" መዝ 118:103 ተመሳሳይ አገላለፆችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት ተደጋግመው እናገኛለን ። መድኃኒታችን ራሱ በተመሳሳይ መልኩ እርሱ የሕይወት ውኃ ምንጭ መሆኑንና ማንም ከእርሱ ቢጠጣ እንደማይጠማ ተናግሯል። ዮሐ. 4:14 የሕይወት ውኃ ምንጭ መሆኑንም እንደዚሁ ዮሐ. 6:3-5። እስራኤላውያንንም ሲገስጽ "እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል የተቀደዱትንም ጉድጓዶች ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል።" ኤር 2:13።

ከዚህ የሕይወት ምንጭ ውኃ እርሱም እግዚአብሔር ከሆነው የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው። እርሱን ይናፍቃሉ ለእርሱ ይታመናሉ በእርሱ አጋርነትና ከእርሱ ጋር በመነጋገራቸው ሐሴት ያደርጋሉ። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል። "አምላኬ አምላኬ ወደ አንተ—እገሰግሳለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች" መዝ 62:1 በተጨማሪም "ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች" መዝ 41:1። በእርግጥ እንዲህ ያለው ጥማት መንፈሳዊ ጥማት ነው። መዝሙር ስለ ምግብም የሚለው አለ "በአንተም ስም እጆቼን አነሳለሁ ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች።" መዝ 62:4-5

መንፈስን እንዲህ የሚያጠግበው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ሰው ከመንፈስና ከአፈር የተፈጠረ ሥጋ ለባሽ ነው። ሥጋ በምድራዊው መና ስትረካ ነፍስ ግን ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጡት ቃላት ሁሉ ትኖራለች። ማቴ 4:4 ፣ ዘዳ 8:3 ከመንፈሳዊው ምግብ የተመገበ ሁሉ ደርሶ በቶሎ ሥጋዊው ረሃብ አይሰማውም። በስሙነ ሕማማት ጾሙ ሥጋችንን የሚጎዳና ከባድ ቢሆንም ሲርበን አይታወቀንም። ይህም የሚሆነው ነፍሳችን ድረስ ጠልቀው የሚሰሙ የጌታችን የመከራው ዜማዎችና በሳምንቱ የሚነበበው ግብረ ሕማማት ምግብ ስለሚሆኑን ነው። የዚህን ስሜት አሳብና ትውስታ



ስለምንመገብ ነው። ስለዚህም ነፍሶቻችን እነዚህን የአጽዋማት በዓላት መጥተው ከመንፈሳዊው ምግብ ይጠግቡ ዘንድ ይራባሉ ፣ ይጠማሉም። ነፍሶቻችን በዚህ ጊዜ የሚሹት ምግብን ሳይሆን በተቃራኒው ለመጾም ነው የሚራቡትና የሚጠሙት።

ሥጋን ለማቆም የምንራበው ዳቦና የምንጠማው መጠጥ ፣ መልካም ምግባርን አሳብን ጥዑመ ዜማንና ንባብን በማጣት የታረዘችው ነፍሳችንን ለማጥገብ ስለ ጽድቅ ስንል የምንራበው መራብና የምንጠማው መጠማት በጣም ብዙ ልዩነቶች አላቸው።

ነፍሳችን ከዚህ በተጨማሪ የቅዱስ ቁርባን ተካፋይ ስለሆነች ይህንንም ትራባለች። ስለዚህ ጌታ ሲናገር "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ" ፣ "ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ" ብሏል። በተጨማሪም "ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል"፣ "እኔ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው፤ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው አስነሳዋለሁ።" ፣ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፣ እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ዮሐ 6:33-56። በማለት ተናግሯል። ይህንን ቅዱስ ምስጢር ለመካፈልና በእርሱ ለመጠንከር የሚራብ ሰው በእውነት ብፁዕ ነው። ልቦናውንም ሆነ ህሊናውን በመቀደስ በመንፈስ የሚያበረታውን ይህን ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ይወዳልና። ቁርባኑ ለእግዚአብሔር የታመነ እንዲሆንና ከመውደቅ እንዲጠነቀቅ ተስፋውን ያጠነክርለታል። በሕይወቱ ስለዚህ ታላቅ ምሥጢር ክብር ሲል በትክክለኛው መንገድ ይሄዳል። ስለዚህም ዘወትር ከእርሱ ለመቀበል ስለሚራብ "ያን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቼ ይሆን የምቀበለው" በማለት ራሱን ይጠይቃል።

### ለ. የሰማያዊው ፍቅር ሕይወት

ስለ ጽድቅ ተራብህና ተጠማህ ማለት እግዚአብሔርን ትናፍቃለህ ማለት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚበልጥ ጽድቅ የለምና።

ይህን በተመለከተ በመኃልየ ውስጥ የተጠቀሰችው ድንግል እንዲህ ትላለች። "እናንት የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ ፣ አምላችሃለሁ ፣ ውዴን ያገኛችሁት እንደሆነ እኔ ከፍቅር የተነሳ መታመሜን ንገሩት።" መኃ 5:8 ይህ የሰውየውን ልቦናና ህሊና በማለስለስ የሚሰርቅ ፍቅር እንዴት ያለ ጠንካራና ጥልቅ ፍቅር ቢሆን ነው በፍቅር እንድትታመም ያበቃት? ይህች ጸሎት ብታደርስም ከከንፈሯ ያይደለ ከልቧ የሚፈልቁትን ውስጣዊ ስሜቶቿን የሚገልጹ የፍቅር ቃላት ስለሚሆኑ ጸሎቷ በሥልጣን ወይም በማስገደድ አይሆንም። እንዲህ ዓይነት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ስለሚጠማ ጥማቱን በሚያደርሳቸው ጸሎታቱ ያረካል።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን በመናፈቅ ምኞት የተሞላ ስለሆነ ከመዝሙረኛው ዳዊት ጋር ሆኖ “ከእግዚአብሔር ጋር የምገናኘው መቼ ይሆን? ይላል። ይህ እግዚአብሔርን ለማግኘት እንዲህ ምኞት ያለው ሰው ለቤተ እግዚአብሔርም ተመሳሳይ ናፍቆት አለው። ስለዚህም ከነቢዩ ከዳዊት ጋር በመሆን እንዲህ ይላል። “የሠራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደ ምን የተወደዱ ናቸው ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች።” መዝ 83:1። ስለዚህም ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚሄደው እንዲሁ በልማድ ወይም መንፈሳዊ ሥራን ሠርቶ ለመመለስ ሳይሆን ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር አደባባዮች ለመግባት ስለምትናፍቅ ነው። ይህ ደግሞ መጢጊያ ለማግኘት የሚፈጸም መራብና መጠማት ነው። ስለሆነም ነቢዩ ጨምሮ እንዲህ አለ “ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ” መዝ 121:1 በተጨማሪም “በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው፤ በዓለምና ለዘላለምም ያመሰግኑሃል።” ፤ “ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች” አለ። መዝ 84:4-10።

አሁንም ይኸው ክቡር ዳዊት “እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ” በማለት ተናገረ። መዝ.26-4

ዳዊት እነዚህን ሁሉ ሲናገር ስትሰማ ምናልባት “ታላቁ ንጉሥ ሆይ አንተ በምቾትና በድሎት እየኖርህ ሳለህ ይህ የምትናፍቀውን ነገር ምን አስመኘህ? ስለምን ትራባለህ? ስለምንስ ትጠማለህ? እንዲህ ያለውንስ ህይወት ትናፍቅ ዘንድ ምን አነሳሳህ?” ትለው ይሆናል። እርሱም “እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ” መዝ 26:4 ብሎ ይመልስልሃል። ይህ ነቢይ ለእግዚአብሔር ካለው ጥልቅ ፍቅር አኳያ ይናፍቅ የነበረው የእግዚአብሔርን አደባባዮች ቃሎቹንና ከእርሱ ጋር መነጋገርን ብቻ ሳይሆን ይራብና ይጠማ የነበረው ራሱን እግዚአብሔርን ነበር ስለሆነም “አቤቱ ፊትህን እሻለሁና ፊትህን ከእኔ አትመልስ” እያለ ይጸልይ ነበር። ጌታን መውደድን እርሱን መራብንና መጠማትን የሚያስከትለው መንፈሳዊነት ነው ትክክለኛው መንፈሳዊነት።

ሁሉ በዚህ መንገድ መከናወን ካለበት ካላስገደድናቸው አብዝተን ካልወተወትናቸውና ይህን እንዲያደርጉ በተለያየ መንገድ ደጋግመን ለማሳመን የምንሞክራቸው ነገር ግን ወደ ቤቱ መገስገስ የማይወዱትን ስለ እነርሱ ምን እንላለን? ለመጸለይ ወይም መጸሐፍ ቅዱስን ለማንበብ መገደድን ስለሚሹና የሥጋ ፈቃዳቸውን ድል ሳይነሱና ሳያስገዙ ስለሚጸሙ ሰዎችስ ምን እንላለን?

መንፈሳውያን እግዚአብሔርን ይራቡታል ፤ ይጠሙታልም ፤ እርሱ የሕይወት ዛፍ ነውና። እውነተኛው የወይን ግንድ እርሱ ነው። ዮሐ 15:1 እርሱ የሕይወት ባለቤትም ነው። የምንጠማው የወይን ቅርንጫፍ ከወይኑ



ግንድ ጋር እንደተያያዘ ሁሉ ከእርሱ ጋር አንድነትን ለመፍጠር ነው። ይህ ቅርንጫፍ የወይኑ ፈሳሽ በውስጡ አልፎ ሕይወት የሚያድልበት ነው።

የእኛ መብል የእርሱን ፈቃድ ማድረግ ነው። ዮሐ 4:34። ስለዚህ እርሱ የእኛን ትእዛዝ ፈጻሚነት ተመልክቶ ደስ ሲሰኝ በዚህ ደስታው ልቦናችን ሐሴትን ታደርጋለች። ስለ ጽድቅ መራብና መጠማት እንዲህ እንዲህ እያለ የሚቀጥል ከሆነ አማኙ መንፈሳዊ እርካታ ላይ ሊደርስ አይችልም፤ ማለቂያ የለውምና። ከእግዚአብሔር መኖሩን እያራዘመ በሄደ ቁጥር ከእግዚአብሔር ጋር እስከ መጨረሻው እንዲኖር የሚያንጉትና መንፈሱን የሚያቀጣጥሉለት አዳዲስ መንፈሳዊ ደስታዎች ይፈጠሩለታል። ስለዚህም በቃላት ለመግለጽ ለሚያዳግቱ ተጨማሪ ደስታዎች መራብና መጠማቱን ይቀጥላል።

ስለ አንዳንድ ምድራዊ መብሎች አስመልክተው ሰዎች ሲናገሩ እንዲህ ያለው መብል የተፈለገ ያህል ቢበላ አይጠገብም ይላሉ። ከዚህ አኳያ መንፈሳዊው ምግብማ እንዴት ሊጠገብ ይችላል?

ቅዱስ ጳውሎስ ባለፈበት መንፈሳዊ ሩጫ ውስጥ የሚያረካውን ያህል ደስታ አግኝቶ ይሆን? አላገኘም። ይህ ሐዋርያ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጥቆ ሰው ሊናገር የማይገባውንና የማይነገረውን ቃል ከሰማ በኋላ ( 2ኛ ቆሮ 12:4 ) እንኳ እንዲህ ነበር ያለው። “ወንድሞች ሆይ! እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ። ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ። በኋላም ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።” ፊል 3:13 ይህ ቀጣይነት ያለው ጥረትና ከፊት ያለውን ለመያዝ የመዘርጋት ፍላጎት ያለጥርጥር ስለ ጽድቅ መራብና መጠማት ነው። እውነተኛው የመንፈሳዊ ሕይወት ሩጫ ከፍጽምና ለመድረስ ስለሆነ ቆም የሚሉበት ገደብ የለውም። ስለሆነም ሰማያዊዋን መንግሥት ለማግኘት ይህ የማያቋርጥ ጥረት ዘላቂነት ካለው ናፍቆት ጋር ያስፈልጋል ማለት ነው።

በምድር ሳለን ስለ ሰማያዊው መንግሥት የምናገኘው ጣዕም የቅምሻ ያህል ነው። ቅምሻ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን አይጠገብም። ይልቁንም ያን የቀመሰውን ነገር በብዛት እንዲያገኘው ቀማሹ በጉጉት ይራበዋል ይጠማዋልም። እንዲህ የሚያደርገውም ብቻውን ሳይሆን ሌሎችንም ወደ እርሱ ጠርቶ “እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ” መዝ 33:8 እያላቸው ነው። በእርግጥ በመንፈስ ለመርካት በሥጋ መድከም የግድ ነው።

## ሐ. መራብና መጠማት ከጸሎት አኳያ

ቅዱሳን አባቶቻችን ከእግዚአብሐር ጋር በነበራቸው ግንኙነት ፍጹም የማይረኩ ስለነበሩ ከሰዎች እየተለዩ ከእግዚአብሐር ጋር ብቻ መሆንን ይመርጡ ነበር። በዚህም ከብዙዎች ተለይተው ከአንድዩ ጋር ህብረት ይፈጥራሉ። ከጌታ ጋር ያላቸውን ህብረት ባጠነከሩ ቁጥር ደግሞ በጣም

www.ethiopianorthodox.org

ይጠሙታል። ስለዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው አንድነት ከእርሱ ጋር ብቻ መሆናቸውና መነጋገራቸው በየዕለቱ እየጨመረ ይሄዳል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ታላላቅ ሰዎች አሉ። አሌክሳንድራውያኑ ቅዱስ አርሴኒዎስና ቅዱስ መቃርዮስ። ቅዱስ አርሴኒዎስ ከሰዎች ጋር ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ይቋረጥብኛል ብሎ ስለሚያምን ሁል ጊዜ ዝምታን ይመርጥ ነበር። ስለሆነም ፀሐይ ጠልቃ እስከትወጣ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ በጸሎት ቆሞ ያድራል። ቅዱስ መቃርዮስ ደግሞ ህሊናውን ከእግዚአብሔርና ከመለኮታዊ ጉዳዮች በስተቀር ሌላ እንዳያስብ አድርጎ ስላለማመደው ከዚህ ውጪ አያስብም ነበር።

ሌሎችም ስለ መንፈሳዊው ፍቅር አርአያ የሚሆኑን ምሳሌዎችም አሉ። “ስምህ ጣፋጭ ነው። የቅዱሳንህም አንደበት ብፁዓን ናቸው” የሚል ቃል አለ። ይህ በቀዳሚ ሰንበት በቤተ መቅደስ የሚዜም ነው። ለዚህ ነው ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 119 ውስጥ “የተወደደው ስምህን ቀኑን ሙሉ እጠራለሁ” ያለው። ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ስም ደጋግመው ከመጥራት መንፈሳዊ ሐሴትን ያገኛሉ። የእግዚአብሔርን ስም መራብና መጠማት የጸሎት ሕግ ወይም መንፈሳዊ ሥርዓት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የልቦናችንን መጠማትና በውስጣችን የከበዱብንን ፍላጎቶች ስለሚያቃልልንም ጭምር ነው።

መራብና መጠማት ከፍቅር ጋር ሲሆን እንባችንን እንዲወርድ ያደርገዋል። ስለሆነም በጸሎታችን መካከል ልናለቅስ እንችላለን። እንዲህ ያለው የእንባ መፍሰስ ከኃይለኛ ናፍቆት የሚመነጭ ነው። ይህም የአባቶች ሁሉ አባት የሆነው ያዕቆብ ለአሥር ዓመታት ያህል ሲናፍቀው የነበረው ልጁ ዮሴፍን ሲያገኘው እንባውን እንድናስታውስ ያደርገናል። “ባየውም ጊዜ በአንገቱ ላይ ወደቀ ፤ አቅፎትም ረጅም ጊዜ አለቀሰ።” ዘፍ 46:29 ይህ እንባ የደስታና የናፍቆት እንባ ነው። እኒህ የእንባ ዘለላዎች ከቋንቋና ከቃላት በላይ ግልፅ በሆነ መንገድ የመራብና የመጠማትን ስሜት ይናገራሉ። አንዳንድ ጊዜ የልቦና ናፍቆት ሲያይል ሊሸከሙት ያዳግታል። በዚህ ጊዜ ሰዎች በዓይናቸው በማየት ብቻ ሊወጡት ስለማይችሉ ያለቅሳሉ። ይህ ዓይነቱ መራብና መጠማት በእንባ ካልሆነ በስተቀር ሊጠግቡት ወይም ሊረኩት አይቻልምና ነው።

ምናልባት የአብዛኞቹ ቅዱሳን እንባ የወረደው ያለ አንዳች መደናቀፍ እስከ ዘለዓለም ሐሴት ከሚያደርጉበትና ከእግዚአብሔር ጋር በተመሠረተው ግንኙነታቸው ውስጥ እርሱን ከመጠማት በተለዩበት ጊዜ ይሆናል።

ረሀብና ጥም ናፍቆትና ጉጉትን ሊገልጹት ይችላሉ። ስለ ናፍቆቱ ብሎ የሚጸልይ መጸለይ ስላለበት ከሚጸልየው ጋር አንድ አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ ናፍቆቱን ሊወጣ የሚጠመውና መጠም ስላለበት የሚጠመው ይለያያሉ። ለሁለቱም ምሳሌ የሚሆነንን ቀጥለን እንመለከታለን።

ከበዓለ አምሳ በፊት ባሉት አምሳ ቀናቶች ውስጥ መጾምም ሆነ መስገድ እንደሌለ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተደንግጓል። ሆኖም አንድ ናፍቆት ያለበት መንፈሳዊ ሰው በእነዚህ ቀናት ውስጥ ይህን ማድረግ እየፈለገ



ባይችል እነዚህ ቀናት ተፈጽመው ጾመ ሐዋርያት በሚጀመርበት ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማው ይሆን? እንዴት ባለ ስሜትና ናፍቆትስ ነው ጾሙን የሚጀምረው? ስግደቱንስ? ጸሎትን ለማድረስ የሚናፍቅ ሰው ጸሎት በሚያደርስበት ጊዜ የሚጠቀምበት የራሱ የሆነ ጥበብ አለው። ጸሎቱን ጀምሮ መደምደሚያው ላይ ሲደርስ ይገድበው ዘንድ ይሳነዋል ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ይበልጥ ይቆራኛልና። ስለዚህም ከእግዚአብሔር ጋር የጀመረውን ንግግር ለማቋረጥ አሻፈረኝ ይላል። ይልቁንም ጸሎቱን የሚያራዝሙለትን አንቀጾችና ሐረጎች እየጨመረ ይሄዳል።

ይህ ሰው ልክ የእናቱን ጡት እንዲጥል የሚታገሉትን ህፃን ልጅ ይመስላል። ይህ ህፃን መላ ናፍቆቱ ለእናቱ ጡት ሆኖ ከእናቱ ደረት መነጠሉን ቢቃወምም በግድ ይነጥሉታል። እንዲህ ያለ ታላቅ የመጸለይ ኃይል ምንም እንኳ ለጸሎት ከቆመ በኋላ ቢጨርስም በዚህ ሰው ልቦናና አእምሮ ውስጥ ገና እፍላ ነው። ከቤቱ ወጥቶ ወደ ሌላ ሲሄድ እንኳ የጸሎቱ ቃላት ተከትለውት ስለሚሄዱ በህሊናው ውስጥ ይመላለሳሉ። በሚራመድና በሚቀመጥበት ጊዜ ሁሉ ያጅቡታል። በሥራው ሁሉ ውስጥ ዘልቀው ስለሚገቡ የተቀደሰ ዝምታን ያድሉታል። ማንም ሰው ሊያናግረው ቢጀምር ከእናቱ ደረት ኃይልን ተጠቅሞ ሊያወጣው የመጣ መስሎ ይታየዋል። ይህም ልክ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወንድሞቹ ሊያደርጉ የወደዱትን አብሯቸው እንዲያደርግ ከጌታ ደረት ላይ ነጥሎ እንደመውሰድ ይቆጠራል። ማርታም እህቷ ማርያም በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ሳለች ነጥላ ወደ ኩሽና ለመውሰድ የሞከረችው ሙከራ ይህንኑ የሚመስል ነው።

የመራብና የመጠማት ምልክቶች በሚጸልይ ሰው ውስጥ የሚገለጹት ጸሎቱን የሚያደርሰው ሰው ምን እንደሚደረግ እንኳ ባለማስተዋሉ ነው። መላው እርሱነቱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ ስለ አካባቢው አንዳች ነገር አይታወቀውም። ይህም ዮሐንስ አጭሩን ባለ ግመሉ እየደጋገመ ሲጠይቀው አለመስማቱን የሚገልጸውን ታሪክ ያስታውሰናል። እንዲህ ያለው ሰው ትኩረቱ ሁሉ የሚሰባሰበው በጸሎቱ ላይ ብቻ ስለሚሆን በህዋው ላይ ከእርሱና ከጌታው በስተቀር ማንም ያለ አይመስለውም። ሁኔታው ሁሉ በጣም ተርቦ በፊቱ የሚጣፍጥ ምግብ የቀረበለትን ሰው ነው የሚመስለው።

ሙሉ ለሙሉ ስሜታቸውን መስጠት የሚችሉ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ ለእግዚአብሔር ቅርብ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ከጀመሩ መላ ስሜታቸውን ወደዚያው ያጎርፉታል። በመሆኑም እግዚአብሔር “ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያመልከኛል ፤ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው።” ማቴ 15:8 በማለት የተናገረባቸው ሕዝብ ከሚያደርጉት ድርጊት የእርሱ በጣሙን የተለየ ነው። ስሜቶቻችን ምን ያህል ወሳኝ እንደሆኑ የምናውቀው ዘማውያን የነበሩ ሰዎች ከኃጢአታቸው ተመልሰው ራሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ሲመሩ ስንመለከት ነው። እነዚህ ሰዎች በሚያስደንቅ ፍጥነት ቅዱሳን ሆነው እናያቸዋለን። ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት በፍጹም ንስሐ

www.ethiopianorthodox.org

አስቀድሞ ወደ ኃጢአት የመሯቸው ስሜቶቻቸውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ስለሚያደርጉና እግዚአብሔርን ብቻ መራብና መጠማት ስለሚጀምሩ ነው።

የሰው ልቡና የተመላው በዓለማዊ ጉዳይ ከሆነ እግዚአብሔርን ከቶ ሊራብና ሊጠማ አይችልም። ዓለምንና እግዚአብሔርንም አጣምሮ ሊወድ አይቻለውም።መውደድ የሚችለው ከሁለት አንዱን ነው። ማንም ደግሞ የዓለም ወዳጅ ከሆነ የእግዚአብሔር ጠላት ነው። ያዕ 4:4 ማንም ከኃጢአት ጋር ከታገለ በኋላ ያን ኃጢአት የሚወደው ከሆነ እግዚአብሔርን መናፈቅ ወይም ስለ እርሱ መራብና መጠማት ሊጀምር አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔርን ከመራብና ከመጠማት አስቀድሞ የሚመጣው ንስሐ ነው። ከዚህ በኋላ ይህ ንስሐው ወደ ሁለተኛው መንገድ ይመራዋል። በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔርን መራብና መጠማትም ወደ ንስሐ ያደርሳል።

ታዲያ እነዚህን ሁሉ የምናደርግበትን ስሜቶች የምናገኘው መቼ ነው? በተለይ ዛሬ እግዚአብሔር መዝጊያችንን ከውጪ ቆሞ ሲያንኳኳ ያልከፈትንለት እኛ?

"ስለ ፅድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ግን ብፁአን ናቸው ፤ ይጠግባሉና።"

## መ. ይጠግባሉና

የሚጠግቡት በሰማያዊ ፍቅር በመንፈሳዊ ደስታና ከሰማይ በሚታደል ተድላ ነው።

ለእግዚአብሔር ያላቸውን ናፍቆት እነርሱ ከሚገልጹት የበለጠ እግዚአብሔር ይገልጽላቸዋል። ስለዚህም ፍቅሩን ስለሚያድላቸው ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን የሚገኘውን ደስታ ይመኛሉ። ይህን ደስታ በቃላት ለመግለጽ እጅግ ያዳግታል። ነገር ግን ይህም ቢሆን ጊዜያዊ መጥገብ ነው እላለሁ ፤ የቅምሻ ያህል።

"ቅመሱና እዩ።" እግዚአብሔር እርሱነቱን ገልጦ ልቡናውን በሰጣቸው ቁጥር ይበልጥ ይራባሉ ይጠማሉም። ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊጠግብ አይችልምና። ይደንቀኛል! የዘላለምን ሕይወት ስንታደል ፍጹም እንጠግበው ይሆን? ወይስ እርሱም የበለጠ እንድንጓጓ ምክንያት የሚሆን ይሆን? ጉጉታችንስ ያረካን ወይስ ያስጠማን ይሆን? ስለ እውነት ከሆነ ግን እኔ አላውቅም የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።



# ምዕራፍ አምስት

## 1. የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ፤ ይማራሉና

## ሀ. ምህረት ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ነው

ምህረት ከእግዚአብሔር ባሕርያት መካከል አንዱ ነው። አንዱ ስለሆነም የሚምር ሁሉ እግዚአብሔርን መስሎታል ማለት ነው።

ስለ እግዚአብሔር ስለ አምላካችን ደግሞ እንደዚህ ተብሎ ተጽፎአል። "እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው። ከቁጣ የራቀ ምህረቱም የበዛ ሁልጊዜም አይቀስፍም ለዘላለም አይቀጣም። እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም ፤ እንደ በደላችንም አልከፈለንም። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ። ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።" መዝ.102፤8-12።

የእግዚአብሔር ድንቅ ምህረት በገሃድና በኃይል የተገለጸው ግን በመስቀሉ ላይ ነው። በዚያ ጌታችን የሰው ልጆችን ሁሉ ኃጢአት በጫንቃው ተሸክሞ ይቅር አለ። እርሱ ኃጢአተኛው ሰው ሲሞት በማየት የሚደሰት አምላክ ስላልሆነ መሐሪና ቸር ነው። ይልቁንም በዚህ ፈንታ ሰዎች ከኃጢአታቸው ሲመለሱ የሚደሰት ጌታ ነው። ሕዝ. 18፤23 እርሱ በቁጣውና ፍርዱ የነነዌ ሰዎችን ሊያጠፋቸው ከወሰነ በኋላ ከክፉ ሥራቸው በንስሐ ሲመለሱ ስለተመለከተ ሊያመጣባቸው ካለው ጥፋት አዝኖና ራርቶ የማራቸው ፈጣሪ ነው። ዮና 3:10 ሊያጠፋ ካለ በኋላ ተጸጽቶ የሚምር እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር በንስሐ የሚመለሱትን ሲምር አይዘልፋቸውም አይሰድባቸውምም። በወንጌላዊው በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 15 ውስጥ ሦስት በንስሐ የተመለሱ ሰዎችን መቀበሉን እንመለከታለን። እነዚህም ስለ ጠፋውና ስለ ባከነው ልጅ ፤ ስለ ጠፋው ድሪምና ስለ ጠፋው በግ የተገለጹት ናቸው። በምዕራፉ ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እነዚህን የጠፉትን እንደ ፈለጋቸውና ሲመለሱም ያለ አንዳች ተግሳጽ እንዴት ባለ ደስታ እንደተቀበላቸው እናነባለን። በተመሳሳይ መልኩ ጌታ ከትንሳኤው በኋላ ስምዖን ጴጥሮስን አግኝቶት ነበር። ይሁን እንጂ "ሰውየውን አላውቀውም" በማለት የከዳውን ክህደት አንስቶ የጴጥሮስን ስሜት ሊጎዳበት አልወደደም።ይልቁንም ወደ ቀደመው የክህነት ማዕረጉ መልሶ "ግልገሎቼን አሰማራ ጠቦቶቼን ጠብቅ በጎቼንም አሰማራ" አለው እንጂ። ዮሐ 21:15-17

በእግዚአብሐር ምህረት ውስጥ ስለተቅበዘበዙት ሕዝብ ጸጸት አለ። መጸሐፍ ቅዱስ ስለዚህ እንዲህ ይላል። "ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበረና አዘነላቸው።" ማቴ 9:36 እኛም እንደነዚህ ላሉት ሰዎች በእኩለ ሌሊት የንስሐ ጸሎታችን "አቤቱ ጌታ ሆይ! ረዳት የሌላቸውን አስብ ፤ በአልጋ ቁራኝነት ያሉትንና አስታዋሽ ያጡትን አንተ አስታውሳቸው" እንላለን።

እግዚአብሐር መሐሪ ነው። ረዳት ያጡትንም ይረዳቸዋል። በጸሎታችን ውስጥ "አቤቱ እግዚአብሐር ሆይ አንተ ረዳት ለሌላቸው ረዳታቸው ፤ ተስፋ ላጡት ተስፋቸው ፤ ላዘኑት መጽናኛቸው ፤ በፈተና ለተጠቁትም መጠለያቸው ነህ" እንለዋለን። ከዚህ ሌላ እግዚአብሐር ያደርግ ዘንድ የምንለው ምን የምህረቱ ሥራ አለ? እንደነዚህ ያሉትን ምስኪናን ሰዎች የሚንከባከብ ሁሉ የጌታውን ፈለግ ተከትሎአል። ማለት ነው። እግዚአብሐር መሐሪ ስለሆነም ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን አስቀድሟል። "ከመስዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ።" በማለት ሆሴ. 6:6።

በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ጊዜ ሰዎች እግዚአብሐር መሐሪ መሆኑን አውቀዋል። ነቢዩ ናታን ለቅዱስ ዳዊት ከሦስቱ ምርጫዎች ውስጥ አንዱን እንዲመርጥ ሲናገረው ዳዊት እንዲህ ነበር ያለው። "ምህረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሐር እጅ እንውደቅ ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ።" 2ኛ ሳሙ 24:14። ይህ ምንኛ ድንቅ ምርጫ ነው! እርሱ ፍጹም ቅዱስ ፤ ቅድስናው እንከን የማይገኝለት ጌታ ስለሆነ በእርሱ የቸርነትና የጽድቅ እጆች ውስጥ ወድቀን "አቤቱ እንደ ምህረትህ እንጂ እንደ በደላችን አይሁን" ብንለው በደላችንን ሸፍኖ እንደ ኃጢአታችን የማይከፍለን አምላክ ነው። በሰው እጅ ከወደቅን ግን ምንም እንኳ ኃጢአትን በማድረግና በድካማችን ቢመስለንም ስለ እኛ አያዝንም። ይልቁንም በየደረሰበት ሁሉ ያማናል ያዋርደንማል።

## ሊ. የምህረት ጠቀሜታ

ምህረት ጠቀሜታው ታላቅ ስለሆነ እግዚአብሐር አምላክ በዳግም ምጽአት ሲገለጥ ከፍርዱ መመዘኛዎች አንዱ እንዲሆን አድርጎታል። በዚያች የመጨረሻ ቀን እግዚአብሐር በግራው ለሚቆሙት እንዲህ ነው የሚላቸው "እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።" ማቴ 25:41 ግን ለምንድን ነው ይህንን ፍርድ የሚፈርድባቸው? ይህን ከፈረደባቸው በኋላ ምክንያቱን ይዘረዝርላቸዋል። "ተርቤ አላበላችሁኝምና ፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና ፤ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና ፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና ፤ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።" ካላቸው በኋላ ቀጠል አድርጎ የበለጠ ሲገልጥላቸውም "ከሁሉ ለሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ



ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም።" ማቴ 25:42-45 ይላቸዋል። ስለዚህ ይህን ያላደረጉት ሰዎች ለተቸገሩት ምህረትን አላደረጉምና ይቀጣሉ። ይህም ማለት አንተም ምን ጸሎት ብታደርስ ፤ ዝማሬን ብታቀርብ ፤ መልካምም ብታስብ ነገር ግን ምህረትን የማታደርግ ከሆንህ በመጨረሻው ቀን "ምህረትን እወዳለሁ መስዋዕትንም አይደለም።" ማቴ 9:13 የሚለው አምላክ ፊት ስለምትቆም ምህረት አይደረግልህም።

ስለዚህም ብላ ቤተ ክርስቲያን በእኩለ ሌሊት ጸሎታችን ውስጥ "በመጨረሻው ፍርድ መሐሪ ላልሆኑት በሙሉ ምህረት አይደረግላቸውም። ነገር ግን የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ይማራሉና" ማቴ 5:7 በማለት እንድንጸልይ የምታስተምረን። ጌታም በመዋዕለ ስብከቱ ምህረትን ከምድራዊ ችግሮች ማለትም ከረሀብ ከጥምና ከህመም አሊያም ደግሞ ከመግባባትና ከመንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር አያይዞ አስተምሯል። እነዚህንም ሁሉ በአንድ አጠቃሎ "በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል።" ማር 4:24 ብሎናል። እናንተ ለሰዎች ምህረትን ሰፍራችሁ ከሆነ ጌታም ለእናንተ ይህንኑ ይሰፍርላችኋል። በሰዎች ላይ በግፍ ፈርዳችሁ ከሆነም የሚጠብቃችሁ ጥፋት ነው። ለዚህም ጌታ እንዲህ ይላል "በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋል።" ማቴ 7:2 ስለዚህ ምህረትን ማግኘት የምትወዱ ከሆነ እናንተም ለሌሎች ምህረትን አድርጉ።

የሚምር ሰው ምህረቱ ቀድማ እንድትጠብቀው ለእግዚአብሐር ያበድራት ዘንድ ይልካታል። ስለዚህም መጸሐፍ ቅዱስ "ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው ፤ እግዚአብሐር በክፉ ቀን ያድነዋል።" መዝ. 40:1 ይላል። በአንፃሩ ደግሞ እንዲህ የሚል ቃል አለ "የድሃውን ሰው ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው እርሱ ራሱ ይጮኻል ፤ አይሰማለትምም።" ምሳ 21:13።

አንተ ለሌሎች የምታደርገው ምህረት ከፊትህ ስለሚቀድም ከእግዚአብሐር ጋር ያማልድሃል ያስታርቅህማል። አንተ ሌሎችን የምትምር ከሆነ እግዚአብሐርም አንተን ይምርሃል። ነገር ግን አንተ ቁጡና ጨካኝ ሆነህ ሳለህ የእጅህን ዋጋ ብታገኝ እንዳታማርር። ይቅር ስለማለትም ጌታ የተናገረው ቃል አለ። ". . . አትኮንኑ አትኮነኑምም። ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ።" ሉቃ 6:37። በዚሁ አንቀጽ ውስጥ "አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም" ብሏል። ከዚሁ በመቀጠልም "ስጡ ይሰጣችሁማል ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋል። የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል በማለት ተናግሯል።" ሉቃ 6:38።

አሁንም ይቅር ማለትን በተመለከተ ጌታ ያለው አለ። "ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና። ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።" ማቴ. 6:14-15። ስለዚህ ይቅር የማይል ሁሉ ይቅር መባልን ከእርሱ እያራቀ መሆኑን ይወቅ። ቀድሞ ይቅር የተባለ

www.ethiopianorthodox.org

ቢሆንም እንኳ ይወሰድበታል። ይህን በተመለከተ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 18:23-35 ባለው ውስጥ በምሳሌ ያስተማረው ትምህርት አለ።

ጠቅለል አድርገን ታሪኩን ስንመለከተው እልፍ መክሊት ከጌታው የተበደረ ባሪያ እንደነበረና ጌታው መክፈል እንዳቃተው ሲረዳ እዳውን እንደሰረዘለት እናያለን። ይኸው ባሪያ እዳው ተሰርዞለት ከጌታው ቤት ከመውጣቱ አንድ መክሊት ያበደረውን የእርሱ ቢጤ ባሪያ ባልንጀራውን ያገኘዋል። በዚህ ጊዜ አንዳችም ርኅራኄ ወይም ይቅርታ ሊያደርግለት ስላልወደደ እዳውን እስኪከፍል ድረስ በወህኒ እንዲጣል አደረገው። ይህን ድርጊቱን ጌታው በሰማ ጊዜ ያን ክፉ ባሪያ አስጠርቶ አንተ ክፉ ባሪያ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ እዳ ተውሁልህ። እኔ እንደማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህም ነበርን? አለው። በዚህም ሥራው ጌታው ስለተቆጣ ያ ባሪያ እዳውን እስኪከፍለው ድረስ በወህኒ ጥለው ለሚያሰቃዩት አሳልፎ ሰጠው። ስለዚህም ጌታ ትምህርቱን ለእኛ እንዲህ ብሎ በማሳሰብ አጠቃለለው። "ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን እንዲሁ ይቅር ካላለ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።" ማቴ 18:35

## ሐ. የምህረት ታላቅነትና ምልክቱ

ጌታ ስለ ምህረቱ ሲል ከሌዋዊውና ከካህኑ ይልቅ ባዕድ የሆነውን ሳምራዊ ነው የመረጠው። ምናልባት ካህኑ ይህን ወንበዴዎች ደብድበው በሞትና በህይወት መካከል ጥለውት የሄዱትን ሳምራዊ ያልረዳው የሚያጥነው ዕጣን ወይም የሚያቀርበው መስዋዕት ስላለ ጊዜ የለኝም ብሎ ለማመካኘት ይሆናል። ሌዋዊውም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የምፈጽመው አገልግሎት አለብኝ በማለት ይቅርታን ይጠይቅ ይሆናል። የሁለቱም ይቅርታ ወይም ምክንያት ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። እርሱ "ምህረትን እንጂ መስዋዕትን አልወድም ብሏልና።" ማቴ 12:7

ደጉን ሳምራዊ ግን ጌታ አወድሶታል። ምክንያቱም ፤ "... አይቶትም አዘነለት ቀርቦም የወይን ጠጅና ዘይት በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው። ተንከባከበውም" ይላልና። ሉቃ. 10:33-34። ባልንጀራ ተብሎ ቢጠራ የሚስማማውም ይህ ሰው እንደሆነ ተናገረ። ምህረትን አድርጓልና።

ምህረት ሰዎች እርስ በእርሳቸው ከሚሰጣጡት ፍርድ ጋር ግንኙነት አለው። አንዳንድ ሰዎች ፍርዳቸው ጠማማና ጭካኔ የተሞላበት ነው። አንዳዶችም ምህረት በውስጡ ስለሌለበት ወደ በደል ያደላ ነው። እንዲህ ያለው ፍርድ ስድብን ዱላንና ስለ ሌሎች ሳይረዱ ተገቢ ያልሆነ አስተያየት መሰንዘርን ያካተተ ነው። ሙሉ ለሙሉ የሚያተኩረውም በስህተት ላይ ብቻ ነው። ኢዮብ "ነፍሴን የምትነዘንዙ በቃልስ የምታደቁኝ እስከመቼ ነው? ይኸው ስትሰድቡኝ አሥር ጊዜ ነው።" ኢዮ 19:1-2፤ "እኔ ደግሞ እንደ እናንተ እናገር ዘንድ ይቻለኝ ነበር፤ ነፍሳችሁ በነፍሴ ፈንታ ቢሆን ኖሮ።" ኢዮ 16:4



"እናንተ ወዳጆቼ ሆይ ማሩኝ የእግዚአብሔር እጅ መትታኛለችና ማሩኝ" ኢዮ 19:21 በማለት እስኪናገራቸው ድረስ ባልንጀሮቹ ያላንዳች ምህረት ይወቅሱት ነበር። የሚምር ሰው ሌሎችን ይቅር ይላል ይቅርታም ይጠይቃቸዋል። በኃይል ሊያሳምናቸው አይሞክርም። ከባድ ወቀሳን ከመሰንዘር ይልቅ ይቅር የሚልበትን መንገድ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ባህርይ ነው። እጅግ ወሳኝ በነበረችው በዚያች ዕለት ለአንዲት ሰዓት እንኳ መትጋት አቅቷቸው ሲያንቀላፉ ይቅር ስላላቸው "መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው" በማለት ተናገረ። ማቴ 26:41. በመስቀል ላይ ሳለም እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ በሰቀሉት ሰዎች ቦታ ተገብቶ ስለ እነርሱ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ይቅርታን ጠይቋል። ሉቃ 23:34

ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ ዓለም በሞት ለሚለዩ በምታደርስላቸው ጸሎተ ፍትሃት ላይ "በዚህች ዓለም በሥጋ ስለኖሩ ይቅር በላቸው። ምክንያቱም በዚህች ዓለም አንድ ቀን እንኳ የኖረውም ቢሆን ከኃጢአት የነፃ አይደለምና" በማለት ትለምንላቸዋለች።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በታሰረ ጊዜ ሊረዱት ስላልቻሉት ወንድሞቹ "በፊተኛው ሙግቴ አንድ ስንኳ አልደረሰልኝም፤ ሁሉም ተውኝ እንጂ። ይህንንም አይቈጠርባቸው።" በማለት ምህረትን ጠይቆላቸዋል። 2ኛ.ጢሞ 4.16። ምህረት የሚያደርግን ሰው ሰዎች ይወዱታል። ይህን በልቡ ትሁትና መሐሪ የሆነ ሰው በተሰበረ ልብና ራስን በማዋረድ ወደ እርሱ የሚመጣውን ሰው የሚያውቅ ስለሆነ ይወዱታል። እርሱ በቁጣው አይገስፃቸውም ፤ መውደቃቸውንም አያንቋሽሽምና። ማንኛውም ሰው ከእርሱ በሚሰማው መጸጸት አይሰቀቅም። ማንንም ሊያጠፋው በሚችል መንገድ አይቀበልም። ሰውየው አወዳደቁ የከፋ ቢሆንም ይራራለታል። እግዚአብሔር ይህን ሰው የሚዋጉት የአጋንንት ኃይል ምን ያህል ከባድ እንደሆኑና የሰዎችንም ድካም የሚያውቅ ሩኅሩኅ አባት ስለሆነ ለዚህ ሰው ብርታትን ንስሐንና ይቅርታን እንዲያድለው በጸሎቱ ይማጸንለታል። ሙሴ ጥቁሩ በመባል የሚታወቀው ቅዱስ ሰው በንስሐ ሲመለስ በዚህ ዓይነት መንገድ ተስተናግዷል።

እግዚአብሔር የዚህን ሰው ንስሐ እንዲቀበል ያዘጋጀው ሰው ስለ ኃጢአተኞች ባለው ርኅራኄው የታወቀውን ቄስ አይሲዲሮስን ነው። ያን ሰው ታዲያ ይህ ቄስ ከመጀመሪያው በእቅፉ ተቀብሎ ወደ ቅድስናው ደረጃ እስኪደረስ ድረስ ተንከባከበው። በአንዲት ሌሊት ይኸው ሙሴ ጥቁሩ ወደዚህ ጻድቅ ካህን ቤት በተደጋጋሚ አሥር ጊዜ ተመላለሰ። ይሁን እንጂ ካህኑ አይሲዲሮስ አልተመረረም። በመጨረሻ እንዲያውም ከእርሱ ጋር እንዲያድር ጠየቀው። ሙሴ ግን በእርሱ ላይ ያለው ውጊያ ከባድ መሆኑን ገልጾ ሊያድር እንደማይችል ይገልጽለታል። ይሁን እንጂ በመጨረሻ በዚህ ብዙ መከራን ስለ እርሱ ሲል በተቀበለለት አባቱ አማካይነት ውጊያው ስለጠፋለት ሙሴ በመንፈስ ለመጠንከር በቃ።

www.ethiopianorthodox.org

መሐሪ የሆነ ልቦና ምንም እንኳ ኃጢአተኞች የከፋ ኃጢአት አድርገው ቢወድቁም እንኳ ይራራላቸዋል። "ምን ጊዜም ቢሆን ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፤ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።" ዕብ 13:3 የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ከፊቱ ያስቀድማል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምንዝር ለተያዘችው ሴት ምህረትን ሲያደርግ በምህረቱ ውስጥ ርኅራኄ ነበረ። በድንጋይ ወግረው ሊገድሏት ከወደዱት ሰዎች እጅ ካዳናት በኋላ "እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ። ከአሁን ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትስሪ" አላት ዮሐ 8:11። ከዚህ በተጨማሪ በፈሪሳዊው በስምዖን ቤት ተገኝታ እግሮቹን በእንባዋ ያራሰችውንም ኃጢአተኛ ሴት አድኗታል። ሉቃ 7:44።

የሚምር ልብ በቀልንም አያውቅም። ክፉን በክፉ አይመልስም። በአንፃሩ "ስለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ" ማቴ5፤44 የሚለውን የአምላኩን ትዕዛዝ ይከተላል። ቢጠሉአችሁም አትጥሏቸው። ቢያመናጭቋችሁም ያንኑ አታድርጉባቸው። ጭካኔና በቀል ከምህረት ጋር ስምምነት የላቸውምና።

## መ. ጭካኔ

ጭካኔ የምህረት ተቃዋሚ ሲሆን በዓይነቱም ሁለት ነው። ይኸውም በሰዎች ላይ የሚፈጸም ጭካኔና በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ጭካኔ ተብሎ ይለያል። በሰዎች ላይ የሚፈጸመው ጭካኔ በግልጽ የታወቀ ነው። ይህም ሰዎችን አለአግባብ በማመናጨቅ ፤ ስሜታቸውን በማቁሰል ፤ በመናቅና በመሳሰሉት ይገለጣል። በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸመው ጭካኔ ደግሞ የሚገለጠው እርሱ በሰዎች ላይ እያደር ለሚናገረው ቃል መልስ ባለመስጠትና ጭራሹን እርሱን በመተው ይገለጣል። ለዚህ ምክንያት የምትሆነን ብዙ ነቢያት ወደ እርሷ ተልከውባት የሚሏትን ከመስማት ይልቅ በድንጋይ እየወገረች የገደለችው ኢየሩሳሌም ናት። በገዛ ቋንቋዋ ይናገራት የነበረውን እግዚአብሔርን አላዳመጠችውም። ስለዚህም መለኮታዊው ቃል እንደዚህ አለ ፤ "ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።" ዕብ 3÷7

በፈርዖን ላይ ግን ሁለቱም የጭካኔ ዓይነቶች ተገልጠዋል። ሕዝበ እስራኤልን በጣም ያሰቃያቸው ነበር። የሥራውንም ጫና እንዲቀንስላቸው ሲማጸኑት ግብሩን ይጨምርባቸው ነበር። የሕዝቡን አስገባሪዎችም ጠርቶ እንደቀድሞ ገለባ እንዲያቀርቡላቸው ይልቁንም እነርሱ ገለባውን ሰብስበው ጡቡን እንዲሰሩና ቀድሞ ከሚያመርቱት የማያንስ እንዲያመርቱ ያደርጉ ዘንድ ትዕዛዝ ሰጣቸው። ሕዝቡም ይህን በመቃወም ሲያንጎራጉሩ "ስልቻቿችኋል ሰንፋችኋል ደካሞች ናችሁ" ነው ያላቸው። ዘጸ 5:6-17።



ፈርዖን ከዚህ በተጨማሪ ሙሴ በፊቱ ድንቅ ድንቅ ተአምራትንና አሥሩ መቅሰፍቶች እንዲወርዱበት እያደረገ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሲያሰማው ልቡን እልከኛ ስላደረገ ሊያደምጠው አልቻለም። የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ በጨካኝ ሰው ልቦና ውስጥ አያድርም። በግትር ፤ በቀል በሞላበትና ምህረት በማያደርግ ልቦና ውስጥም አይኖርም። "የመንፈስ ፍሬዎች ፍቅር ፤ ደስታ ፤ ሰላምና ቸርነት ናቸውና።" ገላ 5:22 አመጻ ግን ከእነዚህ ሁሉ ጋር ይቃረናል። ስለዚህም የእግዚአብሔር መንፈስ በጨካኝና በአመፀኛ ሰው ልቦና ውስጥ ቦታ ሊያገኝ አይችልም።

ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ አይሁድን ስለ ልቦናቸው ጭካኔ ገስፆአቸው ነበር። "እናንተ አንገተ ደንዳኖች ፤ ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ ፤ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ። ከነቢያትስ አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማነው? የጻድቁንም መምጣት አስቀድመው የተናገሩትንም ገደሉአቸው። አሁንም እናንተ እርሱን አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፤ ገደላችሁትም።" ሐዋ 7:51-52። ልባቸውን እልከኛ ያደረጉ ሰዎች ከየሥራዎቻቸው በስተጀርባ የጭካኔ ድርጊቶቻቸው ይከተሏቸዋል። ሌሎችን ያሰቃዩበት ስቃይ በሙሉ እየተከታተለ ከፊታቸው ስለሚደቀን ሰላም ያሳጣቸዋል። ከእነዚህ ክፉ ሥራዎቻቸው ሊያመልጡ አይችሉም። ምህረት አልባ ስለሆነው ልቦናቸው ዘወትር እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ይህም ቃየን ወንድሙ አቤልን በገደለው ጊዜ የነበረውን ትዕይንት ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ቃየንን የተናገረው ቃል ያስጨነቀው በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም እንደነበር ቃሉ ምስክር ነው። "የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።" ዘፍ 4:10

## ሠ. የእግዚአብሔር ምህረት የሚገለጠው ለማን ነው?

ምህረት ከእግዚአብሔር ባህርያት አንዱ እንደሆነ ቀደም ሲል ተናግረናል። ታዲያ የዚህ ምህረት ተጠቃሚ ማነው

1ኛ. በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ምህረቱን የሚገልጠው በሙሉ ልባቸው ለሚጠይቁት ነው። ስለዚህም ነው ያለማቋረጥ በየቀኑ እግዚአብሔር ይምረን ዘንድ የምንማጸነው። በየሰዓቱ በምናደርሰው የጸሎታችን መቅድም ላይ ፤ "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ ፤ እንደ ምህረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።" በሚለው በመዝሙር 51 ላይ ባለው ቃል ጀምረን "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ማረን! አሁንም ማረን!" በማለት የምንደመድመው። ወደ ቤተ ክርስቲያንም ገብተን በቅድስናው ስፍራ ስንሰግድ "እኔ ግን በምህረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ። አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ" የምንለው። መዝ 5:7

www.ethiopianorthodox.org

ካህኑም በሰርክና በነግህ በሚያጥንበት ጊዜ "አቤቱ ጌታ ሆይ ማረን!" ብሎ ነው የሚጀምረው። ይህ ጸሎት ምናልባት ከቀራጩ ጸሎት የተወሰደ ሳይሆን አይቀርም። "አምላክ ሆይ እኔ ኃጢአተኛውን ማረኝ።" ሉቃ 18:13 በጸሎታችንም መካከል "ኪሪያላይሶን" ወይም "አቤቱ ጌታ ሆይ ማረን!" የሚለውን ቃል አርባ አንድ ጊዜ የምንለው የዚህ የምህረት ተጠቃሚዎች ለመሆን ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ምህረትን የሚጠይቅ ሁሉ ያገኛታል። "ጠይቁ ይሰጣችኋል ፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ።" ማቴ 7:7 ይህንን ለማግኘት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸው ይሆን? አዎን አለባቸው። ቀጥለን እናያለን።

2ኛ. እግዚአብሔር ምህረት የሚያደርገው ለሚያደርጉ ብቻ ነው። ለዚህ ነው በቃሉ "የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ፤ ይማራሉና" ያለው። ማቴ 5:7 እኛም ይህንን አስመልክተን በእኩለ ሌሊት ጸሎታችን ላይ "መሐሪ ያልሆነ ሁሉ በመጨረሻዋ ቀን ምህረትን አያገኝም" እያልን የምናውጀው። ለሌሎች ምህረትን የማያደርጉ ጨካኝ ሰዎች የእግዚአብሔር የምህረቱ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ አይችሉም። እነዚህ ሰዎች ባለቀ ሰዓት ክፉ ሥራዎቻቸውን አስታውሰው ምህረትን በሚፈልጉት ጊዜ አያገኟትም።

የዮሴፍ ወንድሞች በግብጽ አገር በስቃይ ውስጥ ከወደቁ በኋላ እርስ በእርሳቸው "በእውነት ወንድማችንን በድለናል። እኛን በማማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን" ተባብለው ነበር። ይህን የሰማው ሮቤልም "ብላቴናውን አትበድሉ ብዬአችሁ አልነበረምን? እኔንም አልሰማችሁኝም። ስለዚህ እነሆ ደሙ ይፈላለገናል" አላቸው። ዘፍ 42፤21-22

ከዚህ በኋላ ዮሴፍ እያንዳንዳቸው እንዲፈተሹ ካደረገና በቢንያም አበይት ውስጥ ጽዋው ከተገኘ በኋላ ይሁዳ በዮሴፍ ፊት ወድቆ ". . . እኛስ በምን እንነፃለን እግዚአብሔር የባሪያዎችህን ኃጢአት ገለጠ" በማለት ተናገረው። ዘፍ 44፤16

3ኛ. ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ እግዚአብሔር ባይጠይቁትም እንኳ ለተበደሉት ምህረትን ያደርግላቸዋል።

የሚኖሩባትን ያቺ ጥቂት እንኳ ፍትህ ያጡባት ሕይወታቸው እግዚአብሔር ፍትህን እንዲሰጣት በራሷ ወደ እርሱ ትጮኻለች። ለዚህም ነው እግዚአብሔር "በግብጽ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ። ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሳ ጩኸታቸውን ሰማሁ ፤ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ። ከግብጻውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ ወረድሁ።" ዘጸ 3፤7-8 ያለው።



በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔር አምላክ በዳዊት ላይ አድሮ "ስለ ድሆች መከራ ስለ ችግረኞችም ጩኸት እግዚአብሔር አሁን እነሳለሁ ይላል" አለ። መዝ 11፤5 ይኸው መለኮታዊ ቃልና መመሪያ ከዚህ በተጨማሪ በመዝ. 145 ላይ ፤ "እግዚአብሔር ለተበደሉት ይፈርዳል ፤ የታሰሩትን ይፈታል ፤ የወደቁትን ያነሳል ፤ ዕውሮችን ጥበበኞች ያደርጋል፤ ስደተኞችን ይጠብቃል፤ ድሀ አደጎችንና ባልቴቶችን ይቀበላል" ይላል።

እግዚአብሔር የተበዳዮችን መብት ከበዳዮች እጅ አውጥቶ ለተበደሉት ይሰጣል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ታላቁ ጻድቅ ቅዱስ መቃርስ ነው። ቅዱስ መቃርስ ገና ወጣት ሳለ አንዲት ልጃገረድ ከዝሙት ጠንቅ የተነሳ አረገዘች። የማርገዟ ነገር ገሀድ እየወጣ ሲሄድ እንድታረግዝ ያደረጋት ኃጢአተኛ ሰው ያረገዘችው በዚያን ወቅት ከሰዎች ተገልሎ ከሚኖረው ከመቃርስ መሆኑን እንድትናገር አግባባት። በዚህ ሰዓት ይህን የሰማው ሁሉ በልጅቱና በተወለደው ሕፃን ላይ ስለፈጸመው በደል እያነሱ በስድብ ዱላ ክፉኛ ደበደቡት። ይሄኔ እግዚአብሔር ስለ መቃርስ ሲል በመካከል ገባ። ልጅቱ በምትወልድበት ጊዜ ምጧ አስጨነቃት ቆየባትም። ሕማሙንና ስቃዩን ልትታገሰው ስላለች ጻድቁን ሰው በሐሰት መወንጀሏን ተናዝዛ ራሷን ከኃጢአት ሞት ከማዳን በስተቀር አማራጭ ስላልነበራት ይህንኑ አደረገች።

ለዚህ ተጨማሪ የሚሆነን ሌላ ምሳሌ ደግሞ በአክአብና በኤልዛቤል ክፉኛ የተበደለው ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ ነው። እግዚአብሔር የናቡቴን ደም ተበቅሏል። በኤልያስ አድሮም አክአብን "ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ሥፍራ የአንተን ደም ደግሞ ይልሱታል" ብሎ ተናገረው። 1ኛ ነገ 20፤19። እግዚአብሔር ለመክዶዮስም ምህረትን አውርዷል። መርዶክዮስን ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ያጉላላውን ሐማ እግዚአብሔር ተበቅሎታል። ሐማ በመርዶክዮስ ላይ የተንኮል ሴራ ሸርቦ ነበር። በመጨረሻ ግን ለመርዶክዮስ ብሎ ባዘጋጀው አምሳ ክንድ ግንድ ላይ ራሱ ተሰቀለ። በዚህ መካከል ግን እግዚአብሔር በጉዳዩ ገብቶ ለንጉሡ ለአርጤክስስ የመርዶክዮስን የቀደመ መልካም ምግባርና የሐማን ክፉ ሴራ ገልጦለታል። ስለሆነም ንጉሡ ባለሟሎቹ ሐማን ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ ላይ ስቀሉት በማለት ትዕዛዝ ሰጠ። አስ 7፤9-10።

ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር ለሙሴና ለሕዝቡ ምህረትን ስላደረገላቸው ከፈርዖን የግፍ አገዛዝ አዳናቸው። ስለዚህም ጌታ እግዚአብሔር የፈርዖንን ሠረገላዎችና ፈረሰኞች ቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞ ሙሴንና ሕዝቡን ከፈርዖን የባርነት አገዛዝ ነፃ አወጣቸው። እግዚአብሔር እንዲሁ ማርያምና አሮን በሙሴ ላይ ሲያንጎራጉሩ ሙሴን ረድቶታል። እግዚአብሔር ለሙሴ በመቆሙም እነርሱን በመገሰጽ እንዲያውም ማርያምን ሙሴ ከጸለየላት እንድትነጻ አድርጎ በለምጽ በመምታት ሙሴን በፊታቸው ሞገስ እንዲያገኝ አድርጎታል። ከዚህም የተነሳ ማርያም ለሰባት ቀናት ያህል ሕዝቡ ከሰፈረበት አካባቢ ተለይታ እንድትቀመጥ ሆናለች። ዘኁ 12፤9-15። በአንጻሩ

www.ethiopianorthodox.org

ደግሞ ሙሴ ግብጻዊውን ሰው ገድሎ በአሸዋ ውስጥ በቀበረው ጊዜ እግዚአብሔር አልረዳውም። ዘጸ 2፤14።

እግዚአብሔር አምላክ ሌሎችንም ጨቋኞች የተቃወመባቸውና በምሳሌነታቸው ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ንጉሥ ሳኦል ፍትሕ አልባ በሆነ መንገድ ብላቴናውን ዳዊት ሲፈታተነውና ሲገድለው ሲሞክር እግዚአብሔር ተራድቶታል። በመጨረሻም የሳኦል ውድቀት በቀረበ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ራቀ። 1ኛ ሳሙ 16፤14።

በመጨረሻ ግን ዳዊት በትረ ሥልጣኑን ጨበጠ። ሆኖም ግን ከናባል ጋር እንደሚገባው ሊግባባ ባልቻለ ጊዜ እግዚአብሔር ይገስጸው ዘንድ አቢግያን ላከበት። 1ኛ ሳሙ 25 ቃየንም አቤልን በገደለ ጊዜ እግዚአብሔር ተቃውሞታል። እግዚአብሔር ከቁጣው በኋላ ስለቀጣውም በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ሆኖ ኖረ። ዘፍ 4

የእግዚአብሔር ምህረት በሰዎች ሁሉ ላይ ናት። ነገር ግን ለእያንዳንዱ በሰፈረበት መስፈሪያ ስለሚሰፈርለት ክፋትን በሚያደርጉ ላይ ርኅራኄ የለውም። ማቴ 7:2 ምናልባት የተቀጡት ቅጣት ሌሎችን ያለ አግባብ ከማንገላታት ከልቦናቸው ጭካኔ የሚመልሳቸው ትምህርት ሊሆን ይችላል። ካልተመለሱም ለሌሎቹ ማስጠንቀቂያ ይሆናሉ። ስለዚህ በሕይወት ሳለህ የተገፋህ እንጂ የምትገፋ አትሁን። ተላልፈህ የምትሰጥ ሁን እንጂ አሳልፈህ የምትሰጥ አትሁን።

4ኛ. እግዚአብሔር ምህረቱ በደካሞች ፤ በተጋዙት ፤ በተጣሉትና ልባቸው በተሰበረላቸው ላይ ናት። ጌታችን ልቡ የተሰበረውን ቀራጭ ጻድቅ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ረድቶታል። በተቃራኒው ደግሞ ሌሎችን ሲወነጅል የነበረውን ትዕቢተኛ ፈሪሳዊ ኮንኖታል። ሉቃ 18:14 ከዚህ ሌላ ኃጢአተኛ ነህ ለሚሉት ሰዎች ትኩረት ሳይሰጥ ጌታውን ይመለከት ዘንድ የሾላ ዛፍ ላይ የወጣውን ዘኬዎስን እግዚአብሔር ረድቶታል። ሉቃ 19:6-7 እግዚአብሔር የተጣለችውና ኃጢአተኛይቱ ሴት በማመንዘር ላይ ሳለች ተይዛ በፊቱ ስትቆም ይዘው ያመጧትን ልበ ደንዳና ሰዎች በመገሰጽ ለእርሷ ምህረትን አድርጎላታል። እነርሱን ግን እንዲህ ነበር ያላቸው "ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት።" ዮሐ 8:7

5ኛ. የእግዚአብሔር ምህረት የሚራራለት ባጣ ሰው ላይ ትገለጣለች። እግዚአብሔር ይህን ምህረቱን ያደረገው ለ38 ዓመታት በቤተ ሳይዳ በምትገኘው የመጠመቂያ ሥፍራ ተጥሎ በደዌ ሲሰቃይ አንድም ወደ ጠበሉ የሚያደርሰው ሰው አጥቶ በማቀቀው በመፃጉዕ ላይ ነው። ዮሐ 5:7። ስለሆነም ለጸሎት በምንቆምበት ጊዜ ረዳት ላጡት ረዳታቸው ተስፋ ለሌላቸውም ተስፋቸው ነው እንላለን። እንዲሁ እግዚአብሔር የሰዶም ሰዎች የሎጥን የቤቱን መዝጊያ ሰብረን ካልገባን ባሉ ጊዜ ምህረቱን አድርጎለት ድኗል። ዘፍ 19።



መሐሪው እግዚአብሔር በምንችለው መጠን ነው ከእኛ ጋር በዝግታ የሚጓዘው። ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይተወንም። በምንፈተንበትም ጊዜ መውጫውን አብሮ ያዘጋጅልናል። 1ኛ ቆሮ 3:2 ሲያዘንም ከርኅራኄው ብዛት ጋር ነው። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ሮሜ 12:18 እኛም ምህረትን ከእግዚአብሔር ተምረን መሐሪዎች እንድንሆን እመኛለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስድስት

## 1.ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው ፣ እግዚአብሔርን ያዩታልና።

### ሀ. ታላቅ ዋጋ

የልብ ንጽህና ለሌሎቹ የብፅዕና ደረጃ ከሚከፈለው ዋጋ አኳያ ሲታይ በጣም ለየት ያለና ከፍተኛ ዋጋ ያለው ስለሆነ ጠቀሜታው በእርግጥ የጎላ ነው።

የሌሎቹ ዋጋዎች "መጽናናትን ያገኛሉና" ፣ "ምድርን ይወርሳሉና"፣ "ይጠግባሉና" ፣ "ይማራሉና" የሚሉ ናቸው። የዚህኛው ዋጋ ግን "እግዚአብሔርን ያዩታልና" ነው የሚለው። በአምላካቸው ከእነርሱ ጋር መሆን ልዩ ደስታን ያገኛሉ ማለት ነው። ስለዚህም ጌታን ለማሳየት የሚመራው መልካም ምግባር ታላቅ ነው እንላለን። ይህንንም ስንል ልበ ንጹሐን የዋሃን ብቻ እንጂ ሌላ ማንም እግዚአብሔርን ማየት አይችልም ማለታችን ነው።

### ለ. እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን አያይም

ከዕለታት በአንድ ቀን ሳራፂዮን የተባለ ጻድቅ ሰው አንዲት ዘማዊት የነበረችን ሴት አስተምሮ በንስሐ እንድትመለስ ያደርጋታል። ይህን በማድረጉም አስቀድማ ኃጢአትን ትሠራ ከነበረበት ሥፍራ ሙሉ ለሙሉ ያወጣታል። ከዚህ በኋላ ይኸው ጻድቅ ሰው ወደ ቅዱስ አትናቴዎስ ይሄድና እግዚአብሔር የሴትዮይቱን ንስሐ መቀበል አለመቀበሉን ይጠይቀዋል። ወዲያውም የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ ሁለቱም በጾም ተወስነው በጸሎት እየተጉ ይጠባበቁ ጀመር። ከዚህ በኋላ ይህ ጉዳይ ለሁለቱም አባቶች ሳይገለጥ ጻድቁ ጳውሎስ ለሚባል ለሌላ ሰው ይገልጥለታል። ይህም ሰው እጅግ የዋህ ነበር።

እግዚአብሔር ለዚህ ሰው በአንድ ታላቅና ብዙ ሕዝብ በተገኘበት ክብረ በዓል ላይ በጣም ብዙ የክብር ዙፋኖችን በራዕይ ይገልጥለታል። ከእነዚህ ዙፋኖች መካከል አንድ በጣም ያሸበረቀና ገና ከሰው ወገን ማንም ያልተቀመጠበት ዙፋን ያሳየዋል። ከዚህ በኋላ አንድ የእግዚአብሔር መልአክ ጻድቁ ጳውሎስን ወደዚህ ጉባኤ ይዞት ይመጣና "ይህ ባዶ የክብር ዙፋን ለማን የተዘጋጀ ይመስልሃል?" ብሎ ይጠይቀዋል። ጳውሎስም "ለአባቴ ለቅዱስ አትናቴዎስ ይሆናላ!" በማለት ይመልስለታል። በዚህ ጊዜ መልአኩ "አይደለም። ይህ በጻድቁ በአባ ሳራፂዮን አማካይነት በንስሐ ለተመለሰችው ለዘማዊቷ ሴት



የተዘጋጀ ነው" ይለዋል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ጻድቁ ጳውሎስ የዋህ በመሆኑ ፈቃዱን ለእርሱ እንደገለጠለት እንመለከታለን።

### ሐ. ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን አያዩትም

ይህን በግልጽ የምንመለከተው በጠርሴሱ ጳውሎስ የመለወጥ ታሪክ ውስጥ ነው። ሳውል ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ላይ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይቶታል። ከእርሱ ጋር አብረው በመንገድ ይጓዙ የነበሩት ግን አላዩትም። "ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን እየሰሙ ማንንም ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ።" ሐዋ 9:7። እግዚአብሔርን ማየትና ድምፁንም መስማት ለሰው ሁሉ የሚታዩ ዋጋዎች አይደሉም። እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በመጻሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ላይ እናገኛለን።

እግዚአብሔር ከብላቴናው ከሳሙኤል ጋር ተነጋገረ እንጂ ከካህኑ ከኤሊ ጋር አልተነጋገረም። ንጹህ ልቦና የነበረው ይህ ብላቴና ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ስለታደለ እግዚአብሔር ለኤሊ ያደርስ ዘንድ የመልእክትን ቃል ተናገረው። 1ኛ ሳሙ 3:1-14። እግዚአብሔር በቀጥታ ከኤሊ ጋር ያልተነጋገረው ይህ ካህን የሚበጅ ባለመሆኑና በእግዚአብሔር የቅጣት ቀለበት ውስጥ የገባ ስለነበረ ነው።

ክፉ ሰዎች ዓይኖች አሏቸው ነገር ግን አያዩም። እግዚአብሔርን ለማየት አልታደሉም። ይህ ደግሞ ለእነርሱ ታላቅ ቅጣት ነው። በውጪ ባለው ጨለማ ውስጥ ስላሉ ዓይኖቻቸው ጌታን ማየት አይችሉም። ማቴ 25:30። መንፈሳቸው ሊመለከተውም ሆነ መኖሩን ሊያረጋግጥ አይችልም።

ባለፉት አስተያየቶቻችን ላይ "እግዚአብሔርን ማየት" ስንል "መንፈሳዊውን ደስታ" ማለታችን ነው። የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ወይም ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ስንልም ትርጉማቸው አንድ ነው። እግዚአብሔር ከቀደመው እባብ ጋር ተነጋገረ ነገር ግን ቀጣው። ዘፍ 3። በመጻሐፈ ኢዮብ ላይ እንደተጻፈልንም እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር ተነጋግሯል። ኢዮ 1እና2። እግዚአብሔር ወንድሙን ከገደለው ከቃየንም ጋር ከተነጋገረ በኋላ ቀጥቶታል ዘፍ 4። በድጋሚ ከሰይጣን ጋር በገዳመ ቆሮንቶስ ተነጋግሯል። ማቴ 4። እነዚህ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው በሙሉ ግን ከመንፈሳዊ ደስታ ጋር ግንኙነት የላቸውም። ምክንያቱም ክፉ አድራጊዎች ከጌታ ጋር ሲገናኙ ደስታ አይኖራቸውምና ነው። መጻሐፍም "በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው ይላል።" ዕብ 10:31።

ስለ ዳግም ምጽአቱም እንዲህ ተጽፎአል። "እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል። ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል ፣ የምድር ወገኖችም ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ" ራዕ 1:7። ይህም ማለት የቸነከሩት ሁሉ ያዩትና ስለ

www.ethiopianorthodox.org

እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ ማለት ነው። በሆሴዕ ላይ እንደተገለጸውም "ተራሮችን ከደኑን ፤ ኮረብቶችንም ውደቁብን ይሏቸዋል።" ሆሴ 10:8 ፤ ሉቃ 23:30።

## መ. ሕሊና የዋህነትና መከራዎች

ሁሉንም ነገር ሊመረምር የሚሞክረውና ሕዋሳቶቻችን የሚቆጣጠረው አእምሮ ሁሉን ነገር ላያይ ይችላል። በየዋህ ሰው ግን እንዲህ አይደለም። እግዚአብሔርን ከዓይንህ ይልቅ በመንፈስህ ነው ልታየው የምትችለው። እይታው ትክክል የሆነው ልቦናህም እግዚአብሔርን ሊያየው ይችል ይሆናል። በአንፃሩ ግን በምኞትና በምርምር እግዚአብሔርን በምናቡ ቀርጾ ለማየት የሚሞክረው አእምሮ ፍጹም ሊያየው አይችልም።

ስለዚህም በመንፈሳዊው ትዕይንት ፊት ለፊት ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ ማለት ነው። ከፊሎቹ ትዕይንቱን የሚያዩ ቀሪዎቹ ደግሞ የማያዩ። ልበ ንጹሐን የሆኑት የዋህ ሰዎች ሊያዩት ይችላሉ። የተጨነቁ ሁሉ ግን እግዚአብሔርን አያዩትም።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን ማየት ልቦናን ከሚያነጻ ህማም ጋር ሊያያዝ ይችላል። ልቦናዎቻቸው ከፈተናና ከዚህ ዓለም ፍቅር ፍጹም ነጽተውና ጌታን ለመገናኘት ግልጽ ሆነው ብዙ መከራ በመቀበልና በአሰቃቂ ህማም መካከል ሳሉ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሲገለጥላቸው ቆይቷል። እግዚአብሔር ስደታቸውና መከራቸው ልቦናቸውን ላነጻላቸው ለተገፉ ሰዎች ተገልጧል። ይህም የአባቶች ሁሉ አባት በመባል በሚታወቀውና ከወንድሙ ከኤሳው ፊት ሸሽቶ ባመለጠው በአባታችን በያዕቆብ ሕይወት ውስጥ ታይቷል። ዘፍ 28።

በመከራችን ጊዜ እግዚአብሔርን በአካል አንየው እንጂ በተደጋጋሚ እናየዋለን። የሚያደርግልንም ሥራዎቹ ይታወቁናል። ዳዊት ስለ ስደተኞችና በመባረር ስለሚኖሩ ለእግዚአብሔር በተቀኘው ዜማው ውስጥ ፤ "አጥንቶቼ ሁሉ እንዲህ ይሉሃል። አቤቱ እንደ አንተ ማነው? ችግረኛን ከሚቀማው እጅ፤ ችግረኛንና ድሀውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህ" ይላል። መዝ 34፤14። ከዚህም በተጨማሪ ይኸው ክቡር ዳዊት "ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየሁት። እንዳልታወክ በፊቴ ነውና" ሐዋ 2:25 በእርግጥ ዳዊት ጌታን በአካል ፊት ለፊት አላየውም ነገር ግን ንጹሕ ልቦናው አብሮት የመኖሩን ዕይታ በመላው ሕዋሳቱ እንዲታወቅ አድርጎለታል።

"እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም" መዝ 34:8። ይህ ዕይታና ቅምሻ በእርግጥ ስሜታችን ሊደርስበት ከሚችለው ውጪ ነው። እግዚአብሔርን ማየት ማለት አብሮን በመኖሩ የምናገኘው መንፈሳዊ ደስታ ማለት ነው። የምናየው ችግሮቻችንን ሲያቃልልን ፤ ከጠላቶቻችን እጅ ሲታደገንና መልካም በሆነው ነገር ሁሉ ሲጎበኘንና ሲባርከን ነው። ይሄኔም የእግዚአብሔርን እጅ ለመያዝ እንደርሳለን። እውነተኛው እምነትም ይኸው ነው።



## ሠ. እግዚአብሔርን በሕያውነቱ ማየት

"እግዚአብሔርን ያዩታልና" የሚለው ቃል ሌላም ትርጉም አለው። ይኸውም ከዚህ ፈራሽ ከሆነው ሥጋችን ውጪ እግዚአብሔርን ማየት መቻላችንን ስለሚያመለክተን ነው። ጻድቅና ቅን የነበረው ኢዮብ የተናገረው ይህን ያብራራልናል። "እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ፤ ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ።"ኢዮ 19:25-27

መጸሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በሕያውነቱ ስለማየት አብዝቶ ይናገራል። ይኸንኑ በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው አለ። "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን። በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን።" 1ኛ ቆሮ 13:12። ከዚሁ ጋር አያይዞም በመቀጠል "ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ ፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ" ይላል። በዚህ ሐረግ ውስጥ እግዚአብሔርን በማየትና በማወቅ መካከል ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን።

ይኸው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉ ክርስቲያኖች በጻፈላቸው በሁለተኛው መልእክቱ ውስጥ "ጌታ ግን መንፈስ ነው . . . የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ብሏል። 2ኛ ቆሮ 3:17-18። ስለሆነም እግዚአብሔርን በመንፈሳዊው አካላችን ሆነን በሕያውነቱ እናየዋለን ማለት ነው።

ይህ መሬታዊ የሆነው አካላችን ሲፈርስ ፤ ይህ የሚበሰብሰውና ሞት የሚስማማው የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን ሲለብስ ንፁህ የሆነውን መንፈሳዊ አካል ይዘን ስለምንነሳ እግዚአብሔርን እናየዋለን። እግዚአብሔርን ለማየት የልብ ንጽሕና ሊኖረን ግድ ነው። የልብ ንጽሕና ለምን አስፈለገ? ይህስ እንዴት ይመጣል? እንዴትስ ሊገኝ ይችላል?

## ረ. የልብ ንጽሕና

በዚህ ርዕስ ውስጥ "ልብ" የምትለው ቃል ታላቅ ናት፤ እግዚአብሔር አምላካችን የሚፈልጋት ራሷ ልቦናህን ነውና። ለዚህም ነው በመጸሐፈ ምሳሌ ውስጥ "ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ" የሚለን። ምሳ 23:26። በተጨማሪም በዚሁ መጽሐፍ "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና" ይላል። ምሳ 4:23።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣል። ክፉ ሰውም ከልቡ ክፉ መዝገብ ክፉን

www.ethiopianorthodox.org

ያወጣል።" በማለት ተናግሯል ሉቃ 6:45። በዚህ መሠረት ውጫያዊው ንጽሕና ምንም አይጠቅምም ማለት ነው። ሰው ህሊናውን ምናልባት በንጽሕና ሊጠብቅ ይችል ይሆናል። በመሆኑም በማየትም ሆነ በመስማት እንዲሁም በመንካት አንዳችም ኃጢአት አይፈጽም ይሆናል። ያም ሆኖ ግን ልቡናው ንጹህ ላይሆን ይችላል።

ቅዱስ ጀሮምም "አንዳንድ ሥጋቸውን በብህትውና ገርተው በመንፈሳቸው ግን ሲያመነዝሩ የሚገኙ አሉ።" ሲል ተናግሯል። ይህ አባባል የሚያስረዳን ምንም እንኳን ኃጢአትን በድርጊት ሲፈጽሙ ባይታዩም ልቡናቸው በዝሙት መነደፉን ነው። ከዚህ ሌላ አንድ ሰው ልቡናው ንጹህ ሳይሆን በቁጣ ፤ በመጥፎ ጥላቻ ፤ በክፋትና በበቀል ተሞልቶ ሳለ አንደበቱ ላይሳሳት ይችላል። እነዚህን ማስመሰያዎች ከሌላ ቦታ አምጥቶ የሚናገራቸው ቢሆኑም እነርሱም ቆይተው ይበከላሉ። ጌታችን ይህንን በሌላ መልኩ ሲገልጸው "ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያመልከኛል ፤ ልቡ ግን ከኔ በጣም የራቀ ነው።" ማቴ 15:8 ፤ ኢሳ 29:13። ብሏል። እንዲሁ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚያን ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን "ጸሎታቸውን ያስረዝማሉ" ሲል ዘልፏቸዋል። ጸሎታቸው ይርዘም እንጂ ልቡናቸው ከእግዚአብሔር በጣም የራቀ ስለነበረ ነው። ከምግብ ታቅበው ፤ በጾም ተወስነውና ራሳቸውን አዋርደው ሥጋቸው በእሳት እንዲቃጠል አሳልፈው እስከ መስጠት የሚደርሱ ቢኖሩም በልቡናቸው ውስጥ ፍቅር ከሌለ እነርሱም የፈሪሳውያንን ባህርይ የተላበሱ ስለሆኑ ዋጋ አይኖራቸውም።

ልበ ንጹህ ሰው ከኃጢአት የራቀ ብቻ ሳይሆን ልቡናው በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ ጭምር መሆን አለበት። መልካም ሥራዎቹ ሁሉ ጌታ እንደተናገረው ከዚህ ፍቅር የሚመነጩ ይሆናሉ። "በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።" ማቴ 22:40።

የልብ ንጽሕና በንስሐ ይጀምራል። ስለዚህ ንጽህናም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ "የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ ፤ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ።" ሕዝ 18:13። ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔር አፍ ይህንን ተናግሯል። "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ ፤ እናንተም ትጠራላችሁ። ከርኩሰታችሁም ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ። የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ።" ሕዝ 36:25-27። እግዚአብሔር የሚፈልገውና እኛም እርሱን በመያዝ እንድናየው በሚያስችለን ንጹሕ ልብ ይህ ነው። ቅዱስ ዳዊትም በንስሐው መካከል ይሰጠው ዘንድ "አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።" በማለት የተማጸነው ይህንኑ ልብ ለማግኘት ነው። ይህ ልቦና ኃጢአትን የሚመኝት ወይም የሚሻት ልቦና ስላልሆነ አይፈጽማትም። ስለዚህም



ነው እግዚአብሔር "ልጄ ሆይ ልቡናህን ስጠኝ ፤ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ" ያለው። ምሳ 23:26።

ልቡናህን ለእግዚአብሔር ከሰጠህ እርሱ ንጹህ ልቡናን መልካም ምግባራትንና መንገዱን የሚከተሉትን ስለሚወድ እነዚህ መልካም ምግባራት ያለ እንዳች ድካምና ጥረት ይከተሉሃል። ልቡናህም ይኸንኑ መንገድ በፍጹም ርካታ ይከተላል። የጽድቅ ሕይወትም ተጊዳኝ ምኞትህ ይሆናል።

የመጀመሪያው ሰው በልቡናው ንጽህናና በግልጽነቱ የታወቀ ነበር። አዳምና ሔዋን ልበ ንጹሐንና ትሁታን ነበሩ። ሁለቱም እርቃናቸውን ሆነው ሳሉ አይተፋፈሩም ነበር። ዘፍ 2:25። ልቡናዎቻቸው ፍፁም ንጹሐን ስለነበሩ እነርሱን የሚመለከት አንዳችም ክፋት አላዩም።መጽሐፍም "ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው" ይላል። ቲቶ 1:15። ስለዚህም እግዚአብሔር በልቡናችን ንጽሕና ወደ ቀደመውና እርሱን እንመስል ዘንድ በምሳሌውና በአርአያው ወደፈጠረብን ማንነታችን እንድንመለስ ይወዳል። ይህን ማድረግ ባንችል እንኳ ይህን ከሚመስል ገፅታ ጋር እንድንመሳሰል ያስፈልጋል። ይህን የልብ ንጽሕና በዘላለም ሕይወት ውስጥ ስለምንታደል በሰማያት እንደ መላእክት ሆነን እንኖራለን። ማቴ 22:30።

እንዲህ ባለው ንጽሕና እግዚአብሔርን ማየት እንችላለን። ስለሆነም በጸሎታችን ውስጥ "አቤቱ ጌታ ሆይ! ይህን ንጽሕና ማግኘት ካልቻልን ፤ ካላገኘንም አንተን ማየት አንችልምና እባክህ ከሆነ ሙሉ ለሙሉ አሊያም ደግሞ ጣዕሙን እንኳ አድለንና ወደ መንግስትህ በመጣን ጊዜ እንይህ። ከዚህ በኋላ በምታድለን ደግሞ ሙሉ እንሆናለን።"

ልበ ንጹሕ ሰው ዓለምንና በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አይወድም። 1ኛ ዮሐ 2:15። ምክንያቱም "ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለምና።" 1ኛ ዮሐ 2:16 እንዲሁም "የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአልና።" ያዕ 4:4 ይላል። ስለዚህ ዓለምን የማይወድ ሰው ከዓለም ጋር ለመወዳጀት ልቡናው ሙት ስለሆነ በእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ የተሞላ ይሆናል። በልቡናውም ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እየተፎካከረ የሚኖር አይቀመጥም። ሐዋርያው ለጌታ ሲናገር "እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ" ብሏል። ማቴ 19:27

በእርግጥም ልበ ንጹሕ ሰው ሁለት ጌቶችን ሊወድ አይችልም። ልቡናው በእውነት ለእግዚአብሔር ይገዛል። ከእርሱ ሌላ አስበልጦ የሚወደው ካለ ግን ለእርሱ ሊሆን አይችልም ማቴ. 10:37። ስለሆነም ልቡናው ከማንኛውም ስስት ይነፃል። ማንኛውም የየዋህነት ፍቅሩም ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ተዋህዶ ይገዛለታል እንጂ ለጌታው ካለው ፍቅር ጋር አይፎካከርበትም።

www.ethiopianorthodox.org

የልበ ንጹህ ሰው ንግግሩም ሆነ ቃላቱ ንጹሀን ናቸው። "በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።" ሉቃ 6:45። ነቢዩ ዳዊትም "ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ" በማለት ተናግሯል። መዝ 44:1። አንድ ሰው በጣም ተቆጥቶ የማይገባ ንግግር ሲናገር ሌላ ሰው በእርሱ ቦታ ተገብቶ "እርሱ እኮ ልበ ንጹህና ባዶ ነው።" በማለት ስለ እርሱ ይቅርታ ይጠይቅ ዘንድ እንዲነሳ አልተፈቀደለትም። ልበ ንጹህ ሰው ንጹሀን ቃላቶችን ብቻ ነው የሚናገረው። መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ የሚያወጣው መልካም ነገርን ነውና። ንጹህ ልበ ሰፊ ስለሆነ ሁሉን ይችላል። ስለ አንዲት ቃል ወይም ችግር ሲል አይበሳጭም። አይቆጣምም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቆሮንቶሳውያንን በትህትና የወቀሰበት ቃላቶቹ ምንኛ ድንቅ ናቸው!? "እናንተ የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ! አፋችን ለእናንተ ተከፍቷል፤ ልባችንም ሰፍቶላችኋል ፤ በእኛ አልጠበባችሁም ፤ ሆዳችሁ ግን ጠቦባችኋል ፤ ልጆቼ እንደ መሆናችሁ ግን እላችኋለሁ።" 2ኛ ቆሮ 6:11-13።

እግዚአብሔር ልቦናው ምን ያህል ሰፊ እንደሆነና ሁሉን እንዴት እንደሚችል እስቲ ለአንድ አፍታ አስተውል! እንዴት ለኃጢአተኛውም ለጻድቁም የፈጠራትን ፀሐይ እንደሚያወጣ! ማቴ 5:45። ሃይማኖትን የካዱትንና ጣዖት አምላኪዎችን ተቆጥቶ ድምጥማጣቸውን ሳያጠፋቸው መቆየቱ ምን ያህል ሰፊ ልቦና ቢኖረው ነው? እግዚአብሔርስ ምን ያህል ታጋሽ ቢሆን ነው ቅዱስ ዳዊት "እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፤ እንደ በደላችንም አልከፈለንም። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምህረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ። ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ይራራል።" መዝ 102:10-12 ያለው።

እስቲ ልበ ንጹሀን ከነበሩት ሰዎች መካከል ምሳሌ የሚሆኑንን ጥቂቶቹን እንውሰድና ልቦናዎቻቸው ምን ያህል ሰፊ እንደሆኑ እንመልከት።

መጸሐፍ ቅዱስ ስለ ነቢዩ ሙሴ እንዲህ ይላል። "ሙሴም በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሁት ሰው ነበር።" ዘኁ 12:3። ስለ ጠቢቡ ሰሎሞን ደግሞ "እግዚአብሔርም ለሰሎሞን እጅግ ብዙ ጥበብንና ማስተዋል በባሕርም ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት ሰጠው።" 1ኛ ነገ 4:29። ይደንቀኛል! እንዲህ ያለ ማስተዋል በአንተ ዘንድ ይኖር ይሆን?

ያለ ምንም ጥርጥር ልበ ንጹህ ሰው የመንፈስ ፍሬዎች አሉት። ይህን በተመለከተ ሐዋርያው የተናገረው አለ። "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ፤ ደስታ፤ ሰላም፤ ትዕግስት ፤ ቸርነት ፤ በጎነት ፤ እምነት ፤ የዋሃት ፤ ራስን መግዛት ነው።" ገላ 5:22-23 ። እግዚአብሔርን ለማየት ከወደድህ እነዚህን ሁሉ ገንዘብ ማድረግ ይጠበቅብሃል።



ስለ "ልብ ንፅህና" በሰፊው ልጽፍ አልወድም። "የንስሐ ሕይወት" በሚል መጻሐፍ ውስጥ በዝርዝር ስለ ጻፍኩት ከዚያ ማንበብ ትችላላችሁ።

በልብ ንጽህና ላይ ልምምድ ካደረግህ "ልበ ንጹሀን ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና።" የሚለው ዋጋ ለአንተም ይሰጥሃል።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## 1. የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።

### ሀ. "የሚያስተረርቁ" የሚለው ቃል ትርጉም

ይህ ቃል ሦስት ትርጊሜዎችን ያካተተ ነው። ይኸውም በሰውና በእግዚአብሔር ፤ በሰዎችና በሰዎች መካከል ሆነው የሚያስታርቁና ራሳቸውን ከገዛ ልቦናቸው ጋር የሚያስታርቁ በማለት ይከፈላል። በሌላ አገላለጽ እነዚህ ሰዎች ሥጋቸው ከነፍሳቸው ከሰዎችና ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይሟገት የሚያስተራርቁ ሰዎች ናቸው።

1ኛ. የሚያስተራርቁ ሰዎች በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን ሲፈጥሩ የሚያስታርቋቸውን ሰዎች ወደ እምነትና ወደ ንስሐ ስለሚመራቸው ለጌታ ያዘጋጇቸዋል። ይህን በሚመለከት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል "በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።" 2ኛ ቆሮ 5:18-20።

2ኛ. በሰዎች መካከልም እርቅን ለመፍጠር ሁለት ዓይነት መንገዶች አሉ። በቅድሚያ በመካከላቸው ጭቅጭቅ እንዲፈጠር ምክንያት መሆን የለብንም። ንትርክ በመካከል ካለ ስለዚያ ንትርክ ፈጽሞ አናነሳም። በሁለተኛ ደረጃ የምንጫወተው ሚና ግብግብን አድቅቀን ፍቅርን ወደ ቦታዋ መመለስ ይሆናል።

3ኛ. ከራሳችን ጋር በምንፈጥረው እርቅ ደግሞ በውስጣችን ያለውን መለያየትና ሙግት በማስወገድ ይከናወናል። ምኞታችን ሁሉ ከመንፈሳዊነታችን ጋር መቃረን የለበትም። አሳቦቻችንም የእኛ ተቃዋሚዎች ሊሆኑ አይገባም። ልቦናዎቻችንም በመደናገር ችግርና በጥርጥር ወጥመድ መያዝ የለባቸውም። በዚህ ምዕራፍ ስለ እነዚህ ስለ ሦስቱ የማስታረቅ መንገዶች የቻልነውን ያህል ጠለቅ ብለን በመግባት ለመናገር እንወዳለን።

### ለ. ሰላም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል

በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ጠብ እንዲፈጠር በመጀመሪያ ምክንያት የሆነው ፍጥረት ሰይጣን ነው። ይህ ጠብ ኃጢአትን በማድረግና ሕግጋትን በመጣስ ተጀመረ። ስለሆነም ሰዎችን ከታላቁ የቅድስና ሥፍራ የለያቸው የጠብ ግድግዳ በመካከል ቆመ። ይህም መጋረጃው ነው። ዕብ 9:3 ይህንንም



የጠብ መጋረጃ ለማውረድ በእምነት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግባት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ዕብ 10:19

የሚቃጠለው መስዋዕት ይቀርብ የነበረው በእኛ ኃጢአት ምክንያት የተቆጣውን የእግዚአብሔርን ልቦና ለማስደሰት ነበር። ከዚህም የተነሳ ይቀርብ የነበረው መስዋዕት ሁሉ ይቀርብ የነበረው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር። ማንም ከእርሱ ይበላ ዘንድ ክልክል ነበር። መስዋዕቱን ያመጣውም ሆነ ባልንጀሮቹ እንዲሁም መስዋዕቱን የሚያቀርበው ካህን ጭምር ከእርሱ አይበሉም። በአንፃሩ የቀረበው መስዋዕት ወደ አመድነት እስኪለወጥ ድረስ ሌት ተቀን እሳት እየነደደበት በመሰዊያው ላይ ይቆያል።

እሳቱ የሚያመለክተን የእግዚአብሔርን ፍትሕ ነው። የሚቃጠለው መስዋዕት ወደ አመድነት መለወጡ ደግሞ መስዋዕቱ እስከ መጨረሻው ውጤታማ መሆኑንና የእግዚአብሔርም ፍትሕ የማይጓደል መሆኑን ነው የሚያመለክተን። ዘሌ 6:8-13። በመሆኑም ስለሚቃጠለው መስዋዕት እንዲህ ተባለ "ይህ የሚቃጠል መስዋዕት ነው . . . በእሳት የሚደረግ ቁርባን . . . በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ ያለው መስዋዕት" ዘሌ 1:9፤13፤17። ከዚህ በተጨማሪ ለኃጢአትና ለበደል ማስተሰረያ የሚቀርበው መስዋዕት የእግዚአብሔር ፍትሕ በሙላት እንዲከፈል ሲባል የሚቀርብ ነበር።ምክንያቱም "ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና።" ዕብ 9:22 ስለ ሞት ፈንታም ሲባል ደም በሙላት መፍሰስ ነበረበት። "የኃጢአትም ደመወዝ ሞት ነውና።" ሮሜ 6:23 የእንስሳቱ ደም ለኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምሳሌ ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ የማስታረቅን ሥራ ሠርቶአል። ይህ ሥራ የተጠናቀቀውም በቅዱስ መስቀሉ ላይ ነው። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው እንዲህ ብሏል። "ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ከታረቀን ይልቁንም ከታረቀን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን።" ሮሜ 5:10 ከዚህ በተጨማሪ ይኸው ሐዋርያ "ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር።" 2ኛ ቆሮ 5:18-19። በመቀጠልም "አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ . . . በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ነው።" ኤፌ 2:13-15 በማለት ጽፎልናል። በመጨረሻም ሲያጠቃልል "በመስቀሉ ደም ሰላም አደረገ" አለ። ቆላ 1:20። የሰው ልጅና የእግዚአብሔር በመሆን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን ያወረደውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁልጊዜ እናመሰግነዋለን።

ስለዚህም አምላካችን የሰላም ንጉሥ ይባላል። እኛም "አቤቱ የሰላም ንጉሥ ሆይ! ሰላምህን አብዛልን" እንለዋለን። ነቢዩ ኢሳይያስም ስለ እርሱ እንዲህ

www.ethiopianorthodox.org

አለ "እርሱ የሰላም አለቃ ነው።" ኢሳ 9:6 መላእክቱም የመወለዱን የምሥራች ለእረኞች ሲያበስሩ "ሰላምም በምድር ይሁን" ብለዋል። ሉቃ 2:14

ጌታ ሰላምን ከማውረዱ በፊት እኛ የቁጣ ልጆች ነበርን። ይህንንም በማስመልከት ሐዋርያው ሲጽፍልን "በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ . . . እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን . . . በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን . . . እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር አስነሳን ፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።" ኤፌ 2:1-6።

ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ የተዘጋጀውን መከራ ሁሉ በመቀበል ከመጣው ቁጣ አድኖ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን። ስለዚህም ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንዳስተማረን "ለያይቶን የነበረው የጠብ ግድግዳ በአንተ አማካይነት ፈርሶልናል። የቀደመው ጠላትነትም ተወግዶአል። አንተ ሰማያዊውንና ምድራዊውን አንድ አደረግህ። የተዋረደውንም ሥጋችንን አከበርከው" እንላለን። በንስሐና በኃጢአት ስርየት ሰውና እግዚአብሔርን ያስታረቀ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እኛም ሰዎችን ወደ እምነት መንገድ በመምራትና ለንስሐ እንዲደርሱ በማድረግ ሰላምን መፍጠር እንችላለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ "አንተን ለእነርሱ እነርሱንም ለአንተ አሳወቅኋቸው፤ አሳውቃቸዋለሁም። የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቼአቸዋለሁና።" በማለት ተናግሯል። ዮሐ 17፤8፤26።

ስለዚህም ሲባል ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያውቁት እንዲወዱትና ከእርሱ ጋር ተጣብቀው እንዲኖሩ እናደርጋለን ፤ እንሰብካቸዋለን ቃሉንም እናገለግላለን። ሐዋ 6። የማስታረቅንም ሥራ እንሰራለን። 2ኛ ቆሮ 5። ከዚህ ጋር ምንጊዜም ቢሆን ይህን የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብን ቃል እናስብ። "ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንደሚያድን የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።" ያዕ 5:20። ከዚህ በኋላ ሌላው ማለትም አገልግሎቱ ፤ ትምህርቱ ፤ ሌሎችን መፈለጉ ፤ በግል መወያየቱ ፤ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲወዱት ማድረጉ ፤ ቤተ ክርስቲያንና ሃይማኖትን ማስተዋወቁ የሚቀጥለው። ይህንን ነው ቅዱስ ጴጥሮስ በአንደኛ መልዕክቱ 1:9 ላይ "የእምነታችሁን ፍፃሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ . . ." በማለት የገለጸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በዚህ ሥልጣኑ ነው በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ሰላም እንዲወርድ ያደረገው። አንተም ባለህበት መስክ በተመሳሳይ መልኩ ይህንን ብታደርግ "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብለህ ትጠራለህ።



ይህ እንዲህ ከሆነ የዚህ ተቃራኒ በመሆን ሌሎች እንዲሰናከሉ እነርሱን ከእግዚአብሔር መንገድ በማራቅ የደማቸው ተጠያቂ ስለሚሆነው ሰው ምን ያህል እንል ይሆን?

ለምሳሌ እንዲህ ያለው ሰው አርነት ትወጣለህ ትድናለህ በሚል ሽፋን መናፍቅነትንና መበረዝን የሚያናፍስ ፤ ከሃይማኖትና ከመልካም ምግባር ከመንፈሳዊ ሕይወት ውጪ ጥርጥርን የሚዘራ ወይም ሌሎች ሰዎችን ወደ ጥፋት የሚመራ ማለትም ፍሬ ቢስ እና ከንቱ ወደ ሆነ ሥፍራ የሚወስድ ነው። ከእንደዚህ ዓይነቶች ጋር የሚፈጠረው ሕብረት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ወዳጅነት የሚለይ ነው።

## ሐ. ሰላም በሰዎች መካከል

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ዓለም በመምጣት በሰዎች መካከል ሰላም እንዲፈጠር አድርጓል። ይህ የተፈጠረው ሰላም በመጀመሪያ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ሲሆን በመቀጠልም በአይሁድና በሳምራውያን መካከል የተፈጠረ ሰላም ነው።

እርሱ የመጣው አሕዛብ በእግዚአብሔር ምግዚትነት ሥር እንዲገቡ ነው። በዚህም "የተመረጠ ሕዝብ" የሚለውን አጥፍቷል። ከአሕዛብ ወገን የነበረውን የመቶ አለቃና ያቺን ከነናዊት ሴት አስመልክቶም እንደዚህ ያለ ታላቅ እምነት በእስራኤል ምድር አላገኘሁም" በማለት ተናገረ። ማቴ 8:10 ሉቃ 7:9።

ጌታ ወንጌልን በሰማርያም ሰብኳል። ለደቀ መዛሙርቱም ". . . በኢየሩሳሌም ፤ በይሁዳም ሁሉ ፤ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ብሎአቸዋል። ሐዋ 1:8። ከዚህ በተጨማሪ " ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።" ማር 16:15 ፤ "ሂዱ አሕዛብን ሁሉ እያጠመቃችሁና እያስተማራችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጊቸው" በማለት ተናግሯል። ማቴ 28:19።

ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ መርህ በመከተል በአንድ ወቅት ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ሰዎች እንዲህ በማለት አስተምሯል። "በዚያን ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ፤ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ ፤ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ፤ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ፤ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል . . . እንግዲያስ ከእንግዲህስ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባለ አገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።" ኤፌ 2:12 ፤ 13:19።

ጌታ አይሁድን ከሳምራውያን አስታርቋል። ይህንን በተመለከተም የደጉን ሳምራዊ ምሳሌ በማስተማር እውነተኛ የእግዚአብሔር ወገንነቱን መስክሮለታል። ከሳምራዊቷም ሴት ጋር ተወያይቷል። ሌሎችንም በብዙዎች ዘንድ

www.ethiopianorthodox.org

ተጠልተውና ተንቀው የነበሩትን ቀራጮችና ኃጢአተኞች አንድ አድርጓቸዋል።የፈሪሳዊውና የቀራጩንም ምሳሌ ሲናገር በፈሪሳዊው የተጠላው ያ ቀራጭ እንዴት በእግዚአብሔር ጸድቆ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ አስተምሯል። ሉቃ 18:9-14።

እኛም ዘወትር በማያቋርጥ ዕርቅና ሰላም እንድንኖር ጠይቆናል። ስለ ጠላቶቻችን እንኳ እንዲህ ነው ያለን "እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት። ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ . . . ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ክፉውን አትቃወሙ።" ማቴ 5:38-44። መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሎናል። "ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ . . . ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ . . . ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማም አጠጣው" ሮሜ 12:17-20።

ቅዱስ ጳውሎስም ተማሪው ፊሊሞናን ሲመክረው "አናኒሞስን እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ተወደደ ወንድም አድርጎ እንዲይዘው በመጠየቅ በሁለቱ መካከል ሰላም እንዲወርድ አድርጓል። እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ብትቆጥረኝ እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው። በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ግን ወይም ብድር ያለበት እንደ ሆነ ይህን በእኔ ላይ ቁጠር። እኔ ጳውሎስ እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ።" ፊል 16:19።

ክርስትና ጠብና ጦርነት እንዳይቀሰቀስ የሚቻለውን ሁሉ አድርጋለች። ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶሳውያን መካከል ጠብና ክርክር እንዳለ በሰማ ጊዜ ገስጾአቸዋል። 1ኛ ቆሮ 1:10 ፤11 ክርስትና ፍጹም ለሆነ ፍቅርና ራስን አሳልፎ ለመስጠት እስከመድረስ ጥሪ የሚያቀርብ እምነት ነው። በክርስትና ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ እንደ ነፍሰ ገዳይ ነው የሚቆጠረው። ጠብና ክርክርን በሰዎች መካከል የሚያመጣው ቁሳዊው ዓለምም ምን ያህል አጥፊ እንደሆነም ክርስትና ያስተምራል። ስለዚህም እያንዳንዱ ሰው በሚቻለው ሁሉ ሰላምን መፍጠር አለበት። ከአንዱ ወደ አንዱ ያልሆነና ያልተባለ ነገር ይዞ የሚመላለሰውን ወሬ አቀባባይ ሰው ከመካከል ማስወገድ ሰላምን በሰዎች መካከል ለማስፈን ዓይነተኛው ጠቃሚ መፍትሔ ነው።

ጥላቻንና ጠብን በሰዎች መካከል የሚዘራ ወሬኛ ሰው በሰዎችና በዕፅዋት ላይ ሰደድ እሳት የሚለቅ ሰውን ይመስላል። በእርግጥም ሰላምን ያጠፋታል። ልትናገረው የምትወደው መልካም ነገር ካለህ ተናገረው። አለበለዚያ ግን ዝም በል።አንዱ ወንድሙን በመጥፎ አንስቶ ለአንተ ቢያማልህ ምንም ነገር እንዳልሰማህ ዝም በለው። በሁለት ሰዎች መካከል ጠብና ክርክር ስትሰማ እነርሱን በማስታረቅ ያጡት ፍቅር ድጋሚ በልቦናቸው እንዲቀጣጠል አድርግ። ይሄኔ የእግዚአብሔር ልጅ ትባላለህ።

ወሬኛ ሰው ሰላምን አውዳሚ ነው ካልን ፤ ሰዎችን ወደ ቀስቀሱት ጸብ መነሻ እየመለሰ ፤ ለክፋት የሚያነሳሱ የማቀጣጠያ ቃላትን እየጨመረ ፤ የራሱን በጎ ያልሆነ አስተያየት እያከለ የሚያፋጀውን ሰው ደግሞ ምን እንለዋለን?



በእውነቱ በመካከላቸው እሳትን ነው የሚያቀጣጥለው። እንዲህ ያለው ሰው "የእግዚአብሔር ልጅ" ሊባል አይችልም። እንደ ጌታው ሰላምን ፈጣሪ አይደለምና።

የቆየና የተዘነጋ አንድ ንትርክን ለሰዎች የሚያስታውሰውንስ ምን እንበለው? ወይም ደግሞ ቀደም ሲል የተነገሩ የጠብ ቃላቶችን በማስታወስና አቀናብሮ በማቅረብ ተናጋሪው ሰው ሊያስታውሳቸው ባይችልም እንዲያስታውሳቸው የሚወተውተውንስ ምን እንለዋለን? ከሁሉ በላይ የሚያስደንቀው ደግሞ ይህ ወሬ አመላላሽ በዚህ መንገድ ሲመላለስ ልቦናው በወንድሙ ላይ ከፍተኛ ጥላቻን አሳድሮ ሳለ ወዳጅነቱን ለማረጋገጥ መሞከሩ ነው። ይህ ሰው ንጹህ የነበረውን ውኃ የሚያደፈርስ ነው።

አንተ ግን የአንድ የወንድምህን ጠላት በማጥቃት ከዚህ ወንድምህ ጋር ወዳጅነትህን ለማጠናከር አትሞክር ፤ አታስብም። በሁለቱ መካከል አስታራቂ ሆነህ መገኘት ብትችል ግን እጅጉን መልካም ነው። ለመሆኑ እንዲህ ባለው አድር ባይነትና ሽንገላ ጠንቅ የተነሳ ስንት ንትርክና ጠብ ተፈጥሮ ይሆን ምን ያህል ሰዎችስ አንዳችም የጠላትነት ስሜት ባላሳደሩባቸው ወገኖቻቸው ላይ እንዲህ ያለውን ክፉ ጠብ እንዲጭሩ ተገደው ይሆን?

በእንዲህ ዓይነት መልኩ የሚፈጠረው ንትርክና ጠብ በጎሳዎች መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ይመስላል። በዚህ ግጭት ውስጥ ደግሞ ሰላምን የሚያወርድ ስለማይገኝ በጎሳዎች መካከል ያለው ጠብ እየሰፋና እየጠነከረ ይሄዳል።

እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ግን "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ዘወትር ሊያስታውሱ ይገባቸዋል።

## መ. ውሳጣዊ ሰላም

በዚህኛው ሰላም አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ትሆናለህ። የእግዚአብሔር ልጆች ሰውነቶቻቸውና ነፍሶቻቸው እርስ በእርሳቸው አይቀዋወሙም። ሁለቱም በእግዚአብሔር ፍቅር ተስማምተውና አንድ ሆነው ይኖራሉ እንጂ።

የእግዚአብሔር ልጆች ውስጣዊ ሕይወታቸው የተከፋፈለ አይደለም። ልቦናቸውን ፈንቅሎ የሚወጣው ሰላም ሌሎችንም ያጥለቀልቃል። በእርግጥም ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም የሚኖር ሰው በውስጡ በሚፈጠረው ደስታ ሁልጊዜ ሐሴት ያደርጋል። ይህ ሰላም የአእምሮና የልብ ሰላም ነው። ይህ ሰላም ያለው ሰው አእምሮው የተረጋጋ ነው። ሕይወቱ በእምነት የተሞላ ነው። ልቦናውም የሰከነና የማይታወክ ነው። አይረበሽም አይፈራምም። ጭንቀት ተስፋ መቁረጥ መደነጋገርና ጥርጣሬ በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም።

www.ethiopianorthodox.org

ስለሆነም ይህ ሰው ሰላማዊ ኑሮን ይመራል። የእግዚአብሔር እንክብካቤና አርቆ አስተዋይነቱ እንደሚጠብቁት ያምናል። ምንም እንኳ የከፋና የበረታ የርኩሳን መናፍስት ኃይል ቢከበውም እግዚአብሔር እጅጉን እንደሚበረታ ያውቃል። እግዚአብሔርም እንዲህ ነው የሚለው"እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፤ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ።" ሐዋ 18:9-10።

በእርግጥም የሰው እምነቱ ደካማ ከሆነ ሰላሙን ስለሚያጣ በቀላሉ ይታወካል። ነቢዩ ዳዊት በሞት መካከል እንኳ ሲሄድ ውስጣዊ ሰላም ስለነበረው አልፈራም። መዝ 22 እኒያ ሠለስቱ ደቂቅም ወደ እቶኑ እሳት ሲጣሉ ውሳጣዊ ሰላማቸውን ጠብቀው ስለነበር አልፈሩም። ዳን 3።



# ምዕራፍ ስምንት

## 1. ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጽጌረዳ አበባ የተንቆጠቆጠ ምንጣፍ የተዘረጋበት ጥርጊያ መንገድን ለሰዎች በፊታቸው አላዘጋጀም። ይልቁንም ለሰዎች ውጣ ውረድ የበዛበትና አድካሚ መግቢያውም ጠባብ እንደሆነ ተናገራቸው እንጂ። "ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና ፤ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" ማቴ 7:14 እንዲህ በማለቱም ሰዎች ስለ ስሙ እንዲሁም ስለ ጽድቅ ሲሉ መከራን መቀበል እንደሚጠብቃቸው ገለጸላቸው።

ስለሆነም "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው ፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቀፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ" አለ። ማቴ 5:10-12 ፤ ሉቃ 6:22-23።

አንድ ሰው የጽድቅን ሥራ ቢሠራ ይደክማል። ይህ እውነታ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ፊት በግልጽ ሊታይ ይገባዋል። ጌታ እንዲህ ነው ያለው "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።" ማቴ 16:24። ከዚህ በተጨማሪ በመጸሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተጽፎአል "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል።" ሐዋ 14:22። የሲራክ ልጅ ኢያሱ ይህን ·አስመልክቶ በእርሱ ለተሾመው መነኩሴ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ የተመረጡ ናቸው። "ልጆ ሆይ! አንተንትህን እግዚአብሔርን ለማገልገል ከሰጠህ ብዙ ፈተናዎችን ለመጋፈጥና ለመቋቋም ካሁኑ ራስህን አዘጋጅ።"

አንድ በእግዚአብሔር መንገድ የሚጊዝ ሰው የመንፈሳዊ ሕይወት ምርጫው ምን ያህል ትክክለኛ መሆኑንና በዚያም እስከ መቼ ድረስ በጽናት እንደሚቆይና እንደማይቆይ ለማወቅ ብዙ አስቸጋሪ መከራዎችን መጋፈጥ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህን መከራዎች የሚያስከትሉ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ። ከእነዚህም አንደኛው ዲያቢሎስ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ሲሆኑ ስለሚቀና ሊያስቸግራቸው መጀመሩ ነው። እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ከዲያቢሎስ ወደነዚህ ሰዎች እየተላኩ በከባድ ፈተና ይፈታተኗቸዋል። በፊታቸውም ብዙ መሰናክሎችን በመደንቀር ከጀመሩት የእግዚአብሔር መንገድ እንዲወጡ ማስገደድ ይጀምራሉ። በእግዚአብሔር መንገድ መጊዝም በጣም አስቸጋሪና ሊዘልቁት የማይቻል አድርገው እንዲያስቡ ማድረግ ይሞክራሉ። ከዚህ ሌላ እነዚሁ ርኩሳን መናፍስት ወደ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች አንዱን በመላክ እንዲወቅሱና በሐሰት እንዲከሰሱ ያደርጋሉ። ወይም ደግሞ ሰይጣናዊ

www.ethiopianorthodox.org

ታሪክ እንዳላቸው አድርገው ይናገራሉ። አልፎ ተርፎም እንዲሰደቡና እንዲሰደዱ ያደርጋሉ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ መከራዎችን ተቀብሏል። በተደጋጋሚም እንፈልግሀም ተብሏል። በቤተ ሳይዳ ለ38 ዓመታት ተዘንግቶ የነበረውን በሽተኛ ከፈወሰው በኋላ "ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር። ሊገድሉትም ይፈልጉት ነበር።" የሚል ቃል በዮሐ 5:16 ላይ ተጽፎ እናነባለን። በአንድ ወቅትም ጌታ በሰማርያ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያልፍ በወደደ ጊዜ በሰማርያ ያሉት ሰዎች ሊቀበሉት አልወደዱም። ሉቃ 9:52-53። ሌላው ቀርቶ ገና በሕፃንነቱ በግብጽ በስደት ላይ የግብጽ ጣዖታቱ በፊቱ በሚያስደንቅ ሁኔታ እየተገረሰሱ ሲወድቁ በዚያ ያሉት ነዋሪዎች አንፈልግሀም ብለውታል። "የግብጽም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ።" ኢሳ 19:1

ልክ እንደ አምላካቸው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙዎች ነቢያትና ሐዋርያት መከራን ተቀብለዋል። ስለዚህም ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ "በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ።" ማቴ 10:23 ከዚህ በተጨማሪ "ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳደዋቸዋልና" አለ። ማቴ 5:12 በብሉይ ኪዳንም ስለነበሩ ስለ ነቢያቱም እንዲህ አለ። ". . . ወደ እነርሱ ነቢያትንና ሐዋርያትን እልካለሁ ፤ ከእነርሱም ይገድላሉ ፤ ያሳድዱማል።" ሉቃ11:49 ከዚህ ሌላ "ከእነርሱም በምኩራባችሁ ትገርፋላችሁ፤ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ" በማለት ተናገረ። ማቴ 23:34

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱም እንደሚያሳድዱአቸው ነግሯቸዋል እንዲህ ሲል "ከዚህም ሁሉ በፊት እጃቸውን በላያችሁ ይጭናሉ ፤ ያሳድዱአችሁማል። ስለ ስሜም ወደ ምኩራብና ወደ ወኅኒ አሳልፈው ይሰጡአችኋል። ወደ ነገሥታትና ወደ ገዥዎችም ይወስዱአችኋል።" ሉቃ 21:12 ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ጌታ ዓይኑን ካበራለት በኋላ ይህን ብርሃን ስላጎናፀፈው አምላክ ሲመሰክር የሰሙት አይሁድ "አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ አንተም እኛን ታስተምረናለህ?" ነበር ያሉት። ዮሐ 9:30-34። ጻድቁ ነቢይ ንጉሥ ዳዊትም በንጉሥ ሳኦል ብዙ ስደት ደርሶበታል።

ሰው ጻድቅ በመሆኑ ቢሰደድ ታላቅ ዋጋ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ "ክፉን የሚያደርጉ ይስታሉ" ይላል። ምሳ 14:22 ስለሆነም ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያው እንዲህ አለ "ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል። ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር።" 1ኛ ጴጥ 4:15-16። እንዲህ ያለው የብፅዕና ብቃት ከአንተ ሕይወት ጋር ከተገጣጠመ በአንተ ላይ የሚመጣው ሁሉ ከጽድቅ ሥራዎችህ የተነሳ ለመሆኑ እርግጠኛ ሁን። ነገር ግን ስለ ክፉ ዐመልህ ስትሰደድ ስትሰደብና ስትወነጀል በጸጋ ብትቀበል ይህ አንዳች ስንኳ ብፅዕና አያስገኝልህም።



መምህራችን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ በማለት ገልጾ አስተምሮናል። "በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገስ ምስጋና ይገባዋል።" 1ኛ ጴጥ 2:19። "በግፍ መከራን የሚቀበል" የሚለውን ሐረግ አስተውል! አንዳች ሳይበድል የሚቀበለው ኃዘንና ሕማም ማለት ነው። ሐዋርያው ከዚህም በመቀጠል እንዲህ አለ። "ኃጢአት ሠርታችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ ምን ክብር አለበት ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱ ኃጢአት አላደረገም ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም።" 1ኛ ጴጥ 2:20-23። ቅዱስ ጴጥሮስ አሁንም ይህን በመሰሉ መመሪያዎች ላይ በማተኮር እንዲህ አለ። "ነገር ግን ስለ ጽድቅ እንኳ መከራን ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ።" 1ኛ ጴጥ 3:14።

ይህም ማለት ስለ እምነታችሁ ብላችሁ ማንኛውም ዓይነት ጉዳትና መከራ ቢደርስባችሁ እናንተ ብፁዓን ናችሁ ፤ ዋጋችሁም በሰማያት ታላቅ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ረገድ ነቢያት ከአገር አገር ተሰደዱ። እናንተም የክርስቶስን ሕማም ትጋራላችሁ ማለት ነው። እርሱ ስለ ጽድቅ መከራን ከተቀበለ በኋላ አሁንም ሊቀበሉት ስላልወደዱ ስለ እርሱ በጣም መጥፎ የሆኑ ቃላትን በመናገር ይወቅሱት ነበር። ሐሰተኞች ናቸው። የሐሰት ምስክሮችንም በእርሱ ላይ በማቆም ከኃጢአተኞች ጋር እንዲቆጠር አደረጉ። ኢሳ 53:9። ስለዚህም ሕማምን እንደ እርሱ ሆነህ የምትቀበል ከሆነ ከሐዋርያው ጋር በመሆን "ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም" በል። ማቴ 10:24። በመቀጠልም እንዲህ በል። "በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ ከሆነ በደረቀውስ እንዴት ይሆን?" ሉቃ 23:31።

በእርግጥ ስለ ጽድቅ ብለህ በምታደርጋቸው ሥራዎች ምክንያት አንተን የሚያሳድዱህ ወደው አይደለም ፤ በሰይጣን ተገደው እንጂ። ስለዚህ ኢላማችንን የምናነጣጥረው በእርሱ ላይ ሳይሆን በራሱ በዲያቢሎስ ላይ መሆን አለበት። ለዚህም ነው ታላቁ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ አርዮስን ባወገዘው ጊዜ "ዋነኛው ጠላታችን አርዮስ አይደለም ዲያቢሎስ እንጂ።" በማለት የተናገረው።

በእነዚህ እውነተኛ አመለካከቶች ላይ ተመርኩዘን በሥጋ ጠላት የሆኑን እነዚህ ጠላቶቻችን እኛን ለማጥፋት ሆን ብለው የተነሳሱ ጠላቶቻችን ስላይደሉ ልንወዳቸው እንዲገባን እንማራለን። የእኛ ቀንደኛ ጠላት ዲያቢሎስ ነው። በሥጋ ያሉ ወገኖቻችን ፈቃዱን በልቦናቸው የሚዘራባቸው የዲያቢሎስ ፈቃድ ተሸካሚዎች እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም። ስለሆነም ይቅር ብለናቸው ስለ እነርሱ በማዘን ከእርሱ የሚላቀቁበትን መንገድ በመሻት መጸለይ አለብን። ይህን ጊዜም "ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ" የሚለው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ትርጉም ገብቶናል ማለት ነው። ማቴ 5:44 እንግዲህ እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ከዲያቢሎስ ባርነት ነፃ እንዲያወጣቸው ጸልዩላቸው። ክርኩሳን መናፍስት

www.ethiopianorthodox.org

እንዲላቀቁና ወደ ንስሐ እንዲያቀኑ በማድረግ አድኑአቸው። ከርኩሳን መናፍስት ነፃ ከወጡ እናንተን ለማጥቃት አይነሳሱምና አሁንም ጸልዩላቸው። ይህን በማድረግም እናንተ ስለ ጽድቅ ብላችሁ ብትሰደዱ ሁሉን በመቻል ይልቁንም ስለ እነርሱ በመጸለይ ታግሳችሁ ስለምትቆዩ ዋጋችሁን በሰማያት ታገኛላችሁ። በምድርም ሳላችሁ የእግዚአብሔር ርዳታ ከእናንተ አይለይም።

አይሁድ ዕውር ሆኖ ተወልዶ ያደገውንና በኋላ በጌታ የተፈወሰውን ሰው ያሳደዱት ከምኩራባቸውም ያስወጡት እንጂ እርሱ ጌታን አገኘ። ዮሐ 9:35። ይህ ሰው እንዲህ ያለውን ግንኙነት ይሻው ስለነበር ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኘ። ነፍሱ የሚረዳትን ትፈልግ ነበር። ስለሆነም ጌታ አገኘው ፤ ወደ እምነት መራው ፤ አይዞህም አለው። ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ ሕይወት በውስጡ ያለ እግዚአብሔር ማፅናናት የሚደረግ ሐዘን እንዳለበት አድርገህ አትቁጠር።

መንፈሳዊው ሕይወትም በሕማም ወይም በስድብ ወይም በወቀሳና በማሳደድ ብቻ የተሞላ አድርገህ አትቁጠር። "እነሆ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ።" ኢሳ 49:16። እንዲሁም "የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሯል።" ማቴ10:30 የሚል ቃል አለና። ቅዱስ ዳዊትም እንዲህ ይለናል "ጻድቃን እጃቸውን ወደ ክፋት እንዳየዘረጉ የኃጥአን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይኖርም።" መዝ 124:3። ምናልባት ይነካቸው ይሆናል እንጂ በእነርሱ ላይ አይኖርም።

በአጠቃላይ መንፈሳዊ ህይወት ከሰዎች መከራን ከእግዚአብሔር ደግሞ ብርታትን የሚያገኙበት የጽድቅ ሕይወት ነው። ቅዳስ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልፅ "በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም . . . ስለዚህም አንታክትም ነገር ግን የውጪው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።" ብሏል። 2ኛ ቆሮ 4:8፤9፤16። ውጪያዊው በውስጣዊው ብርታትና በውጪያዊው የእግዚአብሔር ርዳታ ይደገፋል። ስለዚህም ጌታ "ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገራባችሁ ብፁዓን ናችሁ" አለ።

ጌታ እነዚህን ቃላት ሲናገር እኛ ብቻ እናደርጋቸው ዘንድ ሳይሆን እርሱ ራሱ በማድረግ አሳይቶን ነው። ስለዚህም ሐዋርያው ስለ እርሱ እንዲህ አለ። "እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።" ዕብ 2:18። በተጨማሪም "ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም" ተብሏል። ማቴ 13:57።

ጌታችን በአንድ ወቅት በምኩራብ በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙዎች በመገረም ትኩር ብለው ከተመለከቱት በኋላ እንዲህ ነበር ያሉት። "እነዚህን ነገሮች ይህ ከወዴት አገኛቸው ለዚህ የተሰጠው ጥበብ ምንድናት? በእጁ



ተአምራትን ያደርጋል! ይህ ጠራቢው አይደለምን? የማርያምስ ልጅ አይደለምን? ይሰናከሉበትም ነበር።" ማር 6:2-3። እነርሱ ይህን ሁሉ ይበሉ እንጂ እርሱ "ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም።" 1ኛ ጴጥ 2:23። "ተጨነቀ ተሰቃየም አፉንም አልከፈተም።" ኢሳ 53:7።

ጌታ ስንቱን ስድብና ዛቻ ነው በዝምታ የቻለው! አዎ- ብዙ ተናግረውታል። "ሳምራዊ እንደሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ እኛ መልካም እንል የለምን?" ዮሐ 8:48 "በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል።" ሉቃ 11:15 "በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጪ፤ የቀራጮችና የኃጢያተኞች ወዳጅ።" ማቴ 11:19። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ "ሰንበትን የማያከብር ፤ የሙሴን ህግ የሚሽር ፤ የቄሳር ተቃዋሚ" በማለት ወንጅለውታል። ለፍርድ ባቆሙት ጊዜ ሊቀ ካህናቱ "ተሳድቧል! እንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ስለ ምን ያስፈልገናል?" ብሏል። ማቴ 26:65።

ነቢያትና ቅዱሳን የተጋፈጡትን ዛቻና ስድብ ተከታትሎ ማቅረብስ ምን ያህል ይቀል ይሆን? ይህ ጽሑፍ ከብዙ በጥቂቱ የተውጣጣ ስለሆነ እናንተ መጸሐፍ ቅዱስንና የቅዱሳንን ገድል አንብባችሁ ስለዚህ መረዳት ትችላላችሁ። ምናልባት የነቢያቱን በተመለከተ ሁኔታው ይገልጽልን ዘንድ ጌታ የተናገረውን እንጥቀስ። "ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።" ማቴ 5:12። ቅዱስ ጳውሎስም በአቴና አደባባይ ቆሞ ሲሰብክ "ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል?" ሐዋ 17:18 ብለውታል። ስለ ጌታ ትንሣኤም በሚናገርበት ወቅት "ጳውሎስ ሆይ! አብደሃል እኮ! ብዙ ትምህርትህ ወደ እብደት ያዞርሀል።" ሐዋ 26:24 ተብሏል። የሐዋርያት ሁሉ ሕይወት በደስታ የተሞላ አልነበረም፤ በመናቅና በመዋረድ እንጂ። በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱም ሆነ ስለ ባልንጀሮቹ ሐዋርያት ተገብቶ እንዲህ በማለት ተናገረ። "በክብርና በውርደት በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን። አሳቾችና ሀዘንተኞች ስንባል ዘወትር ደስ ይለናል።" 2ኛ ቆሮ 6:8-10።

በእርግጥም አባቶቻችን ሐዋርያት ወቀሳን መጥፎ ስምንና ክፉ ሰው ተደርጎ መቆጠርን መቻላቸው ዋጋ ያለው ነገር ነው። ይሰደዱ እንጂ ተጽናንተዋል። "እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም።" 2ኛ ቆሮ 4:9። ስለሆነም ሲያሳድዱን የሐዋርያትን መከራ እየተጋራን መሆኑን እንዘንጋ። ከኖሩበት ከቅድስናቸው ድርሻ ካላገኘህ ሌላው ቢቀር እንኳ ከመከራቸው ተካፈል። ቅዱስ ጴጥሮስ ከእኛው ጋር በማዘን እንዲህ ብሏል። "ወዳጆች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ። ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደስ እንዲላችሁ ሐሴት አድርጉ።" 1ኛ ጴጥ 4:12፤13። ይህ ደግሞ የጌታን መከራ መካፈል መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሲጽፍልን "እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ ፤ በመከራውም እንድካፈል፤ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ ብሏል።"

www.ethiopianorthodox.org

ፊል 3:10። ይህም ስለ እግዚአብሔር ስንል ወይም መሸከም እንዲገባን አውቀን የምንሸከመውን የመስቀሉን ሕይወት መጋራት ነው።

ከዚህ በኋላ ከሐዋርያት ጋር እንደ ሐዋርያው "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ።" ገላ 2:20 እንላለን። ግን ለምንድነው መስቀሉን የምንሸከመው? አንድ ልናውቀው የሚገባን እውነታ አለ። ይኸውም ሰይጣን በዓለም መኖሩንና አሁንም ያለ ውዴታ ክፉ ማሰራቱን። አረም አሁንም ቢሆን በእግዚአብሔር ማሳ ውስጥ አለ። እስከ አጨዳው ወቅት ድረስም እየበዛና እየጨመረ ይሄዳል። ማቴ 13:30። ብርሃን በዓለም እንዳለ እንዲሁ ጨለማም አለ። እግዚአብሔርም ብርሃንን ሲፈጥር "ጨለማ ከእንግዲህ አይኑር" አላለም። ነገር ግን "ብርሃን ይሁን" አለ። ስለዚህ ጨለማ እንዳለ ቆየ። ጌታም ለአይሁድ እንዲህ አላቸው። "ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው።" ሉቃ 22:53።

ስለሆነም የርኩሳን መናፍስትም ኃይል ስላለ ጻድቃንንና ቅዱሳንን ይዋጋል። አንዳንድ ጊዜማ ውጊያቸው ወሰን ስለሌለው በጣም ብርቱዎች ይሆናሉ። ጻድቅ ሰው እውነትን ብቻ ይናገር መልካምንም ያደርግ ዘንድ በገደብ ተይዟል። ክፉ ሰው ግን ሐሰትን ይናገራል ፣ ያታልላል ፣ ተንኮልን ይሸምቃል ፣ ሰዎችንም ለመጣል ወጥመዶችን ይዘረጋል። በዚህም ሰዎችን ይጎዳል ፣ ይበቀላል፣ ይፈታተናል ፣ ምሥጢር ያባክናል ወዘተ። ጻድቁ ሰው ግን እነዚህን ሁሉ ክፋቶች አያደርግም። ስለዚህም ሚዛኑ እኩል አይሆንም።

ሰይጣን በመጀመሪያ ድል ሊያደርግ ይችላል። ቢሆንም ጻድቁ ሰው ስለ ጽድቅ ሲል የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀምና ሁሉን በመቻል እግዚአብሔር እስኪታደገው ድረስ በመከራው ይጸናል።

## ሀ. የክፉ አድራጊዎች አርአያዎችና ችግሮቻቸው

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በአንድ የሕዝብ ሆስፒታል ወይም የሕክምና ማዕከል የሚሠራ ሐኪም ነው። ይህ ሐኪም ጻድቅ ስለሆነ ገንዘብን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ለማግኘት ሲል ኃላፊነቱን ሊያጎድፍ አይወድም ። ይህ ሐኪም ታዲያ ወደዚህ ኃላፊነት የመጣው ቀደም ሲል ከእርሱ በፊት በቦታው ላይ የነበረውንና በሽተኞችን በተለይም የቀዶ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ወደ ግል ክሊኒኩ የሚመራና በነፃ እንዲታደላቸው ሆስፒታሉ ያስመጣውን መድኃኒት በገንዘብ የሚሸጥ አሳፋሪ ሐኪምን በመተካት ነው። ነገር ግን ይህ ጻድቅ ሐኪም የዚያን ሰው አርአያ ለመከተል አሻፈረኝ አለ።

ከዕለታት በአንድ ቀን አንድ ገበሬ ወደዚህ መልካም ሐኪም ገንዘብ ይዞ በመምጣት የቀዶ ጥገና እንዲያደርግለት ገንዘቡን ከኑያው እያወጣ ይጠይቀዋል። ያ ሐኪምም ገንዘቡን አልቀበልህም ይለዋል። በዚህ ጊዜ ገበሬው ያወጣሁት ገንዘብ አንሶት ይሆናል በሚል ግምት አሁንም አሁንም መጠኑን እየጨመረ እንዲቀበለው ቢወተውተውም ሐኪሙ ሆስፒታሉ በሽተኞችን የሚያክመው በነፃ



እንደሆነ በማሳመን ገንዘቡን እንደማይቀበለው ሲያስረዳው ገበሬው በአሳቡ ይስማማል።

እነርሱ ይህን ሲነጋገሩ ያዳምጥ የነበረው የጤና መኮንን በሐኪሙ ሁኔታ በመበሳጨት "ለምንድነው ሆስፒታሉ በሽተኞችን በነፃ እንደሚያክም ለገበሬው የነገርከው? የኑሮአችንን ገቢስ ስለምን ብለህ ነው የምትዘጋው? እያንዳንዱ በአንተ ቀዶ ጥገና የሚደረግለት በሽተኛ ለአንተ የሰጠውን ገንዘብ የሚያህል ለእኛ እንደሚሰጠን አታውቅምን? እንዲህ የምታደርግ ከሆነ እኮ ኑሮአችንን ለመደጎም የምናገኛትን ማጣታችን ነው" ይለዋል።

ከዚህ በኋላማ ምኑ ቅጡ። በዚህ ንጹህ ሐኪም ላይ የወቀሳው መዓት አንዱ በአንዱ ላይ እየተፈራረቀ ያወርድበታል። በመጨረሻም በሐሰት ልክ ከመንግሥት ፖሊሲ ውጪ እንደሚሠራ አድርገው ስለ በጎ ሥራው ይከሱታል። ይህም ሰው ስለ ታማኝነቱና ስለ ጽድቅ ሲል ራሱን አሳልፎ ይሰጣል። ራቅ ብሎ ወደሚገኝ ሆስፒታልም እንዲዛወር ያደርጉታል። ይህ ሰው ስለ ጽድቅ ሲሉ ከተሰደዱት መካከል የሚፈረጅ ሰው ነው።

ሌላው ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በሁላችንም ዘንድ የሚታወቀው ጻድቁ ዮሴፍ ነው። ዮሴፍ ከጌታው ሚስት ጋር ዝሙትን አልፈጽምም ያለ ሰው ነው። ታዲያ መጨረሻው ምን ሆነ? የጲጥፋራ ሚስት በማስመሰል ሊያስነውራት እንደሞከረ አድርጋ በሐሰት መሰከረችበት። በእርግጥ ለጊዜው ዝናውን ለማጉደፍ ተሳክቶላታል። ስለሆነም ከተሰጠው የኃላፊነት ቦታ እንዲነሳና ከንጉሡ ቤት እንዲባረር በመጨረሻም በወህኒ እንዲጣል ሆነ። ዘፍ 39። በዚህ ጊዜ ዮሴፍ "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው" የሚለውን የብፅዕና ማዕረግ አገኘ። በእርግጥም ዮሴፍ ስለ ጽድቅ ሥራው ሲል ተገፍቷል። ሰይጣን በመጀመሪያ የውጊያውን የድል ጽዋ ይቀምስ እንጂ እግዚአብሔር ዮሴፍን አልተወውም። ስለሆነም በመጨረሻ ላይ ንጉሡ የመንግስቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር አድርጎ ሾመው። በተጨማሪም የፈርዖን አባት የቤቱ ሁሉ ጌታና የግብጽም አለቃ ተብሎ ሊጠራ በቃ። ዘፍ 45:8።

ይህን ስንመለከት ልክ የእግዚአብሔር መልአክ በዚያን ጊዜ ወደ ዮሴፍ ወርዶ በጆሮው "ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ፣ ሐሴትም አድርጉ።" ያለው ይመስላል። ማቴ 5:11-12። ዮሴፍ ዋጋውን ያገኘው በሰማያት ብቻ ሳይሆን በምድርም ጭምር ነው። በምድር ላይ ከነበሩ የታሪክ ቅዱሳን አንዱ ለመሆን በቅቷልና።

ስለዚህ ነቢዩ ሚልክያስ እንዲህ አለ ". . . እግዚአብሔርም አደመጠ ሰማም። እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ።" ሚል 3:16። እግዚአብሔር ስለ ጽድቅ ሲሉ የደከሙትን የጻድቃን ድካም አይረሳም። እርሱ ራሱ ለሥራቸው ምሥክር ስለሆነ ለእያንዳንዳቸው እንደ ሥራቸው ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል። እግዚአብሔር ስሙ ይባረክና ጽድቅን ለጠበቁት ሃይማኖተኞች የሚከፍለውን ዋጋ በሚገባ ያውቃል። ከዚህም የተነሳ

www.ethiopianorthodox.org

ጻድቅ ሰው ለክፉ አድራጊዎች ፍላጻ የተጋለጠ ነው። መዝሙረኛው "ከትንሽነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ተሰለፉብኝ ፤ ኃጢአተኞች በጀርባዬ ላይ መቱኝ" ይላል። መዝ 128።

እዚህ ላይ የምናስተውለው ምንም እንኳ ለረዥም ጊዜ በተከታታይ ጀርባውን በጅራፍ ቢገርፉትም ምንም እንዳልቆሰለ ነው። በመጨረሻም እግዚአብሔር ስላዳነው "እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ፤ የኃጢአተኞችን አንገታቸውን ቆረጠ።" አለ መዝ 128:4። ይሁን እንጂ ኃጢአተኞች አሁንም ብላቴናውን መዋጋታቸውን አላቋረጡም።

ጻድቅ ሰው ለኃጢአተኛው ሰው ስድቡን በስድብ አይመልስም። ሕሊናቸው እሺ ስለማይላቸውም ጻድቃን ቃላትን አይመላለሱም ፤ አያታልሉም አይደባደቡምም። እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለሚኖሩም በቀልን እነርሱ ይበቀሉ ዘንድ አይሞክሩትም። ሮሜ 12:19 ይልቁንም ሁለተኛውንም ምዕራፍ ጨምረው ይጊዛሉ። እጀ ጠባቡን ለሚወስድባቸውም ሁለተኛውን ጉንጭ ያዞራሉ። መጎናጸፊያቸውን ይተውለታል። ማቴ 10:39-41 ይህን የሚመጣባቸውን መከራ ሁሉ ጌታቸው መጥቶ ፍትሕ እስኪሰጣቸው ድረስ በዝምታና በትዕግስት ይወጡታል። "እርሱ እውነትን ለዘላለም የሚጠብቅ ለተበደሉት የሚፈርድ ነው።" መዝ 145:6-7። ሙሴም ስለ ጌታ መታደግ እንዲህ አለ "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል ፤ እናንተም ዝም ትላላችሁ።' ዘጻ 14:14።

ይህን ሁሉ መከራ ይቀበሉ እንጂ ጻድቃን ከአሳዳጆቻቸውና መከራን ከሚያጸኑባቸው እጅጉን የሚበልጡ ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም። ሌሎችን የሚያሳድዱ ሰዎች የሚያሳድዱት ራሳቸውን ስለሆነ ምስኪናን ናቸው። ይህን በማድረጋቸው የልብ ንጽህናቸውንም ሆነ የዘላለም ሕይወትን ያጣሉ። በደላቸውን የሚቃወመውንም አምላክ ያጡታል። መልካም ስምንም ያጣሉ። ስለ ክፉ ሥራቸውም ሰዎች ስለ እነርሱ በጎ አመለካከት አይኖራቸውም። ከጊዜ በኋላም በዚሁ በክፉ ሥራቸው ጠንቅ ይጠፋሉ። ታሪክ እነዚህ አሳዳጆች ሕይወታቸው እንዴት ባለ አስከፊ ሁኔታ እንዳለፈች በሚገባ እየመሰከረ ይነግረናል። የተሰደዱትንና የተገፉትን ግን እግዚአብሔር በምድርም ሆነ በሰማያት ታድጊቸዋል።

ጻድቅ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሙሉ በልብ ንጽህናው ደስተኛ ነው። ሕሊናው ስለ አንድ ነገር አይከሰውም። እንዲያውም መገፋቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በጾምና በጸሎት እንዲያጠነክር ስለሚያደርገው መንፈሳዊነቱን በስፋትና በጥልቀት ይቀጥላል። እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን እጁን እንደሚዘረጋ ፤ መከራንም በመታገስ ዋጋ እንደሚያገኝ በእምነት ከመኖር ጋር ይማራል። ለዚህ ሰው ውስጣዊ ሰላሙን ለመጠበቅ የመዝሙረኛው ቃል የጎላ ጠቀሜታ አለው። "ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም።" መዝ 126:3 ሰው ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ሕይወቱ ከተቆራኘ መከራን በደስታ ይቀበል ዘንድ ይችላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ የተከበሩ ናቸው!



"በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።" 1ኛ ቆሮ15:19።

ኃጢአተኞች በምድር ሳሉ ሲደሰቱ እኛ ግን እንደክማለን። እኛ በምድር ሳለን ደስተኞች አይደለንም ፤ ሰማያዊውን ደስታ እንናፍቃለን እንጂ። አባታችን አብርሃም ስለ ባለጸጋው ስለ ነዌና ስለ አልዓዛር የተናገረውን ቃል በሚገባ እናስተውለዋለን። "ልጅ ሆይ! አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ። አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሰቃያለህ።" ሉቃ 16:25 ስለዚህ ትኩረታችንን ማለቂያና መጨረሻ ለሌለው ለሰማያዊው ታላቅ ዋጋ እንስጥ። በኃጢአታቸው ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ የጠፉት ሰዎች አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ናቸው። እግዚአብሔር ከዔድን ገነት በማባረር ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይቀርቡ አደረጋቸው። ዘፍ 3:23-24

ስለ ጽድቅ ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞተው ደግሞ ጻድቁ አቤል ነው። ቃየን አቤልን በምድር ገጽ ላይ ያሳድደው ነበር። አቤል ጻድቅ ስለነበር ቃየን በመጨረሻ ጥቃት ሰንዝሮ ገደለው። "አቤል ከቃየን ይልቅ የሚበልጥን መስዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ ፤ በዚህም እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት።" ዕብ 11:4። ከዚህ በኋላ ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ቅዱሳን ቁጥር እየጨመረ መጣ። ገድላቸው በመጻሐፍ ቅዱስ እና በቅዱሳን አባቶች ገድላት ላይ ተጽፎ እናነባለን። ከእነዚህም መካከል እኛ መከራ ሲያጋጥመን በእነርሱ እንድንጽናና ይረዳን ዘንድ እንድንማር ጥቂቶቹን ከዚህ በመቀጠል ለአብነት ያህል ወስደን እንመለከታለን።

## ሌ. የተጋዙና የተሰደዱ ቅዱሳን አርአያዎች

- ነቢዩ ዳዊት

ዳዊት በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር አምላክ በዕድሜ ከሚበልጡት ከሰባት ወንድሞቹ መካከል ነው የመረጠው። ስለሆነም ሳሙኤል የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው። 1ኛ ሳሙ 16:13። ዳዊት ለእግዚአብሔር ያገለግል ዘንድ ስለተቀባም የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ሆነ። በተመሳሳይ ሰዓት ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ራቀ። ርኩስ መንፈስም ስለተላከበት ይሰቃይ ጀመር። 1ኛ ሳሙ 16:14። ይህን ክፉ መንፈስም ከእርሱ ያርቅለት ዘንድ ዳዊትን ያስጠራው ነበር። በዚህ ረገድ ለሳኦል የቀረበለት ሪፖርት እንዲህ የሚል ነበር። "እነሆ መልካም አድርጎ በገና የሚመታ አለ። እርሱ ጽኑዕ ኃያል ነው። በነገርም ብልህ መልኩም ያማረ ነው። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው።" 1ኛ ሳሙ 16:18 በመሆኑም ዳዊት ከሳኦል ላይ ርኩስ መንፈስን ያርቅለት ነበር። 1ኛ ሳሙ 16:23።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ዳዊት ጻድቅ ሰው መሆኑንና እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንደነበር የሚያረጋግጥልን ማስረጃ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ጎልያድን ለመግደል ያሳየው ታላቅ ችሎታውና ድል አድራጊነቱ እምነቱንና እግዚአብሔር አብሮት እንደነበር የሚያስረግጥልን ነው። ከዚህም ሌላ አንበሳና ድብ መግደሉ (1ኛ ሳሙ 17:27) እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ከጠላቶቹ ሁሉ ያድነው እንደነበር የሚያረጋግጥልን ነው።

እግዚአብሔር እንዲህ ከዳዊት ጋር አብሮ በመሆን ለዳዊት ይህን ሁሉ ዕርዳታ ቢያደርግለትና አብሮት ቢቆጋም ቅሉ ዳዊት በሳኦል ምክንያት መራራ የስደት ገፈትን መጨለጡ አልቀረም። መጸሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ሳኦልም እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ አየ . . . ዳዊትን አጥብቆ ፈራው። ሳኦልም ዕድሜውን ሁሉ ለዳዊት ጠላት ሆነ።" 1ኛ ሳሙ 18:28-29።

ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ብዙ ሙከራዎችን አድርጊል። "ሳኦልም ለልጁ ለዮናታንና ለባሪያዎቹ ሁሉ ዳዊትን ይገድሉ ዘንድ ነገራቸው።" 1ኛ ሳሙ 19:1 "ሳኦልም ዳዊትን ከግንብ ጋር ያጣብቀው ዘንድ ጦሩን ወረወረ . . . በዚያም ሌሊት ዳዊት ሸሽቶ አመለጠ።" 1ኛ ሳሙ 19:10 ከዚህ በኋላ ዳዊት ስደተኛ ሆኖ በረሃ ለበረሃ ይንከራተት ጀመር። ሳሙኤል ይገኝበት ወደ ነበረው ወደ አርማቴምም ሄደ። ከዚያም ሁለቱ ተያይዘው ወደ ነዋትዘራማ አቀኑ። በዚያም ተቀመጡ። ሳኦልም ዳዊት በዚያ እንዳለ ሲሰማ ይይዙት ዘንድ ጭፍሮቹን ላከበት። 1ኛ ሳሙ 19:20።

ከዚህ በኋላ ዳዊት ከአርማቴም አገር ከነዋትዘራማ ሸሽቶ የሳኦል ልጅ ወደ ነበረው ወደ ዮናታን ሸሸ። ካገኘውም በኋላ "ምን አደረግሁ? እኔንስ ለመግደል የሚፈልግ በአባቴ ፊት ጠማምነቴና ኃጢአቴ ምንድር ነው?" አለው። 1ኛ ሳሙ 21:10። ይህ ከሆነ በኋላም በኖብ ወደሚገኘው ወደ ካህኑ ወደ አቤሜሌክ ወጣ። 1ኛ ሳሙ 22:1። ሳኦል አሁንም ዳዊትን ማሳደድ ስላላቋረጠ ዳዊት ከዚያ ተነስቶ ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስ ሸሸ። በመቀጠልም ከጌት ወደ አዶላም ዋሻ ኮበለለ። 1ኛ ሳሙ 22:1 አሁንም ስደቱን በመቀጠል ወደ ምጽጳ ከዚያም ወደ ሔሬት ዱር አደረገ። 1ኛ ሳሙ 22:3-5 ዳዊት በሔሬት ዱር ጥቂት ቆይታ ካደረገ በኋላ እንደገና ወደ ቅኢላ ሄደ። 1ኛ ሳሙ 23:1

በእነዚህ ሁሉ የዳዊት ስደቶች ውስጥ አንድ ተደጋጋሚ ድርጊትን እንመለከታለን። ስለ ጽድቅ ሲል መሰደዱን። "ሳኦልም ሁልጊዜ ይፈልገው ነበር። እግዚአብሔር ግን በእጁ አሳልፎ አልሰጠውም።" 1ኛ ሳሙ 23:14 ከዚህ በኋላ ዳዊት በዚፍ ምድረ በዳ በጥሻው ውስጥ ኋላም በዓይንጋዲ አምባዎች ስደተኛ ሆኖ ኖረ። 1ኛ ሳሙ 23:15-29 ሳኦል የዳዊትን በዓይንጋዲ ምድረ በዳ መኖር ሲሰማ ተከታትሎት ስለመጣ ዳዊት ወደ ፋራን ምድረ በዳ መውረዱ ግድ ሆነ። 1ኛ ሳሙ 25:1



ከዚህ ሁሉ ፋታ ከማይሰጥ ተከታታይ ስደት በኋላ ዳዊት ሲድን ሳኦል ግን ሞተ። የሞተው ግን በዳዊት እጅ አልነበረም። ጻድቅ ዳዊት ከሳኦል ሌላ ከብዙ ሰዎች ይህን የመሰለ መከራ ተቀብሎአል። የእርሱ ስደት ለራሱም ሆነ ለእኛ በረከት ነው። ይህ ስደት ባይኖር ዳዊት የትህትናንና የንስሐን ሕይወት ባልተለማመደም ነበር። በሌሎች ሰዎች "የስደተኛው መዝሙራት" ተብለው የተሰየሙት እነዚያ ጣፋጭና የሚያረጋጉ መዝሙራትም ባልተዘመሩ ነበር። ይህ ስደት ባይኖርም የእግዚአብሔር እጅ ተዘርግታ ከዚያ መከራ ስትታደገውና ስትራዳው ለመመልከት በበቃበት በዚያ ታላቅ እምነት ውስጥ ባልኖረም ነበር። ስለዚህም ከልብ በመነጩ ቃላት እንዲህ አለ። "ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች ፤ ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን። ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ።" መዝ 123።

- **ሐዋርያው ጳውሎስ**

ወንጌልን በመስበክና በማስተማር ሥራ ከሐዋርያት ሁሉ በላይ የደከመው (1ኛ ቆሮ 15:10) ጻድቁና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጽድቅ ሲል ተሰዷል።

በፊልጵስዩስ ሳለ እግዚአብሔር በእርሱ አድሮ ድንቅ ተአምራትን ስላደረገ ጳውሎስ ከባድ መከራ ደርሶበታል። በዚያች አገር በምዋርተኝነት መንፈስ መጪውን ጊዜ የምትጠነቁል አንዲት ገረድ ነበረች። በዚህ በጥንቆላ ሥራዋ ለጌቶቿ ብዙ ትርፍ ታስገኝ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ግን አድሮባት የነበረውን ርኩስ መንፈስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእርሷ አስወጣላት። ጌትዎቿም የትርፋቸው ተስፋ እንደ ወጣ ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያው ሥፍራ በሹማምንቱ ፊት ጎተቱአቸው ፤ ወደ ገገርዎችም አቀረቡአቸው። የወህኒ ጠባቂው መጥቶ ከእስር ቤቱ በማስወጣት እስኪሸኛቸውና ከተማዋን ለቀው እንዲወጡ እስኪመክራቸው ድረስም በወኅኒ ተጣሉ። በዚህ ሰው አማካይነት እግዚአብሔር አዳናቸው ማለት ነው። ሐዋ 16:16-39።

ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን ሳለም እንደዚህ ያለ ስለ ጽድቅ የደረሰበት ተመሳሳይ መከራ አለ። የወንጌል ስብከቱ በዚያን ጊዜ ለአርጤምስ ቤተ ጣዖት ምስሎችን ይሰራ ለነበረው ለድሜጥሮስ ሰላም አልሰጠውም። በዚያች ከተማ ባለችው በአርጤምስ ቤተ ጣዖት ውስጥ ታላቋ አርጤምስ በመባል የምትታወቅና ከሰማይ እንደወረደች የሚታመንባት የጣዖት ምስል ነበረች። ቅዱስ ጳውሎስም ለሕዝቡ በሰው እጅ የተሰሩ ጣዖታት እነርሱ አምላክ እንዳልሆኑ በማስተማር ብዙዎችን ወደ እምነት ሊያቀርብ ሞከረ። በዚህ ጊዜ ጉባኤው ሁሉ ታወከ። ታላቅ ሰልፍም ሆነ። ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ድምፅ ሆነው "የኤፌሶኗ አርጤምስ ታላቅ ናት!" እያሉ ጮሁ። ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ኤፌሶንን ትቶ ወደ መቄዶንያ አለፈ። ሐዋ 19:23፤20:1።

አድማጭና ተቀባይ ያጣው ቅዱስ ጳውሎስ ብቻ አልነበረም ፤ ክርስቲያኖች ሁሉ እንጂ። ከዚህ ከቅዱስ ጳውሎስ ስብከት አስቀድሞ

www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆኖ ነበር። "በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ። . . . ሁሉም ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።" ሐዋ 8:1

እግዚአብሔር ግን ይህን የተበተነ ጉባኤ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ምክንያት ይሆን ዘንድ ተጠቀመበት። ለዚህ ማስረገጫ የሚሆነንን መለኮታዊና ሕያው ቃል እናስተውል! "የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።" ሐዋ 8:4 ስለሆነም ለክፋት የተደረገውን እግዚአብሔር ለበጎ አደረገው። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱም ብፁዓን ናቸው አለ።

- ነቢዩ ኤርምያስ

እግዚአብሔር "በሆድ ሳልሰራህ አውቄሃለሁ። ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።" ኤር 1:5 በማለት የተናገረለት ታላቁ ነቢይ ኤርምያስ ስለ ጽድቅ ሲል ተሰዷል - መከራንም ተቀብሏል።

በእርሱ ዘመን የነበሩት ሕዝብ አእምሮአቸው ከማስተዋል የዘገየ ስለነበር የኤርምያስን ተልዕኮ ሊቀበሉት አልቻሉም። ስለዚህም ክፉኛ ተሰቃየ። እግዚአብሔርንም እንዲህ እስከማለት ደረሰ። "አቤቱ ከአንተ ጋር በተሟገትኩ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ ፤ ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለ ፍርድ ልናገር። የኃጢአተኞች መንገድ ስለ ምን ይቃናል? በደልንስ ስለሚያደርጉ ሁሉ ስለ ምን ደህንነት ይሆናል?" ኤር 12:1

ኤርምያስ የትንቢቱን ቃላት በተናገረ ቁጥር ከሕዝቡ ከፍተኛ ሙግት ይገጥመው ነበር። ይረግሙትና የነቢይነት ሥራውን ሁሉ ክፉኛ ይቃወሙበት ስለነበር እንዲህ አለ። "እናቴ ሆይ! ወዮልኝ! ለምድር ሁሉ ለክርክርና የጥል ሰው የሆንሁትን ወለድሽኝ . . . ነገር ግን ሁሉ ይረግመኛል።" ኤር 15:10 በዚህም ኤርምያስ ፍትሕ ማጣቱን ለጌታው አቤት አለ። በተመሳሳይ መልኩ አቤቱታውን ሲያቀርብ "ሊይዙኝ ጉድጓድ ቆፍረዋልና ለእግሮቼም ወጥመድ ሸሽገዋልና . . . አንተ ግን አቤቱ ይገድሉኝ ዘንድ በላዬ የመከሩትን ምክር ሁሉ ታውቃለህ።" ኤር 18:22-23። በተጨማሪም "ቀኑን ሁሉ መሳለቂያ ሆኛለሁ ፤ ሁሉም ያላግጡብኛል . . . የእግዚአብሔር ቃል ቀኑን ሁሉ ስድብና ዋዛ ሆኖብኛልና" አለ። ኤር 20:7-8።

በመጨረሻም ኤርምያስ ወደ ጉድጓድ ተወርውሮ በጭቃ ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ። ደበደቡት በወኅኒም ጣሉት። ኤር 37:15-21። ይህም የሆነው በንጉሡ በሴዴቅያስ ትዕዛዝ አማካይነት ነው። ኤርምያስ ትንቢቱን በተመለከተ ታማኝ ስለነበር ንጉሡም ሆነ የሕዝቡን አለቆች ይሸነግል ዘንድ አልወደደም። ስለሆነም በግዞት ቤቱ አደባባይ ወደነበረው ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ መልክያ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። "ኤርምያስንም በገመድ አወረዱት" ይላል። በጉድጓዱም ውስጥ ጭቃ እንጂ ውኃ አልነበረበትም። ኤርምያስም ወደ ጭቃው



ውስጥ ገባ። ኤር 38:6 እስኪያወጡትም ድረስ በዚያ ጉድጓድ ውስጥ ቆየ። ከዚያ ከወጣ በኋላም በግዞት ቤት አደባባይ ተቀመጠ።

- ነቢዩ ሚክያስ

ነቢዩ ሚክያስም ንጉሡን ማቆላመጥና መሸንገልን ስላልወደደ እንደ ኤርምያስ ተመሳሳይ ችግር ደርሶበት ነበር።

ከሸንጋላው ይልቅ ሚክያስ ንጉሡን "ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር የሚነግረኝን እርሱን እናገራለሁ።" ነበር ያለው። 1ኛ ነገ 22:14። ከዚህ አስከትሎም ትንቢቱን ይናገር ጀመር። ንጉሡም ሚክያስ በተናገረው ትንቢት ደስ ስላልተሰኘ "በደህና እስክመለስ ድረስ ይህን ሰው በግዞት አኑሩት ፤ የመከራ እንጀራ መግቡት ፤ የመከራም ውኃ አጠጡት" አለ። 1ኛ ነገ 22:27።

- ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ

ቅዱስ አትናቴዎስ ሃይማኖቱን ለማስጠበቅ ሲል ባደረገው የጽድቅ ሥራ በተደጋጋሚ ግዞትን ስደትንና መጻተኝነትን ተጋፍጧል። ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ አራት ጊዜ ያህል ተግዟል። ለረዥም ዓመታትም ከአንዱ አገር ወደ ሌላው በመንከራተት ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በስደት ተንከራቷል። አርዮሳውያን አመፅ አስነስተውበታል ፤ የተቃውሞ ጉባኤ አድርገውበታል ፤ በሐሰት ወንጅለውታል ፤ ነገሥታቱንም አነሳስተውበታል። አትናቴዎስ ሆይ ዓለሙ ሁሉ በአንተ ላይ ተነስቶብሃል። የሚል ሐረግ የተነገረውም ለእርሱ ነው።

ይህ ተመሳሳይ ሐረግ ለብዙ በፓትርያርክነት መንበር ላይ ለነበሩ አባቶች ሊጠቀስ ይችላል። ለምሳሌ ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ስለ ሃይማኖት በመቆሙ ከኤጲስ ቆጶስነት መንበሩ ተሰዷልና ይህ ቃል ይስማማዋል። ይህንኑ ጳድቅ ከቄልቄዶን ጉባኤ በኋላ እስከ ዓረቦች ወደ ግብጽ መምጣትና ከ641-644 ዓ.ም ለ190 ዓመታት ያህል የተከተሉት አባቶችም ይህንኑ መከራ ተቀብለዋል። አሚር ኢብን ኤል አሳም ወደ ግብጽ በመጣ ጊዜ በወቅቱ የነበረውን ጳጳስ ብንያምን ከመንበሩ ስላሳደደው ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ ከአንዱ መንደርም ወደ ሌላው መንደር እየተንከራተተ ሰዎች በእምነታቸው እንዲፀኑ አድርጓል። በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የነበረው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስም ስለ ጽድቅ ሥራው በግዞት ኖሯል። ከመንበሩ ተሰዶ ለ28 ዓመታት ያህል በግዞት የኖረውም በግብጽ ነው።

ሐ. ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ

ጌታ ይኼኛውን የብፅዕና ደረጃ "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው።" በማለት ከጀመረው በኋላ ሲደመድመው ፤ "ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ፤ ሐሴትም አድርጉ። ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ

www.ethiopianorthodox.org

አሳድደዋቸዋልና።” ማቴ 5:12 አለ። ስለ ነቢያት ስደትና ግዞት ቀደም ሲል ምሳሌዎችን አቅርበናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መሰደድ ብቻ አይደለም የተናገረው። “ታገሱም” ብሏል። ከሁሉ በላይ ደግሞ “ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ” አለ።

የድል አክሊል ተዘጋጅቶላችኋልና ደስ ይበላችሁ። መንግስተ ሰማያት ለዘላለም ትኖሩባት ዘንድ ትጠብቃችኋለችና ሐሴት አድርጉ። ወደ ሕይወት የምትወስደውን ጠባቧንና እውነተኛይቱን መንገድ መርጣችኋልና ደስ ይበላችሁ። ማቴ 7:14 እንደ ጌታችሁ መስቀሉን ተሸከማችሁኋልና አሁንም ደስ ይበላችሁ። አባቶቻችሁ ነቢያትን እየገረፉና እያሰቃዩ ሲለቋቸው ደስ ይላቸው እንደነበር እናንተም እንደ እነርሱ ደስ ይበላችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል። “እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ።” ሐዋ 5:41። ሐዋርያት በመናቃቸውና በመሰደዳቸው ሐሴት ያደርጉ ነበር ማለት ነው።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## 1. እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።

### ሀ. የሚያስደንቅ ቅደም ተከተል።

በእግዚአብሔር የተሰጡን የብፅዕና ደረጃዎች በአርግጥም በሚያስገርም ቅደም ተከተል የተቀመጡ ናቸው። ከሁሉ አስቀድሞ ጌታ ትህትናንና ራስን ዝቅ ማድረግ ለመንፈሳዊው ሕይወት ሁሉ መሠረት አድርጎ አስቀመጣቸው። “በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው” በማለት።

ሕይወቱን በትህትና ያልመሠረተ ሁሉ የሚያደርጋቸው መልካም ሥራዎች ረብ የሌለው ክብርና ኩራትን የሚያስከትሉ ናቸው። በመንፈስ ድሀ የሆነው ግን በመንፈሳዊው የዕድገት ደረጃ እስከ ላይኛው ቢደርስም ልቦናው የተሰበረ ስለሆነ የትዕቢት መንፈስ በእርሱ ዘንድ ፈጽሞ አይታይም። ስለዚህም ትህትናው የመልካም ሥራዎቹ ሁሉ ጠንካራ አጥር ሆኖ ይኖራል። ይህም በመሆኑ ምግባራቱን በሚገባ ያስጠብቃቸዋል።

አንድ ሰው ደግሞ መልካም ምግባራቱን አስጠብቆ ስለሚደርስበት የልብ ንፅህና ደረጃ በእርሱና በጌታው መካከል በሚፈጠረው ሰላም ርኩሳን መናፍስት እጅጉን ስለሚቀኑ ስለ ጽድቅ ሥራው ያሳድዱት ዘንድ ይነሳሱበታል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው” ካለ በኋላ “የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው” አለ። ከዚህ በኋላ ነው “ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው” ያለው። መንፈሳዊ የሆነ አንድ ሰው መሰደድን ከታገሰ የተሸከመው የክርስቶስ መስቀል መሆኑንና በዚህም በመንግሥተ ሰማያት ዋጋው ታላቅ መሆኑን ስለሚረዳ ሐሴትን ያደርጋል።

ጌታችን እነዚህን ሁሉ የብፅዕና ደረጃዎች ከዘረዘረ በኋላ በስተ መጨረሻ “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ” ፤ “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።” አለ። ማቴ 5:13-16 እዚህ ላይ ሊገልጽልን የሚወደው በግል መልካም ምግባሮቻችን ርካታን አግኝተን እንድንቀመጥ ሳይሆን በሌሎች መካከል የምንፈጽመው ተልዕኮ እንዳለን ነው። የመንፈስ ድህነት የዋህነትና የልብ ንጽህና የራስ ተግባራት ናቸው። ይህ ከሆነ ታዲያ የእኛ ተልዕኮ ምንድርን ነው? የምድር ጨው መሆን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ለ. እናንተ የምድር ጨው ናችሁ።

ጨው ያልገባበት ምግብ አይጣፍጥም። ጨው መልካም ጣዕምን ለምግቡ ይሰጠዋል። ሌላው ቢቀር በአራት ዘመን ቀድሞ ስለሚቀርበው መስዋዕት እግዚአብሔር የተናገረው ቃል አለ። "የምታቀርበውን የእህል ቁርባን ሁሉ በጨው ታጣፍጠዋለህ። የአምላክህንም ቃል ኪዳን ጨው ከእህል ቁርባንህ አያጎድልም ፤ በቁርባንህ ሁሉ ላይ ጨው ታቀርባለህ።" ዘሌ 2:13።

አሁን ግን ጌታ "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። እኔ እናንተን በምድር ሁሉ ላይ ያስቀመጥኳችሁ ዓለሙን በማደስና በመጠገን መልካም ጣዕም እንዲኖረው ታደርጉ ዘንድ ነው" አለ።

ማንም ሰው ቢሆን ስለ ሌሎች ካለበት ኃላፊነት በመሸሽ እንደ ቃየን "የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?" ማለት የለበትም። ዘፍ 4:9። በእርግጥ አንተ የወንድምህ ጠባቂ ነህ። ወንድምህን ከልብና በእውነት የምትወደው ከሆነ ፍቅርህ ከዓለማዊው አደጋም ሆነ ከመንፈሳዊው ስህተት በአንተ ትህትናና መንፈሳዊነት እንዲጠበቅ ግድ ይልሃል። ለዚህም ነው ሐዋርያው "ወንድሞች ሆይ! ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየዋህነት አቅኑት . . . ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም ፤ እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ" በማለት የተናገረው። ገላ 6:1-2 በዚህ ቃል መሠረት እስከምትችለው ድረስ ለሌሎችም ኃላፊነት አለብህ ማለት ነው።

አንተ በአካባቢህ አብረውህ ለሚኖሩት ሰዎች መልካም ሥራን የመሥራት ኃላፊነት አለብህ። አንተ ከክርስቶስ ጋር ኖረህ የክርስቶስን ጣዕም ያጣጣምክ ከሆነ እንደ ነቢዩ ዳዊት "እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም" ማለት ይጠበቅብሃል። መዝ 33:8 ይህን ቃል ለሚያዳምጡህ በሙሉ እና ጣዕሙን በአንተ ሕይወት ውስጥ ለሚያጣጥሙት በሙሉ ትነግራቸዋለህ። አንተ ወደ እግዚአብሔር ከደረስህ በኋላ ሌሎችም ከአንተ ጋር በመሄድ ጣዕሙን ይቀምሱት ዘንድ ተዋቸው። ያቺ ሳምራዊት ሴት ከኃጢአቷ ተመልሳ ብዙም ሳትቆይ ጌታን ገና እንዳወቀችው ይህን መልካም ዜና ወደ መንደርዋ ገብታ ለሰዎች ሁሉ አወጀች። ስለሆነም በወንጌሉ ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጻፈ። ". . . ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት።" ዮሐ 4:39

ይህች ሴት ዝም ብትል ማንም አይወቅሳትም ነበር። ነገር ግን ዝም ልትል አልቻለችም። እንደዚሁም ጌታን ያወቀው ሁሉ ዝም ይል ዘንድ አይችልም። የካህናት አለቆቹ ሽማግሌዎቹ የተለያየ ዘዴ በመጠቀም የጌታ ሐዋርያት ዝም እንዲሉ ያልሞከሩት ሙከራ አልነበረም። ነገር ግን ዝም ያሰኛቸው ዘንድ አልቻሉም። እነርሱም "እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም" አሉአቸው። ሐዋ 4:20



እስቲ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ትጠይቅ ዘንድ ለራስህ አቅርባቸው። "አንተ የምድር ጨው ነህን? የዓለም ብርሃንስ? ስለ ሌሎችስ ምን አድርገሃል?"

እንደ ክርስቶስ ቋሚ መመሪያዎች የሚጊዙና በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳን በዓለም መካከል ተልዕኮ ሊኖራቸው ይገባል። እነዚህ የጌታ መመሪያዎች ወደ ዓለሙ ዘልቀው መግባት ያለባቸው በእነዚህ ቅዱሳን ነው።እንዲህ ያለው ተልዕኮ በቤተ ክርስቲያንና በግለሰብ ደረጃ እንዴት ሊከናወን ይችላል?

## ሐ. ምሳሌ የመሆን ተልዕኮ

በሰዎች መካከል ያለው አኗኗራችን ለእነርሱ ምሳሌና አርአያ መሆን አለበት። እኛ ምሳሌና አርአያ ከሆንናቸው በእምነት የመኖርንና የንጽህናን ተግባራዊ መንገድ ያገኙታል። አዎ! ክርስቶስ እግዚአብሔርን ለእኛ እንዳሳየን እኛም ለሰዎች እግዚአብሔርን የማሳየት ኃላፊነት አለብን።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን መልበስ ዋነኛው ምክንያት እኛን ከኃጢአታችን ለማንፃት ሲሆን ከሌሎች ምክንያቶች አንዱ ደግሞ ሰው ያጣውን የእግዚአብሔር መልክ ለማሳየት ነው። ስለሆነም እርሱ በመምጣቱ በእግዚአብሔር መልክ መኖርን እንዴት እንድንችል አመለከተን። ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዋርያቱን እግር ካጠበ በኋላ የተናገረውን ቃል እስተውል። "እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በራሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።" ዮሐ 13:14-15። ቅዱስ ጴጥሮስም ይህንኑ በመመርኮዝ እንዲህ አለ። ". . . ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ . . .' 1ኛ ጴጥ 2:21 በተመሳሳይ መልኩ ቅዱስ ጳውሎስም "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ።" 1ኛ ቆሮ 11:1።

በዚህ መሠረት አባቶቻችን ሐዋርያት የዓለም ብርሃን ሆነዋል። ሌሎችም መልካም ምሳሌዎች ሆነዋል። ስለዚህም ሐዋርያው በመንፈስ የወለዳቸው ልጆቹ እርሱን ይመስሉት ዘንድ ከአንድ ጊዜ በላይ አሳስቦአቸዋል። 1ኛ ቆሮ 4:16 ፤ 2ኛ ተሰ 3:9። "እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ።" ፊል 3:17

ማንም ቢሆን የጌታን መንገድ በብርሃን እንጂ በጨለማ ቢመላለስ አያገኘውም። ስለዚህም ነው የዓለም ብርሃን የሆኑት የቅዱሳን ተልዕኮ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እስኪደርሱ ድረስ ያለውን መንገድ ለማሳየት ምሳሌዎች የሆኑት። "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ . ." ማቴ 5:16

www.ethiopianorthodox.org

ሕይወት በራሷ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ናት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተማሪው ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎታል። “በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።” 1ኛ ጢሞ 4:12 እንዲሁ ደግሞ ለሌላኛው ተማሪው ለቲቶ “በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ።” ቲቶ 2:7 ምናልባት ያስተምሩ ዘንድ የተሰጣቸው መልካምና ብቁ ለሆኑ ሰዎች ስለሆነ እያንዳንዱ ሰው ለማስተማር ችሎታውም ሆነ አቅሙ ላይኖረው ይችላል። ምሳሌ መሆን ግን ለሁሉም ተሰጥቷል። ማንም ሰው መልካም ከሆነ ይከተሉታል። መድረክ ላይ ለመስበክ ብቁ ያልሆነው ሰው በሕይወቱ መስበክ ይችላል። ስብከት የቃል ትምህርት ሲሆን ምሳሌ መሆን ግን ተግባራዊ አርአያነት ነው። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ሲናገር “ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልዕክታችን እናንተ ናችሁ። . . . በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልዕክት እንደሆናችሁ የተገለጠ ነው።” 2ኛ ቆሮ 3:2-3 አለ። ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ አለ “በእኛም በየሥፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ . . . የክርስቶስ መዓዛ ነንና።” 2ኛ ቆሮ 2:14-15

ስለዚህ እኛ አኗኗራችን መልካም ከሆነ የሚያየን ሁሉ ባንናገርም እንኳ በሁለንተናችን ይሰበካል። ሳንሰብክም ባነጋገራችንና በሕይወቷችን ሕይወቱ ትጠቀማለች። ስለዚህ በአንድ በኩል ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ቃል ይልቅ ሕይወታቸው ይበልጡን ሲሰብካቸው በሌላ በኩል ደግሞ ሰባኪው የሚኖርበት ሕይወት መንፈሳዊ ካልሆነ የሚሰብከው ስብከት በሌሎች ዘንድ ፍሬያማ ወይም ጠቃሚ አለመሆኑን እንገነዘባለን። ከዚህ በተጨማሪ ልትሰብካቸው በማትችላቸው ሰዎች ፊት ምሳሌ መሆን ጠቀሜታ አለው። በዕድሜ ከአንተ በታች የሆኑትንና በዕውቀትም ሆነ በመረዳት የሚያንሱህን መምከር መስበክና ማስተማር ትችል ይሆናል። ነገር ግን ከአንተ በሚበልጡህ ሰዎች ዘንድ እንዲህ ማድረግ ያሳፍርህ ይሆናል። እንዲህ ያሉት ሰዎች በሚከተሉት ምሳሌዎች መጠቀም ይችላሉ።

ስብከትን የማይሰሙ ቢሰሙም የማይቀበሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በኩራታቸውና በራሳቸው ማስተዋል ስለሚደገፉ እነርሱን ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመልስ ማንኛውም ዓይነት ቃልም ሆነ ምክር ሊቀበሉ አይወዱም። ስለሆነም እንኳን እንዲታረሙ የሚነግራቸውን ሊቀበሉ ቀርቶ ሊማሩና ሊሰበኩም አይፈልጉም። ስለዚህ ይህን ዓይነቱን ሰው የሚጠቀምበትን ነገር ብትነግረው እንኳ የተሰደበ ያህል በመቁጠር ወዳንተ እየተመለከተ “አንተ እኔን ልትሰብከኝ ነው?” ይልሃል። እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ግን በዝምታ ከሚናገራቸው ምሳሌነትህ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ምሳሌ ስለ መሆን ጠቃሚነት ሐዋርያው ሲናገር እንዲህ ብሏል። “በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።” ሮሜ 17:17 ይህንኑ ዘርዘር አድርጎ ሲጽፍም “በጌታ ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለንና።” 2ኛ ቆሮ 8:21 ብሏል።



በዚህ ረገድ ነው የአማኝ ሕይወት ለሌሎች ብርሃን ሊሆን የሚችለው። ብርሃን መሆንም ሦስት ዐበይት ጠቀሜታዎች አሉት።

1ኛ. ይህ ሰው ተግባራዊ የሆነ መንፈሳዊ ምሳሌን ለሰዎች ስለሚያሳይ ለሌሎች ከፍተኛ ጠቀሜታን ይሰጣል።

2ኛ. በሌላ መልኩ ደግሞ ለማንም የማሰናከያ ድንጋይ አይሆንም።

3ኛ. ይህ መልካም ሕይወቱም ጌታ እንደተናገረው ሰዎች በሰማያት ያለው አባታቸውን እንዲያከብሩ ይመራቸዋል።

ስለዚህ አንተ መልካም ሕይወት ካለህ ሰዎች ሃይማኖታቸውን እንዲወዱ ታደርጋቸዋለህ። በተቃራኒው መጥፎ ሕይወት የሚኖርህ ከሆነ ደግሞ ሰዎች እግዚአብሔርን በአንተ ምክንያት የሚሳደቡ ይሆናሉ። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ያለው “የተጠራችሁበትን መልካሙን ስም የሚሰድቡ እነርሱ አይደሉምን?” ያዕ 2:7

ከዚህ በማስከተል የዓለም ጨውና ብርሃን የሆኑ ሰዎች ስላላቸው ዐቢይ ጠቀሜታ እንመለከታለን።

## መ. ከሞቱም በኋላ ምሳሌ መሆን

ለእምነቱ ታላቅ ፍቅር ያለው ሰው በሕይወት በምድር ሳለ ብቻ አይደለም። ከሞተም በኋላ ሰዎች የእርሱን ፈለግ ይከተላሉ። ስለዚህ ከሞተም በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ መልካም ምሳሌ እንደሆነ ይኖራል።

ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልዕክቱ ሲጽፍ እንዲህ አለ። “ወንድሞች ሆይ! የመከራና የትዕግስት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ . . . ኢዮብ እንደ ታገሰ ሰምታችኋል ፤ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል።” ያዕ 5:10-11 ሐዋርያው ያዕቆብ ይህን ምሳሌነት በተናገረበት ጊዜ ቅን የነበረው ኢዮብ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት አልፎ ነበር። ያን ያህል ረዥም ዘመናት በመካከል ይኑሩ እንጂ እርሱ እስከ ዛሬ ድረስ መልካም የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን ምሳሌ እንደሆነ ቀርቶአል።

መንፈሳዊ ሰው ልክ እንደ ብርሃን ያበራል። ሕይወቱ በሚቀጥሉቱ ትውልዶች ሁሉ ላይ የተዘረጋ ነው። ከሞተ በኋላም ገድሉ ለሌሎች እንዳበራ ይኖራል። በእኛ ዘንድ ያሉ መነኮሳት አባቶቻችን ምን ያህል የዓለም ብርሃንና የምድር ጨው እንደሆኑ አስተውሉ! ብዙዎች ከአንደበታቸው የሚወጣውን ቃል ሰምተው ለመጠቀም ብዛት ያላቸው አገሮችን አቋርጠው ይመጣሉ። ከሞቱም በኋላ ቅዱስ የሆነው ገድላቸው እስከ አሁን ድረስ በዓለም ባሉ ሕዝቦች ላይ ጥበብን ፤ መንፈሳዊ መረዳትንና ማገናዘብን እንዳበራ አለ። ይደንቀኛል! እውን የአባ እንጦንስ ሕይወት አልፋለችን? በእርግጥ አላለፈችም። እርሱ እስከ አሁን ድረስ አለ። እርሱ ሰዎችን ዛሬም ቢሆን በገድሉ እየተናገራቸው እየሰበካቸውና

www.ethiopianorthodox.org

እያስረዳቸው ነው። ልክ ለጻድቁ ለአቤል እንደተባለለት ማለት ነው። "ሞቶም ሳለ በመስዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።' ዕብ 11:4

ምሳሌ ስለ መሆን ካነሳን አይቀር በጎም ይሁን መጥፎ የጋንዲን የሕይወት ታሪክ እንመለከታለን።

ታላቁ የሕንድ መሪ የነበረው ጋንዲ በክርስትና እምነት ልቡ በጣም የተነካ ሰው ነበር። በአንድ ወቅት ፈረንሳይን በጎበኘበት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ በሚያሳየው የስነ ስቅለት ስዕል ፊት ለፊት ቆሞ እንዳለቀሰ ይነገርለታል። አዘውትሮም "ክርስትናን እወደዋለሁ ግን..." በማለት ሲናገር ይደመጥ ነበር። ያም ሆኖ በወቅቱ የነበሩት ክርስቲያኖችም ሆኑ ጭካኔያቸው ከነዚህኞዎቹ የማይተናነሰው ቅኝ በተገዛችው በሕንድ ውስጥ የሚኖሩት ክርስቲያኖች ሥራ ግፍ የተሞላበት እንጂ መልካም አልነበረም። ስለዚህም ክርስትና አስከፊ ገጽታ እንዳለው አድርገው ነበር የሚያሳዩት።

ነገር ግን በዚያን ወቅት በደቡብ አፍሪካና በሕንድ የነበሩት ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ሕይወቱ ቢኖራቸው ኖሮ ጋንዲ በክርስትናው ልቦናው የበለጠ ስለሚነካ እርሱ ብቻ ሳይሆን በሥሩ የሚተዳደሩትን አራት መቶ ሚሊዮን ሕንዳውያንን በዚህ እምነት ውስጥ በማስገባት እንዲከተሉት ያደርግ ነበር።

በተቃራኒው የብራህማኑ ጋንዲ በጊዜው ህያውና የተዋጣለት መንፈሳዊ ሰው ነበር። እርሱ ያን ጊዜ ከሁሉም ክርስቲያኖች በላይ ነበር። ከምግብ ቢታቀብ ደግሞ የእንግሊዝን ፓርላማ ያናውጠው ነበር። መከራን በመቻሉና በሕማሙ በሰዎች ዘንድ በተለይም ክርስቲያኑን ሕዝብ እጅግ አድርጎ አስደንቋል። ስደትን የተጋፈጠው ያለ አንዳች ትግልና በቀል ነው። በስም ክርስቲያኖች በምግባራቸው ግን ክርስትናን ያጎድፉ የነበሩትን ጨቋኝና ግፈኛ መሪዎች እያወገዘ ነው የሞተው።

መልካም ምሳሌዎች ከሚሆኑት መካከል አንዱ አባ እንጦንስ ነው። ስለዚህ ሰው ቅዱስ አትናቴዎስ ሲናገር "የተረበሹት የተጨነቁትና ነፍሳቸው የመረራቸው የአባ እንጦንስን ፊት ሲመለከቱ ልባቸው ሰላምን ይሞላል" ብሏል። እስከዚህ ድረስ የሚስቡ ስለሆኑ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ፤ እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" ያለው።

እኔን በዚህ መልኩ ከሚያስደንቁኝ ሰዎች መካከል አለቃ ሀቢብ ጊርጊስ ነው። አለቃችን ሊቀ ዲያቆናት ሀቢብ ጊርጊስ የትውልዱ አስተማሪ ብቻ ሳይሆን ታዋቂም ሰው ነበር። ይሄን ታላቅ ሰው ልጎበኘው በሄድኩ ቁጥር የሚናገረኝን እጅግ ጠቃሚ ቃላት በማስታወሻ ደብተሬ ላይ እሰፍር ነበር። ትህትናውንና ቅን ልቦናውን ስመለከተው ደጋግሜ "አንድ ሰው እንዲህ ያለ ትህትናን መላበስ የሚችል ከሆነ በበግ የተመሰለው ጌታችንማ እንዴት ይልቅ?" በማለት ራሴን እጠይቅ ነበር። ስለሆነም በዚህ ሰው ባህርይ ምክንያትነት እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ስለዚህም ማንኛውም መንፈሳዊ ትርጓሜ ልንረዳው ቢያዳግተንም እንደነዚህ ባሉት ሰዎች አማካይነት እናየዋለን።



ለምሳሌ ትህትና የሚለውን ቃል ትርጉም ልንረዳው ቢያዳግተን ትሁት ከሆነ ሰው በሚገባ በተግባር እንረዳዋለን። ስለዚህም መንፈሳውያን የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች የመልካም ምግባር ሁሉ መገለጫዎች ስለሚሆኑ ሳይናገሩም ሆነ ሳይሰብኩ ሰዎች ከሕይወታቸው ይማራሉ።

ሠ. ጨውና ብርሃን ለምን ተለይተው ተመረጡላ

እናንተ ዓለም የሚጣፍጥበት ጨው ናችሁ። ጨው ዓለምን በመለወጥ ጣፋጭና ለሰውነት የሚስማማ ያደርጋታል። እናንተ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ ላይ የምታበሩ ብርሃን ናችሁ። እዚህ ላይ ጌታ የአድማጮቹን ስሜት ከፍ በማድረግ እነርሱ ዓለምን የሚያጣፍጡና የሚባርኩ እንደሆኑ ተናግሮአቸዋል። ሌላስ ምን አላቸው? እነርሱ ለሰው ሁሉ ብርሃንን የምትሰጥ በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ መሆናቸውንም ገልጾላቸዋል።

የተራራው ስብከት የሚጀምረው በብፅዕና ደረጃዎች ነው። በመቀጠልም ጌታ የሚያበረታቱና ምስጋናን የተሞሉ ቃላቶችን በመናገር የዛለ ክንዳቸውና የደከመ ጉልበታቸው እንዲጠነክር አድርጓል። ዕብ 12:12 እንዲህ ሲላቸው የወደደ ነው የሚመስለው "የማትታወቁ አይደላችሁም። መላው ዓለም መኖራችሁን ይመሰክራል ፤ ያውቃልም።"

አንድ ሰው ማንኛውም ምግብ ቀርቦለት ሲመገብ በውስጡ ያለው የጨው መጠን ይብዛ ወይም ይነስ ወይም ደግሞ መካከለኛ ይሁን ይታወቀዋል። እውነተኛ ክርስቲያንም እንደዚሁ ነው። በማንኛውም ኅብረተሰብ ወይም ጉባኤ መካከል ቢገኝ በዙሪያው ያሉት ሰዎች መኖሩ ይሰማቸዋል ፤ ይወቅሳቸውማል። አንዳንዶች ልበ ንጹህ የሆነ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ መካከል ሳይታወቅና በሌሎችም ተቀባይነትን አጥቶ መኖር አለበት ብለው እንደሚናገሩት ግን አይደለም። ራስን ክዶ ትህትናን በመላበስ መኖርና የሌሎችን ትኩረት ስቦ መኖር ሁለቱ የተለያዩ ናቸውና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ነበር። አንዳንዶች የእርሱ ደቀ መዛሙርት መሆንን ሲመኙ ሌሎች ደግሞ ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። እርሱ ግን መኖሩን ስላረጋገጠላቸው ሁሉም መስክረውለታል። መጥምቁ ዮሐንስም ከምድረ በዳ ወጥቶ ወደ ሕዝቡ ሲመጣ በመካከላቸው ህልውናውን አረጋግጦላቸዋል። ራሱን ቢክድም ሰዎች ለእርሱ ትኩረት ሰጥተውት ነበር። ስለዚህ ሰው ራሱን ቢክድም እንኳ በሚኖርበት ኅበረተሰብ ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ብቃት ሊክድ አይቻለውም ማለት ነው።

ረ.. የምስጋና ቃላት

አመድና ትቢያ የሆነውን ሰው ያመሰግነው ዘንድ ያነሳሳው የእግዚአብሔር ፍቅሩ ድንቅ ነው። ምንም እንኳ የሰው ልጆችን ድካም በሚገባ

www.ethiopianorthodox.org

ቢያውቀውም ድፍረት የሌላቸውን ያጽናናቸዋል። 1ኛ ተሰ 5:14 ምንም እንኳ የሰው ልጆች ጽድቃቸው በፊቱ እንደ መርገም ጨርቅ ቢሆንም የሰው ልጆችን ያወድሳቸዋል። ሕዝ 36:17 ለእኛም እንደዚህ ብሎናል። "እንዲሁ ደግሞ እናንተ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ፤ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ።"ሉቃ 17:10 ከሁሉም በላይ ደግሞ እኛን "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" አለን።

ጌታ ይህን ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር ድካማቸውንና በዕለተ ዓርብ እጁ ሲያዝ ሁሉም ብቻውን ትተውት እንደሚሸሹ እያወቀ ነው። እርሱ ማን እንደሚከደው ፤ ማን እንደሚፈራ ፤ ማን ትንሣኤውን እንደማያምንና ማንስ በጥርጥር እንደሚሞላ ያውቅ ነበር። ይህን ሁሉ ይወቅ እንጂ "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ብሎ ተናገረ።

ጌታ ይህን ያለው በዓለም ውስጥ እንደ ሞኝ ተቆጥሮ ሳለ ጥበበኛ ነኝ የሚለውን ሰው ለሚያሳፍረው ነው። በተጨማሪም ደካማ ሳለ ብርቱውን ለሚረታው ጌታ ይህን አለ። በእርሱ አገላለፅ "የዓለምን ሞኝ ነገር . . . የዓለምን ደካማ ነገር" 1ኛ ቆሮ 1:27 በማለት ለተናገረላቸው ይህንን አለ። እግዚአብሔር ለልጆቹ ካለው ፍቅር ከሚያጽናናቸው ማጽናናትና ከሚሰጣቸው ምስጋና አኳያ ሲመረመር ዕፁብ ድንቅ አምላክ ነው።

እግዚአብሔር በባሪያው በኢዮብ ተመክቷል። ለሰይጣን እንዲህ ነበር ያለው "በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም።" ኢዮ 1:8 ይህንኑ ቃል እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ለሰይጣን ከደገመለት በኋላ በዚያው ላይ በማከል "እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል" አለው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የኢዮብን ድካም ቢያውቅም ይህንን አለ። ኢዮ 40:8 እግዚአብሔር የሰዎችን ሞራል ያነሳሳል ሰዎች ግን አይነሳሱም።

በሥራው ሁሉ ፍጹም የሆነውና ለፍጽምናው ወሰን የሌለው አምላክ የሕዝቡን ድካም ታግሶአል። "የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም ፤ የሚጤሰንም ክር አያጠፋም።" ኢሳ 42:3። የሰው ልጅ ግን ምንም እንኳ ለመንሸራተት ብሎም ለመውደቅ የተጋለጠ ቢሆንም አንዱ የሌላውን ድካም ሲሸከም አይታይም። በአንድ ወቅት በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሳለን አንድ እጅግ የሰፋና የጠለቀ እውቀት ያለው መምህራችን እንዴት አድርጎ የተማሪዎቹን የእውቀት ደረጃ ይንቅ እንደነበር ትዝ ይለኛል። የተማሪዎቹን ወረቀት ሊያርም ከወሰደ በኋላ "በጣም ደካማ" በማለት የመጨረሻውን የትምህርት ቤቱን የዝቅተኛነት ማዕረግ ሰያሚ መጻፍ እንኳ ስለማያረካው በአንዳንድ ወረቀቶች ላይ "ዋጋ ቢስ" እያለ ይጽፍ ነበር።



## ሰ. የጨው ጠቀሜታ

ጨው በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ስለሆነም እንዲሁ የምትተወው አይደለም። በእርግጥም ከስኳር ይልቅ ጨው እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነገር ነው። ሰው ስኳርን መተው ይቀለዋል እንጂ ከጨው መከልከል እጅግ ያዳግተዋል። በእርግጥ ስታርችነት ያላቸው ነገሮች በሰውነታችን ውስጥ ወደ ስኳርነት መለወጥ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን ስታርችነት ካላቸው ነገሮችም መለየት ይቻላል።

ጨው ግን ሊተውት የማይቻል በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ለምሳሌ ያህል በቤት ውስጥ ያለ አንዳንድ የቤት ቁሳቁስ የራስ ምስሎችና ብርቅ ጌጣጌጦች ባይኖሩም መኖር ትችላለህ። ያለ ውኃ ግን በፍፁም መኖር አትችልም ፤ ውኃ የጨውን ያህል አስፈላጊ ነውና። ሰው ሥጋና ውድ የሆኑ ፍራፍሬዎችን መብላት ሊተው ይችላል። ጨውን መተው ግን ያዳግተዋል። አንዳንድ ሰዎችም ከሰዎች ጋር ያላቸውን ጥብቅ ወዳጅነትና መቀራረብ ለመግለጽ ሲወዱ "እኛ ዳቦና ጨው አብረን ተቋድሰናል" ይላሉ። ለእግዚአብሔር የሚቀርበውም የእህል ቁርባን በጨው ይጣፍጥ ነበር። ዘሌ 2:13

ምንም እንኳ ታዲያ ጨው ይህን ያህል አስፈላጊ ቢሆንም ዋጋው በጣም ርካሽ ነው። ርካሽና በየትኛውም ስፍራ ስላለ ሁሉም ሰው በቀላሉ ያገኘዋል። ጠቀሜታው የሚመዘነው ከዋጋው አኳያ ሳይሆን ከአስፈላጊነቱ አንፃር ነው። ይህም በዓለም ስላሉ የእግዚአብሔር ልጆች ሊጠቀስ ይችላል። ከእነርሱ አንዳንዶቹ ዓሣ አጥማጆች ሌሎቹ ድንኳን ሰፊዎች ሌሎቹ ደግሞ እረኞች ይሁኑ እንጂ ለዓለም ታላቅ ጥቅምን አበርክተዋል። ይህንንም ወንጌል ይመሰክርላቸዋል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆችም አስፈላጊና ሊገኙ የሚችሉ ናቸው። ዓለሙ ሊተዋቸው የማይችል ጨው ናቸው። ዓለሙ ያለ እነርሱ የማይጣፍጥና ዋጋ የሌለው ነው። ዓለሙ ደግሞ ሊጣፍጥ የሚችለው በቀሳውስቱ በሰባክያኑና በሃይማኖት ሰዎች ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ባመኑት ሁሉ ነው። ጌታ ይህንን ቃል በተራራው ስብከቱ የተናገረው ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ነውና። ቁም ነገሩ ያለንበት የማዕረግ ደረጃና አቅማችን ሳይሆን ብቃታችንና ፍሬያማነታችን ነው።

የነቢዩና የጻድቁ የኤልሳዕ አቋም በጣም የሚያስደንቅ ስለነበረ ጥቂት ብላቴናዎች ከከተማ ወጥተው እያፌዙበት "አንተ መላጣ! አንተ መላጣ!" አሉት። እንዲህ ይበሉት እንጂ እርሱ ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያደረገና ሙት ያስነሳ ነቢይ ነበር። በእርሱ ዘመን ለነበረው ትውልድ ጨውም ብርሃንም ነበር። ነገሥታቱም እንደ አባትና መሪ ይመለከቱት ነበር። 2ኛ ነገ 13:14 የጻድቁ ሮዊስ አቋምም ብዙዎች እንዲያላግጡበት ምክንያት ሆኖበት ነበር። እርሱ ትውልዱን የሚባርክ አባት ሆኖ ሳለ እንደ እብድ የሚቆጥሩት ሰዎች ነበሩ። ብዙ ተአምራትን አድርጊል። ያበራው ብርሃን አሁን ድረስ እያበራ ነው።

ምናልባት ጌታ "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" ያለው ለማን ነው? ብለን እንጠይቅ ይሆናል። መልሱ በተራራው ስብከቱ ላመሰገናቸው ሁሉ

www.ethiopianorthodox.org

የተናገረው ነው የሚል ይሆናል። በመንፈስ ድሀ ለሆኑት ፣ ለየዋሆቹ ፣ ለሚምሩት ፣ ለልበ ንጹሖቹና ለሚያስተራርቁት ይህንን አለ። ይህን ያለው ለአስተማሪዎችና ለሰባክያን ብቻ አይደለም። ምክንያቱም ሃይማኖት ባዶ ቃላት አይደለም ፣ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ እንጂ። ዮሐ. 6:63 በዚህ መልኩ ነው ዓለሙ የሚጣፍጠው። ሰባክያኑ የምድር ጨው መሆንን ከወደዱ ከብፅዕና ደረጃዎች ጋር ህብረት ይኑራቸው።

ቀሳውስቱና ሰባክያኑ እጅግ ብዙ ይሁኑ እንጂ ሕይወታቸው የአንዱን ሐዋርያ የቅዱስ ጳውሎስን ያህል ሌሎችን አይሰብከም። ይህም የሆነበት ምክንያት ምናልባት እግዚአብሔር በቅዱስ ጳውሎስ ላይ አድሮ የተናገረውን ያህል በእነርሱ አድሮ ባለመናገሩ አሊያም ደግሞ በቃላት ብቻ የተሞሉ ብርሃን የማይፈነጥቁ ሰባክያን ስለሆኑ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ግን እኛ ቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መውቀስ አንችልም። ይልቁንም ሁላችንም ኃላፊነት ስላለብን ልንል የሚገባው ልክ እንደ ኢያሱ መሆን አለበት። "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።" ኢያ 24:15

ማንኛውም የቤተሰብ ኃላፊ ቤተሰቡን ለማስተማር መንፈሳዊ ፍቅር በውስጡ ካለ የሃይማኖት ሰባኪም ሆነ አስተማሪ እንዲሁም መመሪያ የሚሰጥ ባላስፈለገን ነበር። ወላጆች ለወንዶችና ለሴቶች ልጆቻቸው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መመሪያ ብርሃናት መሆን ቢችሉ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ትሞላ ነበር። ይህን የምለውም ልጆቻቸው ይጠመቁላቸው ዘንድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ለሚመጡ ወላጆች ነው።

የሙሴ እናት ለልጇ የነበራትን ስሜት እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን። የሙሴ እናት የሆነችው ቅድስት ዮካብድ ልጇ ሙሴን ገና የሦስት ወር ህፃን ሳለ ከፈርዖን ሴት ልጅ ወሰደችው። ከዚህ በኋላ ያጠባችው የጡቷን ወተት ብቻ ሳይሆን እምነትንና እውነተኛውን ነገረ ሃይማኖት ጭምር እንጂ። ከዚህ በኋላ ሙሴ ምን ያህል ዓመታት ከእናቱ ጋር ኖረ? ሦስት? አራት? አምስት? ምንም እንኳ ከእናቱ ጋር የኖረበት ጊዜ አጭር ቢሆንም ቅሉ በቤተ መንግሥት ውስጥ በንግሥታቱና በፈርዖን የአምልኮ ጣዖታት ተከቦ በኖረበት ጊዜና ከዚያም በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ባሳለፈው የሕይወት ዘመኑ አብሮት ሊቆይ የቻለ እምነትን ነበር የያዘው። በዚህም ሙሴ በእምነት የቆየ ሰው ብቻ ሳይሆን በጊዜው የነበሩት የአማኞች ሁሉ ቁንጮና ለተከተሉትም ትውልድ እምነትን ያስረከበ ሰው ነው። ቅድስት ዮካብድም ብርሃንና ጨው መሆን ስለቻለች ብፅዕት ናት።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የማስታውሰው አንድ ያጋጠመኝ ነገር አለ። ከዕለታት በአንድ ቀን አንዲት ዳክዬ ጫጩቶችዋ እስኪፈለፈሉ ድረስ እንቁላሎቹን እንደ ታቀፈች ተቀምጣ አየሁ።ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሃያ በሚደርሱ ጫጩቶችዋ ታጅባ በታላቅ ደስታ ወዲያና ወዲህ ስትል ተመለከትኳት። እይታው የሚያስገርም ነበር። ሁኔታው ሁሉ ከነቢዩ ጋር "እነሆ እኔና እግዚአብሔር የሰጠን ልጆች" እያሉ የማመስገን ያህል ይመስላል። ኢሳ 8:18 እስቲ ልጠይቅህ! "አንተ በዚያች በአስፈሪዋ የመጨረሻ የፍርድ ቀን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት



ስትቆም በእግዚአብሔር ፊት የምታቀርባቸው ልጆችህ እነማን ይሆኑ?" "ብዙ ልጆች መዳንን ከክብር ጋር ያገናኙ ዘንድ . . ." ዕብ 2:10-13 በዚያች ቀን ፍሬ እንደሌለው ዛፍ ብቻህን ልትቆም ይሆን? የተባረከው ወንድሜ ሆይ! ይህን ከአንተ ያርቅልህ!

ዘወትር ያ አምስት መክሊት ወስዶ ያተረፈውን ሰው ምሳሌ አስታውስ። ወደ ጌታው መጥቶ እንዲህ ነበር ያለው። "ጌታ ሆይ! አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ፣ እነሆ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት።" ጌታውም ይህን ደስ የሚያሰኝ ቃል በሰማ ጊዜ "አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል ፣ በብዙ እሾምሃለሁ ፣ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" አለው። ሁለት መክሊት ወስዶ የነበረውም እንዲሁ አደረገ። ማቴ 25:20-23

እንደነዚህ ያሉቱ የዓለምን ገጽታ ወደ መንፈሳዊነት የሚለውጡ ጥቂት ሰዎች ሁኔታ ይደንቀኛል! በምድር ሁሉ ላይ የተሰማው የ12ቱ ሐዋርያትና የቅዱስ ጳውሎስ ድምፅ ከፍተኛ ስሜትን ነው የሚያሳድርብኝ። በዚያን ዘመን ለነበረው ትውልድ ሁሉ የእምነትን መልዕክት ያስተላለፉት ጥቂት የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ያስገርሙኛል። ቁጥራቸው ጥቂት ነው። ነገር ግን የዓለም ብርሃን የምድርም ጨው ነበሩ። በእነርሱም አማካይነት ትውልዱ ከሌሎቹ ሁሉ የተከበረ ሆነ። ስለሆነም "ይህ የኤልያስ ትውልድ ነው ፣ ያ ደግሞ የኤልሳዕ ትውልድ ነው" እንላለን። ከዚህም የተነሳ በእያንዳንዱ ትውልድ እግዚአብሔር አምላክ መመሪያውን ያስተላለፈበት የራሱ የሆነ ብርሃን ነበረው ማለት ነው። ይህንንም መሠረት በማድረግ "ይህ የኤርምያስ ጊዜ ነው ፣ እነዚያ ደግሞ የሳሙኤልና የዳዊት ጊዜያት ናቸው" እንላለን። ስለ ነቢያትና ስለ ሐዋርያት ዘመን ስንናገርም ታሪክ ነው የምንናገረው።

በተመሳሳይ መልኩ በቅዱስ አትናቴዎስ ዘመን ፣ በቅዱስ ቄርሎስ ዘመን፣ በታላቁ በቅዱስ እንጦንስ ጊዜ ፣ የፋዩም ጳጳስ በነበሩት በአባ አብርሃም ጊዜ እንላለን። እነዚህ ሁሉ ለትውልዳቸውና ለሚተካው ትውልድ ሁሉ ብርሃናት ነበሩ። በእርግጥም ፍሬያማ ነበሩ። እመኑኝና ከስንዴ ዘር በጣም ጥሩ ትምህርትን እንማራለን። መሬት ውስጥ እንዘራታለን - ከበቀለችና ካደገች በኋላም ብዙ ፍሬ ትሰጠናለች። "ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች።" ማር 4:28 እነዚህ ሁሉ ፍሬዎች ግን የሚገኙት ከአንዲቱ የስንዴ ቅንጣት ነው። ሌሎች የፍራፍሬ ዛፎችም እንዲሁ። እያንዳንዱ የፍራፍሬ ዛፍ በየወቅቱ ምን ያህል ፍሬ ይሆን የሚያፈራው?

አንተስ ምን ዓይነት ፍሬ ነው የምትሰጠው? መልካም ፍሬን? ብርሃን ከሆንህ ፍሬያማ ትሆናለህ። ንቃና በመንፈሳዊው ሥራህ ርካታን አግኝ። መጽሐፍ ቅዱስ "እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ፣ ወደ እሳትም ይጣላል" እንደሚል አታውቅምን? ማቴ 3:10።

www.ethiopianorthodox.org

ያለ አንዳች ማቋረጥ በራሷ ዛቢያ ከምትሽከረከረው ምድር ትምህርትን ተማር። ከብዙ ሺህ ዓመታት አስቀድሞ ከፍጥረታት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በራሷ ዙሪያ ትሽከረከራለች። እያንዳንዱም ሽክርክሪት አንድ ቀንና አንድ ሌሊት ይሰጣል። ያለ አንዳች ማቋረጥ ብዙ ሚሊዮን ሽክርክሪቶች! ይደንቀኛል። ነገር ግን በአንድ ወቅት ምድር መሽከርከሩ ደክሟት ሥራ ብትፈታና በዛቢያዋ ላይ ደገፍ ብላ እረፍት ብታደርግ ዓለሙ ሁሉ ግራ በመጋባት አይቸገር ይሆን? ነገር ግን ምድር ከእግዚአብሔር በተሰጣት ትዕዛዝ መሠረት እየዞረች በማያቋርጥ ሽክርክሪት ቀንና ሌሊትን የመስጠት ወይም የማፈራረቅ ሥራን እያከናወነች ነው።

እንዲሁ ጨውን ከሚፈለገው መጠን ሳይበዛ ወይም ሳያንስ በጥበብ ነው መጠቀም የሚቻለው። በጣም ከበዛ ምግቡን ያበላሸዋል። ካነሰ ደግሞ ምግቡ አይጣፍጥም። በመልካም መኖርም እንዳዚሁ ነው። ለሚያስተምረው ሕዝብ ከአዕምሮአቸው በላይ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርትን በማስተማር ከንቱ ንግግር ሆኖባቸው እንዳያደክማቸው አሊያም ከአቅማቸው በታች የሆነውንና አዕምሮአቸው ሊቀበለው የማይችለውን በመናገር እንዳያሰለቻቸው መሆን አለበት።

ዳዊት ወደ ጦር አውድማው ሲገባ እንደ አንዲት የጨው ቅንጣት ሆኖ ነበር የገባው። በአንፃሩ ጎልያድን ስንመለከት የእስራኤልን ክብርና ማዕረግ በማዋረድ ነበር የተንጎራደደው። ዳዊት በወቅቱ ለሕዝቡ ታላቅ በረከት ነበር። በእርሱ አማካይነት ድል ማድረግና ደስታ ተገኙ። ገና ወደ ፍልሚያው አውድማ ብቅ ሲል የበላይነቱ ታይቷል። ምንም እንኳ አትናቴዎስም በእነዚያ በ318ቱ የሊቃውንት ጉባኤ መካከል ገና ወጣት ዲያቆን ቢሆንም ትውልዱን ሁሉ ያጣፈጠ ጨው መሆን ችሏል። ለሕዝቡ እውነተኛይቱን ትምህርትና እምነት አስተምሯልና። ቅዱስ እስጢፋኖስም እንዲሁ ደቃቅ የጨው ቅንጣት የነበረ ዲያቆን ነው። እርሱ ቄስም ጳጳስም ሐዋርያም አልነበረም። ነገር ግን ከሠራቸው ተአምራትና ሊመልሱለት ካለመቻላቸው የተነሳ ሃይማኖት እንዲስፋፋ አድርጓል። "ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም።" ሐዋ 6:10።

አንተስ? ምን ሠርተሃል? ለሌሎች ብርሃን መሆን ችለሃልን?

## ሸ. ጨውና ብርሃን

ጨው በጣም አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ብርሃንም ያን ያህል አስፈላጊ ነው። "እናንተ ጨው ናችሁ ፤ እናንተ ብርሃን ናችሁ።" የሚሉት ሐረጎች ትርጉም እናንተ ለራሳችሁ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ ጥቅም የቆማችሁ ዓለሙን ሁሉ በጣም የምትጠቅሙ ናችሁ ማለት ነው። በእናንተ አማካይነት እምነት ለዓለሙ ሁሉ ይዳረሳል ፤ በእናንተም ምክንያትነት ሰዎች መንፈሳዊውን መንገድ ያውቃሉ ማለት ነው። በእናንተ ርዳታ የወደቁት ሁሉ ተነስተው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ - ብርሃን ለሁሉም ይበራልና።

ስለሆነም ምንም ዓይነት ዘርና ቀለም ቢኖራቸውም ራስህን በሁሉም የሰው ልጆች ጉዳይ ውስጥ ለማስገባት ቸል አትበል። ወደ ሳምራውያኑም ሆነ



ወደ አሕዛቡ እንዲሁም ወደ ይሁዳውያኑ ሂድ። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።" ማር 16:15 እንደ ፀሐይቱ ለሰዎች ሁሉ አብራ። እንክብካቤህና ርዳታህ ከአንዱ ይልቅ ለሌላው የሚያደላ ሆኖ ልዩነትን አይፍጠር። "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።" በሚሉት ሐረጎች ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ዓለማት ማለትም ምድር እና ዓለም በሁሉም ሥፍራ ለማለት የተጠቀሱ ናቸው። በምትኖርበት ቦታ ሁሉ ብርሃንህ ልክ እንደ ፀሐይ ያለ አድልዎ ለሁሉም ማብራት አለበት ማለት ነው። በደረስክበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ስለ አንተ "በእውነት ይህ ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ ነው" ይላሉ። ስለዚህም ሁሉም ከአንተ ይጠቀማሉ። የሄድክበት አካባቢ ሁሉ በመንፈሳዊ ደስታና እንቅስቃሴ የሚበረታ ይሆናል። በአንተም ብርሃንነት የእግዚአብሔር መንግሥት በሁሉም አካባቢ ትስፋፋለች። የፀሐይ ጨረር የንጉሡን ቤተ መንግስትም ሆነ የባሪያውን መኖሪያ ቤት እንዲሁም የደሀ አደጉን ጎጆ ዘልቆ ይገባልና።

ሻማን ተመልከት! ብርሃኑን ለሚኒስትሩም ሆነ ለዘበኛው እኩል ነው የሚፈነጥቀው። ብርሃኑ በቤተ መንግስት ውስጥ ደምቆ በደሳሳዋ ጎጆ ውስጥ አይደበዝዝም። ብርሃኑ ለሁሉም እኩል ስለሆነ ሁሉም ይጠቀሙበታል። ስለዚህም ሁላችሁም ከዚህ ሻማ ትምህርት ወስዳችሁ ሰዎችን በምትጠይቁበት ጊዜም ሆነ በአገልግሎትና ራስን አሳልፎ በመስጠት ለሁሉም እኩል አብሩ። ብርሃን ደግሞ ሁሉን አጥርቶ ያሳያል እንጂ በጨለማው አይዋጥም። ብርሃን በመስፍኑም አዳራሽ በደሀውም ጋጣ ያለ አንዳች ችግር ይበራል። ስለዚህ ወደ ኃጢአተኞች በሄድክ ጊዜ በእነርሱ ተሰነካክለህ ሳትወድቅ ወደ ንስሐ ምራቸው። ፀሐይ ብርሃንን የምትፈነጥቀው በጻድቃንም ሆነ በኃጢአተኞች ላይ ስለሆነ ጨረሯንም የምትልከው ለሚጠቅመውም ለማይጠቅመውም በመሆኑ የአንተም ልግስና እንዲሁ ለሁሉም መሆን አለበት።

የአንተ ሥራ መስጠት እንጂ መቀበል አይደለም። ኤልያስ ለመበለቲቱ ቤት፤ ዮሴፍ ለግብፅ ምድር ፤ አብርሃምም ለዓለም ሕዝብ ለበረከት እንደሆኑ አንተም ለበረከት መሆን አለብህ። ብርሃን የሚፈነጥቀው አንተ ፈንጥቅ ስላልከው አይደለም። ፀሐይም ሆነች ጨረቃ አንተ ብርሃንን ስጡኝ እስክትላቸው አይጠብቁም። ሁለቱም ያለ አንተ ጥያቄ ብርሃናቸውን በመፈንጠቅ መንገድህን ይመሩሃል። የእግዚአብሔርም ልጆች እንዲሁ ናቸው። እርሱ ወደ ዓለም የላካቸው ዓለሙ እንዲያበሩ ባይጠይቃቸውና ከብርሃናቸው ርቆ ቢቀመጥም እንኳ ብርሃናቸውን እንዲያበሩና በውስጣቸው ያለውን መልካም አርአያነት እንዲፈነጥቁ ነው።

ዋናው ቁም ነገር አንተ ብርሃን ነህን? ወይስ ጨው ሆነሃል? የሚለው ነው። "ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።" 2ኛ ጢሞ 4:12 መጽሐፍ ቅዱስ "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው የለም ፤ አንድ ስንኳ" ነው የሚለው። ዮሐ 1:18 ነገር ግን አንተ የእግዚአብሔር አምሳል ነህ። ሰዎች በአንተ ውስጥ እርሱን ያዩታል። አንተ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠርክ

www.ethiopianorthodox.org

ከመሆንህም በላይ (ዘፍ 1:27) የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆንክም ሰዎች በአንተ ውስጥ የሚያዩትን እግዚአብሔር ይወዱታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል። "እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንማልዳለን።" 2ኛ ቆሮ 5:20 አምባሳደር ማለት ለአገሩ መንግስት የሚሾም ወይም የሚወክል ማለት ነው። ስለ አገሩ ማንኛውንም አስተያየት ይሰጣል። የእግዚአብሔርም አምባሳደር ስለ ክርስትና ያለውን አሳብ ሁሉ ገልጦ ይናገራል። በመንፈሳዊ ሕይወት የምንመራ ከሆነ ስለ መንፈሳዊነትና ስለ ክርስትና መልካም አርአያነታችንን መግለጥ አለብን ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በጥፋት መንገድ የምንሄድ ከሆነ ሳናውቀው ክርስትናን እናደማለን። ሰዎች ስለ ክርስትና እምነት ሳይማሩ ከእኛ ሕይወት ብቻ ሊቀስሙት ይችላሉ።

ብዙዎች በሃይማኖትና ሃይማኖትን መቀበል በሚለው መካከል ያለውን ልዩነት ለይተው ማወቅ ሲሳናቸው ይስተዋላሉ። የሕንድና የደቡብ አፍሪካ የሃይማኖት አባቶች ካላቸው ምግባር አኳያ ክርስትናን ቢያደሙ የእኛም ሃይማኖት በእኛው አማካይነት የመድማቷ ነገር በጣም ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው። ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች የክርስትና እምነት በማይፈቅደው መንገድ ጋብቻን ቢያፈርሱ ከውጪ የሚመለከቱት ፤ ተመልከቱ ለካስ በክርስትናም በሆነ ባልሆነው ምክንያት መፋታት ይቻላል! ሃይማኖቱ ይህ እንዲደረግ ይፈቅዳል ይላሉ። ክርስትና ግን ይህን አይፈቅድም።

## ቀ. እግዚአብሔር በስሙ ይጠራናል

ጌታ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ማለቱ ድንቅ ነገር ነው። የሰጠን በእርሱ ስም ላይ የተቀደሰውንና ለእርሱ የሆነውን ስም ነውና። እርሱ ስለ ራሱ ሲናገር "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም" ብሏል። ሐዋ 8:12 "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።" ዮሐ 9:5 በማለትም ተናግሯል። "ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው።" ዮሐ 3:19 የሚል ቃልም አለ።

እግዚአብሔር ብርሃን ነው። እኛም ብርሃናት ነን። ይህ እንዲህ ከሆነ በእግዚአብሔር ብርሃንና በእኛ ብርሃን መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው? እርሱ በዮሐ 1:19 ላይ እንደተገለጸው ለሰዎች ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ነው። ከዚህ ሌላ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል እርሱን የሚያክል የለም ስለተባለለት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ (ማቴ 11:11) ደግሞ "ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ብርሃን አልነበረም" ተብሎ ተጽፎአል። ዮሐ 1:8 አዎን- እውነተኛው ብርሃን እግዚአብሔር ነው። በእርሱ ውስጥ ብርሃንን



እናያለን። ወደ እውነተኛው ብርሃን ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ እየተጠጋን በሄድን ቁጥር እያበራንና እየደመቅን እንሄዳለን። ይህ ብርሃንነትም ከፀሐይና ከጨረቃ ብርሃንነት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ፀሐይ አፈጣጠርዋ ራሱ ብርሃን ሲሆን ጨረቃ ደግሞ ፕላኔት ሆና የተፈጠረች ናት። ብርሃንን የምታገኘው ከፀሐይ ነው። ጨረቃ ወደ ፀሐይ በተጠጋች ቁጥር ከፀሐይ የሚፈነጠቅላት ብርሃን የበለጠ ያደምቃታል። ጨረቃ ከፀሐይ በጣም ርቃ ያለች ቢሆን ኖሮ እንደ ጨለመች ትቀር ነበር። ይህንንም ጨረቃ ተወለደች በሚባልባቸው በእያንዳንዱ ወራት ማየት ይቻላል።

ታዲያ ጌታ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ሲል ምን ለማለት ነው? አዎን- "ብርሃናት ለመሆን ከፈለጋችሁ ወደ እኔ ቅረቡ ፤ ከዚህ በኋላ ከእኔ የምታገኙትን ብርሃን በሌሎች ላይ ታበራላችሁ" ማለቱ ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጆች ሆነን ብንመላለስ የብርሃን ልጆች እንሆናለን። ሉቃ 16:8 "እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ህብረት አለን።" 1ኛ ዮሐ 1:7 ስለዚህም ጉዳይ አስተማሪያችን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ። "ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ . . . ስለዚህ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ።" ኤፌ 5:8 ከዚህ በተጨማሪም እንዲህ በማለት ተናግሯል። "ሁላችሁም የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁ።" 1ኛ ተሰ 5:5

ማንም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ሰው በእርሱ ላይ የሚያበራውን ብርሃን ከእግዚአብሔር ስለሚቀበል ሰዎች ሁሉ ብርሃኑን ይመለከታሉ። በመንፈሳዊ ጎኑ የእግዚአብሔር ብርሃን በሕይወቱ ይገለጣል። በሥጋዊ ጎኑ ደግሞ ብርሃኑ በገጹ ላይ ይንፀባረቃል። ለምሳሌ አድርገን የሙሴን ታሪክ ብንመለከት ሙሴ የቃል ኪዳኑን ጽላቶች በእጆቹ ይዞ ከተራራው ላይ በወረደ ጊዜ ፊቱ ያንፀባርቅ ነበር። አሮንና እስራኤላውያን ሊቀርቡት አልደፈሩም። ስለሆነም ከገጹ ላይ የሚንፀባረቀውን ብርሃን ለመሸፈን በፊቱ ላይ መሸፈኛ ጨርቅ አደረገ። ዘጸ 34:30-35

የጌታ መልክ በተለወጠበት በታቦር ተራራ ላይ የተገለጡት ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ ስለነበሩና ብርሃኑ ስላጥለቀለቃቸው በአንፀባራቂው ደመና ሊዋጡ በቅተዋል። ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር ኑሩ። ብርሃንንም ከእርሱ ተቀበሉ። ከብርሃኑ ምንጭ ርቃችሁ ሳላችሁ የዓለም ብርሃናት እንደ ሆናችሁ አድርጋችሁ በመቁጠር ራሳችሁን አታመጻድቁ። እግዚአብሔር "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ሲል በመንፈሳዊነት እየጎለመሳችሁ በሄዳችሁ ቁጥር በእምነታችሁ የጸናችሁና የተረጋጋችሁ ትሆናላችሁ ማለቱ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## በ. በተራራ ላይ

ጌታችን "በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም" ብሏል። ይህ አባባል የሚያስረዳን ልንደርስበት የሚገባውን የመንፈሳዊነት ደረጃ ነው። አባባሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገታችን በተራራ ላይ የተከተመች ከተማን እስከ መሆን ድረስ እንዳለበት ያስገነዝበናል ማለት ነው። ስለሆነም ጌታ በዚሁ በተራራው ስብከቱ እንዲህ አለ "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።" ማቴ 5:48

መንፈሳዊ ሕይወት ወደ ክርስትናው የፍጽምና ደረጃ የሚያደርስ ጅምር ነው። እኛ የእግዚአብሔር አምሳያዎች እንደ መሆናችን መጠን ፍጹም እርሱን ወደ መምሰሉ ደረጃ መድረስ አለብን። የዓለም ብርሃን ለመሆን የምንሻ ከሆነ የመንፈሳዊነት ተራራ አናት ላይ መውጣት ወይም ከፍ ማለት አለብን። በጣም ተቸግረህ የምትድን ከሆነ እንዴት ምሳሌ መሆን ትችላለህ? ሰዎችስ እንዴት በአንተ ሕይወት እግዚአብሔርን ማየት ይችላሉ? አንተ ግን እዚህ ከፍታ ላይ ከደረስህና ከተመለከትህ ነፍስህ ትሁት ትሆናለች። ትህትናህ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ደግሞ እግዚአብሔር የበለጠ ከፍ ያደርግሃል። ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር ብፅዕናን ለትሁታን ስለሚያድል ነው። ራስን የማዋረድ ሕይወትም ለሌሎች ብርሃንነትና መልካም ምሳሌ ነው። የተራራው ምሳሌና በመቅረዝ ላይ ያለ ሻማ ምሳሌ ተመሳሳይነት አላቸው።

ነገር ግን እኛ ወደ ተራራው አናት መውጣት አቅቶን በግርጌው እየቧጠጥን የምንድህ ከሆነ ምን ይፈጠራል? ጨውነታችንስ ወደ አልጫነት ተለውጦ ጨውነቱን ቢያጣስ ምን ይመጣል?

## ተ. ጨው አልጫ ቢሆንስ ?

ጨው ጨውነቱን ወይም ጣዕሙን ቢያጣ ምን ይሆናል? አንድ ባሪያስ ያለውን የሥራ ብቃት ቢያጣ ምን ይደርስበታል? ክርስቲያንስ ምሳሌነቱን ቢተው ምን ይመጣል? መቅረዙስ ከስፍራው ቢወሰድ ምን ይከተላል? ራእ 2:5። ይህ የሚሆን ነገር ግን የማይመስል ነው። ሆኖም ግን የማይሳሳት ደግሞ የለም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አባባል እንዲህ በማለት ነው የገለጸው። "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።" ማቴ 5:13። ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ ጌታ ብርሃንነትን ስለማጣትም በዚሁ በተራራው ስብከቱ ውስጥ እንዲህ በማለት ተናግሯል። "እንግዲህ በእናንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማውስ እንዴት



ይበረታ?" ማቴ 6:23። በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያበራ ወይም በራሱ በባለቤቱ ላይ የሚያበራ ብርሃን ወደ ጨለማነት ከተለወጠ ለዚህ ሰው ብርሃን ከወዴት ሊገኝለት ይችላል? ለምሳሌ ያህል ዓይን ለባለቤቷ ብርሃን መልካም ናት። እርሷ ብትጠፋ ከሌሎች የሰውነታችን ብልቶች እርሷን ተክቶ ብርሃን ሊያበራ የሚችል ይኖራልን ? የጠፋው ዓይናችንስ ጥቅም ይሰጣልን? በአንተ ውስጥ ያለው ጨው ጨውነቱን ቢያጣም ውጤቱ ይኸው ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቀሳውስትና አስተማሪዎች ሰዎችን የሚያሳስቱ ከሆኑ ምን ሊፈጠር ይችላል? ይህ በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ ተፈጥሮ ነበር። ይህንኑም አስመልክቶ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏቸዋል። "ሕዝቤ ሆይ! የመሩአችሁ ያስቷችኋል፤ የምትሄዱበትን መንገድ ያጠፋሉ።" ኢሳ 3:12። "ይህን ሕዝብ የሚመሩ ያስቱአቸዋል" ኢሳ 9:16።

ጌታችን ሥጋን ለብሶ በዚህች ምድር በተመላለሰበት ወቅት ሕዝቡን ይመሩ የነበሩት ሰዎች የተሳሳቱ ነበሩ። በሚሰጡት መመሪያና የተሳሳተ ወግ ሕዝቡን ወደ ጥፋት ይመሩት ነበር። ከእነዚህም መካከል ለመጥቀስ ያህል ፤ ፈሪሳውያን ፤ ሰዱቃውያን ፤ ጸሐፍት ፤ የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ይገኙባቸዋል። መሪዎች እንዲህ ሲስቱ ምን ሊከሰት ይችላል? ጌታ መልሱን ተናግሯል። "ዕውርንም ዕውር ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ።" ማቴ 15:14። ስለሆነም እንደነዚህ ያሉትን መሪዎች ጌታችን፤ "ዕውሮች መሪዎች" አላቸው። ማቴ 15:14። እነዚሁ ሰዎች በሰዎች ፊት ላይ መንግሥተ ሰማያትን ስለሚዘጉ በጌታ ወዮላቸው ተብሏል። ማቴ 23:13። በተጨማሪም "አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕር በደረቅ ስለምትዞሩ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሀነም ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ!" ተብለዋል። ማቴ 23:15-16።

ጨው ጣዕሙን የሚያጣው አስተማሪው ሰው የሃይማኖትን የት መጣና የትእዛዛቱን መንፈሳዊነት በተሳሳተ መልኩ ሲረዳቸው ነው። ታሪክ በአንድ ወቅት ለትውልዳቸው የምድር ጨውና ብርሃን ሆነው ከቆዩ በኋላ ከትክክለኛው የእምነት ጎዳና ስለወጡ ሰዎች ብዙ ምሳሌ ይሰጠናል።

- አርዮስ።

ይህ ሰው በኖረበት ዘመን የተዋጣለት ሰባኪ ነበር። ብሩህ አዕምሮና ጥልቅ የሆነ እውቀትም ነበረው። በመጨረሻ ግን ከእምነት አፈንግጦ ቢመከር እንኳ አልመለስም ስላለ በእርሱ ምክንያት የመጀመሪያው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተደረገ። በዚህ ጉባኤም ክህነቱ ተሽሮ ከቤተ ክርስቲያን እንዲለይ ተደረገ።

www.ethiopianorthodox.org

- ንስጥሮስና መቅዶንዮስ።

እነዚህ ደግሞ የቁስጥንጥንያ ፓትርያርኮች ነበሩ። ሁለቱም የሕዝብ መሪዎችና አስተማሪዎች ነበሩ። መቅዶንዮስ በጥርጥር ወደቀ። ስለሆነም ሁለተኛው ጉባኤ ተሰብስቦ አወገዘውና ከቤተ ክርስቲያን ተለየ። ንስጥሮስም እንዲሁ በኑፋቄ ስለወደቀ ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተደርጎ በውግዘት ተለየ። በመሆኑም እነዚህ ሰዎች ክብራቸውንና የክህነት ማዕረጋቸውን ስላጡ በሰዎች ከመረገጥ በስተቀር ያተረፉት ነገር የለም።

- አውጣኪ

ይህ ሰው በቁስጥንጥንያ ከነበሩ መነኮሳት ሁሉ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የነበረና ትክክለኛውን የብህትውና ሕይወት የሚመራ ሰው ነበር። በመጨረሻ ግን እንደ ሌሎቹ በጥርጥር ማዕበል ስለተመታ በቤተ ክርስቲያን አባቶች ተወግዞ ተለየ።

- ኦሪገን

ይሄኛው ሰው ደግሞ በጊዜው ከነበሩትና ኋላም ከተነሱት ሰዎች ሁሉ ይልቅ የተማረና ታላቅ የቲዮሎጂ ሰው ነበር። በመጨረሻ ግን እርሱም በኑፋቄ ስለተያዘ ቅዱስ ድሜጥሮስና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶች እንዲሁም ጉባኤው በአጠቃላይ አውግዞ ለየው። ከነቢያትም ወገን ጨውነታቸውን ያጡ አሉ። ከነዚህም መካከል በቅድሚያ የምንመለከተው . . .

- በለዓም

በለዓም የእግዚአብሔር መንፈስ ስለወረደበት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት የተናገረ ሰው ነው። ዘኊ 24:17 ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ድምፅ የሰማና የመለኮትን ራዕይ በውኑ በዓይኖቹ የተመለከተ ሰው ነበር። ዘኊ 24:2-4 ከዚህ በኋላ የሞዓብ ንጉሥ የነበረው ባላቅ ወደ አገሩ አስጠርቶ ሊቀበለው በወጣ ጊዜ በለዓም እንዲህ ነበር ያለው። "ባላቅ በቤቱ የሞላውን ብርና ወርቅ ቢሰጠኝ መልካሙን ወይም ክፉውን ከልቤ ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል እተላለፍ ዘንድ አይቻለኝም። እግዚአብሔር የተናገረውን እርሱን እናገራለሁ።" ዘኊ 24:13 በለዓም አስቀድሞ የመለኮትን ራዕይ ከተመለከተ በኋላ ይህን የመሰለ ትንቢትና ቃል ይናገር እንጂ በተሳሳተ መንገድ መሄዱ አልቀረም።

በዮሐንስ ራዕይ ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን በተጻፈው ክታብ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ በለዓምን በመቃወም ምስክርነት ሰጥቷል። ሰዎች የእርሱን ትምህርት ተከትለው በመሄዳቸው ጌታ ክፉኛ ወቅሶታል። ራዕ 2:14 በመሆኑም ይህ ጨው ጣዕሙን ስላጣ በሰዎች ተረገጠ። በአንድ በኩል ጨው ጨውነቱን



የሚያጣጣ ከሰዎች አስተሳሰብ የተነሳ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከሰውየው ባሕርይ የተነሳ ይሆናል። ለምሳሌ . . .

- ሶምሶን

የእግዚአብሔር መንፈስ በሶምሶን ላይ ገና ልጅ ሳለ ስለወረደ ሊያነቃቃው ጀመረ። መሳ 13:25 እግዚአብሔር በእርሱ አድሮም ብዙ ተአምራትን አደረገ። እንደ መልአኩም ብሥራት ከመወለዱ አንስቶ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ሆኖ አደገ። በመጨረሻ ግን ይህ ጨው ጨውነቱን ለተወሰኑ ጊዜያት አጣ። ደሊላና ሌላይቱ አመንዝራ ሴት ለጥፋት ዳረጉት። ጌታም ከእርሱ ተለየ። በዚህ ጊዜ ነው ፍልስጤማውያን ዓይኖቹን ካወጡትና እጆቹንና እግሮቹን በናሐስ ሰንሰለት ካሰሩት በኋላ በግዞት እንዲፈጭ ያደረጉት። መሳ 16:20-21

ሶምሶን በሰዎች እጅ ተረገጠ ማለት ነው። ነገር ግን ለጊዜው ነበር። ይህ ጨው በአንድ ወቅት ጨውነቱን ለጊዜው ካጣ በኋላ ወደ ቀደመ ጨውነቱ ተመልሷል። ኃይሉ የሚገለጥበት የሶምሶን ጠጉር እንደገና ያድግለት ጀመር። መሳ 16:22 በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ምንም እንኳ ሕይወቱን ጭምር ለሞት አሳልፎ ቢሰጥባትም እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እጅ ነፃ አወጣው። ቅዱስ ጳውሎስ የዚህን ሰው ስም በእምነት ጠንካሮች ከነበሩ ሰዎች ስም መካከል አስገብቶ ጠቅሶታል። ዕብ 11:32

በተመሳሳይ መልኩ ጠቢቡ ሰሎሞንም ከዚሁ ጋር እናስታውሰዋለን። እርሱም የምድር ጨው ነበር። እግዚአብሔር ከአንድም ሁለቴ ጊዜ በኢየሩሳሌምና በገባዖን ተገልጦለታል። 1ኛ ነገ 9:2 መገለጥ ብቻ አይደለም በዓለም ካሉ ጠቢባን ሁሉ የበለጠ ጥበብን ሰጥቶታል። 1ኛ ነገ 3:12 እግዚአብሔር አምላክ በአፉም በጆሮውም ይነጋገራል። መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊው ኃይሉ የሚናገረውን በአንደበቱ ያናግርለት ነበር። ስለዚህ ከመጻሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምሳሌንና ጥበብን ሙሉ ለሙሉ ሊጽፍ በቅቷል። ከዚህ በኋላስ ምን ተፈጠረ? ጨው ጨውነቱን አጣ።

በሰሎሞን ሕይወት ማብቂያ ላይ አሳዛኝ ክስተት ተፈጠረ። ስለዚህ አሳዛኝ ሁኔታም መጻሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ እንዲህ ይላል። "ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶ ቁባቶችም ነበሩት። ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉበት። ሰሎሞንም ሲሸመግል ሚስቶቹ ሌሎች አማልክትን ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉበት። የአባቱ የዳዊት ልብ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም እንደነበረ የሰሎሞን ልብ እንዲህ አልነበረም። የሲዶናውያንን አምላክ (ጣዖት) አስታሮትን የአሞናውያንንም ርኩሰት ሚልኮምንም ተከተለ። ሰሎሞን በእግዚአብሔር ፊት ክፉን አደረገ። እንደ አባቱም እንደ ዳዊት እግዚአብሔርን በመከተል ፍጹም አልሆነም። . . . ለሞአብ ርኩሰት ለካሞሽ ለአሞንም ልጆች ርኩሰት መስገጃ ሠራ። ለአማልክቶቻቸውም ዕጣን ለሚያጥኑ

www.ethiopianorthodox.org

መስዋዕትም ለሚሰው ለእንግዶች ሚስቶች ሁሉ እንዲህ አደረገ። 1ኛ ነገ 11:3-8።

ይደንቀኛል! ይህ ጨው ታድያ ወደ ውጭ ተጥሎ በሰዎች ተረግጠ ይሆን? አልተረገጠም። እግዚአብሔር ምህረትን አወረደለት። በመጨረሻዎቹ ቀናቶቹ ሰሎሞን በንስሐ ተመልሶ በዓለም ስላሳለፋቸው ደስታዎቹ የሚገልጸውንና ሁሉም ከንቱ መሆኑን የሚያስረዳውን መጽሐፈ መክብብን ጻፈ። ከመጽሐፉ መግቢያ ላይ ጀምሮ "ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነበር" አለ። መክ 1:2-11። እግዚአብሔር ለዳዊት በተናገረው ቃል ውስጥ ለሰሎሞን ምህረት ማድረጉን አረጋግጧል። "ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሳለሁ ፤ መንግስቱንም አጸናለሁ . . . ክፉ ነገርም ቢያደርግ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገስጸዋለሁ። ከፊቴም ከጣልሁት ከሳኦል እንዳራቅሁት ምህረቴን ከእርሱ አላርቅም።" 2ኛ ሳሙ 7:12-15።

እዚህ ላይ የቆሸሸውን ጨው ሙሉ ለሙሉ የተፈጥሮ መልኩንና ጣዕሙን ከአጣው ጨው ጋር ልናነጻጽር እንችላለን። ሰሎሞን ጣዕሙን ሳያጣ የቆሸሸውን ጨው ነው የሚመስል። በተፈጥሮው አምላኩን የሚወድ ሰው ነበረና። አባቱ ዳዊትም እንዲሁ በአንድ ወቅት ለተወሰነ ጊዜ ቆሽሾ ነበር። ዳዊት በእግዚአብሔር የተቀባና መንፈሱም በላዩ የወረደበት ሰው ሲሆን ጌታ ስለ እርሱ እንዲህ በማለት የመሰከረለት ሰው ነው። "የዳዊትን ልብ መርምሬሁት እንደ እርሱም እንደ ልቤ የሚሆንልኝ ሰው አላገኘሁም።" ይህ ጨው ነው የቆሸሸው። ዳዊት በዝሙት ፣ በግድያ ፣ በስቀልና የሰዎችን ደም በማፍሰስ ኃጢአት ተበከለ። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ወደ ውጪ ተጥሎ በሰዎች እንዲረገጥ አልወደደም። ይልቁንም ጌታ አምላኩ ከበረዶ ይልቅ አነጻው እንጂ። መዝ 50

ቻ. በሰዎች መረገጥ

ሳኦል በሰዎች ከተረገጡት መካከል አንዱ ንጉሥ ሳኦል ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ስለወረደ ለእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ተቀባ። ይህም በመሆኑ በሰዎች እርስ በእርሳቸው "በውኑ ሳኦል ከነቢያት ወገን ነውን?" እስኪሉ ድረስ ትንቢት ተናገረ። 1ኛ ሳሙ 10:10-11 ቆይቶ በአንድ ወቅት ይህ ጨው ጣዕሙን አጣ። ትዕቢተኛነት ስለ ያዘው ራሱን ከእግዚአብሔር ለየ። በራሱ ማስተዋል ስለተደገፈም የእግዚአብሔርንም ፍቃድ ሆን ብሎ የታላቁን ነቢይ የሳሙኤልን ቃል አልሰማ አለ። ስለዚህም መለኮታዊው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ሕይወቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ለህልፈት በቃች። "የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ። ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሰቃየው።" 1ኛ ሳሙ 16:14



በሰው ከተረገጡት የጨው ዓይነቶች መካከል ቀደም ሲል ካነሳነው ከበለዓም ሌላ ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አስቀድሞ ተነስተው የነበሩት ቴዎዳስና የገሊላው ይሁዳ ይገኙበታል። ሐዋ 5:36-37 እነዚህ ሰዎችና መሰሎቻቸው ጌታ እንዲህ ብሎ የተናገረላቸው ሰዎች ናቸው። "ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው። ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም። ዮሐ 10:8

ሌሎቹ ጨውነታቸውን ያጡት ሰዎች አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ናቸው። አዳም በእግዚአብሔር መልክና አርአያ ነበር የተፈጠረው። አምላካችን እርሱን ከፈጠረ በኋላ ሔዋንን ደግሞ እርሱን አስመስሎ ፈጠራት። ዘፍ 1:26 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ በባሕር የሚኖሩ ዓሦችን ፤ በሰማይ የሚበሩ አዕዋፋትን ፤ በምድር ያሉ እንስሳትና በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ እንዲገዛና እንዲነዳም ሥልጣንን ሰጠው። አዳምና ሔዋን አስቀድሞ ንጹሐን የቀሆችና ቅኖች ነበሩ። ከእነርሱ በኋላ ከተነሳው ትውልድ ውስጥ እነርሱን የሚመስል አልተነሳም ፤ ኃጢአትን አያውቁም ነበርና። ይህም ስለሆነ ሁለቱም እርቃናቸውን ሆነው ፍጹም አይተፋፈሩም ነበር።

ከዚህ በኋላ ግን ይህ ጨውነታቸው ጣዕሙ ጠፋ። የሰው ልጅ ባህርይ ጎሰቆለ። እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋንን ከገነት አባረራቸው። ልጆቻቸውም በእነርሱ መንገድ ሄዱ። አባቢቱም የሰው ልጆችን ስኮና ትንክስ ዘንድ ሥልጣን ተሰጣት። ዘፍ 3:15 እግዚአብሔር ግን የሰዎችን ሥጋ ለብሶ ፤ እስከ ሰው ልጆች ደክሞና ሞቶ አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ ከፍ በማድረግ ያጣውን ጨውነቱ መለሰለት። በዚህም ጨው ጨውነቱን ቢያጣም እንኳ እግዚአብሔር መልሶ ሊያጣፍጠው እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን። ጨው ቢቆሽሽም ጌታ ያጠራዋል። በውስጡም መልሶ ይህን የተበከለ ፍጥረት እንዲጣፍጥ መልካም መዓዛን ያደርግበታል። ፍጹም እንደማይጠቅም ጨው አድርጎ አይተወውም ማለት ነው።

ሌላ ተጨማሪ ምሳሌ እንስጥ። ይኸውም ጴጥሮስ ጌታውን አላውቀውም ባለ ጊዜ የተፈጠረው ሁኔታ ነው። የተለያዩ ስሞችን በመጥራት እየማለና እየተገዘተ "ይህን የምትሉትን ሰው አላውቀውም" አለ። ስለሆነም ተደራራቢ ኃጢአቶችን ፈጸመ። ፍርሃት ፤ ጌታውን መካድ ፤ የእምነት ማነስ ፤ ሐሰት መናገር ፤ መሐላና ርግማንን በአንድ ጊዜ ፈፀመ። ይደንቀኛል! በውኑ ቅዱስ ጴጥሮስ የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን ነበርን? አልነበረም። አዎን-በዚያች ሰዓት አልነበረም። ሆኖም ግን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጨውነቱን መልሶለታል። ይህ ቅዱስ ሰው በሰዎች ይረገጥ ዘንድ አልፈቀደም። ይህም የሆነው የክህነት ሥልጣኑን አጽንቶለት ከቀደመ ሕይወቱ ነፃ ባደረገው በዚህ ቃል ነው። "በሰው ፊት የሚክደኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።" ማቴ 10:13 በመሆኑም ከትንሣኤው በኋላ ጌታ እንዲህ ሲል አደራ ሰጠው። "ጠቦቶቼን ጠብቅ ፤

በጎቼን አሰማራ . . .” ዮሐ 21:15-16። አቤቱ ጌታ ሆይ! አልፎ አልፎ ጣዕሙንና ጨውነቱን በሚያጣው ጨው ላይ የአንተ ምህረት ትደረግ።

አንዳንድ ጊዜ ድንገት ሳይታወቀው ሰዎች በሚፈጽሙት ስህተት ውስጥ የሚገባውና ጨውነቱንም በዚህ እንዳያጣ አጥብቆ የሚጠነቀቀው ግን “ ጌታ ሆይ! አንተ ሁሉን ታውቃለህ እንድወድህም አንተ ታውቃለህ” ይላል። ዮሐ 21:17 በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው ፈጽመው የራቁት ግን ልክ እንደ መናፍቃኑና እንደ ዕውራኑ መሪዎች የጨውነታቸውን ጣዕም እንዳጡ ይቀራሉ።

ጨው በመጥፎ ባህርይ አማካይነትም ጣዕሙን ሊያጣ ይችላል። ይህም ንጉሥ ዳዊት ዝሙትን በፈጸመ ጊዜ ፣ በለዓም የሕዝቡን ንጽህናና ቅድስና ሊያደፈርስ የሚያደርግ የምክር ቃል በተናገረ ጊዜ ታይቷል። ጌታ እግዚአብሔር ዳዊትንና ሶምሶንን ይቅር ሲል በለዓምን ግን ቀጥቶታል።

ትዕቢተኛነትም የጨውን ጣዕም ያጠፋዋል። ሰይጣን ከመጣሉ አስቀድሞ ገና ሲፈጠር ጨው ነበር። ለቅዱሳን መላእክት በተሰጠው ክብርና ብርሃን እርሱም አሸብርቆ ነበር። ነገር ግን በልቡ “ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ።” ኢሳ 14:13-14 ባለ ጊዜ ጨውነቱን አጣ። ለዚህ ትዕቢቱም የተሰጠው ምላሽ ከነ መልዕክተኞቹ ከገነት መባረርና እግዚአብሔር እባቡን ጊንጡን የጠላትንም ኃይል ሁሉ እንዲረግጡ ሥልጣንን በሰጣቸው ሰዎች መረገጥ ሆነ። ጨው ጨውነቱን በሚያጣበት ጊዜ ጣዕሙን የማጣቱ ነገር ከነበረው የኃላፊነት ደረጃ አኳያ እየጨመረ ነው የሚሄደው። ለምሳሌ ሰይጣን የብርሃን መልአክ ነበር። ጣዕሙን ማጣቱ ደግሞ ከፍተኛ ውርደት ነው። ስለሆነም በቅድስናውም ሆነ ከዚያ በላይ ባሉት የክህነት ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ካህናት በሚገባ የዓለም ብርሃንና የምድር ጨው መሆን አለባቸው። ይህንንም አስመልክቶ ጌታ በሎዶቅያ ላለው የቤተ ክርስቲያን አለቃ እንዲህ በማለት አጸፈ። “ ከአፌ ልተፋህ ነው” ራዕ 3:16 በዚህ ዓይነት መልኩ ነው ምንም ጥቅም የማይሰጥ ስለሆነ ወደ ውጪ የሚጣለው። ይህም በመሆኑ መስዋዕቱን የሚያቀርበው ካህን የእያንዳንዱን ሰው የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ አስመልክቶ “ የሕዝቡን ፣ ኃጥዕ የምሆን የእኔንም የአገልጋይህን ጸሎት ተቀበል።” የሚለው። የካህኑ መውደቅ እንደ ሌላው ምዕመን ሳይሆን ለእርሱ ታላቅ ኃጢአትና በደል ነው የሚሆንበት። ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ነውና ሰዎች ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል። ሚል 2:7 በመሆኑም ካህን ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም ማለት እንኳ አይችልም። ከዚህ አኳያ የሰውየው መንፈሳዊ የእድገት ደረጃ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለሚፈጽማቸው ኃጢአቶች ያለበት ኃላፊነት እየከበደ ይሄዳል ማለት ነው። በተለይም በመምህራንና በሚከተሏቸው ሕዝብ ዘንድ ታላቅ ምሳሌና አርአያ የሆኑ አባቶች። ከአንደኛ ፎቅ ላይ የወደቁና ከአሥረኛ ፎቅ ላይ የወደቁ ሰዎች ጉዳት አንድ አይደለምና።



ጣዕሙን ያጣ ጨው ወደ ውጪ ይጣላል ሲል ምን ማለቱ ነው?

## ነ. ወደ ውጪ መጣል

“ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። እናንተ የምድር ጨው ናችሁ” በማለት ሕዝቡን ያበረታታው ጌታ ይህንኑ በተናገረበት አንደበቱ በቀጥታ ያለ አንዳች ማወላወል ጨው ካልጣፈጠ የሚመጣበትን ችግር “ ጨው አልጫ ቢሆን ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ምንም አይጠቅምም” አለ። እዚህ በምድር ሳለ ከቤት ወደ ውጪ ይጣል እንጂ በወዲያኛው ዓለም ለዘላለም በገሀነም እሳት ውስጥ ይጣላል ማለት ነው። ለዚህም ነው በምድር ሳለ እንዲህ ስላለው ጨው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በ2ኛ ዮሐ 10 ሲጽፍ “በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት” ያለው።

የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ረዳት በነበረውና በአገልግሎቱ ሁሉ ይላከው በነበረው በዴማስ ላይም የደረሰው ይኸው ነው። ዴማስ በአንድ ወቅት ሰባኪ (ጨው) ነበር። ነገር ግን የጨውነት ጣዕሙን ባጣ ጊዜ ራሱን ከአማኞች ህብረት በማግለል ወደ ውጪ ጣለ። ስለ እርሱ ቅዱስ ጳውሎስ ሲጽፍ “ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና” አለ። 2ኛ ጢሞ 4:10

እንዲህ ባለ መልኩ የሚመላለሱትን ቤተ ክርስቲያንም ከጉባኤ ትለያቸዋለች። ይህም ሁሉንና የተለያየ መልክ ያላቸውን የመናፍቃን ድርጅቶች ከአማኞች ህብረት መለየትን ያጠቃልላል። የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ሁሉንም ይመለከታልና። “ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።” ገላ 1:8 ይህ ማለት ከቤተ ክርስቲያን ህብረት እንዲለይ ተወገዘ ወይም ወደ ውጪ ተጣለ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ህብረት ስለሆነች ቅድስናዋን ጠብቃ መኖር አለባት። ይህ አባባል በአብዛኛው በመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ጉልህ በሆነ መልኩ ተቀምጧል። ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ወደ ኤፌሶን ሰዎች ሲልክ “ በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን . . .” ኤፌ 1:1 በማለት ነው የላከው። በፊልጵስዮስ ለሚኖሩትም ጽፎ ሲያጠቃልል “ ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላምታ አቅርቡ። . . . ቅዱሳን ሁሉ ይልቁንም ከቄሳር ቤት የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል” ብሏል ፊል 4:21-22 ወደ ዕብራውያን ሲጽፍም “ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ . . .” አለ። ዕብ 3:1 በቆላስይስ መልዕቱም “ እንዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ ምህረትን ፣ ርኅራኄን ፣ ቸርነትን ፣ ትህትናን ፣ የዋህነትን ትዕግስትን ልበሱ።” አለ። ቆላ 3:12 ወደ ቆሮንቶስ ሲጽፍም “ በአካያይ አገር ሁሉ ከሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ ጋር በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን . . .” አለ። 2ኛ ቆሮ1:1

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ህብረት እስከሆነችም ድረስ ከመዝሙረኛው ጋር በአንድነት አብራ " አቤቱ እስከ ረጅም ዘመን ድረስ ቅድስና ለቤትህ ይገባል።" እያለች ትዘምራለች። መዝ 92:5 በዚህ ቃል መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡት ቅዱሳን ብቻ ሲሆኑ ኃጢአተኞች ደግሞ ከውጪ ቆመው ወደ ውስጥ የዘለቁት እንዲጸልዩላቸው ይማፀናሉ። የዲያቆኑም ረዳት በቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ ቆሞ በኃጢአቱ ምክንያት እንዳይገባ የታገደውን ሰው ከመግባት ይከላከለዋል። እንዲህ ባለው ጥብቅ ክትትል ቤተ ክርስቲያን ቅድስናዋን ትጠብቃለች።

ቅዱስ የተባለውና ጻድቁ ዮሐንስ ከእርሷ ጋር ልትተካከል የማትችለውን አንዲት ደሀ አደግ መበለት የተጋፋችውን ንግሥት ወደ ቤተ መቅደስ ከመግባት አግዷታል። በወቅቱ የእርሷ ንግሥት መሆን ለእርሱ የሰጠው ልዩ ትርጉም አልነበረም። ይህን በድፍረትና በኃይል በማድረጉም ንግሥቲቷ ልታመጣብኝ የምትችለው ቅጣት ይኖራል ብሎም አልሰጋም።

ይህን በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን ሕግጋት በጣም ግልጽ ናቸው። አማኞች የክርስቶስ ብልቶች ናቸው። 1ኛ ቆሮ 6:15 የክርስቶስ ብልቶች ደግሞ የተቀደሱ ስለሆኑ ማንም ይህ ቅድስና ሳይኖረው እንደ ብልት ሊቆጠር አይችልም፤ በውጪ ይቆያል እንጂ። በመጨረሻም ይህ ጨውነቱን ያጣው ጨው ለዘላለም ወደ ውጪ ይጣላል።

መጽሐፍ ቅዱስ በውጪ ስላለው የጨለማ ቅጣት ብዙ ይነግረናል። ስለ እነዚህ ስለሚጣሉ ሰዎች ጌታ ራሱ ተናግራል። " . . . በውጪ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" ማቴ 8:12 ለዚያ መክሊቱን ቆፍሮ ለቀበረው ባርያም እንደዚህ ብሏል። " የማይጠቅመውን ባርያ በውጪ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" ማቴ 25:30 እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ከዘላለማዊ መንግሥት ፤ ከቅዱሳን ህብረት፤ ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ መኖሪያ እንዲሁም ከብርሃን ርቀው በጨለማ ይሆናሉ ማለት ነው። " ወደ ውጪ" እና " በውጪ ወዳለው" የሚሉት ቃላት ዘላለማዊውን ቅጣት በማጉላት ረገድ በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል። ስለ ቆነጃጅቱ ጌታ ባስተማረበት ምሳሌ ልባሞቹ ቆነጃጅት ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ አዳራሽ ሲገቡ በማሰሮአቸው ዘይት ያልያዙት ሰነፎቹ ግን በውጪ ቆመው " ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ክፈትልን" አሉ። ማቴ25:11 እርሱ ግን መልሶ " እውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም" አላቸው።

ይህን ጉዳይ ጌታ ግልጽ በሆነ መልኩ አስቀምጦታል። " በጠበበው በር ለመፍባት ተጋደሉ ፤ እላችኋለሁና ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም። ባለቤቱ ተነስቶ በሩን ከቆለፈ በኋላ እናንተ በውጪ ቆማችሁ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ክፈትልን እያላችሁ ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ። እርሱም መልሶ ከወዴት እንደሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል። . . . . አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ



ጊዜ እናንተ ግን ወደ ውጪ ተጥላችሁ ትቀራላችሁ።" ሉቃ 13: 24:28። ወደ ውጪ የሚጣለው ጨው ታሪክ ይህን ይመስላል።

ጌታ በመጸሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ጨው እንዲህ በማለት ተናግሯል። " ጨው መልካም ነው ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ለምድር ቢሆን ለፍግ መቆለያም ቢሆን አይረባም ፤ ወደ ውጪ ይጥሉታል። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ " ሉቃ 14:34-35።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አሥር

## 1. ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ።

ጌታ እንዲህ አለ "በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከእንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል፤ በቤትም ላሉት ሁሉ ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ። ማቴ 5:14-16

### ሀ. ከተማና መብራት ።

ጌታችን ስለ ከተማና መብራት ሊናገር የወደደው፤ በተናጠል ለሰው በአጠቃላይ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን በመመሰል ነው። ሁለቱም ለኅብረተሰቡና ለዓላሙ ሁሉ የብርሃን ምንጮች ናቸውና። ግለሰቡን ወይም እረኛውን በመብራቱ ሲመስለው ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ በከተማው መስሏታል። በሰዎች ፊት እናበራውና በእርሱ መርተን ከጨለማው ነፃ በማውጣት ወደ እግዚአብሔር እንመራቸው ዘንድ እርሱ ብርሃንን ለእኛ ሰጥቷል። ይህንንም አስመልክቶ ጌታ ለአይሁድ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ሲናገር እንዲህ አለ። "ዮሐንስ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበር፤ እናንተም በብርሃኑ ጥቂት ዘመን ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ።" ዮሐ 5:35 አማኝ የሌሊት ብርሃን ወይም መብራት ስለሆነ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ ብርሃኑን ይሰጣል።

ብርሃን የእግዚአብሔር ሕግ ወይም ይህንን ሕግ ተሸክመው የሚጊዙ ሰዎች ምሳሌ ነው። በመዝሙራት መጸሐፍ እንዲህ የሚል ቃል አለ። "የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ብሩህ ነው፤ ዐይንንም ያበራል።" መዝ 18:8 በተጨማሪም "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው።" ይላል መዝ 118:105 የእግዚአብሔር ቃል በመንፈሳዊው ጎዳና ላይ ለሰዎች ብርሃንን የሚፈነጥቅ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት በቅዳሴ ላይ ከመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲነበብ መብራት (ጧፍ) የሚበራው የእግዚአብሔርን ቃል ብሩህነት ለማመልከት ነው። ጳጳሳት ሲመጡም መብራት አብርተን የምንቀበላቸው ወደ እኛ ሲመጡ ብርሃንን ይዘውልን እንደሚመጡ ወይም እነርሱ ራሳቸው ብርሃን ሆነው እንደመጡ ለማመልከት ነው። በተመሳሳይ መልኩ በቅዱሳኑ ስዕል ፊት መብራት እናበራለን።

በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን አባቶችና ለቤተ ክርስቲያን የተጠቀሰ ተመሳሳይ ንጽጽር እናገኛለን። አብያተ ክርስቲያናቱን በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ሲመስላቸው ሰባቱን ከዋክብት ደግሞ ከጌታ በስተ ቀኝ ባሉት



በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን መላእክት (አለቆች) ይመስላቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ናት። ቀሳውስትም ብርሃናት ናቸው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በእነርሱ አማካይነት ብርሃንን ለልጆችዋ ታድላለች። ስለዚህም ብርሃን የሆነችው እርሷ ብቻ ሳትሆን ብርሃናትንም ያቀፈች ናት።

ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን እንዳቀፈች ወይም ለእነርሱ መጠለያ እንደሆነች ሳለች ከተማ ተብላ ልትጠራ ትችላለች። በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏልና። "ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።" ራእ 21:2 ሐዋርያው ዮሐንስ ስለዚህችው ከተማ በተመሳሳይ መልኩ በመቀጠል ሲጽፍ እንዲህ አለ። " ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለሆነ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጊትም።" ራእ 21:23 ይህ ብርሃን ያለው ማንኛውም ሰው ወደ ኢየሩሳሌም ወደምታበራው ከተማ ሊገባ ይችላል። " ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።" ራእ 21:27 ምክንያቱም ጨለማ ስለሆኑ ነው። " ሰዎችም ክፉ ሥራ ነበራቸውና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ።" ዮሐ 3:19

እነዚህ በጌታ አማካይነት ወደ ዓለም የተላኩት ብርሃናት ግን ሊሰወሩ ፈቃደኞች አይደሉም። ሊሰወሩ አይችሉም ማለት ነው።

### ለ. ሊሰወሩ አይቻላቸውም

" በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም።"

ዝቅተኛና ደካማ የሆኑ ደረጃዎች ሊሸሸጉ ይችላሉ ወይም ደግሞ በሁሉም ሰዎች ሊታዩ አይችሉም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ እስከ ጫፍ ድረስ ከፍ ከፍ ያደረጋቸው በምንም ዓይነት ኃይል ሊሸሸጉ አይችሉም። እንደ ምሳሌ አድርገን ቅዱስ ጳውሎስን ብንወስድ ብዙ መከራና ስቃይ በግፍ ይድረስበት እንጂ ብርሃኑ በሰዎች ሁሉ ፊት ብሩህ እንደሆነ ቆይቷል። ሌሎች ሐዋርያት ወንድሞቹንም ሊቃነ ካህናቱ እንዲሁ ነበር ያሏቸው። " በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆ ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል ፤ የዚያንም ሰው ደም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስባላችሁ።" ሐዋ 5:28

ሌሎችንም ብዙ መብራቶች ከእንቅብ በታች ሊደብቋቸው ሞክረው ነበር።ነገር ግን ጌታ ይህን ሽፋን እያስወገደላቸው ብርሃናቸው እንዲታይ አድርጓል። እነዚህ ብርሃናት ብርሃናቸው ጥቂት እንኳ እንዳይፈነጥቅ በእነርሱ ላይ የሐሰት ወሬ በማስወራትና ከአገር አገር በማሳደድ ሊያጠፉሳ ሞክረዋል። ጌታችን በሰንበት ያን ዐይነ ሥውር በማዳኑና ተአምራትን በማደረጉ በሰንበት

www.ethiopianorthodox.org

ያልተፈቀደውን የሚሠራ ኃጢአተኛ ነው እንዳሉት ትዝ አይላችሁም? ዮሐ 9:24 “ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም” ማቴ 12:24 ማለታቸውንስ “በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጪ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ?” ማለታቸውንስ? ማቴ 11:19 ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ሳምራዊ ነው ጋኔንንም አለበት ብለውታል። ዮሐ 8:48 ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ዕንቅፋቶች የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን ሊሸሽጉ አልቻሉም አይችሉምም።

የቅዱስ አትናቴዎስን ብርሃን ለመጋረድስ ስንት ዕንቅፋቶችን ተጠቅመው ይሆን? ምን ያህል ጉባኤዎችንስ እርሱን በመቃወም አዘጋጅተው ይሆን? ከመንበረ ጵጵስናውስ ስንት ጊዜ ተሰደደ? ብዙ ጊዜ። ይሁንና እነዚህ ሁሉ መከራዎች ይድረሱበት እንጂ አትናቴዎስ ቀድሞ የነበረው ማንነቱ አልተለወጠም። እርሱ ያወጣቸው የመመሪያዎቹ ብርሃናት እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ዙሪያ ያበራሉ። በእርግጥም የእምነት ጀግና ነበር።

የሚያበራውን መብራት ገና ማብራት መጀመሩን እንደተመለከቱ ዕንቅብ ሊደፉበት የሚሞክሩ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ዲያቢሎስ ምንጊዜም ቢሆን የመልካም ነገር ሁሉ ተቃዋሚ ስለሆነ መልካም የሆነውን ሁሉ ይቃወማል። ስለሆነም በእግዚአብሔር ልጆች ስለሚቀናና እርሱ ራሱ ጨለማና የጨለማውም ገዢ ባለሥልጣን ስለሆነ እነርሱንም እንደ እርሱ ለማድረግ ሁልጊዜ ለዓለም ብርሃን እንዳይሆኑ ይቃወማቸዋል። በመሆኑም ዘወትር የእርሱ ባለሟሎች የሆኑት እነዚህን የእግዚአብሔር ልጆች እንዲዋጉ ቅስቀሳ ያካሂዳል ማለት ነው።

ሰይጣን ያደረባቸው ሰዎች እነዚህን የእግዚአብሔር ልጆች የሚዋጉት ዲያቢሎስ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ በጥላቻ የተሞላ ቅንዓት ስላለበት ወይም ተገቢ ያልሆነ እኔ ብቻ ልታይ ባይነት ትዕቢት ስላለበት አሊያም ደግሞ የጻድቃኑ ብርሃን የእነርሱን ኃጢአት ስለሚገልጥባቸው በዚህም ሰዎች መልካሙን ከክፉው ለይተው እንዳያውቁ ስለሚወድ ወይም ደግሞ በእግዚአብሔር መንግሥትና በሰይጣን መንግሥት መካከል የማያቋርጥ ውጊያ ስላለ ነው። እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይሆናሉ።

የመደበቅ ወይም የመሸሸግ ምኞት ደግሞ ግድያን ያስከትላል። ይህ እንደተፈጸመ የምናየው ደግሞ ንጉሥ ሄሮድስ በመጥምቁ ዮሐንስ ላይ የወሰደውን እርምጃ ስንመለከት ነው። የዮሐንስ ብርሃን የእርሱን ኃጢአት ስለገለጠበትና ብርቱ ማስጠንቀቂያ ስለሰጠው ሊያጠፋው ወደደ። ማቴ 14:3-5 ኤልዛቤልም በተመሳሳይ መንገድ ይህን እርምጃ ልትወስድ ትመኝ ነበር። 1ኛ ነገ 19:1-2 ከዚህ በተጨማሪ ከክፉ ሥራዋ እንድትመለስ በነገራት በዚያ በጻድቁ ዮሐንስ ላይ ያቺ ንግሥት ተመሳሳይ ርምጃ ወስዳለች። እነዚህ ሰዎች ይህን በማድረጋቸው እነርሱን ለመሸሸግ የተደረገው ሙከራ ወደ ኃይል ተለውጦ ለማጥፋትና በሚቻለው ሁሉ የእውነትን ድምፅ ፀጥ ለማሰኘት ገንፍሎ መውጣቱን ያመለክተናል።



ዕንቅብ አንድም ሊያደርጉ የሚወዱትን እንዳያደርጉ የሚያግድ አሊያም ደግሞ ግድ የለሽነት ነው። ይህ እንዳይሆን ጥበብን ገንዘብ ለማድረግ ለእነዚህ አገልጋይ ከመሆን መራቅ ይቻላል።

እንዲህ ላለው ግርዶሽ ለሚጋለጡት መብራቶች እግዚአብሔር ከሌላ ራቅ ካለ ሥፍራ እንዲያበሩ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል። እንዲህ ባለ መልኩ ምንም ዓይነት ከፍተኛ ማዕረግ ወይም ሥልጣን ሳይኖራቸው ነገር ግን ታላላቅ ሥራዎችን የሠሩ ብዙ ብርሃናት አሉ። ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስን ብንመለከት የዓለም ብርሃን ሆኖ ሳለ ሥጋን ለብሶ በዚህች ምድር በተመላለሰበት ወቅት እንዳችም ምድራዊ ማዕረግና ሥልጣን አልነበረውም። የእኛ ኃላፊነት የሌሎችን አገልግሎት መጫን ወይም ደግሞ ብርሃናቸው ላይ ዕንቅብ መድፋት አይደለም።

ፉክክር ግርዶሽን ሊያመጣ ይችላል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት በሚደረገው ግልጋሎት እርስ በእርሳቸው አንዱ የሌላውን አገልግሎት ለማደብዘዝ የሚያደርገው ፉክክር እንግዳ ነገር ነው። እንዲያውም በመካከላቸው ጠላትነትን ሲፈጥር ይታያል። ስፊና ለሁሉም የሚበቃ የአገልግሎት መስክ እያለ አንዱ በሌላው አገልግሎት ላይ ዕንቅብ ለመድፋት ሲሽቀዳደም ይስተዋላል። “መከሩስ ብዙ ነው ፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው።” ማቴ 9:37

ራስ ወዳድነት በሌላው መብራት ላይ ዕንቅብን ይደፋል። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ያህል ሰፊ እንደሆነች የማያሳይ በእንጻሩ በአገልግሎት ሁሉ ውስጥ ለእኔ ብቻ ይሁን ማለትን የሚያመጣ ነው። የእርሱ ብርሃን ብቻ እንዲያበራና የሌሎቹ እንዲጠፉ በዚህም እርሱ ብቻ እውነተኛ አገልጋይ መስሎ ለመታየት የሚያስመኝ ስሜት ነው ፤ ራስ ወዳድነት።

ሌላም እንቅብ አለ። ይህም ራስን በመካድ ስም የሚከደን ዕንቅብ ነው። ሳይሆኑ እንደ ሆኑ መስሎ በመቅረብ ማለት ነው። እስቲ በመቀጠል በእግዚአብሔር ቃል እንመልከተው።

### ሐ. ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው

“ጌታ መልካሙን ሥራችሁን አይተው” አለ እንጂ “ሰምተው” አላለም። ለሰው ልጅ በውስጡ ፍጹም ክፋትን ቋጥሮ በአንደበቱ መልካምን መናገር በጣም ቀላል ነገር ነው። ከሆነ ሰው አንደበት እርሱ ለማንም የማይጠቅምና ኃጢአተኛ እንደሆነ የሚመስክሩ ትህትናን የተላበሱ አነጋገሮችን ታዳምጣለህ። ይህ ማንነቱን ለማረጋገጥ በሆነ መንገድ ቀርበህ ስትመረምረው ግን ደርሶ ቁጡ ስለሚሆን ባዶነቱን ትመለከታለህ። እዚህ ላይ አንድ መንፈሳዊ ምሁር የተናገረውን ለመጥቀስ እወዳለሁ። “እነርሱ በጭቃ ውስጥ እየተንደባለሉ ዝናም ሊዘንም መድመኑን የሚነግሩህ አንዳንድ ሰዎች ኣሉ።”

www.ethiopianorthodox.org

ጸሐፍት ፈሪሳውያን የሚናገሩት ቃልና የሚሠሩት ሥራ ፍጹም አይመሳሰልም ነበር። የሚሰብኩትን ትተው የማይሆንና ከንቱ ነገር ነበር የሚሠሩት። “ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ። እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።” ማቴ 23:4 አንተ እኔን እንደምትወደኝ የምትነግረኝ ቃልና እኔ ለአንተ ፍቅር ያለኝ አመለካከት እንዲሁም በእኔ ላይ የሚያሳድረው ስሜት ከእኔ ጋር በምታደርገው ግንኙነት ሊገለጽ መቻል አለበት። ይህን ስንል የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ ቃላት ምን ያህል ጥልቅ እንደሆኑ እንገነዘባለን። “ልጆቼ ሆይ! በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።” 1ኛ ዮሐ 3:18

ሃይማኖት ማለት የቀላል ቃላት ስብስብ ወይም የሚሸመድዱት ስንኝ ወይም ደግሞ የሚያዜሙት ዜማ አይደለም ። መንፈስና ሕይወት ነው እንጂ። ሰዎች ለሰዎች የሚበልጠውን ብርሃን የሚያበሩት በአንደበታቸው ሳይሆን በሕይወታቸው ነው። የአንዳንድ ሰዎች ንግግር እንዲያውም ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም በሕይወታቸው የሚያሳዩት ሥራ እንደ ታላቅ ግድግዳ ሆኖ ተቀባየነታቸውን ስለሚያሳጣቸው ነው። አንድ መንፈሳዊ የሆነ ሰው በሚሠራውና በሚናገረው ንግግር መካከል ርቀት ሊኖር አይገባም። አነጋገሩ ድርጊቱን የሚገልጥ ድርጊቱም ለተናገረው ንግግር ተግባራዊ ምሳሌ መሆን አለበት። ሁለቱ አንድ ናቸውና። ዋናው ቁም ነገርም ድርጊቱ መልካምና በሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚያመሰግነው መሆኑ ላይ ነው። እስቲ አንድ ዐቢይ ጥያቄ እናቅርብ። እንዴት አድርጎ ነው ከሰዎች ራስን የማዋረድ ምግባርና በጎ ተግባርን የመሰወር ሥራ ጋር የሌሎች ሰዎች አመለካከት ሊጣጣም የሚችለው?

### መ. መገለጥና መሰወር

ጌታችንና በተደጋጋሚ መልካም ሥራን በስውር ስለመፈጸም ጥቅም በዝርዝር አስተምሯል። “በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ያስረክብሃል።” ማቴ 6:4፤6-18። መልካሙን ሥራቸውን በሰው ፊት ለሚያደርጉ ሰዎች ደግሞ ሲናገር ፤ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። ማቴ 6:2-5 ብሏል። ጌታችን ይህን ስውር ሥራ አስመልክቶ በምጽዋት በጾምና በጸሎት በምሳሌ አስተምሯል።

ይህ ከሆነ እንዴት አድርገን ነው “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ” ከሚለው ጋር ይህን በስውር የመሥራት ትዕዛዝ ልናጣጥመው የምንችለው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ በሁለት ነጥቦች ላይ እናተኩራለን።

1. ሊሰወሩ የማይቻላቸው መልካም ምግባራት እንዳሉና
2. “ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን ይዩ” ማለትና “ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን እንዲያዩላችሁ ስትሉ አድርጉት” ማለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን እናያለን።



መጾምህን መጸለይህንና መመጽወትህን በስውር ልታደርግ ትችላለህ። ነገር ግን እውነት መናገርህን ታማኝነትህንና ለሰዎች ያለህን እኩል የሆነ አመለካከት ማሰወር ይቻልሃል? ወይስ ደግሞ በጥንቃቄ ተመርጠው ማንንም የማያዋርዱት የማያቃልሉትና ግትርነት የሌለበቸው አሊያም የሰዎችን ስሜት የሚያቆስሉትን የጨነጋገር ዘዴዎችህን መሰወር ይቻልሃልን? አይቻልህም። ሌሎችም ብዙ ልትሰውራቸው የማትችላቸው ባሕርያት አሉ። ቁጣ ፤ ትህትና፤ ጥበብ ፤ አቋምና ዓይናፋርነት ሊሰወሩ አይችሉቸውም። እነዚህ ሁሉ አንተ ሳትወድ በአንተ ላይ በሌሎች ዓይን በግሃድ የሚታዩ ናቸው።

አንተ ትህትናንና ራስህን ማዋረድህን ልትሰውር ትወዳለህ። ይህ መልካም ምግባር ነው። ነገር ግን ወደ ዝምታና ጨዋነት የሚያዘነብል ፀባይህን መሰወር ይቻልሃል? ወይስ ተወዳጅና ደስ የሚያሰኝ ፈገግታህን መሰወር ትችላለህን? ሰዎችን ስትገናኝ በፈገግታ የሚቀበል ገጽታህንስ ትሰውር ዘንድ ይቻልሃልን? ዝግተኛና ሰላምን የተሞላ ድምፅህንስ? የመታገስህን ብዛትና ሌሎችን ይቅር የማለት ባህርይህንስ? መልካሙን ሥራህን ሰዎች እንዲያዩልህና እንዲያመሰግኑህ ስትል ነው የምታደርገው ወይስ ሰዎች ያዩብኛል ብለህ ሳታደርገው የምትቀርየነህ?

ልታደርገው የሚገባ ነገር ቢኖር በሚቻልህ ሁሉ ከሰዎች ምስጋናና ውዳሴን ሳትሻ መልካም ሥራዎችህን ሁሉ በስውር ለማንም ሳትናገር ለማድረግ የሚያስችልህን ንጹህ ልቦና በውስጥህ እንዲፈጥርልህ መጠየቅ ነው። ስለራስህ የምትናገረው አንተ ሳትሆን መልካሙ ሥራህ አንተ ዝም ብለህ ሳለህ ስለ አንተ ይናገራል። ልክ ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚናገሩትና የሰማያትም ጠፈር የእጁን ሥራ እንደሚያወሩት የአንተም መልካም ሥራዎች ስለምታመልከው አምላክና ስለምትከተው ሃይማኖት ይናገራሉ። መዝ 18:1 ይህም የሚሆነው በፍጹም ፀጥታ ወይም በሚናገር ፀጥታ ውስጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ጌታ “መልካሙን ሥራችሁን አይተው እናንተን እንዲያመሰግኑ” ሳይሆን “መልካሙን ሥራችሁን አይተው የሰማዩን አባታችሁን እንዲያመሰግኑ” ማለቱን አስተውሉ።

### ሠ. ታላቅነት ከእግዚአብሔር ነው

የምታደርጋቸው ማናቸውም ሥራዎችህን ማድረግ ያለብህ አንተ እንድትከብርበት ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲከብርበት መሆን አለበት። ስለዚህም ጉዳይ ከመዝሙረኛው ጋር ሆነህ “ለእኛ አይደለም አቤቱ ለእኛ አይደለም ነገር ግን ለስምህ ክብርን ስጥ” ትላለህ። መዝ 115:1 ስለ ራስህ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው “ከሰው ክብርን አልቀበልም” ማለት አለብህ። ዮሐ 5:41 የምታደርገው ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔርና ለመልእክተኞቹ የሚደረግ መሆን አለበት። እንደ መጥምቁ ዮሐንስም ስለ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር "እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል" ማለት አለብህ።ዮሐ 3:30

ለአንተ መልካም ሥራህን እግዚአብሔር ቢያይልህ ይበቃሃል። ሰዎች ቢያዩትም እግዚአብሔርን ሊያከብሩበት መሆን አለበት። በተራራ ላይ ያለች ከተማ የማንንም ዓይን የሚስብ ነገር ሳይኖርበት በሁሉም ሰው ትታያለች። የሚያዩኋትም እዚያ ላይ ድረስ ከፍ ያደረጋትን ጌታዋን ያመሰግናሉ። መልካም ሥራ በሁለት መልኩ እግዚአብሔርን ያስከብራል። በእምነትህና በዕመልህ። ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት የእርሱን ማልክ በአንተ ውስጥ ስለሚያዩና ክርስቲያናዊ ጨዋነትህን ስለሚመለከቱ ነው። በዚህም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛትን በተግባር ማሳየት እንደሚቻል ጨምረው ይረዳሉ። ስለሆነም መልካም ፍሬዎችን ታፈራ ዘንድ ጸጋውን ያበዛልህንና ለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ ብቃት ያደረሰህን አምላክ ዘወትር ያመሰግኑታል። እምነትን ያደለህንም ጌታ ያወድሱታል።

እነዚህ መልካም ተግባራትህን የምታከናውነው በአንተ ሳይሆን በእግዚአብሔር ክንድ መሆኑንና የሚመራህም መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ሲረዱ ጌታን ያከብሩታል። ስሙ የተባረከ ይሁንና በእርግጥም ማንኛውም ነገር የሚከናወነው በእርሱ ነው። ሰዎችም ይህንን የእግዚአብሔር በረከት ተመልክተው እርሱን ሲያከብሩ መንፈሳዊ ቅንዓት የአንተን ፈለግ በመከተል ከአንተ ጋር እኩል ለመራመድ እንዲችሉ ያመላክታቸዋል። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር 'በእነርሱም ከፍ ከፍ ይላል። እግዚአብሔር በአንተ አድሮ የሚያሠራህን መልካም ሥራ በማድነቃቸው እንኳ መንግሥቱ በእነርሱ አማካኝነት እንድትስበክ ያደርጋል። ስለሆነም አንተ የምታደርገው መልካም ተግባር በውስጡ የእግዚአብሔርን ሥራ አጉልቶ ይናገራል።

ለደህ ምጽዋት ስትሰጥ "ይህንን ያዝ!" ብለህ ከምትሰጥ "እግዚአብሔር ይህን ልኮልሃልና ተቀበለኝ" ብትል የበለጠ የሚሻል ይሆናል። ወይም ደግሞ "በመጨረሻ ችግሩን ልናቃልለው ቻልን" ብለህ ከመናገር "በመጨረሻ እግዚአብሔር በመካከላችን ሊገኝ ስለቻለ ችግሩ ሊቃለል በቃ" ብትል ይሻላል።ስለሆነምሁልጊዜም በሥጋም ሆነ በነፍስህ የምታደርጋቸውን ማናቸውንም ዓይነት ሥራዎች ስትመለከት የሐዋርያውን ቃል አስታውስ። "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" 1ኛ ቆሮ 6:20 የምታከብረዉ አምላክህም ለአንተ ባዕድ ሳይሆን በሰማይ ያለ አባትህ እንደሆነ አስተውል!

"ብርሃናችሁ ይብራ" የሚለው የጌታ ቃል ሰማያዊ ትዕዛዝም ነው። ይህም ማለት ለማብራትም ሆነ ለማንጸባረቅ የሚሰጥ ትዕዛዝም ሆነ በመብራቱ ላይ ያለው ዕንቅብ ብርሃኑን እንዳይጋርድ መወገድ አለበት የሚለው ትዕዛዝ ሰማያዊ ትዕዛዝ ነው። ይህ ደግሞ ጌታ ብርሃናችን ያለማቋረጥ በሰዎች ፊት እንዳበራ እንዲኖር በመፈለጉ ይህን መልካም ሥራ የሚያዩ ሰዎች በሰማይ ያለውን አባታችንን ያለማቋረጥ እንዲያመሰግኑ ያደርጋቸዋል ማለት ነው።



እግዚአብሔር አስቀድሞም እንዲህ በማለት ተናግሯል። "እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ፤ ብርሃንም ሆነ።" ዘፍ 1:3 አሁን ደግሞ "ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" አለ። ይህም ብርሃን በሰዎች ፊት ያበራል። እግዚአብሔር "ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል ፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም" ብሏል። ኢሳ 55:11 እግዚአብሔር በአንተ እንደበት የሚናገር ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በአንተ ይተረጎማሉ። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ይሄዳል። ሐዋ 6:7

እግዚአብሔር ብርሃንን ይወዳል። እርሱም ራሱ እንዲህ ብሏል "በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቼአለሁ።" ዮሐ 12:46 እግዚአብሔር በዚህ በቁሳዊው ዓለም ላይ እንዲያበሩ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትንና ፕላኔቶችን እንደፈጠረ ሁሉ መንፈሳዊውም ብርሃን በዚህ መልኩ በሰዎች ፊት እንዲያበራ ይወዳል። ስለዚህ መብራቱ ከዕንቅቡ በላይ ደምቆ በማብራቱና ሰዎችም መልካሞቹን ሥራዎቻችሁን በማየታቸው በጌታችሁ ደስ ይበላችሁ።

## ፫. በሰማያት ያለው አባታችሁ

በተራራው ስብከቱ ውስጥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን አባታችሁ በማለት በሰውና በእርሱ መካከል ያለውን ግንኙነት አጉልቶ አሳይቶናል። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት ባይገለጽም በተራራው ስብከቱ ውስጥ የሰማዩ አባታችሁ የሚለው ሐረግ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል።

- በሰማይ ያለው አባታችሁን እንዲያከብሩ መልካም ሥራዎችን ሥሩ
- ስትጸልዩም በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ በሉ
- መልካም ሥራን በስውር አድርጉ አባታችሁ ይከፍላችኋልና
- የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ፍጹማን ሁኑ
- ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር በሉ ፤ የሰማዩ አባታችሁ ይቅር ይላችኋልና
- ምን እንበላለን ምንስ እንጠጣለን [illegible] ፤ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና
- የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ ፤ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል
- በሰማያት ያለ አባታችሁ ለሚጠይቁት [illegible] ይሰጣል

በተራራው ስብከት ውስጥ ስለ ሰማዩ አባታችን የተሰጠው ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ ለጌታችን የመጀመሪያው የትምህርቱ ፍሬ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ሰ. መንግሥትና ሰማያት

"የሰማዩ አባታችሁ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኘው በተራራው ስብከት ላይ በብዛት እንደተጠቀሰው ሁሉ መንግሥት፣ ሰማያት ፣ መንግሥተ ሰማያት የሚሉትንም ቃላቶች እንደዚሁ እናገኛለን። ጌታ ሰዎች ትኩረታቸውን ወደ መንግሥትና ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲያደርጉ ወዷል ማለት ነው።

ጌታ በተራራው ስብከቱ መግቢያ ላይ ስለ መንግሥተ ሰማያት እንዲህ ብሎ ነበር። "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።" ማቴ 5:3 አምላካዊ ሥራውን በጀመረ ጊዜም "... የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ . . ." የሚል ቃል ተጽፎለት እናነባለን። ማቴ 4:23 ይኸው ቃል በድጋሚ በማቴ 9:35 ላይ እና በሌሎችም ቦታዎች በተደጋጋሚ ተጽፎአል። እስከ ዓለም ፍጻሜም መደጋገሙ ይቀጥላል። "ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።" ማቴ 24:14 "መልካሙ ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው።" ማቴ 13:38 እነዚህ አማኞች ናቸው ማለት ነው።

"በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ።" ማቴ 13:43 "እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።" ማቴ 25:34።

**የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ !**

**በነውን ሁሉ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን!**

www.ethiopianorthodox.org